ዶን ኪኾቴ

በሰርቫንቴስ

ትርጉም

በዳምጤ አሰማኸኝ

ለጀግንነት መታጠቅ

ከብዙ ዘመናት በፊት በስዷን አገር የሚኖር አንድ ወግ አጥባቂ ሰው ነበር ። ይህን ሰው ምንው ቀደም ባሉት ዘመናት ባወቅነው ኖሮ የሚያስኝ አያሌ ድንቅ ነገሮች ፈጻሚ በመሆኑ ፡ በአስገራሚ ድርጊቶቹ ሲደነቁ ፡ ጓደኞቹ ግን በጣም ያዝኑ ነበር ። ቢሆንም ሰውዬው በድርጊቶቹ አስገራሚነት የተነሣ ስሙ በዓለም ታውቋል ።

ከጐረቤቶቹና ከመንደሩ ነዋሪዎች በስተቀር ትክ ክለኛ ስሙን የሚያውቅ ሰው አልነበረም ። ግማሹ ስሙ "እገሌ ይባላል" ሲል ፡ ሌላው ደግሞ ፡ "የለም እገሌ ይባ ላል "ይል ነበር ። የቅርብ ጐረቤቶቹ ግን ፡ "መልካሙ አቶ ኪኻና" ብለው ስለሚጠሩት ፡ ይህ መጠሪያ ትክክለኛ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም ።

ሰውዬዉ ጨዋ ፡ ቸርና በጣም ጀግና በመሆኑ ፡ የሚ ያውቁት ሁሉ ይወዱት ነበር ። ሚስትም ሆነ ልጅ አልነ በረውም ። ላማንቻ በተባለው ክፍለ ሀገር ከአንዲት እን ስተኛ መንደር አጠገብ ከእኅቱ ልጅ ጋር ፡ በራሱ የርሻ መሬት ላይ ይኖር ነበር ።

የእኅቱ ልጅ ገና ኻያ ዓመት ያልሞላት ወጣት ነበረች። ስለሆነም ቤቱን የምትጠብቅለት ከብልህነት ይልቅ ሞኝ ነት ፡ ከዝምተኛነት ይልቅ መቀባጠር የምትወድ አንድ

ጅላጅል አሮጊት ነበረች ። አንድ ምስኪን ሰው ያም በገ በሬንት ተቀጥሮ የእርሻ ሥራውን ያከናውንለታል ። ቢሆ ንም ጌትየው ስለማይቈጣጠረው ሠራተኛው ብዙ የዕ ረፍት ጊዜያት ነበሩት ።

አቶ ኪሻና በአለባበሱ ፣ በሁኔታውና እንደዚያ ዘመን ወግ አጥባቂ መኳንንት ሁሉ አስቂኝ ነበር ። ዕድ ሜው ከሃምሳ ዓመት በላይ ፣ ቁመቱ ረዥም ፣ ሰውነቱ ቀጠን ያለ ፣ ፊቱ ከሲታ ፣ አፍንጫው ስልካካ ሆኖ፣ጸጉሩ በመሸበት ላይ ነበር ።

በአለባበሱ ተራ ቢሆንም ፣ በዕረፍት ቀናት ግን ፣ግል ድምና ከቤት ማግ ፈትል የተሠራ አረንጓዴ ሱሪ ይታጠ ቃል ። በሰንበት ቀን (እሑድ) ግን ከከፈይ የተሠራ ኮትና አጭር ሱሪ ለብሶ ፣ በብር ጥብጣብ የተጠለፈ መጫሚያ ይጫማ ነበር ።

በዚያ አሮጌ ቤቱ ጓዳ ግድግዳ ላይ ፣ አንድ ያረጀና የዛገ አጭር ጐራዴ ተሰቅሎ ይታያል ። እንዲሁም በግድ ግዳው ላይ የዛገ ጦርና ጋሻም ይገኛል ። እነዚህ መጫሪያዎች የቅድመ አያቶቹ ሲሆኑ ፣ ጥንት የሰው ልጅ ጠመንጃና ጥይት ከመሥራቱ በፊት የነበሩ ናቸው ።

በማዕድ ቤቱ መግቢያ በር ላይ ፣ አንድ ያረጀ አዳኝ ውሻ ተጋድሞ ይውላል ። ይህ ውሻ ከሲታ ከመሆኑም በላይ ፣ የአዳኝነት ተግባሩን ካቋረጠ ዘመናት ዐልፈው ታል ። በዚያን ዘመን ወግ አጥባቂዎች የዘመኑ መኳንንት አዳኝ ውሻ ማሳደግ ልማዳቸው ነበር ።

በጋጣው ውስጥ ልክ እንደ ውሻው አጥንቱ የወጣና ያረጀ ፈረስ ነበር ። ስለዚህ ፈረስ ወደፊት በታሪኩ ሒደት ውስጥ በሰፊው እንረዳለን ።

እንደዚያ ዘመን ሌሎች ሰዎች ሁሉ ፡ አቶ ኪዳኔም ምንም ዐይነት ሥራ በእጁ ሳይኖር ጊዜውን በሙሉ በማን በብ ፡ በማንበብ ፡ በማንበብ ፡ ነበር የሚያጠፋው ።

ከእጁ መጽሐፍ ይጠፋል ማለት ዘበት ነው ። አየሩ ጥሩ ሲሆን በትንሿ ቤቱ መጻሕፍት ውስጥ ፤ ወይም በአት ክልት ሥፍራው ከሚገኙት የናፌ ዛፎች ጥላ ሥር በመ ሆን ቀኑን ሙሉ ሲያነብ ይውላል ።

አብዛኛውን ጊዜ ምሳውን ይዘነጋል ። መጻሕፍት በማንበብ ከመጠመዱ የተነሣ ፈረሱን ፤ ውሻውንና የእ ኅቱንም ልጅ ይረሳቸው ነበር ። ጓደኞቹንና ራሱንም ቢሆን ዘንግቷል ። አንዳንድ ጊዜ ሌሊቱን በሙሉ ሲያነብ ያነ ጋል ። ለመሆኑ ምን ዐይነት መጻሕፍት ያነባል ብላችሁ ታስቡ ይሆን ? የተረቷ-ተረትም ሆኑ የግብ መጻሕፍት ጨርሶ አያነብም ። ለግጥምም ሆነ ለፍልስፍና መጻሕፍት ደንታ የለውም ። አእምሮው በሙሉ በጀብዱ ሥራና በጥ ሩር-ለባሽ ፈረሰኞች ገድሎች የተሞላ ነበር ።

እነዚህን አያሌ የጥሩር ለባሽ ፈረሰኞች ገድሎች አዘ ውትሮ ከማንበቡ የተነሣ ፣ በዙሪያው ለሚገኙ ጉዳዮች ቁብ አልነበረውም ። አእምሮው ፤ በጀግኖች ገድሉና ወኔ በተአምራዊ ድርጊቶቻቸውና በአስማት ሥራቸው ፤ በጦር ሜዳ ግዳያቸውና በወንድነታቸው ታሪክ ተወጥሯል ።

ጥቂት ቢያነብ ኖሮ ብልህ በሆነ ነበር ፤ የሱ ዐይነት ማንበብ ያንድን ሰው አእምሮ ያበለጽጋል ማለት አይደ ለምና ።

በመጨረሻም ፣ ይህ ወግ አጥባቂ ሰው ለራሱ እንዲህ አለ ፤ "እስከ መቼ ድረስ ተራ ገበሬ ሆኜ ከቤት እውላለሁ? እኔስ ጥሩር-ለባሽ ፈረሰኛ ለመሆን ምን ይጐድለኛል ?

በዚህ ጉዳይ ላይ ደጋግሞ ባሰበ ቁጥር በመጻሕፍት ውስጥ ታሪካቸውን እንዳነበባቸው ጀግኖች ፣ እሱም ጀግና ለመ ሆን ይናፍቀው ጀመር ።

“እንዴታ ! ጀግና መሆን አለብኝ ” አለና ለራሱ ፣ “ ቆርጫለሁ ። ጥሩር ፣ የብረት ልብስ ፣ እለብሳለሁ ። ያንን ሡንጋ ፈረሴን እጭናለሁ ። ወደ ሰፊው ዓለም ወጣ ብዬ የጥሩር - ለባሽ ፈረሰኛነት ክብር እቀዳጃለሁ ። ምንም ዐይነት አደጋ አያስፈራኝም ። በጠንካራው ክንዴ ደካ ሞችን እታደጋለሁ ፤ ወገን ላጡ ወገናቸውና መከታቸው እሆናለሁ ። አዎን! ጀግና እሆናለሁ ። በየትኛውም ቦታ የተበላሸን ለማቃናት ዝግጁ ነኝ ” አለ ድምፁን ከፍ አድ ርጎ ። ዓላማውንም በተግባር ለመፈጸም ዝግጅቱን ተያ ያዘው ።

የመጀመሪያ ተግባሩ ተስማሚ ጥሩር ፣ የብረት ልብስ ፣ መፈለግ ነበር ። በጥንት ዘመን ጥሩር ሳያጠልቅ ፣ የጦር መሣሪያ ሳይታጠቅ ጥሩር ለባሽ ፈረሰኛ ለመባል አለ መቻሉ ይታወቃልና ።

እና ፣ በቤቱ ጓዳ ቆጥ ላይ አንድ አሮጌ ጥሩር ተሰቅ ሏል ። ይህ ጥሩር ቨረሪት አድርቶበት ፣ ከመቶ ዓመታት በላይ ፣ በአያት ቅድመ አያቶቹ ዘመን እዚያው ተረስቶ የኖረ ነበር ። ያ ጥሩር ዝጎና ሻግቶ አንዳንድ ክፍሎቹም ወላልቀው ጠፍተዋል ። እንዲህ ያለ የጀግና ዕቃ በእንዲህ ዐይነት ሁኔታ መገኘቱ ያሳዝናል ! ዕቃው በዘመኑ ጥሩም ቢሆን ዛሬ ወዳቂ ሆኗል ።

የተቻለውን ያህል አጽድቶ በጥንቃቄ ወለወለው ። የጐደሉትን አንዳንድ ክፍሎች ከርታስ ቆራርጦ ከሟላ በኋላ ፣ ብረት እንዲመስል የብረት ቀለም ቀባው ። ጥገ ናው ከተገባደደ በኋላ መሣሪያው አማረ ። በተለይ ፍል

ሚያ በማይደረግበት ወቅትማ ግሩም የጦር ፈረስ ያሆ ናል! ከጥሩሩ ጋር አንድ አሮጌ የብረት ቀለበት ፤ የብረት ቆብ ነበር ። ተሰባብሮ ፤ የማሠሪያ ጠፍሮቹም ተሬተዋሌ ። ሆኖም ፤ አቶ ኪኻና በአሬሬ መሳይ ጨርቆች ገመድ ቀሩን ጠፍሮ በማሰር አሳምሮ አጠበቀው ። ቀሩን ከፍ ዝቅ እያደረገ አዟዙሮ ከተመለከተው በኋላ ፤ ኩራት ኩራት አለው ። ለራስ ቅሉ ተስማሚ የጅግና ልዩ ቀር በማግኘቱ አድናቆት እንደሚያተርፍም ተሰማው ።

ከመሣሪያዎቹ ጋር አብሮ የሚሔድ ሠንጋ ፈረስ ማግ ኘት አስፈላጊ ነው ። ማንኛውም ጥሩር- ለባሽ ቀር ያሬ ጀግና ፤ በሠንጋ ፈረስ ተጓዥ መሆን አለበትና ። በጋጣው ውስጥ ያለው ፈረስ ግን ረሃብ ያጠቃው አጥንቱ የሚቈ ጠር ነበር ። ግትርና ጅማታም የጦር ፈረስ በመሆኑ ለርሱ ተስማምቶታል ። ይህ ወግ አጥባቂ ሰው ፈረሱን ትክ ብሎ ከተመለከተው በኋላ ፤ እምባያ የማይገኝለት እንዲህ ያለ ውብና ፈጣን ፈረስ ታይቶ እንደማይታወቅ ተሰማው ።

"ኩርቶ የሚያስጋልበኝ ብርቱ ፈረስ ነው" አለ ፤ ንግግሩን በመቀጠል ። "እኔም በፈረሴ እመካበታለሁ ። እረ እንዲያው ምን ዐይነት ስም ባወጣለት ይሻላል ? የጀ ግና ሰው ፈረስ ስም ድንቅና ብርቅ መሆን አለበት "አለ አቶ ኪኻና ። እና ፤ ለፈረሱ ስም ለማውጣት አራት ቀን ሙሉ ፈጀበት ።

በመጨረሻም ፤ ድምፁን ከፍ አድርጎ ፤ " ለፈረሴ ራሴ ስም አገኘሁለት ! ‘ ሮሲናንቴ ’ መባል አለበት" ብሎ የደስ ደስ ሲሰማው የእኅቱ ልጅ ትመልክት ነበርና ፤

" እረ ለምን ብለህ ነው እንግዳ በሆነ ስም ፈረስህን የምትወይመው ? " ብላ ጠየቀችው ።

“ቆይ አስረዳሻለሁ ፡፡ ‘ሮሲን’ ማለት ተራ ፈረስ ማለት ሲሆን ፡ ‘አንቴ’ ማለት በሩቂን ቋንቋ ፡ በፊት ወይም ቀድሞ ማለት ነው ፡፡ የጥንቱን ተራ ፈረሴን ፡ ማለት የዛሬውን ብርቱ ፈረስ ፡ እንደ ጥንቱ ተራ ፈረስ አልለውም ፡፡ ዛሬ ግን ትርጉሙ ሲማንም ግልጽ እንደሚሆን አልጠራጠርም፡ ፈረሴ ተራ አይደለም ፡፡ ገባሽ ? ስለሆነም የፈረሴን መጠሪያ ‘ሮሲናንቴ’ ብዬዋለሁ” አለ በኩራት መንፈስ ፡፡ ፈረሱንም በእጁ መታ መታ አድርጎ በፍቅር ዐይን ከተመለ ከተው በኋላ ፡ “ሮሲናንቴ ! ሮሲናንቴ” ይል ጀመር እየመላለሰ ፡፡

እንደ ፈረሱ ለራሱም መጠሪያ ተስማሚ ስም ቢያ ገኝ ፡ ወዲያው ወደ ጀግንነት ተግባር ተሠማርቶ ወንድነ ቱን በተግባር ለማሳየት እንደሚችል ያሰላስል ጀመር ፡፡ ሁሉም ተሟልቷል ፤ የቀረ ቢኖር የርሱ የራሱ ስም ብቻ ነው፡፡

“ ማንኛውም ጥሩር-ለባሽ ጀግና ‘ ዶን ’ የሚል የማዕ ረግና የክብር ቅጽል ከስሙ በፊት ማስቀደም መብቱ ነው ፡፡ እና ፡ እኔም ራሴን ፡ ‘ ዶን-ዶን-ዶን ’ ማንትስ ብዬ መጥራት አለብኝ፡፡ ነገር ግን ፡ ማን ብዬ ራሴን ብሠይመው ይሻላል?” ይህን የስም ፍለጋ ጥያቄ ለመመለስ ስምንት ቀን ሙሉ ፈጀበት ፡፡ ከዚያ በኋላ አንድ አስደሳች ሐሳብ መጣለት ፡፡

“ራሴን ዶን ኪኾቴ እለዋለሁ ”አለና ድምፁን ከፍ አድርጎ በመጮህ ፡ “የትውልድ መንደሬ ላ ማንቻ ስለ ሆን በዓለም በሙሉ ‘የላ ማንቻዉ ዶን ኪኾቴ’ ተብዬ እታ ወቃለሁ ፡፡ ከዚህ የላቀስ የክብር መጠሪያ ከየት ይመጣል? ከዚህ የበለጠስ ምን ማዕረግ ይገኛል?” እያለ ተንጐራደደ፡፡

እውነትም አዲሱ ስም ከፊተኛው ስሙ እምብዛም የራቀ አልነበረም ፤ ለምን ቢባል ፡ ጎረቤቶቹ ሁሉ ኪኻና እያሉ ይጠሩት ነበርና ፡፡

መልካሙ አዛውንት ጥሩሩን ጠጋግኖና ወልውሎ ፡ ለፈረሱና ለራሱም አዲስ ስም አውጥቶ ከበቃ በኋላ ዝግጅቱ ለጀግንነት ተግባር መሆኑ ተሰማው ። ነገር ግን ፤ አንድ ቆፍጣና ጀግና ሙያውን ለማሳየት ፡ እውነተኛ ጉበዝ ለመባልም ሌላ ያላሟላው ጉዳይ እንዳለ ትውስ አለው ። ባነበባቸው መጻሕፍት ውስጥ ሁሉ ማንኛውም ለጀግንነት ማዕረግ የበቃ ሁሉ ፣ አደጋ ሲያጋጥመው ስሟን የሚያነሣት ፣ በአሸናፊነት ሲወጣ ምርኮና የሽልማት ዕቃዎች የሚያስረክባት ፣ አንዲት ውብ “እመቤት ሆይ”ሊትዋረው እንደሚገባ ታሰበው ። ከእያንዳንዱ የጀብዱ ሥራው በኋላ ከጉልበቷ ሥር ተንበርክኮ ግዳይ መጣሉን የሚያስመሰክርላት አንድ ውብ ሴት ታስፈልጋለች ። የአሸናፊነቱን አክሊል የምትደፋለት ይህችው ሴት ናት ። ወጉ ነውና፤ አንዲት ውብ የቤት ጓደኛ ወይም ወዳጅ እንደ ፈረሱና እንደ ብረት ልብሱ ሁሉ አስፈላጊ ሆና ተገኘች ።

ዶን ኪኾቴ ከብዙ ሴቶች ጋር ሰውቂያ አልነበረውም። ቢሆንም ፣ እንደ ማንኛውም ጉበዝ ሐሳቡን በአንዲቷ ሴት ላይ ማሳረፍና ፣ ያችም ሴት ፣ ለጀግንነት ወደ ሰፊው ዓለም ሲሠማራ ፣ እንደ መሪ ኮከብ ትሆነው ዘንድ በጥብቅ ታስፈልገዋለች ። እና ፣ ማንን ይምረጥ ! ከሌላው ይልቅ ይህ ሐሳብ ይበልጥ አስጨነቀው ። ሁለት ሳምንት ሙሉ በዚህ ጉዳይ ላይ ብቻ አጥብቆ አሰበ ።

የእኅቱስ ልጅ ብትሆን በምን ትርዳው ? ገና ጩጣት ነች ። በዚህ ላይ ደሞ እሱ አጎቷ ስለሆነ አትደፍረውም ። በቤቱ መጻሕፍት ውስጥ ካሉት መጻሕፍት ውስጥ ጥሩር ለባሽ ፈረሰኛ ከግዳይ በኋላ በእኅቱ ልጅ ጉልበት ሥር ሲንበረከክ የሚተርክ ፈጽሞ የለም ። ስለሆነም የልጅቱ ጉዳይ በዚህ አበቃ ። የቤት ሠራተኛውም ብትሆን በእር

ጀናዋ ላይ መሳከ ጥሩ ነች ። ከዚህች ባሌቴት ጉልበት ጋር ተንበርክኮ ጀግና መባል የማይታሰብ ነው ።

በመጨረሻም ፣ ቶቦሳ ከተባለው መንደር ወይም አቅራቢያ የምትኖር እንዲት ውብ ወጣት ታወሰችው ። አዶንሳ ሎሬንሶ የምትባለው ይህች ወጣት ፣ ከብዙ ዓመታት በፊት በዚያ መንገድ ሲያልፍ ፈገግታ መግባው እንደ ነበር ትዝ አለው ። ካደገች በኋላ አይቷት ባያውቅም ፣ ዛሬ በጣም ውብና ወጣት ሴት እንደምትሆን አረጋገጠ ። ማንም ሴት በዓለም ላይ ከርሷ እንደማትሻልና ፣ የጀግንነት ግዳይ ጥሎ የሚንበረከክላት ተስማሚና ውብ ፣ እሷ ብቻ መሆኗን በሐሳቡ እያሰላሰለ ይደሰት ጀመር ።

"የኔዋ ውብ እመቤት አዶንሳ ሎሬንሶ መሆን አለባት" እያለ በደስታ ፈንድቆ እጆቹን አፍተለተለ ። ድንቅ ስም አጋጥሟታል ! ከጀግናው ዶን ኪኾቴ ዲ ላማንቻ ስም ጋር ሲቀናጅማ ግሩም ድንቅ ይሆናል ። ብቻ ስሙ በጣም ተራ ሀይነት በመሆኑ ፣ ከልዕልታት ስም ጋር መቃረብ እንዳለበት ወሰነ ። ታዲያ ይህች ውብ ማን ተብላ ትጠራ ?

ይህንን ጉዳይ ለብዙ ቀናት ካወጣ ካወረደ በኋላ ፣ በመጨረሻ አንድ ደስ የሚለውን ስም በማግኘቱ ፈነደቀ።

'ዱልሲኒያ' መባል አለባት" እያለ ድምፁን ከፍ አድርጎ ጮኸ ። "የቶቦዋሳ ዱልሲኒያ ትባላለች ። ይህን የመሰለ ጣፋጭና ተስማሚ ፣ ልክ እንደ እርሷ ውብ የሆነ ስም ከቶ አይገኝም" አለ በደስታ እና ፣ ከብዙ ሳምንታት ድካምና ፍለጋ በኋላ ። ዶን ኪኾቴ ዲ ላማንቻ ወደ ዓለም ወጣ ብሎ የጥሩር ለባሽ ፈረሰኛ ጀግና ግዳጅን ለመፈጸም መዘጋጀቱን አረጋገጠ ። ዕቅዶቹን ሁሉ በተግባር የሚተረጉምበትን መልካም አጋጣሚ ቀን ይጠባበቅ ጀመር ።

የሆቴል ቤቱ ፍልሚያ

አንድ ቀን በበጋ ወር ፡ ማንም ሰው ከእንቅልፉ ሳይ
ነቃ ዶን ኪኾቴ ማልዶ ተነሣ ። ጥሩሩን አጥልቆ ፡ በክር
ታስ የለበጠውን ያንን አሮጌ ቊር በራሱ ላይ አጠለቀ ።
የቅድመ አያቱን አጭር ጉራዴ ታጠቀ ። ረዥሙንም ጦር
አጥብቆ ያዘ ። በቆዳ የተጠፈረውንም ጋሻ በትከሻው ላይ
አነገበ ።

በዝግታ ርምጃ በኋላ በር በኩል ባይወጣ ኖሮ ፡ የእ
ኅቱን ልጅ ወይም የቤት ሠራተኛውንም ከእንቅልፋቸው
በቀሰቀሳቸው ነበር ። ያላንዳች ኮሽታ ወደ ጋጣው እም
ርቶ ፡ ፈረሱን ጫነ ። ርካቡን ረግጦ ፡ ፈረሱ ላይ ጉብ ካለ
በኋላ ፡ በእንቅልፍ ላይ የነበሩትን መንደርተኞች ጸጥታ
ሳያደፈርስ ወደ አውላላው ሜዳ ዘልቆ ጉዞውን ተያያዘው።

ያላንዳች ችግር ከመንደሩ በመውጣቱ ደስታ ተሰ
ማው ። ምንም እንቅፋት ሳያጋጥመው ከቤቱና ከመንደሩ
ራቀ ። ትንሽ እንደ ተጓዘም ፡

"ሩቅ ሳልሔድ በቅርቡ አንድ ርባን ያለው ጀብዱ
ሥራ እንደምፈጽም እተማመናለሁ " አለ ለራሱ ። ወዲ
ያው አንድ አስደንጋጭ ሐሳብ አእምሮው ገብቶ እንደ
መብረቅ መታው ። ለካ ገና ጥሩር ለባሽ ፈረሰኛ አይደለም!
ያን እስካልሆነ ደግሞ ይህን ማዕረግ ካገኙ ጋር መፋለምም

ሆኑ መጋጠም ሥርዓት ወይም ወግ አይፈቅድለትም ። ስለዚህ ከሁሉ አስቀድሞ ሥነ ሥርዓቱን አሟልቶ ፤ "የጥሩር ለባሽ ፈረሰኝነቱን" ማዕረግ መቀበል አለበት !

"ቼ ! ሮሲናንቴ ! ስለዚህ አሳሳቢ ጉዳይ አንድ ውሳኔ ላይ መድረስ አለብኝ ! " አለና ከአንድ የዛፍ ጥላ ሥር ለሰዓታት ዐርፎ ያስብ ፤ ያሰላስል ጀመር ። ሁሉን ነገር ትቶ ታዲያ ቤቱ ይመለስ? ከተቀመጠበት ድንገት አፈፍ ብሎ ፤

"በጭራሽ አላደርገውም !" እያለ ጮኸ ። "የወደፊት ጉዞዬን መቀጠል አለብኝ ። መጀመሪያ የማገኘው ሰው 'የጥሩር ለባሽ ፈረሰኝነትን' ማዕረግ ያቀዳጀኛል" አለ በኩራት መንፈስ ።

ፈረሱን ሮሲናንቴን ቼ ! ብሎ ፤ በልጓሙ ገጩት አድርጎ ጉዞውን ቀጠለ ። ፈረሱ ቢፈልግ ወደ ግራ ፤ ቢፈልግ ወደ ቀኝ መለስ ቀለስ እያለ እንደ ልቡ እንዲሔድ ልጓሙን ላላ አደረገለት ።

"እንዲህ ነበር ጀግኖች የሚጓዙት — ፈረሶቻቸው ወደ መሯቸውና መልካም ዕድል ወደሚገጥማቸው አቅጣጫ" አለ በደስታ መንፈስ ።

እና ፤ ተመቻችቶ ኮርቻው ላይ ተቀምጦ ፤ ሮሲናንቴም የሰው ኮቴ ባልነካቸው መንገዶች እየተጓዘ ፤ ግራና ቀኝ የሚያጋጥመውን ለምለም ሣር እየነጨ ፤ ሲያሻውም ጥላ ሥር ቆም ይል ነበር ። ሰዓታት በጉዞው ላይ ነጐዱ፤ ነገር ግን አንድም ሰብአዊ ፍጡር ወይም የዱር አውሬ በርቀትም ሆነ በቅርበት አላጋጠመውም ።

"እንዲህ እንዲህ እያልን ስንጓዝ አንድ ጀብዱ የሚጠይቅ ሥራ ያጋጥመናል" አለ ዶን ኮኾቴ ፈረሱን ፤ ለስለስ ባለ ድምፅ ።

ፀሐይ በምዕራብ በኩል መጥለቅ ጀምራለች ። ሮሲናንት ለምለም ሣር ፍለጋ ጌታውን ተሸክሞ ወደ አንድ ጉብታ አናት ላይ ወጥቷል ። ከታች ከሸለቆው መኻል ፤ ከአውራ መንገዱ ዳርቻ አንዲት አነስተኛ የመንገድ ዳር ሆቴል ወለል ብላ ለዶን ኪኾቴ ታየችው ። ድምፁን ከፍ አድርጎ ፡

“እዎን! አንድ የጀብዱ ሥራ የሚጠይቅ ጉዳይ ያጋጥመናል ብዬ አልነበረም?” እለና ወዲያው ልጓሙን ስበረኸርም ጠሩን ጨበጠ ። እንደልቡ ይንቀሳቀስ የነበረ ፈረሱን ኰርኵሮ ያንን ቁልቁለት በአርሻ ፈረስ ፍጥነት ይንደረደር ጀመር ። ያቺ ሆቴል ፡ ባለ አራት የዕንቁላል ግንብ ዙሪያውን ውሃ ሙሉ በሆነ እና በላዩ ላይ ትንሽ ተዘርጊ የዕንጨት ድልድይ ባላት ቦይ ዙሪያውን የተከበበ ታላቅ ሕንፃ መስላ በምናቡ ታየችው ።

ከሆቴሏ አቅራቢያ ዋናው መግቢያ በር ላይ እንደ ደረሰም የፈረሱን ልጓም ገታ አድርጎ ይጠባበቅ ጀመር ። የጀግናንና የእንግዳን መምጣት በመለከት ድምፅ ከቤተ-ግንቡ አጥር ላይ ቆሞ የሚያበሥር በዘመኑ የተለመደውን ድርጊት ፈጻሚ ድንክዬ ሰው ለማየት ዶን ኪኾቴ ጓጉቷል ። ባነበባቸው መጻሕፍት ውስጥ ፣ ለጀግኖች ሁሉ የዚህ ዐይነት ሥነ ሥርዓት ተደጋግሞ እንደሚፈጸም ጠንቅቆ ያውቃል ።

አንድም ሰው ብቅ ሳይል በመቅረቱ ፡ ዶን ኪኾቴ ተበሳጨ።በመጨረሻም ሮሲናንቴን ወደፊት በዝግታ እንዲንገዘ ኰረኰረውና ወደ ሆቴሏ ደጅ ደረሰ ። እንደ አጋጣሚ ሆኖ ፡ በአካባቢው የሚገኝ አንድ የዐሣማ መንጋ እረኛ ዐሣሞቹን ለመጥራት በቀንድ ጥሩንባ ድምፅ አሰማ ።

"ሃሃ! . . . . ሃሃ!" እያለ ዶን ኪኾቴ ድምፁን ከፍ በማድረግ ፡ "እነሆ ድንክዬው በመጨረሻው መጣ ። የኔን መድረስም ለማስማት ይኸው መለከቱን መንፋት ጀመረ" እያለ በከፍተኛ ደስታና ኵራት ወደ ሆቴሏ በር አመራ ።

የሆቴሏ ባለቤት ፈርጠምጠም ያለ ሰው ነበር ። ዶን ኪኾቴ ወደ ሆቴሏ በር መጠጋቱን እንዳየ ፣ እንኳን ደኅና መጡ ለማለት ቀረብ አለው ። በእንግዳው የጦር ልብስ አለባበስ ፣ በረዥም ጦሩ ፣ በሻገተ ጋሻው ፣ በጥንታዊ ጥሩሩና ባጠቃላይ ሁኔታው ፣ ባለ ሆቴሉ ሣቅ መጥቶበ ታል ። ሆኖም በተቻለው መጠን ሣቁን አፍኖ በትሕትና ሊያነጋግረው ሞከረ ።

"ክቡር ጥሩር ለባሽ ጌታዬ ሆይ! መልካም ፈቃድዎ ሆኖ ከፈረስዎ ላይ ቢወርዱልኝ ? አልጋ ብቻ የለኝም እንጂ፣ ሌላ ማንኛውንም የፈለጉትን ነገር በማቅረብ ላስተ ናግድዎ ፈቃደኛ ነኝ " አለው በትሕትና ።

ዶን ኪኾቴ አሁንም ቢሆን ያቺ ትንሽ ሆቴል ቤተ- ግንብ (ካስል) ፣ ባለቤቷም አገረ ገዥው መሆን አለበት በማለት በሐሳቡ ደምድሟል ። ድምፁን ከፍ አድርጎ ኰራ ባለ ግርማ ሞገስ እየተጀነነ ፣

" ክቡር ሆይ ! ቤትዎ ያፈራው ማንኛውም ነገር ይስ ማማኛል ፤ እኔን የሚያስጨንቀኝ የጦር መሣሪያ ጉዳይ ብቻ እንጂ ፣ ሌላ አይደለም ። ምንም ዐይነት ምቾ አልጋ የጦር ሜዳን ያህል አይስማማኝም " አለ ።

የሆቴሏ ባለቤት እጅግ በጣም ተገረመና ፣ "ጀግናው ጌታዬ ሆይ ! ንግግርዎ ፀሙሉ ማስፈያ ነው ። ፍላጐትዎ ሁሉ የተወሰነ ስለሆነ፣ምንም እንደማይጐድልብዎ ቃል

እገባለሁ ። እባክዎን ከፈረስዎ ላይ ይውረዱና ይግቡ ” አለውና የፈረሱን እርካብ ይዞለት ዶን ኪኾቴ ወረደ ።

ምስኪኑ አረጋዊ ቀኑን ሙሉ እህል ሳይቀምስ ነበር የዋለው ። የለበሰው ጥሩርም እጅግ ከባድ በመሆኑና፣ረዥሙም ጐዳና በመጓዙም ሰውነቱ ዝሏል ። በገዛ እግሮቹ መቆም ተስኖታል ። በሆቴል ቤቱ ጌታ ድጋፍ ከሆቴል ቤቷ ወጥ ቤት ምቹ ቦታ አግኝቶ ዐረፈ ።

“ጌታዬ እባክዎን የፈረሴን ነገር አደራ ! በጥንቃቄ እንድትይዙልኝ እለምንዎታለሁ ። በዓለም ላይ እሱን የሚስተካከል ፈረስ አይገኝም” አለ ዶን ኪኾቴ በኩራት መንፈስ ። የሆቴሏ ባለቤትም ፈረሱ ምንም ነገር እንደማይጐድልበት ቃል ገብቶ ወደ ጋጣ ወሰደው ።

ፈረሱን ከጋጣ አድርሶ ወደ ማዕድ ቤቱ ሲመለስ ፣ ዶን ኪኾቴ ጥሩሩን ለማውለቅ ሲታገል ደረሰ ። የጥሩሩን አብዛኛውን ክፍል በትግል አውልቋል ። የራስ ቍሩ ግን በአራራ ጥብጣብ ተቋጥሮ ታስሮ ነበርና ፣ ካልቆረጡት በስተቀር ለማውለቅ የማይሞከር ሆነበት ።

“ማንም ሰው ይሆን ጥብጣቡ ቆራርጦ ለመበጣጠስ ከቶ አይቻለውም ” በማለት ዶን ኪኾቴ ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ ። ስለዚህ ፣ ራሱ ለመፍታት ጊዜውን አባክኖና ደክሞ ሳይቻለው ሲቀር እንዳለ መተው ግድ ሆነበት ። ራስ ቍሩ በዚያ በተጣጣፈ አሮጌ ቍር ውስጥ እንደ ተጠፈረ ተቀምጦ ሲያዩት እጅግ በጣም አሥቂኝ ትርዒይት ነበር ።

የሆቴሏ ጌታም ፣ “ጀግናው ጌታዬ ሆይ ! አሁን ጥቂት ምግብ ቢቀምሱልን ? የራት ሰዓታችን ዐልፏል ! እንግዶቻችን ሁሉ ተመግበዋል ። ብቻምንም ቢሆን ጥቂት ምግብ ቢያገኙ መቼም ቅር አይሰኙም” አለ በአክብሮት እንጋገር ።

"እንዴታ ! ጥቂት የምቀምሰው ምግብ ካገኘሁ ግብግሣውን በደስታ እቀበላለሁ" አለና ዶን ኪኾቴ ፣ "አሁን ፣ አንድ ሁለት ጉርሻ በዓለም ካለው ነገር ሁሉ ይበልጥ ይጥመኛል ።"

መጥፎ አጋጣሚ ሆነና ዕለቱ ዓርብ የጾም ቀን ስለ ሆነ ሥጋ በቤቱ ውስጥ አልነበረም ። የተቀመጠውን ጥቂት የዐሣ ምግብ ሌሎች እንግዶች አስቀድመው አጣር ተውታል ።

"ከወንዝ ካጠመድናቸው ትኩስ ዐሣዎች ጥቂት ቢቀምሱስ ? ትናንሽ ቢሆኑም ፣ ተስማሚ ናቸው » አለ የሆቴሏ ባለቤት ።

"መልካም ፣ ብዛት ያላቸው ከሆኑ እንደ አንድ ትልቅ ዐሣ ቈጥሬ እጣጥማቸዋለሁ ። ብቻ ቤት ያፈራውን ፣ ያላችሁን ቶሎ አምጡልኝ ፤ የለበስኩት ጥሩር ክብደትና ረዥሙ ጉዞዬ ተዳምረው ከሳቴ ከርስ ሆነውኛል " አለ ዶን ኪኾቴ ።

ነፋሻ አየር እንዲያገኝ ተብሎ እንስተኛ ጠረጴዛ ወጥ ቤቱ በር አጠገብ ተዘጋጅቶለት ነበርና ፣ ዶን ኪኾቴ ወን በር ሳብ አድርጎ ተቀመጠ ። የሆቴሏ ባለቤትም በወጉ ያልበሰሉ ጥቂት የዐሣ ቁርጥራጮች አቀረበለት ። ያቀረ በለትም ዳቦ ልክ እንደ ዶን ኪኾቴ ጥሩር የሻገተ ነበር ። ከጥሩ ውሃ በስተቀር ሌላ የመጠጥ ዐይነት አልተገኘም ።

ምስኪኑ ዶን ኪኾቴ ፣ የቀረበለትን ምግብ ወደ አፉ እንዳያስጠጋ ከራስ ቅሉ የተጠፈረው ቍር ችግር ፈጠ ረበት ። በአንድ እጁ ቍሩን ወደታች ብሎ ይዞ ፣ በሌላው እጁ ምግብ ወደ አፉ ያስገባ ጀመር ። ረሃብ እንገብግቦት ነበርና አበላሉን ላየ በጣቅ ፍርስ ያደርግ ነበር ።

‘እውነተኛ ጀግና ለቀረበለት ምግብ በጭራሽ እቃ ቂር አያወጣም ’ አለ ለራሱ ።

ነገር ግን ፡ ድንገት የጥሩር-ለባሽ ፈረሰኝነትን ወግ ያልፈጸመ ፡ ያልተቀበለ መሆኑ ትውስ ሲለው ጊዜ መብላቱን አቆመ ። የመጨረሻይቱ ቁራጭ ፀሣ ሳትነካ ማዕዱ ላይ ቀረች ። የምግብ ፍላጎቱ ተገታ ።

‘ጉድ ፈላ ! ጉድ ፈላ ! ለካንስ የጥሩር-ለባሽ ፈረሰኝነት ማዕረግና ክብር ሕጋዊ በሆነ መንገድ ሳልቀዳጅ ለጀብዱ ሥራ መሠማራት አይቻለኝምና ። ይህ ጉዳይ በአስቸኳይ መፈጸም አለበት ’ አለና ፡ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ የሆቴሷ ባለቤት እስከ ፈረሶቹ ጋጣ ድረስ አብሮት እንዲሔድ ምልክት ሰጠው ። ቀጠል አደረገና ፡

“አንድ የማዋይዎት ጉዳይ አለኝ ” አለ ዶን ኪኾቴ በሹክሹክታ ድምፅ ።

“ ክቡር ሆይ ! ስለ ፈረስዎ ከሆነ አይጨነቁ ! የሚ በላው እጁ ተሰጥቶታል ። እንክብካቤ እንደምናደርግለት አረጋግጥልዎታለሁ ,, አለ የሆቴሷ ባላቤት በችኩላ ።

“እኔ ስለ ፈረሱ አይደለም በግል ላዋይዎት የፈለግ ሁት ” አለና ፡ ዶን ኪኾቴ በዝግታ መዝጊያውን ከበስተ ኋላቸው ሳብ አድርጎ ዘጋ ። ሳይጠበቅ ድንገት ከሆቴሷ ባለቤት እግር ሥር ተንበረከከና ፡ “ ጌታው የምለምንዎትን ጉዳይ ሊፈጽሙልኝ ቃል ካልገቡ በምንም ዐይነት ከተን በረከኩበት አልነሣም ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“የሆቴሷ ባለቤት የሚያደርገው ነገር ጠፋው ።ተጨ ነቀ ። ምስኪኑን ፍጡር ከተንበረከከበት ሊያነሣው ቢሞ ክርም ፡ ሳይቻለው ቀረ ። በመጨረሻም የግዱን ፡ “ እሺ ቃል እገባለሁ ፤ የማደርግልዎን ጉዳይ ካወቅሁት ልፈጽ ምልዎ ዝግጁ ነኝ ” አለ የሆቴሷ ባለቤት ።

" የተከበሩ ጌታዬ ሆይ ! የምለምንዎትን እንደማይ ነፍጉኝ አተማመናለሁ ። የምለምንዎትም ጉዳይ ፣ የጦር መሣሪያዎቼን እቤተ - ግንብዎ ጸሎት ክፍል ውስጥ ዛሬ ማታን አሳድሬ ከዚያም እስከ ንጋት ድረስ እንድጠብቅ ይፍቀዱልኝ ፤ ከዚያ - ከዚያ - ነገ በማለዳ . . ."

" ማለዳ በጾም ምን እንዳደርግልዎ ይሻሉ ? " የሆቴሏ ባለቤት አጥብቆ ጠየቀ ።

«ደግ ጌታዬ ሆይ ! ፈቃድዎ ከሆነ ፣ የጥሩር - ለባሽ ፈረሰኝነትን ክብር ያጐናጽፉኝ ። ዓለምን ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ እየዞርሁ የጀግንነት ጀብዱዬን እንድፈጽም ፣ ዓላማ ዬንም ከግቡ እንዳደርስ አስቀድሚ ሥርዓቱ በሚያዘው መሠረት ጥሩር ለባሽ ፈረሰኛ መደረግ አለብኝ ፤ መባል አለብኝ " አለ ዶን ኪኾቴ ።

የሆቴሏ ባለቤት በፈገግታ ዐይኖቹን አቁለጨለጨ ። ፈዘኛ በመሆኑና የሚያሥቀው ነገር በማግኘቱም ፍንድቅ ድቅ አለና ፣

" እንዴታ ! እንዴታ ! ጌታው የጥሩር - ለባሽ ፈረ ሰኝነትን ሙያ በመምረጥዎ ጀግና መባል አለብዎ ። እኔም ይህንን ክብርና ማዕረግ አጐናጽፍዎታለሁ ። እነሆ የጠየቁት ሁሉ ይፈጸምልዎታልና ከተንበረከኩበት እንዲነሡ እጠ ይቅዎታለሁ " አለ ሣቁ እፍን እያደረገው ።

"ምስጋና ይግባዎት ጌታዬ ! አሁን ወደ ቤተ -ግንብ ጸሎት ክፍልዎ ይምሩኝና የጦር መሣሪያዎቼን እዚያ ሳኑር ፤ እውነተኞቹ ጀግኖች አባቶቻችን ጥንት ይፈጽሙ የነበ ሩትን ሥነ - ሥርዓት እኔም እንዳከናውን ይሁን ።"

" በደስታ እወስድዎ ነበር ። ነገር ግን ለጊዜው በዚህ ቤተ-ግንብ ውስጥ የጸሎት ቤት የለም ። ቢሆንም የጦር

መሣሪያዎችዎን የሚኖያሩበትና ተገቢውን ሥነ ሥርዓት የሚያከናውኑበት ሌላ ተስማሚ ሥፍራ ልናገኝ እንችላለን ። ብዙዎቹ ታላላቅ ጀግኖች የጸሎት ክፍል በሌለበት ቦታ ሥነ ሥርዓቱን ማከናወናቸው ይታወቃል ” አለ የሆቴሏ ባለቤት ።

“ ክቡር ጌታዬ ሆይ ! ንግግርዎ ሁሉ ሐቅ እንደሆነ አምናለሁ ። የጥንት ጀግኖች እርስዎ እንዳሉትም በዚህ ዘዴ ሥነ ሥርዓቱን ይፈጽሙ ነበር ። የጸሎት ክፍል ስለ ሌለዎ ሥነ ሥርዓቱን በማንኛውም ቦታ ብንፈጽም ደስ ይለኛል ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“ እንግዲያው የጦር መሣሪያዎችዎን በቤተ-ማንፀ ደጃፍ ያኑሩና ልበ ሙሉ ሆነው እስኪነጋ ይጠብቁ ። ማለዳ በሐይ ብርሃንዋን ስትፈነጥቅ የጥሩር - ለባሽ ፈረሰኝነትን ማዕረግ እቀዳጅዎታለሁ ” አለ የሆቴሏ ባለቤት ኩራት እየተሰማው ።

“እመሰግንዎታለሁ ክቡር ጌታዬ ! መሣሪያዎቼን በፍጥነት ማምጣት አለብኝ ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“ቆዩ እስቲ ! ለመሆኑ ገንዘብ አለዎት ? ” በማለት ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ ።

“ቤሳ ቢስቲን የለኝም ። ባነበብኳቸው መጻሕፍት ውስጥ ሁሉ አንድም ጀግና ገንዘብ ይዞ ስለ መጓዙ አላጋጠመኝም ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“ እንግዲያውስ ተሳስተዋል ። ያነበቧቸው መጻሕፍት ስለዚህ ጉዳይ ምንም አላወሱም ይሆናል ። ደራሲያኑ እንደ ገንዘብና እንደ ንጹሕ ሸሚዝ የመሰሉትን ቀላል ጉዳዮች በድርሰቶቻቸው ውስጥ የማያነሡት እኮ ዋጋ እንደሌለው በማሰብ ነው ። ”

“ ይህን በሚመለከት አንድ ማሳመኛ ሊነግሩኝ ይች ላሉ ? ”

“ በቂ ማስረጃ ማቅረብ እችላለሁ ። ማንኛውም ጀግና ብሩን በኮረጆው አጭቆ ፣ ንጹሕ ሸሚዞችንና የቁስል ማከሚያ መድኃኒት መያዣ ትንሽ ሣጥን እንደሚይዝ አረጋግጬ ዐውቃለሁ ” አለ የሆቴሏ ባለቤት ።

“ ነገሩ ትክክል ይመስላል ። ብቻ እኔ ይህን ያህል አስቤበት አላውቅም ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“ እንግዲያውስ አባት ልጁን ምክር እንደሚለግሰው ሁሉ እኔም ልምከርዎ ። የጥሩር ለባሽ ፈረሰኝነትን ማዕረግና ክብር እንደ ተቀዳጁ ፈጥነው ወደ ቤትዎ ይመለሱና እነዚህን አስፈላጊ ነገሮች ሁሉ ያሟሉ ” አለ የሆቴሏ ባለቤት ።

“ ትእዛዝዎን እቀበላለሁ ፣ ክቡር ጌታዬ ” አለ ኪኾቴ ትሕትና በተመላበት አነጋገር ።

ዶን ኪኾቴ ፣ ፈጠን አለና የጦር መሣሪያዎቹን ሰብሰብ አድርጎ ወደ ፈረሶች ማሰሪያ ከወሰደ በኋላ ፣ ለፈረሶች ውሃ ማጠጫ ከተሠራው ገንዳ ውስጥ ጨመረ ። ጊዜው እየመሸ ሔዶ ፣ ጨለማው ለዐይን ያገ፣ ፣ ደንገዝገዝ ማድረግ ጀምሯል ። ዶን ኪኾቴ ፣ ጋሻውን በግራ ክንዱ አንግቦ በቀኝ እጁ ያንን ረዥም ጦሩን አጥብቆ ያዘ ። ከዚያም በፈረሶች ማሰሪያ ዙሪያ ከወዲያ ወዲህ ይንጐራደድ ጀመር ። ልክ ለግዳጅ እንደ ተሠማራ ወታደር ራሱን በንቃት ቀና አደረገ ። በአራፊ ጨርቅ የተበተበውን አሮጌ ቍር በግንባሩ ላይ ደፍቶ ሲታይ ፣ ግርማ ሞገስ ያለው ጀግና ከመምሰል ይልቅ አሥቂኝና ማስፈራሪያ መሰለ ።

የሙሉ ጨረቃ ብርሃን ጦር መታየት ጀመረ ። የፈረሱቹም ጋጣ ልክ እንደ ቀን ብርሃን ወለል ብሎ ይታያል ። የሆቴሏ ጌታና በውስጧም ያሉት እንግዶች በሆቴሏ መስኮት በኩል ዶን ኪኾቴ ምን ሊያደርግ እንደሚዘጋጅ ይመለከቱ ጀመር ። እንደ አጋጣሚ አንድ በቅሎ ነጂ በቅሎውን ውሃ ሊያጠጣ ወደ ገንዳው ሲጠጋ ፤ ገንዳው ውስጥ ምናምን ተከምሮበት አየ ። ከጉድጓዱ ውስጥ ውሃ ቀድቶ ገንዳውን ከመሙላቱ በፊት ፤ በውስጡ የተቆለለውን የጦር መሣሪያ አውጥቶ መጣል ሲጀምር ፤ ዶን ኪኾቴ ተንደርድሮ ወደ በቅሎ ነጂው ጠጋ አለና ፤

"ዕረፍ አንተ ክልፍልፍ ፤ ጥሩር-ለባሽ ፈረሰኛ ! እቻ የማይገኝለትን እነዚህን የጦር መሣሪያዎች አትንካ ! መሣሪያዎች ናቸው ። እንዳትነካ ብዬሃለሁ ። ከነካህ ግን የሕይወትህ ፍጻሜ ይሆናል " እያለ ዶን ኪኾቴ ያምባርቅ ጀመር ።

በቅሎ ነጂው ደደብና ፈዛዛ ቢጤ ነበርና ፤ የዶን ኪኾቴን ማስጠንቀቂያና ቁጣ ከጉዳይ ሳይጥፍ ፤ የጦር መሣሪያዎቹን ከገንዳው እያወጣ አሽቀንጥሮ ጣለ ። ዶን ኪኾቴ ደሙ ፈልቶ ፤

"አ ! የምማጠንሽ እመቤቴ ዱልሲኒያ ሆይ ! እነሆ በዚህ በመጀመሪያው ጀግንነት ክብርና ማዕረግ በምጐናጸፍበት ፍልሚያ ጊዜ እርጂኝ ! "ብሎ ድምፁን ከፍ አድርጎ ጮኸ ።

የረኸርሟ ጦሩን ሶማያ በሁለት እጆቹ በወኔ ጨብጦ ተንደርድሮ በበቅሎ ነጂው ሰውነት ላይ ቢያሳርፈው ፤ ምስኪኑ በቅሎ ነጂ በጋጣው አፏራ ላይ ተዘረረ ። እንደ መጀመሪያ አሰነዛዘሩ ቢደግመው ኖሮማ ፤ የበቅሎ ነጂው ሕይወት ባለፈች ነበር ። ነገር ግን ፤ ዶን ኪኾቴ በወደቀ ጠላት

ላይ እጅ ማንሣት የጀግንነት ክብሩን እንደሚቀንስበት ተሰማውና በንቀት ተወው ።

ጥሩሩን ከተጣለበት አንሥቶ ገንዳው ውስጥ መልሶ አስቀመጠ ። ምንም ነገር እንዳልተፈጸመ ሁሉ ዶን ኪኾቴ ከወዲያ ወዲህ ይንጐማለል ጀመር ። ምስኪን በቅሎ ነጂ ሕይወቱን ስቶ ገንዳው አጠገብ እንደ ተዘረረ ቀረ ። የሆቴሏ ባለቤትና እንግዶቹ በመስኮቱ በኩል ይህን ሁሉ ትርዒይት ይመለከቱ ነበር ።

"ይህ ሰው እጉል ግትር መሆን አለበት" አለ ከተመልካቾቹ አንዱ ።

"እረ እንዲያውም ንክ ሳይሆን አይቀርም" ሌላው ተመልካች አስተያየቱን ሠነዘረ ።

ወዲያው አንድ ሰፍላፊ ጋሪ ነጂ ፈረሶቹን ውሃ ሊያጠጣ ወደ ጋጣው መጣ ። ከገንዳው ውስጥ የነበረውን የጦር መሣሪያ አውጥቶ ፈረሶቹን ሊያጠጣ ዝግጅቱን ቀጠለ ።

ዶን ኪኾቴ ፣ ከዳር ሆኖ ሊያጠቃው እንዳደባ ምስኪኑ ጋሪ ነጂ ግን አላወቀም ነበር ። አንዳች ቃል ሳይተነፍስ ፣ ዶን ኪኾቴ ጦሩን ሰብቆ የጋሪ ነጂውን ራስ ቅል ፈነከተው ። እንደ አመታቱ ቢሆን ራስ ቅሉ ለሁለት ክፍል ብሎ ያለመውደቁ ተአምር ነው ። ጋሪ ነጂው መሬት ላይ ተዘርሮ በኡኡታ አካባቢውን አደበላለቀው ። የሆቴል ቤቷ እንግዶች ሁሉ በዚህ አስገራሚ ድርጊት ተደናግጠውና ተሸብረው ፣ ይህን የምር ጨዋታ ለመሣታት ወደ ፈረሶቹ ጋጣ ተግተልትለው ይጎርጎጡ ጀመር ።

የሰዎቹን ወደ እርሱ መጐርጐጥ ተመልክቶ ፣ ዶን ኪኾቴ ጋሻውን አመቻችና ጐራዴውን መዝዞ በወኔ ሲጽቋግጥ ይጠባበቅ ጀመር ።

'የኔዋ ዱልሲኒያ ! አንቺ የቁንጅና ንግሥት ! እባክሽን ክንዴን አፈርጥሚው ፤ በእጅጉ ለሚመታው ልቤም ድፍረት ስጭው !' አለ ዶን ኪኾቴ ሰራሱ ። ትንፋሹን ቀጥ ካደረገ በኋላ ፤ በዓለም ላይ የሚገኙትን ጋሬ ነጂዎችና በቅሎ ጫኞች ሁሉ ወግቶ ማንበርከክ የሚችል እንደሆነም ታሰበው ። ነገር ግን ፤ ወዲያው የተጐዳው ነጂ ወዳጅ በመዶች ተሰብስበው ወደ ጋጣው እየሮጡ መጡና፣የድንጋይ ናዳ ያወርዱበት ጀመር ። ያ ሁሉ የድንጋይ መዓት ራስ ቅሉን እንዳይመታው ዶን ኪኾቴ በጋሻው ይከላከል ገባ ። ይህ ሁሉ ሲሆን ፤ በልበ ሙሉነት ከነበረበት ቦታ ፈቀቅ ሳይልና መሣሪያውንም ሳይጥል ጉብዝናውን በአደባባይ አስመሰከረ ።

"በርቱ ! የቻላችሁትን አድርጉ ! እኔ እስከ ቆምኩበት ክልል ድረስ መቅረብ ትችላላችሁ ፣ ሞክሩ !" እያለ ዶን ኪኾቴ ፉከራውን አቀለጠው ። ድርጊቱንና ፉከራውን የሰሙ ሁሉ በፍርሃት ተርበድብደው ወደ ኋላ ያፈገፍጉ ጀመር ። ገሚሶቹም የፈረሶቹን ጋጣ ምሽግ አድርገው በድንጋይ ውርጅብኝ ያጣድፉት ገቡ ።

የሆቴሏ ባለቤትም ድምፁን ከፍ አድርጎ ፤ "እባካችሁ ተውት አድርጓቸው ፤ የእሳቸው ፍላጎት ማንንም የሚጐዳ አይደለም ። 'ጥሩር - ለባሽ ፈረሰኛ' ለመባል ፣ ክብርና ማዕረጉንም ለመቀዳጀት ብቻ ነው ዓላማቸው ። ብሁ በማንበብ ናላቸው የዞረ በመሆኑ ፤ እባካችሁን ለቀቅ አድርጓቸውና እናንተም ሰላሙን ስጧቸው ፤ ወደ መጣችሁበት ተመለሱ" እያለ ወተወተ ።

ይህን እንደ ሰሙ ሰዎቹ ወዲያው ድንጋይ ውርወራቸውን አቆሙ ። ዶን ኪኾቴም ጋሻውን ከመከተበት አውርዶ ፡ በውሃ ግጠጫውና በጋጣው መካከል በኩራት ይን

ጐራደድ ጀመር ። አሽከሮች መጥተው ቁስለኛውን ጋሪ ነጂና ሕሊናውን የሳተውን በቅሎ ጫኝ ከየወደቁበት አን ሥተው እንዲወስዱ ዶን ኪኾቴ ፈቃደኛ ሆነ ። በእጁ ስበብ ሳይሆን በመትረፋቸው ሊደሰቱ እንደሚገባ ዐይኑን እያጉረጠረጠ ገለጠላቸው ።

የሆቴሏ ባለቤትም ይህ ቀልድ መሰል ጨዋታ መፆ መር እያለፈ የምር መሆኑ በጣም አሳሰበው ። የባሰ አደ ጋና ችግር እንዳይፈጠርም ተጨነቀ ። በጨዋ ደንብ ወደ ዶን ኪኾቴ ቀረብ አለና ፤

"የተከበሩት ጀግና ሆይ ! ከሚገባዎ በላይ ጀብዱ ፈጽመዋል ። የጦር መሣሪያዎችዎንም በቆራጥነትና በክ ብር ጠብቀዋል ፤ ለጥሩር-ለባሽ ፈረሰኝነት ብቁ መሆንዎ ንም አስመስክረዋል ። ስለዚህ ለአንድ ጀግና የሚገባውን ክብርና ማዕረግ አሁኑኑ እጐናጽፍዎታለሁ " አለ የሆ ቴሏ ባለቤት ።

ዶን ኪኾቴም ጀነን ብሎ ፡ "ሌሊቱ ገና አልነጋም ፤ ጐህ እስኪቀድ ድረስ መሣሪያዎቼን መጠበቅ ይገባኛል" አለ ።

"ሌሊቱ እስኪነጋ መጠበቅ አስፈላጊ አይደለም ። አንዳንድ በጣም ስመ ጥር ጀግኖች ለሁለት ሰዓታት ብቻ ዘብ ሆነው የጦር መሣሪያዎቻቸውን እንደ ጠበቁ ከመ ጻሕፍት አንብቤአለሁ ። እርስዎ ግን አራት ሰዓት ሙሉ ከመጠበቅ ዐልፈው የተፈታተኑዎትን ጠላቶች ሁሉ ድባቅ መትተዋቸዋል "አለው የሆቴሏ ባለቤት ፤ በፈገግታ ።

"አንድ ሰው የጀግንነት ግዳጁን በሚያከናውንበት ወቅት ሰዓታት ይነጉዳሉ " ካለ በኋላ ፤ ጀግና ጀግንነ ቱን የሚያስመሰክረው ንዴቱን ሲቈጣጠር ብቻ ነው ።

ከእንግዲህ ግን ፣ ማንም ሰው ሊያጠቃኝ ቢቃጣ ቁጣዬን እንታስሁ ማለት ዘበት ነው ። እንዲያውም እርስዎን ለማ ስደሰት ካልሆነ በቀር ከዚህ ቤተ-መስፍን ውስጥ አንድም ሰው አይተርፈኝም ” አለ ዶን ኪኾቴ እየተጐማለለ ።

“እረ ማንም ከእንግዲህ አይደፍርዎትም ። የጦር መሣ ሪያዎችዎን ለበቂ ጊዜ ጠብቀዋል ። እና ፣ ፈቃድዎ ከሆነ አሁኑኑ ለጀግኖች የሚገባውን ክብርና ማዕረግ ላቀዳጅዎ” አለ የሆቴሏ ባለቤት ።

“ከዚህ የበለጠ የሚያስደስተኝ አንዳችም ነገር አይ ኖርም” አለና ጒንበስ ብሎ ጦሩን ከጥሩሩ ገዶን አጋደመ ። የሆቴሏ ባለቤትም ፣ በሆቴሏ ውስጥ የሚገኙትን እንግዶችና አስተናጋጆች በሙሉ መጥተው ለጀግና ክብር የሚፈጸ መውን ሥነ ሥርዓት እንዲመለከቱ ጠራቸው ። የማር ድርቆሹና የገለባ ሒሳብ የሚያሰፍርበት መዝገቡን እንደ መጽሐፍ ገልጦ ያዘ ። ያንን መዝገብ በታላቅ ክብር እፊት ሲይዝ ፣ ዶን ኪኾቴ ዐይኖቹን ከድኖ ጥሩሩ አጠገብ ቆመ ። በሆቴሏ ውስጥ የሚያገለግሉ ሴቶችም በዶን ኪኾቴና በሆ ቴሏ ጌታ ዙሪያ ተሰባሰቡ ። የሆቴሏ ባለቤት ሊሥነ ሥር ዓቱ ተገቢውን ምዕራፍ ከመጽሐፉ (ከመዝገቡ) ውስጥ እንደሚያነብ ሲያስመስል አንድ ወንድ ልጅ ደሞ የሻማ ቁራጭ አብርቶ አጠገቡ ቆመ ።

“የንባቡ ሥነ ሥርዓት ከተፈጸመም በኋላ ፣ ዶን ኪኾቴ አቧራ ላይ እንደ ተንበረከከ ቀረ ። የሆቴሏ ባለቤ ትም እጁን በዶን ኪኾቴ ላይ ዘርግቶ ትርጉም የለሽ ቃላት ከቀበጣጠረ በኋላ ፣ የዶን ኪኾቴን አንገት በጁ አጮለና ፣ በጐራዴው ጠፍጣፋ ገዶን ጀርባውን ጠንከር አድርጎ ጠሩና ፣ “የተከበሩት ጥሩር ለባሽ ፈረሰኛ ! ከተንበረከኩ በት ይነሡ ! የጀግኖች ጀግና የላማንቻው ዶን ኪኾቴ ማለት

እርስዎ ነዎት ። ደፋርይ ሁኑ ፣ ደፋር ይሁኑ ፣ ለዘለዓለም ደፋር ሁን !" አለ የሆቴሏ ባለቤት ድምፁን ከፍ አድርጎ።

ዶን ኪኾቴም ፣ በርግጥ የጀግና ክብርና ማዕረግ እንደ ተቀዳጀ ተሰምቶት ፣ ጀብዱ ሥራዎች ለማከናወን ይበልጥ መንፈሱ ነቃቅቶ ከተንበረከከበት ተነሣ ። ከሴቶቹ መካከል እንዷ ጉራዴውን እንሥታ በእጁ ካስጨበጠችው በኋላ ፣ "ዕድለኛ ጥሩር- ለባሽ ፈረሰኛ እንዲሆኑ እመኛለሁ" አለችው ። ሌላዋ ወይዘሮ ፣ ከራሱና ከቍሩ ጋር የተጠፈረውን አረንጓዴ እራፊ ጨርቅ እያስተካከለች ፣ "ብልጽግናና የጀብዱ ሥራ በየሔዱበት ሁሉ ያጋጥምዎ" አለችው ።

ዶን ኪኾቴ ፣ መሣሪያውን እንዲያዘ ከሆቴል ቤቷ ጌታ አንገት ላይ ተጠመጠመና የምስጋና ቃላት አጕረፈለት ። አንድ የጀብዱ ሥራ ካልፈጸመ ልቡ ዕረፍት እንደማያገኝ ለዶን ኪኾቴ ተሰማው ። ሌሊቱን ሙሉ የጦር ልብሱን ሲወለውልና በማግሥቱ ስለሚፈጽመው ጀግንነት በእንክሮ ሲያሰላስል ፣ እንዳይነጋ የለምና ነጋ ።

ከገበሬው ጋር የተደረገ ፍልሚያ

ማለዳ ፀሐይ ብርሃንዋን ስትፈነጥቅ ፣ ዶን ኪኾቴ የጀብዱ ሥራውን ለመጀመር ዝግጁ ሆነ ። ጥሩሩን ለብሶ ቍሩን አጥልቆ ፣ ጦሩን ሰብቆ ፣ ጋሻውን አንግቦ በአዲስ መንፈስ ተነሣሣ ። ቅብጥብጥ ፈረሱ ሮሲናንቴ በኮርቻ አምሮ በሎኮ ተይዞና ተለጉሞ ፣ ከሆቴል ቤቷ በር ላይ በንቃት ይጠባበቃል ።

ዶን ኪኾቴ በሆቴሏ ባለቤት አንገት ላይ ዳግመኛ ተጠምጥሞ ፣ "ታላቁ የክብሬና የማዕረጌ ጌታ ሆይ !

የጥሩር ልባሽ ፈረሰኝነትን ክብር ስላቀዳጃኝ በረከቱን ይስጥዎ ። በቸር ይግጠመን ። ደህና ይሁኑ ! ” በማለት ድምፁን ከፍ አድርጎ አመሰገነ ።ከዚያም ፣ አንድ የሆቴል ቤቱ ሮባልደራስ”ርካቡን ይዞለት ዶን ኪኾቴ ሡንጋ ፈረሱ “ሲናንቴ ላይ ጉብ ብሎ ለሌላ ጀብዱ ተሠማራ ።

ጉዞው የደስ ደስ የተሞላበት ነበር ። ምክንያቱም እንደ ፍላጐቱ በርግጥም የጀግንነት ክብርና ማዕረግ ተቀዳጅቷል ። መንፈሱ ሁሉ በታላላቅ የጀብዱ ሥራ ውጥኖች ተወጥሯል ። ሮሲናንቴም በአውራ ጐዳናው ላይ በሶምሶማ ሲጋልብ ፣ በኩራት ራሱን ቀና አድርጎ ነበር ። የወንዶችን ወንድ ዶን ኪኾቴን መሸከሙን ያውቅ የለምን ?

ጥቂት እንደ ተጓዘ ፣ የሆቴሏ ባለቤት አንድ ጀግና በቂ ገንዘብ ፣ ንጹሕ ሸሚዞችና የቁስል መድኃኒት መያዝ እንደ አለበት ያዘዘው ጉዳይ ትዝ አለው ።

‘ ትእዛዙ በሙሉ መከበር አለበት ፤ ወደ ቤት ተመልሼ እነዚያን ጠቃሚ ዕቃዎች መያዝ አለብኝ ’ አለ ዶን ኪኾቴ ። ወዲያው የፈረሱን ልጓም ሳብ አድርጎ ወደ ራሱ መንደር የሚወስደውን ጐዳና ተያያዘው ።

በዚህን ጊዜ ፣ ሮሲናንቴ ከሲታ ሰውነቱና ደካማ ጉልበቱ አዲስ ሕይወት አገኘ ። ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለ በፍጥነት ሲጋልብ እግሮቹ መሬት የሚረግጡ አይመስሉም ነበር ። ዶን ኪኾቴም ፣ ‘ የጀግኖች ሙያ ይሏል ይህ ነው ። ቢሆንም የሚጐድለኝ አንድ ነገር አለ ። ዘወትር ከእኔ ጋር በዓለሙ ሁሉ የሚዞርና የሚያገለግለኝ አንድ ታማኝ ጋሻ ጃግሬ ያስፈልገኛል ። ማንኛውም ጥሩር-ለባሽ ከሥ ር ከሥሩ ሆኖ ግዳይ መጣሉን የሚመሰክርለት ጋሻ ጃግሬ ያስከትል እንደ ነበር ያነበብኳቸው መጻሕፍት ይተርካሉ ። ስለዚህ ገንዘብና ሸሚዞች ከያዝኩ በኋላ ፣ ጋሻ ጃግሬም ማግኘት አለብኝ ’ አለ ዶን ኪኾቴ በኩራት መንፈስ ።

ዶን ኪኾቴ፤በፈረሱ ላይ ሆኖ ጭውና ጭር ባለ ሥፍራ ሲያልፍ አሳዛኝ የጩኸት ድምፅ ድንገት የሰማ መሰለው ፤ የጩኸቱም አቅጣጫ ጥቅጥቅ ካለ ጫካ ውስጥ ሆኖ ከመንገዱ ትንሽ ገባ ይል ነበር ።

ዶን ኪኾቴም የፈረሱን ልጓም ገታ አደረገና ፤ ‘ ለዚህች ዕድሌኛ ጊዜ ምስጋና ይገባታል ። እነሆ የጀግን ነት ግዳይ (በለስ) ሊገጥመኝ ነው ። አንድ አደጋ የደረሰ በትን ሰው በተጋድሎ እንደማድነው አልጠራጠርም ። ወይም አንዳች የሆነ በደል በመፈጸም ላይ ይሆናልና በዳዩን ልክ አገባዋለሁ ’ አለ የልብ ልብ እየተሰማው ።

ሮሲናንቴን በእርካቡ ኰርኰር አድርጎ ፡ ፍጥነቱንም በተቻለው መጠን ጨምሮ የጩኸት ድምፅ ወደ ሰማበት ጥቅጥቅ ጫካ አካባቢ ደረሰ ። በጫካው ጠርዝ አንድ ፈረስ በአንስተኛ ዛፍ ላይ ታስሮ አገኘ ። በዚያው አካባቢ አንድ የዐሥራ አምስት ዓመት ወጣት በሌላ ዛፍ ግንድ ላይ ታስሮ አየ ። ትከሻውና ጀርባው ራቁቱን ሆኖ የታሰረው ወጣት ነበር ፡ ያንን አሳዛኝ ጩኸት የሚያሰማው ። የሚጮኸውም አንድ ወጣት ገበሬ ያለ ርኅራኄ በአለንጋ ይገርፈው ስለ ነበር ነው ።

ዶን ኪኾቴ ቀረብ ብሎ፡ “አቁም ብየሃለሁ ! አቁም !” ብሎ አምባረቀና ፡ “ መልሶ ሊመታህ የማይችለውን ምስኪን ሰው መግረፍ ከወንድነት አይቈጠርም ! አቁም !” አለ በቍጣ መንፈስ ። ገበሬውም ሳያስበው አንድ ጥሩር ለባሽ ፈረሰኛ ድንገት ከተፍ በማለቱ በፍርሃት ተርበደበደ ። አለንጋውን ወዲያ ጥሎ ፡ ጭንቀት ገብቶት ሰውነቱ እየራደ ፡ ምን እንደሚያደርግ ግራ ገብቶት ተገትሮ ቀረ ።

ዶን ኪኾቴም ድምፁን ከፍ በማድረግ ፤ “ ጌታው ! ና ወዲህ ” አለና ትክ ብሎ ከተመለከተው በኋላ ፡ “ ጦርህን

ያዝ ። ፈረስህም ላይ ውጣ ፤ ይህንን ጉዳይ በመጣሪያ ዳኛ ነት እንወጣዋለን ’ አለ በቁጣ እንደበት ።

ገበሬው ግን በትሕትና እንዲህ ሲል መለሰ ። “ክቡር ጥሩር- ለባሽ ፈረሰኛ ሆይ! ይህ ልጅ አሽከሬ ነው ።ሥራ ውም በጎቼን ማገድ ነው ። ሰነፍና ግድየለሽ ከመሆኑ የተነሣ ፣ በርሱ ንዝህላልነት እነሆ ካረባኋቸው በጎች ውስጥ ግማሾቹን አጥቻለሁ ” አለ ገበሬዉ ።

“ቢሆንስ?”አለና ዶን ኪኾቴ ፣ “መልስ እንደማይ መታህ እያወቅህ ፣ እሱን ለማጥቃት መብትህ አይፈቅድ ልህም ” አለ ኮስተር ብሎ ።

“መልካም ልጅ ይሆን ዘንድ ነው ፣ የምቆጣው ። አስተዳደጉ እንዲሰምር ስቀጣው እሱ ግን፡በሐሰት ቀለቡን ለማስቀረት ያደረግሁ አስመስሎ ይወነጅለኛል ። አሁን እዚህ እየቀጣሁት እንኳ ከመዋሸት አልተመለሰም ” አለ ገበሬዉ ።

“ምን አልክ? እዚሁ እኔ ፊት፣ ‘ውሸታም ነው’ ብለህ ትናገራለህ? በያዝኩት ጦር ገላህን ልበሳሳው ተዘጋጅቻ ለሁ ። በል ፈጥነህ ልጁን ከታሰረበት ፍታውና ፣ ገንዘቡ ንም ክፈለው ። አሁኑኑ ትእዛዜን መፈጸም አለብህ ። እን ዳች የቅሬታ ቃል ካንተ መስማት አልሻም ” አለ ዶንኪ ኾቴ ድምፁን ከፍ አድርጎ ።

ገበሬው በፍርሃት ሰውነቱ ራዶና ልጁን ከታሰረበት ግንድ ፈትቶ ለቀቀው ።

ዶን ኪኾቴ ወደ ልጁ ፊቱን መለስ አድርጎ ፣ “ አንተ ጉብል ! ለመሆኑ ይህ ገበሬ ሊከፍልህ የሚገባው ገንዘብ ምን ያህል ኖሯል ? ”

"በወር ሰባት ብር ሒሳብ የዘጠኝ ወር ቀለቤን አል ከፈለኝም" አለ ልጁ ።

" ዘጠኝ ጊዜ ሰባት ስድሳ ሦስት ነው" አለና ዶን ኪኾቴ ፡ "ጌታው ! ለዚህ ልጅ ስድሳ ሦስት ብር ልትከፍ ለው ይገባል ። ሕይወትህን ለማትረፍ ከፈለግህ ከመቅጽ በት እንድትከፍለው ይሁን !" አለ በቁጣ ።

ገበሬዉ ፡ ከበፊቱ አሁን ይበልጥ በፍርሃት ይናጥ ጀመር ። በጉልበቱ ተንበርክኮ እጆቹን ለምሕረት ልመና ወደ ሰማይ ዘርግቶ ተንሰፈሰፈ ።

"የተከበሩት ጌታዬ ሆይ! የጠየቀኝ ገንዘብ እጅግ ብዙ ነው ። እንዲያውም ሦስት ሙሉ ጫማ ፣ እያንዳንዱን በብር ሒሳብ ገዝቼለታለሁ ። ሁለት ጊዜ ታሞ ለሐኪም ብር ከፍዬለታለሁ" አለ ገበሬዉ ።

ዶን ኪኾቴም ፣ "ሊሆን ይችላል ። ነገር ግን ፣ ይህ ሒሳብ ያለ በቂ ምክንያት ለደበደብከው ካሣ ይታሰብለ ታል ። ጠቅላላውን ሒሳብ በል አሁን ክፈለው" አለ በቁጣ ።

ገበሬዉም ፣ "ትእዛዝዎን በደስታ እፈጽማለሁ ። አሁን ለጊዜው በኪሴ አንድ ሳንቲም እንኳ አልያዝኩም ፤ ልጁ ከእኔ ጋር ቤቴ ድረስ እንዲሔድ ትእዛዝ ከሰጡልኝ ገንዘቡን በሙሉ እከፍለዋለሁ" ሲል ገበሬዉ በትሕትና መለሰ ።

ልጁም ድምፁን ከፍ አድርጎ እየጮኸ ፣ "እኔ እሱ ቤት ልሔድ? አላደርገውም ! ደብድቦ ይገድለኛል እንጂ ገንዘቤን እንደሆነ አይከፍለኝም ።"

"ብጭራሽ አያደርገውም ። እንዲከፍልህ አዝዝ ዋለሁ ፤ ትእዛዜን መፈጸም አለበት ። ገንዘቡን ግን ፣ ቤቱ

ስለሆነ ፣ ሑዶ እንዲያመጣ ፈቅጄለታለሁ ። የጥሩር-ለባሽ ፈረሰኝነት ክብሩክ ዕዳውን እንዲከፍልህ ያስገድደዋል” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“የምን ጥሩር-ለባሽ ፈረሰኛ! ኧረ እሱ ጥሩር- ለባሽ ፈረሰኛ አይደለም ፤ ጆን ሐል ዱዶ የተባለ ገበሬ ነው እንጂ” አለ ልጁ በማናናቅ ።

“ታዲያ ምን አለበት! ከሐልድዶ ቤተሰብ ጥሩር-ለባሽ ፈረሰኛ ሊወጣ ለምን አይችልም?”አለ ዶን ኪኾቴ በፌዝ ድምፅ ።

“ጥሩር-ለባሽ ፈረሰኛ ነው ካሉም ይሆን አይመስለኝም ። ቢሆንም ዕዳውን በከፈለ ነበር!” አለ ልጁ ለስልስ ባለ አንደበት ።

“እዝዤዋለሁና ይከፍልሃል” አለና ዶን ኪኾቴ ፊቱን ወደ ገበሬው መለስ አድርጎ ፣ “ትእዛዜን መፈጸምህ ይረጋገጥ ዘንድ በል አሁን ሒድ ። እኔም በዚሁ መንገድ በፍጥነት እመለሳለሁ ። ያዘዝኩትን ባትፈጽም ግን አንተን አያድርገኝ ። እንደ እስስት ሰውነትህን ለዋውጠህ ብትሸሸግ እንኳ የገባህበት ገብቼ አገኝሃለሁ” አለ ዶን ኪኾቴ በሚያስፈራራ ገጽታ ።

ገበሬዉ ከተንበረከከበት ብድግ ብሎ ፣ ሐሳቡን ሲናገር ሲል ፣ ዶን ኪኾቴ ሊያዳምጠው አልፈለገም ። ከዚያም ድምፁን ከፍ አድርጎ ፣ “አንድ ቃል ልሰማ አልሻም ፤ መታዘዝ እንጂ መልስ መስጠት ያንተ አይደለም ። ይህን የሚያዝህ ሰው ማን እንደሆነ ማወቅ ከፈለግህ መልሱ ፣ አጥፊዎችን ቀጪው የጭቁኖች አለኝታ ጥሩር-ለባሹ ፈረሰኛ ዶን ኪኾቴ ዴ ላ ማንቻ መሆኑን ብትጠይቅ ትረዳለህ” አለና ፣ “ለማንኛውም ደኅና ሁን!” ብሎ ሮሲናንቴን ኰርኵሮ ግልቢያውን ቀጠለ ።

ገበሬዉም ዶን ኪኾቴ ከዐይኑ እስኪርቅ እተኩሮ ተመለከተው ። ርቆ መሔዱንም ካረጋገጠ በኋላ ፡ ወደ ልጁ መለስ ብሎ ፡ "አንድሪው ! ወደ እኔ ጠጋ በል ! ያለብኝን ዕዳ እከፍልሃለሁ ። ለተጨቆኑ ሰዎች አለኝታ የሆነውን ሰውዬ ትእዛዝ እንድፈጽም ና ወዲህ " አለ በፌዝ አነጋገር ።

"ትእዛዙን መፈጸም ይበጅሃል ። አሁን ገንዘቤን ካል ከፈልከኝ ተመልሶ ይመጣና ነገሩን ያከርብሃል " አለ ልጁ ።

"እንዴታ በውቃለሁ ! ደኅና አድርጌ እከፍልሃለሁ ፤ ምን ያህል እንደማፈቅርህም በተግባር አሳይሃለሁ " አለና ገበሬዉ ሌላ ቃል ሳይጨምር ፡ ወዲያው ልጁን ጨምድዶ ከዛፍ ጋር ጠፍሮ አሰረው ። ልጁም አምርሮ ይጮኽ ጀመር ። ዶን ኪኾቴ ርቆ ሔዷልና ማን ይድረስለት ።

ገበሬዉም በቡጢና በዱላ ልቡ እስኪጠፋ ድረስ ልጁን እንክት አድርጎ ደበደበው ። ቁጭቱን ከተወጣ በኋላ ፈትቶ ለቀቀውና ፡

"በል ወዳጄ አንድሪው ፡ አሁን የጭቁኖች አለኝታ የሆነውን ጓደኛህን ፈልግና ፡ ደኅና አድርጌ እንዴት እንደ ከፈልኩህም ግለጽለት " አለው በፌዝ አነጋገር ።

ምስኪኑ አንድሪው ቃል አልተነፈሰም ። እየተሽ መደመደ በዝግታ መንገዱን ቀጠለ ። ገበሬዉም ፈረሱ ላይ ቁብ አለና በአረመኔያዊ ድርጊቱ እየተኩራራ ወደ ቤቱ አመራ ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ፡ ዶን ኪኾቴ ወደ ራሱ መን ደር በመገሥገሥ ላይ ነበር ። በመጀመሪያ በአጋጠመውና በፈጸመው የጀብዱ ሥራ እጅግን ተደስቷል ። በጀግንነ ቱም ልቡ በኩራት ተሞልቷል ። በጉዞውም ላይ ፡

‘ ዱልሲኒያ ሆይ! አንቺ የቆንጆዎች ቆንጆ ፣ ደስ ሊልሽ ይገባል! ዛሬ ያንቺ ጥሩር - ለባሽ ፈረሰኛሽ ታላቅ ጀብዱ ፈጽሟልና ! ’ እያለ ጦሩን ከጥሩሩ እየሰካ በወኔ ልቡን ሞልቶ ፣ ጉዞውን ወደፊት ቀጠለ ።

ከገበያተኞች ጋር ጦርነት

ዶን ኪኾቴ ሦስት ኪሎ ሜትር ያህል እንኳ ርቆ ሳይጓዝ ፣ ብዙ ፈረሰኞች ወደ እርሱ አቅጣጫ ሲገሠግሡ ተመለከተ ። የቶሌዶ ነጋዴዎች ሲሆኑ ፣ የሐር ጨርቃ ጨርቅ ለመሸመት ወደ አንድ ከተማ የሚጓዙ ነበሩ ። ብዛታቸው ስድስት ሲሆን ፣ እያንዳንዳቸው ለፀሐይ መከ ላከያ ጥላ አጥልተዋል ። አራት እግረኞችና ሦስት በቅሎ ጫኞችም ተከትለዋቸዋል ። ዶን ኪኾቴ፣ይህንን የሰው አጀብ ባየ ጊዜ ልቡ ክፉኛ ይመታ ጀመር ።

‘እነሆ ለእኔነቴ መፈተኛ የጀብዱ ሥራ አጋጠመኝ’ አለ ድምፁን ከፍ አድርጎ ።

እርካቡን ቆንጥጦ ፣ ጦሩን ነቅንቆ ፣ ጋሻውን ከደረቱ ፊት መክቶ ፣ ስፍልሚያ ተዘጋጀ ። በመንገዱ መኻለኛ ሥፍራ ካለው ጉብታ ላይ እንደ ምሰሶ ቀጥ ብሎ ቆመ ። ነጋዴዎቹ ወደ እርሱ አካባቢ እንደ ተጠጉና እንደሚሰሙትም ካረጋገጠ በኋላ ፣

“ባለህበት ቁም ! አንድም ሰው እንዳይነቃነቅ ! የቶቦሳዋ ዱልሲኒያ በዓለም ካሉት ሴቶች ሁሉ ወደር የማይገኝላት እመቤት መሆንዋን ለማወጅ ዝግጁ ካልሆነ በቀር ማንም በዚህ ማለፍ አይችልም” በማለት ዶን ኪኾቴ ድምፁን ከፍ አድርጎ ትእዛዝ ሰጠ ።

ነጋዴዎቹም ይህ መንገድ ዘግቶ የተገተረው ፍጡር እስደንጿቸው ባሉበት ቆሙ ። ሆኖም የጠረጠሩትን ጉዳይ እውነትነት ለማረጋገጥ ጊዜ አልፈጀባቸውም ።

‘ ናላው የዞረ አንድ ምስኪን መኾንን መሆን አለበት፡’ ኢያሉ እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ ። የነጋዴዎቹም መሪ ጥቂት ርምጃዎች ወደፊት ከተራመደ በኋላ ፣ ለጀግናው የአክብሮት ሰላምታ ሰጠ ። ቀጥሎም ፣ “ ክቡር ጥሩር-ለባሽ ፈረሰኛ ሆይ ! አሁን ስሟን የጠሯትን ውብ እመቤት ማን ነት በእውነቱ እኛ አናውቅም ። ነገር ግን ፣ እንድናውቃት ቢያደርጉና እርስዎ እንደሚሉትም ቆንጆ ሆና ብትገኝ እኛ እንድንፈጽምለዎት የሚፈልጉትን ሁሉ ልናደርግ ዝግጁ ነን ” አለው በትሕትና ።

“ብትፈልጉ ላሳያችሁ እችል ነበር ።እንዲያውም እንዳ ላሳያችሁ የሚያግደኝ ነገር አይኖርም ። ቁም ነገሩ ይህ ሳይሆን ፣ ሳታዩዋት በቁንጅናዋ እንድታምኑና እንድታ ረጋግጡ እፈልጋለሁ ። በሉ አሁን ቀኝ እጃችሁን ወደ ላይ እንሠ ብላችሁ እንምታችሁ ፣ የምጠይቃችሁን ሁሉ እንድትፈጽሙ እሻለሁ ” አለ ዶን ኪኾቴ ድምፁን ከፍ አድርጎ ።

ነጋዴዎቹም እንዳች መልስ ሳይሰጡ ኮርቻዎቻቸው ላይ በጸጥታ ተቀመጡ ።

ዶን ኪኾቴ ደሙ ፈላና ፣ “እንዴ ! ጸጥ አላችሁ ! እን ግዲያው ጠላታችሁ መሆኔን ተረዱ ፤ እዚችው ቦታ ላይ አሁኑኑ እፋለማችኋለሁ ” አለ በቁጣ እንደበት ።

በኮርቻው ላይ ተመቻችቶ ጦሩን ሰበቀ ። ነጋዴዎቹ ግን ንግግሩን ከምንም ሳይቆጥሩ መልስ ሳይሰጡት ቀሩ።

“ፈርታችኋል መሰለኝ እናንተ ቡከኖች ! አንድ በአ ንድ ኑልኝ ። ብትፈልጉ ሁላችሁም በአንድነት ግጠሙኝ፣

ለፍልሚያው ዝግጁ ነኝ!" አለ ጀግናው ዶን ኪኾቴ ጉብታው ላይ ሆኖ ድምፁን ከፍ አድርጎ ። ከዚያም ፈረሱን ኮርኩሮ በሚያስፈራ እንቅስቃሴ ለጉድ ወደሚመለከቱት ነጋዴዎች ቁልቁል ጋለበ ። ፈረሱ ሮሲናንት ገራም ባይሆን ኖሮ ፡ ከባድ አደጋ በደረሰ ነበር ። ነገር ግን የጉትጎታ ፈረስ ኻያ ሜትር እንደ ተራመደ ተደናቀፈና አጠገባል መንገድ ላይ ተንከባለለ ። ዶን ኪኾቴም ፡ በጭንቅላቱ አቧራው ላይ ተተከለና ከዚያው ተዘረረ ። ረዥም ጦሩ ከእጁ ተፈትልኮ ከመንገድ ወዲያ ማዶ አራሙቻ ውስጥ ወደቀ ። ጋሻው ደግሞ በአንድ በኩል ቁጥቋጦ ውስጥ ገብቶ ተመስገ ። ጀግናው ዶን ኪኾቴ አቧራ ላቧራ ሲንከባለል ላየው የሚያሥቅ ነበር ። የሻገተው ጥሩር ከብደት ከወደቀበት እንዳይነሣ ከመሬቱ ጋር አጣብቆና ተጭኖ ያዘው ።

አቧራ ውስጥ ወድቆ ፡ እንዳች ረዳት አጥቶ በነበረበት ወቅት እንኳ ፡ እንደበተ ጀግና ነበር ። "ጠብቁኝ እናንተ ፈሪዎች! ሽሽቱ ወዴት ነው? የወደቅሁት በፈረሴ ጥፋት እንጂ በኔ ስሕተት አይደለም" እያለ ይጮህ ጀመር ።

ነጋዴዎቹ በሣቅ ፍርስ አሉ ። ከሚያሳዝነው ሁኔታው ይልቅ ፡ ጀብደኝነቱ አስገርሟቸው ሁሉቹም ጥላቸውን ዘርግተው ሽቅብ ተራራውን ተያያዙት ። ሆኖም ከበቅሎ ጫኞቹ አንዱ መልካም ምግባር የጎደለው ሰው ነበር ። ጌታው 'ፈሪ' ተብሎ መሰደቡ አበሳጭቶት ፡ ተሸቀንጥሮ የወደቀውን የዶን ኪኾቴን ጦር አንሥቶ ከሰበረው በኋላ ረዘም ባለው ጉማጅ የዶን ኪኾቴን ወገብ እንክት አድርጎ እጁ እስኪዝል ድረስ ደበደበው ።

ይህም ሁሉ ሆኖ ዶን ኪኾቴ አልተበገረም ። የዱላ መዓት ቢወርድበትም እግሮቹን እያወራጨ ጠላቶቹ የቻ

ሉትን ሁሉ እንዲያደርጉ ተፈታተናቸው ። እንዲያውም ድምፁን ከፍ አድርጎ፤ "ብትፈልጉ እረዱኝ እንጂ ፤ የኔዋ እመቤት ሆይ ዱልሲኒያ በዓለም አቻ የሌላት ውብ መሆኗን አሁንም አረጋግጣለሁ!" አለ ዶን ኪኾቴ፤ እዚያው እንደ ተዘረረ ።

በመጨረሻም ፤ በቅሎ ነጂው ዶን ኪኾቴን ትቶ ፤ በቅሎቹንና ጌታውን ተከትሎ መንገዱን ቀጠለ ። ዶን በቅሎቹንና ጌታውን እንደ ሆነ ካረጋገጠ በኋላ ፤ ከወደቀ ኪኾቴም ብቻውን እንደ ሆነ ካረጋገጠ በኋላ ፤ ከወደቀ በት ተነሥቶ በእግሮቹ ሊቆም ሞከረ ። እንኳንስ ተደብ ድቦ ፤ አጥንቶቹም ተቀጥቅጠው ቀርቶ ፤ቀድሞውንስ ቢሆን ዶን ኪኾቴ ለንቋሳ አልነበረም?

ዶን ኪኾቴ፤ በጀርባው ተንጋሎ ረዳት እጥቶ ሳለ አንድ አራሽ እንደ አጋጣሚ በዚያ በኩል መጣ ። ይህ አራሽ እህል አስፈጭቶ በአህያዉ ጭኖ ወደ ቤቱ በመ መለስ ላይ የሚገኝ የዶን ኪኾቴ መንደር ሰው ነበር ። ገበሬዉ ዶን ኪኾቴን ጠጋ ብሎ ሲመለከት፤ አቧራ ላይ የተዘረረ ጥሩር ለባሽ ፈረሰኛ ሆኖ አገኘው። አህያዉም ከመ ንገድ ዳር ቆሞ ሣር ይግጥ የነበረውን ሮሲናንቴን ጠጋ ብሎ በማሽተት የእንስሳ ለእንስሳ ትውውቅ ማድረግ ጀመረ ።

"ጤና ይስጥልኝ፤ ውድ ወዳጄ?" አለ ገበሬዉ ድም ፁን ከፍ አድርጎ። ቀጠል አደረገናም፤ "ምን ሆነሃል?" አለው ።

ዶን ኪኾቴ መልስ አልሰጠም ። ወደ ሰማይ አን ጋጦ ፤ ከመጻሕፍት ውስጥ ያነበባቸውን ረዣዥም ሀረ ፍት ነገሮች እንደ ውዳሴ ይደግም ጀመር ።

መንገደኛዉ ገበሬም ፤ "ኧረ ይህ ሰው ናላውን ስቷል" እያለ አጉመተመተ። ከዚያም የጦረኛዉን ቀር

ከፊቱ ላይ ገለጥ አድርጎ ተመለከተ ። በአረንጓዴ እራፊ
ጨርቃ ጨርቅ የተተበተበ ፤ በቁርጥራጭ ካርቶን የተሰ
በጠ ቆብ ሆኖ ፤ ያ በቅሎ ጫኝ በቡጢና በርግጫ የበታ
ተነውን ቆር ነበር፡ዶን ኪሆቴ ራሱ ላይ የደፋው ። መንገ
ደኛዉ ገበሬ የጦረኛዉን ገጽ እንዳየ ፡ ወዲያው ማንነቱን
ዐወቀና ፤

"መልካሙ ጐረቤቴ ኪሻና እንዴት እዚህ ልት
መጣ ቻልክ? ምንስ ደረሰብህ?"ብሎ ጠየቀው ። ምስኪኑ
ዶን ኪሆቴ ግን ምንም ሳይናገር ፤ ከመጻሕፍቱ ውስጥ
ያጠናቸውን ጥቅሶች ይተረትር ጀመር ። እንደ እውነቱ
ከሆነ ግን ፡ ትንፋሽ የሚያሳጣ ከባድ ድካምና ጉዳት ደር
ሶበት ነበር ። ገበሬዉ በብዙ ድካምና ጥረት ዶን ኪሆቴን
ከተጋደመበት እንሥቶ ፤ አህያዉ ላይ በደረቱ ተደፍቶ
እንዲተኛ አደረገ ።

የጦረኛዉን ጥሩር ፡ ቆርና የተሰባበረውን ጦር እንኳ
ሳይቀር ሰባስቦ ባንድነት ሮሲናንቴ ጀርባ ላይ ጠፍሮ
ጫነ ። ገበሬዉ ሁሉም ነገር መስተካከሉን ካረጋገጠ በኋላ
ፈረሱን በልጓሙ ፤ አህያዉን በመሳቢያው እየጐተተ
እሱ ከፊት ሆኖ የቤቱን መንገድ በዝግታ ተያያዘው ።
የዶን ኪሆቴ መቁሰልና መጐዳት እያሳዘነው ፤ ወደ ኋላ
መለስ እያለ ፤ በለሰለሰ አንደበት ቢያነጋግረውም ፡ገበ
ሬዉ አንዳች መልስ አላገኘም ። ዶን ኪሆቴ አህያው ላይ
ሆኖ ያቃስትና ያጉመተምት ጀመር ። የደረሰበትን ችግ
ርና ፈተና ለገበሬዉ ሳይገልጽ ፤ እዚህ መከራ ላይ የወ
ደቀበትን ሳይናገር ፤ በጣም ያማርራል እንጂ ፡ ምክንያቱን
ግን አይገልጽም ።

"ውድ ወዳጄ ኪሻና እኔ ማን እንደ ሆንኩ ያወቅሽኝ
አልመሰለኝም" አለ መንገደኛዉ ገበሬ በመጨረሻ ።

“ምንቱ መታወቅ አይደለም ቁም ነገሩ ፤ እኔ ማን ነቴን በቅጡ በውቀዋለሁ ። ዋናው ነገር ግን እኔ ብቻዬን አይደለሁም - ብዙ ጀግኖች ተሰብስበው አንድ የሆንኩ፣ ታላቅ ጥሩር ለባሽ ፈረሰኛ ነኝ ” አለ ዶን ኪኾቴ ፤ ራሱን እንደ ደፋ ።

ዶን ኪኾቴና መንገደኛዉ ገበሬ መንደራቸው ሲደርሱ ፀሐይ ጠልቃ ደንገዝገዝ ብሎ ነበር ። ዶን ኪኾቴ እንዲያ ተጐሳቁሎ ፤ ተደብድቦና ቆስሎ በሚገኝበት ሁኔታ ማንት የሚያከብሩት ጐረቤቶቹ እንዲያዩት ገበሬው አልፈለገም ። ስለሆነም እስኪመሽ ድረስ ከመንደራቸው ወጣ ካለ ቁጥቋጦ ውስጥ ለመቆየት ወሰነ ። መምሸቱን ካረጋገጠ በኋላ ፤ ገበሬዉ ዶን ኪኾቴን ወደ ቤቱ ወሰደው ።

በዝግታ ወደ በሩ ሲጠጋ ፤ ከቤቱ ውስጥ የሰዎች ድምፅ ይሰማ ነበር ። የመንደሩ ንስሐ አባትና ወዳጁ የነበረው ጸጉር አስተካካይ እዚያው ዶን ኪኾቴ ቤት ውስጥ ነበሩ ። እነዚህ ሁለት ሰዎች የዶን ኪኾቴ ጐረቤት ከመሆናቸውም በላይ፣ ዘወትር ማታ ማታ እየመጡ ከእርሱ ጋር በጭውውት ጊዜያቸውን የማሳለፍ ልምድ ነበራቸው ።

ከዶን ኪኾቴ ጋር የነበረው ገበሬ ፤ ሰዎቹ ምን እንደሚያወሩ ወደ በሩ ተጠግቶ ያዳምጥ ጀመር ።

የዶን ኪኾቴ ሠራተኛም በሚያሳዝን ድምፅ ፤ “ምን ይሻላል ትላላችሁ? ጌታዬ ከጠፋ ሁለት ቀን ሆኖታል ። ፈረሱ ከጋጣ ፤ ጦርና ጋሻው ከጓዳ ፤ የቅድመ አያቶቹ አሮጌ ጥሩርም የለ” አለች ።

የንስሐ-አባቱ ‘እንዲያው የት ደርሶ ይሆን ?’ በማለት ለማወቅ ጓጓ ።

“የት ደርሰ ነዉ የሚሉት ? እሱማ ለዓለም ፤ ጥሩር ለባሽ ፈረሰኛነቱን ለማሳየትና ለማሳመን በፈረሱ ላይ

ሆኖ በመሀዋወር ላይ ነዋ!'' ብላ ሠራተኛዋ ፣ ንግግሯን ቀጠል አድርጋም ፤ ''ለዚህ ሁሉ ያበቁት ፤ እነዚያ ራሱን በወትር ድፍቶ ሲያነባቸው የነበሩት መጥፎ መጻሕፍት ናቸው'' አለች በቁጭት ።

የእኅቱም ልጅ በብሽቀት እንጋገር ፤ ''ያላንዳች ጥር ጥር ይህ ሁሉ መዘዝ ሊመጣ የቻለው ፣ በእነዚያ ጠንቀኛ መጻሕፍት ሳቢያ ነው ። መጻሕፍቱ ጅላ-ጅል አደረጉት ። እንዴ! ለዐርባ ስምንት ሰዓታት ያለ ማቋረጥ እንደሚያነብ እኔ ዐውቃለሁ ። እንዲያውም አንብቦ ከጨረሰ በኋላ መጻ ሕፍቱን አሽቀንጥሮ ጥሎ ፣ ልክ ሻምላ እንደሚመዝና እንደ ሚዋጋ ዐይነት በሚያስፈራ እንቅስቃሴ ራሱን በማታለል እንደ ጦረኛ ይንጐራደድ እንደ ነበር አይቻለሁ'' አለች ።

ሠራተኛዋ ቀጠል አለችና ፤ ''እረ ከዚህ የባሰ አስ ፈሪ ነገሮች ሲፈጽም አይቻለሁ ። አንድ ቀን በዚህች ክፍል ውስጥ እየተሯሯጠ 'ከትላልቅ የቤተ ክርስቲያን ደወል ቤቶችን ያህል የረዘሙ ጭራቆች ገድያለሁ' እያለ ሲፎክር ሰምቼዋለሁ ። ለዕብደት ያበቁት እነዚህ የሚያ ነባቸው መጻሕፍት ናቸው''አለች ወገቧን በሁለት እጆ ችዋ ይዛ ።

''በእርግጥ ነገሩ እውነት ነው'' አለች የዶን፡ኪኾቴ የእኅቱ ልጅ ። ''እነዚህ ጠንቀኛ መጻሕፍት ናቸው ለዕብ ደት ያበቁት ። በሙሉ መቃጠል አለባቸው'' አለች በም ሬት ።

''እውነትሽን ነው'' አለና የንስሐ አባትዬው ንግ ግሩን በመቀጠል ፣ '' እነዚህ መጻሕፍት ናቸው አእምሮ ውን ጤና የነሡት ። በዛሬዋ ጀንበር ለፍርድ ቀርበው በእ ሳት መጋየት አለባቸው'' አለ ።

ይህን ሁሉ ውይይት ዶን ኪኾቴና ገበሬዉ ከጨለማ ውስጥ ሆነው ፣ ሲያዳምጡ ማንም አላያቸው ነበር ። ገበ ሬዉ የሚበቃውን ያህል ከሰማ በኋላ ጊዜ ሳያባክን ፣

"ቤቶች! እዚህ ቤት! በሩን ክፈቱልን ። እነሆ ጥሩር ለባሽ ፈረሰኞች በአጀብ መጥተዋል ፤ አስረኛም ይዘዋ ልና ይከፈት!" አለ ድምፁን ከፍ አድርጎ ።

የቤት ሠራተኛዋ ከድንጋጤዋ የተነሣ ይዛው የነ በረው መጥረጊያ ወደቀ ። የንስሐ አባቱና ጸጉር አስተ ካካዩ ወደ በሩ ተንደርድረው ሲሮጡ ፣ የዶን ኪኾቴ የእኅት ልጅም የሚበራ ሻማ ይዛ ተከተለቻቸው ። ዶን ኪኾቴ አህያ ላይ ተጭኖ ባዩት ጊዜ ፣ ሁሎቹም ሲያቅ ፋትና ሲደግፉት ወደ እርሱ ሮጡ ።

"ጠንቀቅ በሉ! በጣም ስለ ተጐዳሁ ትዕግሥት ይኑ ራችሁ ። ይህ ሁሉ ሊደርስ የቻለው ፈረሱ ጥሎኝ ነው ። ወደ አልጋዬ ውሰዱኝ ፤ ያቺን ወጊሻ አርጋን ዳንም ጥሩ ልኝና ቁስሌን ታክመኝ"አለ ዶን ኪኾቴ ፣ ሙትት ባለ ድምፅ ።

"ይኸዋ! ብዬ አልነበረም!"አለች ሠራተኛዋ ለን ስሐ አባትዬው እያንሾካሾከች ። "ጭንቅላቱ ሙሉ በእነ ዚያ መጻሕፍት እኩይ ሐሳብ ተመልቷል "አለች ።

"ምንህ ላይ ነው የቆሰልከው አጐቴ?"ጠየቀች የእ ኅቱ ልጅ በጉጉት ።

"ቆሰልክ? . . . እኔ አልቆሰልኩም ። ትንሽ ቅጥ ቅጥ ነው ። ከዐሥር ጭራቆች ጋር ስፋለም ፣ ከፈረሴ ከሮ ሲናንቴ ላይ ከፉኛ ወድቄ ጥቂት ጉዳት ደረሰብኝ ። እነ ዚያን የመሳሰሉ ጭራቆች እናንተ በፍጹም አይታችሁ አታውቁም ። እነዚያ ዓለምን የሚዞሩ ከንቱ ፍጡራን

ናቸው ። ታዲያ እኔ ብቻ ነበርኩ የተቋቋምኳቸው ” አለ ዶን ኪኾቴ ፣ በኩራት ድምፅ ።

“ስሙት ! ” አለ ንስሐ አባትዬው ፣ ወደ ሠራተኛዋ ፊቱን መልሶ ። “ይኸውላችሁ የፈራነው ደረሰ ። የሚያወራው ሁሉ ስለ ጭራቆች ነው ። እነዚህ ጠንቀኛ መጻሕፍት ተበይኖባቸዋል ፣ ወዲያው መቃጠል አለባቸው ” አለ በቁጣ ።

ዶን ኪኾቴን ከአህያው ጀርባ አወረዱትና ደጋግፈው ወደ ቤት ካስገቡት በኋላ ፣ ከሚወደው ወንበር ላይ አስ ቀመጡት ። ሁለቱ ሴቶች በብዙ ጥያቄዎች አጣደፉት ፤ ዶን ኪኾቴ ግን ፣ ጥቂት የሚቀመስ ምግብ እንዲሰጡትና ብቻውን እንዲሆን ጠተወተ ። የፈለገውን አደረጉለት ። ራቱን ጥስቅ አድርጎ ከበላ በኋላ ፣ ደኅና አደሩ እንኳ ሳይ ላቸው ወደ አልጋው እየተጉተተ ሔደ ።

በመጻሕፍት ላይ የደረሰ ፍዳ

በማግሥቱ ማለዳ የንስሐ አባትዬውና ጸጉር አስተካካዩ ተመልሰው መጡ ። ዶን ኪኾቴ ድብን ያለ እንቅልፍ እንደ ወሰደው ነው ። እንዲያውም ሳይነቃ ከግ ማሽ ቀን በላይ ዐልፎታል ።

“ለሕመሙ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች ልናስወግድ መጥተናል ” አለና የንስሐ አባትዬው ፣ የእኅቱን ልጅ ዶን ኪኾቴ መጻሕፍት የሚያኖርበትን ክፍል ቁልፍ እንድ ትሰጠው ጠየቃት ።

እሷም ፈጠን ብላ ፣ “ይኸውልዎ ! የማያዳግም ሥራ እንደሚያከናውኑ ተስፋ አለኝ”አለችና ቁልፉን ሰጠችው።

ቤት መጻሕፍቱን ከፍተው ገቡ ። የቤት ሠራተኛዋም ተከተለቻቸው ። በመቶ የሚቈጠሩ ትላልቅ ጥራዝ መጻሕፍትና ሌሎች አያሌ ትናንሽ መጻሕፍት በወጉ መደርደሪያ ላይ ንጽሕናቸውን ጠብቀው ያገኛሉ ። የዶን ኪኾቴ ንስሐ አባት የመጻሕፍቱን አርዕስት ያነብ ጀመር ።

“አንድ ጊዜ ቆዩኝ !” አለችና የቤት ሠራተኛዋ በአንድ በሚያንጸባርቅ ጐድጓዳ ማሆን ውሃ ይዛ በፍጥነት ተመለሰች ። “ይኸውልዎ አባ በዚህ ውሃ ላይ ያጣመው የክፍሉን ጥግ ጥግ (ጥጋት) አንድ ቦታ እንኳ ሳይቀር ፤ ይርጩት ። ርኩስ መንፈስ አያጋ ሲያደርስ በየመጻሕፍቱ ውስጥ ሳይሸሸግ አይቀርምና ፤ ጸበሉ ወዲያው ያባርረዋል ” አለች ።

የንስሐ አባትዬውም በነገሯ እንደ ማሾፍ ብሎ ፈገግ አለና ፤ ጸጉር አስተካካዩ መጻሕፍቱን አንድ በአንድ እንዲያቀብለው ጠየቀ ። የሚሰጠውን መጻሕፍት እየከፈተ አርዕስቶቹን መመርመር ጀመረ ።

“ይህን ያህል ሁሉም መጥፎ አይደሉም ። ምናልባትም ከመኻከላቸው መቃጠል የማይገባቸው እንዳሉ ይታየኛል ” አለ የንስሐ አባትየው ።

“ፍጹም የማይሆን ነው ። አጐቴን ጥፋት ያደረሱበት እነዚህ ርኩስ መጻሕፍት ናቸውና ፤ አንዳቸውም ከመቃጠል አይድኑም ” አለች የዶን ኪኾቴ የእኅት ልጅ ።

“ሁሉንም መጻሕፍት በመስኮት አሽቀንጥራችሁ ወርውሯቸው! ከዚያም እያነሣን ወደ ጓሮ ወስደን ጢሱ ማንንም በማያስቆጣ ሥፍራ እናጋያቸዋለን ” አለች ኮስተር ብላ ።

ከሰዓት በፊት መጻሕፍቱን ሲመርጡና ሲጥሉ ዋሉ ፤ አብዛኛውን ጊዜ የንስሐ አባትዬው አንዳንድ ትላልቅ

መጻሕፍት ሲያጋጥመው ፣ መምረጡን እያቆመ በንባብ ይጠምዳል ። ገጾችን በጥንቃቄ እያገላበጠ በተመስጦ ይመለከት ነበር ። አንዳንዴም ቀና ይልና ፣

"ይህን መጽሐፍ ማቃጠል አይገባም" ይልና የንጉሠ ነገሥቱ ፣ ለራሱ ይጠቅመኛል የሚላቸውን ወደ ጐን ያስቀምጣል ።

አብዛኛዎቹ ታላላቅ ቅጾች ፣ ስለ ጀግኖች ገድልና ስለ ፍቅር የሚያወሱ በመሆናቸው ፣ በርግጥም በእነርሱ ግምት ረብ አልነበራቸውም ። የንስሐ አባትዬው ዐይን ኋኚያን ረብ የሌላቸውን መጻሕፍት የመለየት ችሎታ ነበ ራቸውና ፣ ወደ ውጭ ተወርውረው በእሳት በመጋየት የጥፋት ፍርዳቸውን እንዲቀበሉ ያደርግ ነበር ።

ቀትር ላይ ፣ ሁሉም መጽሐፍ ማገላበጡ እየደከማ ቸው ሔደ ። የንስሐ አባትየውም ፣ "ከእንግዲህ እነዚ ህን መጻሕፍት እገላብጦ መመርመሩ ፋይዳ የለውም ። ሁሉም መጥፎ ናቸውና ወዲያ ጣሏቸው" አለ በስለቸ እንጋገር ።

የቤት ሠራተኛዋ እጅግ ደስ አላትና ፣ ጓሮ እሳት አነደደች ። የንስሐ አባትዬውና ጸጉር አስተካካዩ ጥቂት ዕረፍት በማድረግ ላይ ነበሩና ፣ ሠራተኛዋ ፣ እንዲቃጠሉ የተፈረደባቸውን ብቻ ሳይሆን ፣ እነዚያን አስደሳች መጻ ሕፍት ፣ የንስሐ አባትዬው ለራሱ መርጦ ለብቻ ያስቀ መጣቸውን ጭምር እያነሣች እሳት ውስጥ ጨመረቻቸው ። ደኅናዎቹ መጻሕፍትም እንደ ደመራ ችቦ ነደዱ ።

ከቀትር በኋላ ፣ ዶን ኪኾቴም ከረኸም እንቅልፉ ነቃ ። ሆኖም ፣ እጥንቱ ተቀጥቅጦ መላ ሰውነቱ ዝሏልና መላወስ አልቻለም ። አልጋው ላይ እንደ ተጋደመ

የእኅቱን ልጅና ሠራተኛውን በየስማቸው ሲጣራ ፣ መጽ ከሙ በድምፁ ይታወቃል ። ጥቂት ምግብ አቅርበውለት ከቀማመሰ በኋላ ፣ እንደገና እንቅልፍ ወሰደው ። የንስሐ አባትዬውም ፣ “በጸጥታ እንዲያርፍ ብንተወው ይሻላል” አለና ሁሉቹም ትተውት ወጡ ።

ጀግናው ዶን ኪኾቴም ፣ ሁለት ቀን ሙሉ ከመኝታ ክፍሉ አልተንቃነቀም ። የእኅቱ ልጅና የቤት ሠራተኛው ተንከባከበው ስለ ያዙት ፣ ሥቃዩ እምብዛም አልተሰ ማውም ነበርና ፣ ብዙም ሳያማርር ሕመሙን ያስታምም ጀመር ።

ዶን ኪኾቴ ፣ በእንዲህ ያለ ሁኔታ አቤቱ ተኝቶ ሳለ ፣ የንሥሐ አባቱና ጸጉር አስተካካዩ አዘውትረው ይጉበኙት ነበር ። አብዛኛውን ጊዜአቸውን ፣ የቤተ መጻሕፍት የነ በረችውን ክፍል መግቢያ በዘዴ ለመድፈን አዋሉት ። የቤት ሠራተኛዋ ራሷ እንኳን በሩ በየት በኩል እንደ ነበር በትክክል ለመናገር እዳጋች እስኪሆንባት ድረስ ብልሃት በተመላበት ሁኔታ ደብዛውን አጠፉት ።

“የመጻሕፍት ቤቱን ክፍል ለማግኘት ካልቻለ የመ ጻሕፍቱን ጉዳይ ወዲያው ይረሳል” አለ የንስሐ አባትዬው።

ዶን ኪኾቴ በአራተኛው ቀን ጥቂት መራመድ ቢችልም ፣ ይህን ያህል በራሱ ወይም በአካባቢው ባለ ነገር ሊተማመን አልቻለም ።

ትንሽ ሻል እንዳለው ፣ በመጀመሪያ ያደረገው ቤተ መጻሕፍቱን መፈለግ ነበር ። ድክምክም ባለ ርምጃ በሳ ሎኑ አቅጣጫ በመሔድ በሩን ለማግኘት ፍለጋውን ቀጠለ። የግድግዳው አቅጣጫና በሩ የነበረበትን ሊያውቅ ችሏል ። ነገር ግን ፣ ከወዲያ ወዲህ ቢሯሯጥ ፣ ዐይኑን ጐልጉሎ አካ ባቢውን ቢቃኝ ፣ በሩ የነበረበትን ግድግዳ ማግኘት ተሳ ነው ።

በመጨረሻም ተስፋ ቆርጦ ፍለጋውን ቢያቆምም ፣ ይህንን ጉዳይ ግን ለማንም አልተነፈሰም ።

በማግሥቱ የቤት ሠራተኛዋን ጠርቶ ፣ "ወደ ጥናት ክፍሌ የሚያመራው መንገድ የጠፋብኝ መሰለኝ" አላት ።

"የምን የጥናት ክፍል? የጥናት ክፍል የሚባል እዚህ ቤት ውስጥ ጨርሶ የለም" አለችው ፈርጠም ብላ ።

"ከዚህ በፊት ብዙ መጻሕፍት ያሉበት የጥናት ክፍል እንደ ነበረኝ እርግጠኛ ነኝ" አለ ዶን ኪኾቴ ።

"እሱማ የመቸውን ነው የምትለው? ከብዙ ጊዜ በፊት ነበር ። ነገር ግን ፣ አንተ ታመህ በነበርክበት ወቅት በየመጻሕፍቱ ውስጥ ስለ ነርሱ ታነብ የነበሩት እኒያ እኩይ አጋንንቶች የጥናት ክፍሉን ብቻ ሳይሆን ፣ መጻሕፍቱ ንም ጭምር ወሰዷቸው" አለችው የቤት ሠራተኛዋ ።

ዶን ኪኾቴ አጉረመረመ ። የእኅቱ ልጅም ፣ እውነት ነው አጐቴ ፤ አጋንንት ነው ቤተ መጻሕፍቱን እንዲህ ያደረገው ። እንዲያውም አንድ ቀን እሳት በሚተፋ ዶራ ጎን ሲጋልብ መጣና ፣ መብራት አብርቶ ወደ ጥናት ክፍልህ ገባ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፣ በጭስ መውጫው በኩል ወጥቶ ሲሔድ ፣ ቤቱን በሙሉ በጭስ ሞልቶት ነበርና ፣ ዐይናችን ማየት አልቻለም ነበር ። ከዚያም እኛ መጻሕፍትህንና የጥናት ክፍልህን ፈልገን ለማግኘት ተሳነን" አለችው ።

ዶን ኪኾቴም ፣ "ይህን ያደረገው ማን እንደሆነ ዐውቃለሁ ። የታወቀው አጋንንት 'ፍሬስቶን' ነው ። ጠላቴ እሱ ነው" አለ ።

"እውነትክን ነው አንጐቴ ። 'ፍሬስቶን' ወይም 'ፍሪስቶን' መሆን አለበት ፤ ለማንኛውም ስሙ በ'ቶን' ነው የሚያልቀው " አለች የእኅቱ ልጅ ።

"በጣም መጥፎ ፍጡር ነው ። እንዲያውም ሌላ ክፉ ነገር እንደሚያደርስብኝ አልጠራጠርም ። እኔ የት እንደ ምኖር ስለሚያውቅ ዘወትር ይመጣል ። እኔ ግን ፈጽሞ አልፈራውም ። አንድ ቀን ፊት ለፊት ተጋጥመን እንደ ማያባየው ግን አልጠራጠርም" አለ ዶን ኪኾቴ ፣ኩራት በተመላበት አነጋገር ። መከራ ከደረሰበት ወዲህ ተንቀሳ ቅሶ የማያውቀው ዶን ኪኾቴ ፣ እኒያን ደካማ እጆቹን ዘር ግቶ ጉራዶውን ከተንጠለጠለበት አወርዶ ፤

'ወዮልህ ፍሬስቶን ፍሬስቶን ! የዶን ኪኾቴ ዲ ላ ማንቻን ታላቅ ጀግንነት የምትረዳበት ቀን ሩቅ አይሆ ንም ' እያለ ከወዲያ ወዲህ ይንጐራደድ ጀመር ።

አንጋች መረጣ

ዐሥራ አምስት ቀን ያህል መልካሙ አዛውንት ዶን ኪኾቴ ከቤቱ ውስጥ ከረመ ። በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ በመ ዘዋወር በቆየባቸው ጊዜያት ሁሉ የተደሰተና የረካ ይመ ስል ነበር ። የቤተ መጻሕፍቱ መጥፋት ግን እምብዛም አላስጨነቀው ። እንዲያውም ጉዳዩን በማቃለል ፤

"እውነተኛ ጀግና በሕይወቱ ላይ የደረሰበትን ፈተና ሁሉ ለመቋቋም ቆራጥ መሆን ይኖርበታል" አለ ዶን ኪኾቴ ፣ ኮስተር ብሎ ።

የንስሐ አባትዬው ፣ በየቀኑ እየተጠራ ይጐበኘውና ስለ ብዙ አስደሳች ጉዳዮች ብዙ የሚያስደስቱ ቃሎች

ተስዋውጠዋል ። ሆኖም ፣ ዶን ኪኾቴ ከንግግሮቹና ከጭ ውውቶቹ ማክተሚያ ላይ ፣ በአእምሮው ውስጥ እንደ ከፍተኛ ቁም ነገር ወደ ቈጠረው ሐሳብ ይመለሳል ።

"ውድ ወዳጄ ሆይ! እኔ ልንገርዎት ። አያሌ ጥፋር ለባሽ ፈረሰኞች ቢኖሩ ኖሮ ዓለም በተሻሻለች ነበር ፤ ዛሬ እኛ በጣም የምንፈልገው ብዙ ጦረኞች ጀግኖች ነው" ይሉዋል ካህኑን ። ከአንድ ሰዓት በላይም ፣ ደስ ስለሚ ለው ጉዳይ ፣ በረዥሙ ይናገራል ። ደጉ የንስሐ አባትም አንገቱን አቀርቅሮ ፈገግ ይላል ። ምስኪኑን ጓደኛውን ማስደሰትና ዶን ኪኾቴም እንደ ፍላጐቱ መሆን እንዳ ለበት የንስሐ አባትዬው ያውቅ ነበር ።

ቀናት ባለፉ ቁጥር ዶን ኪኾቴ መሰልቸት ይታይ በት ጀመር ። ቤቱ በጣም ጸጥታ የሰፈነበት ሆነበት ። ጦሩን ይዞ በፈረሱ ጋልቦ ፣ ሌላ የጀግንነት ጀብዱ ለመ ፈጸም ጉጉቱ እየለበት ። ከዚህ በስተቀር የሚያስበውም ሆነ የሚናገረው ሌላ ጉዳይ አልነበረውም ።

ከንስሐ አባትዬው ጋር ጭውውት ሲያደርጉ ፣"... ግን አንድ የሚጐድለኝ ነገር አለ፤ጋሻ ጃግሬ (አንጋች) ማግ ኘት አለብኝ ። ባነበብኳቸው መጻሕፍት ሁሉ ማንኛ ውም ጀግና በተኳዘበት ሥፍራ ታማኝ አንጋች እንደ ነበረ ውና ፣ ጀግናውም ግዳይ ሲጥል የዐይን ምስክር የሚሆን ሰው እንዳለው አረጋግጫለሁ" አለ ዶን ኪኾቴ ። የን ስሐ አባትዬውም ፈገግ ብሎ ዝም አለ ።

በዶን ኪኾቴ መንደር ውስጥ ሳንቾ ፓንሳ የሚባል አንድ ድሀ ሰው ይኖራል ። ይህም ሰው የቀን ሠራተኛ በመሆኑ ፀዶን ኪኾቴ እርሻ አካባቢ አንዳንድ ጊዜ እየ ተቀጠረ የቀን ሥራ የሚሠራ ነበር ። ታማኝ ፣ ግን ምንም

ያልነበረው ምስኪን ነበር - ድህንቱ በገንዘብም በአእምሮም የሆነ ።

ዶን ኪኾቴ ፡ ስለዚህ ሰው በሐሳቡ ያወጣ ያወርድ ጀመር ። በየቀኑ ዶን ኪኾቴና ሰውየው በአውራ መንገዱ ላይ እየተንሸራሸሩ ያወጉ ጀመር ። ይህም ሰው ዶን ኪኾቴ ለአንጋችነት ይሆነኛል ብሎ የተመኘው ዐይነት ሆኖ አገኘው ።

በመጨረሻም ፡ ዶን ኪኾቴ ጉዳዩን እንዲህ ሲል አነሣለት ። "ፓንሳ ! ጥሩር ለባሽ ፈረሰኛ ስለሆንኩ ፡ በቅርቡ ለጀግንነት ተግባር እሠማራለሁ ። የኔ አንጋች ሆነህ ከእኔ ጋር ከመጓዝ በስተቀር ሌላ የተሻለ አማራጭ አይኖርህም። ከእኔ ቀጥለህ ታላቅ ዝናን እንደምታተርፍ ቃል እገባለሁ" አለ ዶን ኪኾቴ ።

ሳንቾም ድምፁን ከፍ አድርጎ ፡ " ዝና አሉ ጌታዬ? ይኸ ዝና የሚሉት ነገር ምንድን ነው ? " ሲል ጠየቀ ።

"ስምህ በታዋቂነት በየሰዉ ሁሉ አፍ ይገባል ማለት ነዋ ! ታላላቅ ወይዛዝርትና መኳንንት ሙያህን እያነሡ ስለ አንተ ያወጋሉ" ሲል ዶን ኪኾቴ መለሰ ።

" ይህማ እንዴት ድንቅ ነበር ! " አለ ሳንቾ ።

"ይህ በቅርቡ የሚፈጸመው የጀግንነት ተግባር ጊዜ እውን ይሆናል ። እንዲያውም ድል መትቼ አንዲት ደሴት መያዜ አይቀርም ። ከዚያ በኋላ አንተ ከእኔ ጋር ከሆንክ የደሴቷ አገረ ገዥ አደርግሃለሁ " አለ ዶን ኪኾቴ ።

"ስለ ደሴት እንኳ እምብዛም የማውቀው ነገር የለም ። ሆኖም የአንድ ደሴት ገዥ መሆን አልጠላም ። ስለሆነም በመጀመሪያ የምትይዛት ደሴት ገዥ እንድሆን ቃል ከገ

ባህልኝ ጋሻ ጃግሬህ(አንጋችህ) እሆናለሁ ። ካንተም ጋር በመጓዝ ፈቃድህን ሁሉ እፈጽማለሁ ” አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

“ቃሌ እገባለሁ !” አለ ዶን ኪኾቴ ፡ “አዎ ! አንጋች ትሆናለህ ። የድካሜ ተካፋይ እንደ መሆንህ የግዳዩም ትሆናለህ ” በማለት ዶን ኪኾቴ ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ ።

ከአንጋች ምልመላ በኋላ ፣ የቀረው ጊዜ ዶን ኪኾቴ በሥራ የተወጠረባቸው ቀናት ነበሩ ። የአርሻውን እኩሌታ በመሸጥ ለኪሱ የሚሆን ገንዘብ ቋጠረ ። የተሰበረ ውን ጥሩር ጠጋግኖ ሲያበቃ ፣ ከአንድ ጐረቤት ወዳጁ ላይ ጦር በውሰት አገኘ ። አሮጌ የብረት ቊሩን ደኅና አድ ርጎ በማሠሪያ ተብትቦ ጠጋገነ ።

በመጨረሻም ሁሉም ነገር ዝግጁ ከሆነ በኋላ ፣ ጀግ ናው ጦረኛ ከሳንቾ ፓንሳ ጋር ለመወያየት ፡ ወደ አውራ ጐዳናው ወጣ አለ ። በምን ሰዓት መነሣት እንዳለባቸው ለሳንቾ ፓንሳ ምክር ሊያካፍል ፈለገ ።

ሳንቾ ፓንሳም ፡ “ዝግጁ ሆኘ እጠባበቃለሁ ” አለ ።

“መያዝ ያለብህን ለጉዞ አስፈላጊ ነገሮች ሁሉ መዘ ጋጀታቸውን ርግጠኛ ሁን ! ከሁሉም ይልቅ ትልቁን ኮረ ጆህን መያዝ አለብህ ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“በርግጥ እርስዎ ያሉኝን አደርጋለሁ ጌታዬ ። እን ዲሁም ያንን ግራጫ አህያዬን ይገፍው እመጣለሁ ፤ ምክ ንያቱስ ? ቢሉ ብዙ በእግር የመጓዝ ልምድ ስለሌለኝ ነው ” አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

በሳንቾ ፓንሳ አነጋገር ዶን ኪኾቴ ግራ ተጋባ ። ባነበባቸው መጻሕፍት ሁሉ ፣ የየትኛውም ጥሩር ለባሽ

ፈረሰኛ ጋሻ ጃግሬ በአህያ ሆኖ ጌታውን ሲያጅብ የሚገልጽ ሊታወሰው አልቻለም ። ቢሆንም የሳንቾን ሐሳብ ሊቃወም አልፈለገም ። ምክንያቱም በአሁኑ ጊዜ ጠቃሚ ሆኖ ያገኘውን የሳንቾን ሐሳብ ሊያጣ አልፈለገምና ።

“ግራሚ አህያን ? ትክክል ነህ ! . . .የዕድልህ መልካም ዕጣ ጥሩ ፈረስ እስኪያጋጥምህ ድረስ ፣ በአህያህ ተቀምጠህ ልትከተለኝ ትችላለህ ። እንዲያውም በመጀመሪያ የሚያጋጥመን ባለጌ ጥሩር-ለባሽ ፈረሰኛ ድል ከተመታ በኋላ ፣ ፈረሱን ለአንተ እንዲያስረክብ የማደርግ መሆኔን ቃል እገባለሁ” አለ ዶን ኪኾቴ፣በኩራት መንፈስ ።

ሳንቾ ፓንሳም ፣ “ከልብ አመሰግናለሁ ጌታዬ ። ነገር ግን ሡንጋ ፈረስ ከምጋልብ ፣ አህያ መጋለብ ልክ በቤቴ ውስጥ በምቾት እንዳለሁ ያህል ይሰማኛል” አለ ሳንቾ ፓንሳ፤ሁለቱም ለጉዞው ተዘጋጁ ።

በወፍጮ ቤቶች ላይ የተከፈተ ጦርነት

በማግሥቱ ፣ ጀግናው ዶን ኪኾቴና ጋሻ ጃግሬው ሳንቾ ፓንሳ በማለዳ ጉዞአቸውን ጀመሩ ። ከቀበሌአቸው ነዋሪ አንዱን እንኳ ሳይሰናበቱ፣ሹልክ ብለው መንደራቸውን ለቀው ወጡና ጉዞአቸውን ተያያዙት ። ፀሐይ ብርሃንዋን ስትፈነጥቅ ለመጓዝ የፈጠኑበት ምክንያት ፣ ማንም ዱካቸውን እንዳይደርስበት በማሰብ ነው ።

ዶን ኪኾቴ፣ጥሩሩን ከነሙሉ ትጥቁ ለብሶ ፣ ከሲታ ፈረሱ ሮሲናንቴ ላይ ጉብ ሲል፣በዓለም ከፍተኛው ቆፍጣና ጀግና መሆኑ ተሰማው ። እውነትም ግርማ ሞገሱ የሰጠ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም ። ጋሻ ጃግሬው ሳንቾ ፓን

ሳም ቢሆን አህያ ጀርባ ላይ መንኩሴ መሰሎ ተቀምጦ ፣ ሁለቱ እግሮቹ መሬት እየነኩ የውሃ ቅምጫውን በአንድ በኩል ፣ ኮረጆውን በሌላ በኩል ፣ አንጠልጥሎ ነበር የሚጓዘው ። በሳንቾ ፣ አእምሮ የሚመላለሰው ግን በቅርቡ ገዥ ስለ ሚሆንበት ደሴት ጉዳይ ነበር ።

ፀሐይ በተራሮች አናት ብርሃንዋን መፈንጠቅ ጀመረች ። ሁለቱ ተጓዦች የሞንቲየልን መስክ እያቋረጡ መንገዱን ቀጥ አሉት ። ሁለቱም ተጓዦች በትልቅ ዓላማና ግብ ሐሳባቸው ስለ ተወጠረ ፣ ጭውውት ማድረግ እንኳ አልቻሉም ነበር ።

ከረዥም ጉዞ በኋላ ፣ ሳንቾ ፓንሳ ትንሽ ተንፈስ አለና ፣ “ ጀግናው ጌታዬ ሆይ ! ቃል የገቡልኝን የደሴቱን ጉዳይ እንዳይዘነጉብኝ አደራ እላለሁ ። ደሴቱ የፈለገውን ያህል ሰፊ ቢሆንም ፣ በደንብ እንደማስተዳድረው እርግጠኛ ነኝ” አለ ።

ዶን ኪኾቴም ፣ መልስ ለመስጠት ክብር እየተሰማው ፣ “ወዳጄ ሳንቾ ሆይ! ማንኛውም የጦር ጀግና ደሴቶችን በድል አድራጊነት ከያዘ በኋላ ፣ የራሱን ጋሻ ጃግሬ ገዥ አድርጎ መሾም ወግና ደንብ እንደሆነ ማወቅ አለበት ። እና ፣ ያንን ወግና ደንብ መጠበቅና መፈጸም ግዴታዬ ነው” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“እውነትም እርስዎ አቻ የሌለዎት ጌታ ነዎት” አለ ሳንቾ ፓንሳ በፈገግታ ፣ ልቡ የደስታ ከበሮ እየመታ ።

ዶን ኪኾቴም ፣ “እንዲያውም ያንን ጥሩ ወግና ደንብ ይበልጥ ላሻሽለው አስቤአለሁ ። ከአንድ ይልቅ ሦስትና አራት ደሴቶች አድርጌ አንተን የነዚያ ሁሉ አስተዳዳሪ ባደርግስ ምን አለበት ? ” አለ በኩራት መንፈስ ።

"ከዚህ ይበልጥ እኔን የሚያስደስት አንዳችም ነገር በጣለም ሊኖር አይችልም" ሲል ሳንቾ መለሰ ።

ይህን እያወጉ ሲጓዙ ከዋሉ በኋላ ፤ በነፋስ ኃይል የሚሽከረከሩ አያሌ የወፍጮ ቤት መዘውር አውታሮች ካሉበት ሥፍራ ደረሱ ። ሠላሳና ፀርባ የሚሆኑት እኒህ የወፍጮ ቤት መዘውር አውታሮች በመስኩ ላይ ጉች ብለዋል ። ነፋስ በነፈሰ ቁጥር ረዣዥምና ነጫጭ መዘውሮቻቸው የሚያደርጉት አስቀያሚ እንቅስቃሴ ተመልካችን የሚያሸብር ነበር ።

ዶን ኪኾቴ ፣ ጉዳናው መኻል በድንገት የፈረሱን ልጓም ገታ አድርጎ ቆመና ፣ "ይኸውልህ ! ይኸውልህ !" እያለ ከጮኸ በኋላ፥ « ዕድላችን አማረ ሳንቾ ! እዚያ ማዶ ተመልከት! ቢያንስ ቢያንስ ሠላሳ ግዙፍ ጭራቆች ይታዩኛል ፤ ገጥሜ ሁሉንም ልወጋቸው አስቢያለሁ ። ተዋግቼ ድል ከመታኋቸውና ሁሉንም ካረድኳቸው በኋላ ከእነርሱ በምንማርከው ሀብት እንከብራለን " አለ ወኔውን ለፍልሚያ ቀስቅሶ ።

"የምን ጭራቆች ?" ሳንቾ ፓንሳ ጠየቀ ።

"ምን ነካህ ? እኒያ ከፊት ለፊታችን መስኩ ላይ የተገተሩት ናቸዋ ! ረዣዥም እጆቻቸውን ተመልከት እንጂ ! እንዲያውም የእነርሱ ዝርያዎች ርዝመቱ ከሁለት ኪሎ ሜትር የሚበልጥ የጦር መሣሪያ እንደሚይዙ አንብቤ አለሁ" አለ ዶን ኪኾቴ ትንሽ ቆጣ ብሎ ።

"እረ ጌታዬ በቅጡ ይመልከቷቸው ። ጨርሶ ጭራቆች አይደሉም ። በነፋስ የሚሽከረከሩ አውታሮች ናቸው ። እጆች አይደሉም" አለ ሳንቾ ፓንሳ ፈርጠም ብሎ ።

"ወዳጄ ሳንቾ" አለ ትክ ብሎ እየተመለከተው ፤

“ለጀግንነት ተሠማርተህ እንደማታውቅ ግልጽ ነው ። እኒህ የምታያቸው ጭራቆች ለመሆናቸው እኔ እርግጠኛ ነኝ ። ፈርተህ እንደሆነ ሒደህ ተሸሸግና ጸልይ ፤ እኔ ግን አሁኑኑ አጠቃቸዋለሁ” አለ ዶን ኪኾቴ በድፍረት አነጋገር ።

አንድ ቃል ሳይተነፍስ ፈረሱን ሮሲናንቴን ኮርኩሮ በቀጥታ ወደ ወፍጮዎች መዘውሮች(ክንፎች) በወኔ ተፈተለከ ።

“እናንተ ቡከኖች ንቅንቅ እንዳትሉ ! ባላችሁበት ቁሙ ! ከሁላችሁም ጋር በቀጥተኛ ፍልሚያ ሊገጥማችሁ ደፍሮ ከመጣ አንድ ቆራጥ ጀግና ፊት እንዳትፈረጥጡ” እያለ ዶን ኪኾቴ ያምባርቅ ጀመር ።

በዚያን ወቅት ነፋሱ የወፍጮዎቹን መዘውሮች ማንቀሳቀስ ጀምሮ ነበርና ንግግሩን ሰምተው ሊቋቋሙት የተዘጋጁ መሰለ—እንቅስቃሴያቸው ።

ዶን ኪኾቴ ጥቂት ቆም አለና ፤ “የውቦች ውብ የሆንሽው የኔዋ ዱልሲኒያ ሆይ! በዚህ አደገኛ ፍልሚያ እንድታግዢኝ እማፀንሻለሁ !” አለ ድምፁን ከፍ በማድረግ። ከዚያም ያንን ረዥም ጦሩን ሰብቆ ፤ ጋሻውን በክንዶቹ ወጥሮ አነገበና ፤ ሮሲናንቴን ኰርኩሮ በከፍተኛ ፍጥነት በቅርብ ወደሚገኘው የወፍጮ ማዞሪያ ተምዘገዘገ ።

ያ ረዥም ጦር በኃይል በሚሽከረከረው በአንደኛው መዘውር ጨፍሮ ሲሰካ ፤ ከመቅጽበት ከጀግናው እጅ አምልጦ ወደላይ ጉኖ ወዲያው ከመሬት ተንከትክቶ ተሰነጣጠረ ፤ ጀግናውና ፈረሱ ተፈናጥረው ወደቁ ። ከእሽከርካሪቱ ፍጥነት የተነሣ ዶን ኪኾቴ በወደቀበት ሥፍራ ሰማይና ምድሩ ዞረበት ፤ የፈረሱና የዶን ኪኾቴ አወዳደቅ የሚያሳዝን ነበር ።

ሳንቾ ፓንሳ ፣ ተደናግጦ ግራጫ አህያው የቻለችውን ያህል እንድትጋልብ አድርጎ ፣ ምስኪኑ ጌታው ከወደቀበት ሥፍራ ደረሰ ። ጌታው በሚያሳዝን ሁኔታ በመንገዱ ዳርቻ ወድቋል። የራስ ቍሩ ወልቆአል ፣ ጋሻው ወዲያ ይጣ ተፈናጥሮአል ።

ሳንቾ ፓንሳ ጠጋ ብሎ ፡ "ጌታዬ እኔን ሊያመሰግኑኝ ይገባል ፤ ቀደም ብዬ በነፋስ ኃይል የሚሽከረከሩ መዘውር ወፍጮዎች ናቸው ብዬዎት አልነበረም ?" አለ ።

"ወዳጄ ሳንቾ ! ሰላም ላንተ ይሁን" አለና የዐይኖቹን ሽፋሽፍት ከጠራረገ በኋላ ፣ "በዓለም ላይ የማያስተማምን ነገር ቢኖር ጦርነት ነው ። ይህን ሁሉ ነገር ያደረገብን ፣ መጻሕፍቶቼን የሰረቀኝ ያ እኩይ መንፈስ ፣ 'ፍሬስቶን' ነው ፤ እንዳሜወትነሁህ እኒህ የምታያቸው ነገሮች ጭራቆች ነበሩ ። ነገር ግን 'ፍሬስቶን' ወደ ነፋስ መዘውረ ወፍጮ በምትሐት ለወጣቸው ፤ ድል እንዳልቀዳጅ ክብር እንዳላገኝ ያደረገው ደባ ነው ። ቢሆንም በመጨረሻው ከእርሱ ጋር በወኔ ሙሉነት መጋጠሜ እንደማይቀር ልብ በልልኝ" አለ ዶን ኪኾቴ ።

"እንደ አፍህ ያርግልህ እላለሁ" አለ ሳንቾ ፓንሳ ከአህያው እየወረደ። ሳንቾ ፣ ዶን ኪኾቴን ከወደቀበት ቀና አደረገውና ፣ ጋሻውን ከተፈናጠረበት አምጥቶ ፣ የራስ ቍሩንም በወጉ አስተካከለለት ።ያንን ዕድለ ቢስ ፈረሱንም ጎትቶ አቀረበለትና ፣ ዶጋግሮ ኮርቻው ላይ እንዲቀመጥ ፎዳታውን አበረከተ ።

ፀሐይ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ የዕለት ጉዞዋን ለማከተም ትገሠግሣለች ። ጀግናው ዶን ኪኾቴና ጋሻ ጃግሬው ሳንቾ ፓንሳ በትካዜ መንፈስ ተውጠው የሞንቴዬል ምስክ ዘልቀው ፈኸሙን ጉዞ ቀያያዙት ።

ፍልሚያ ከመነኮሳት ጋር

በነፋስ ከሚንቀሳቀሱት መዘውረ ወፍጮዎች (ዊን
ድሚል) ጋር የተፈጸመው ጦርነት እንዳበቃ ፣ ዶን ኪኾ
ቴና ጋሻ ጃግሬው ፣ በዚያኑ ቀን ከቀትር በኋላ እየተንጠ
ራወዙ ሲጓዙ ፣ በመንገዳቸው ላይ አንድም ቤት ወይም
የሚጠጉበት መከለያ አላጋጠማቸውም ። ፀሐይዋ ጠልቃ
ጨለማው ለዐይን ድንግዝግዝ ሲል ፣ በአቅራቢያቸው ለማ
ረፊያ ምቹ የሚመስል ችምችም ያለ አረንጓዴ ቅጠል የበ
ዛበት ጫካ አገኙ ።

ዶን ኪኾቴም ቆም አለና ፣ "ይኸውልህ ሳንቾ!
ከእንግዲህ ርቀን እንሔድም ፤ በዚህ ጭው ያለ ቦታ አን
ድም ቤተ- ግንብ ወይም ትንሽ ሆቴል ስለ ሌለ፣ከዚህ ችም
ችም ባለው ቁጥቋጦ ውስጥ ማረፍ አለብን" አለ በደከመ
ድምፅ ። ሁለቱም ከእንስሶቻቸው ላይ ወረዱ ። ሳንቾ እን
ስሳቱን ሲመግብ ፣ ዶን ኪኾቴ እጆቹን አጣምሮ በዛ
ፎኛ ጥላ ሥር ይንሸራሸር ጀመር ።

ቀና ሲል ፣ በአንዱ አርጌ ባሉጥ ላይ ዐሥር ክንድ
የሚሆን ለስለስ ብሎ ቀጥ ያለ ፣ ግን የጠወለገ ረዥም ቅር
ንጫፍ ተመለከተ ። በብዙ ድካም ያንን የደረቀ ቅርንጫፍ
ከዛፉ ላይ ገነጠለ ። ቅርንጫፉን ለማረፊያነት ወደ መረ
ጠው ሥፍራ ወስዶ ፣ በትዕግሥት ቅጠሎቹን መለመለ ።

'ከነፋስ ወፍጮዎች ጋር ባደረግሁት ጦርነት በጠ
ፋው ጦሬ ምትክ ይህ በጣም ይረዳኛል ' አለ ዶን ኪኾቴ
ረዥሙን ዕንጨት እየነካካ ። ቀጨል አደረገና ' እንዴ

ያውም ብዙ ጀግኖች ይህን መሳይ አልባሌ መጣሪያ ይዘው ነገር ግን ተአምር እንደ ሠሩባቸው አንብቤአለሁ ’ እያለ ለራሱ ይናገር ጀመር ።

ጊዜው መሸ ፤ ዶን ኪኾቴ አባዶ መሬት ላይ በጸጥታ ተቀምጦ ከዋክብትን እንጋጦ መመልከቱን ቀጠለ ። አእምሮው ከዚህ ቀደም በየመጻሕፍቱ ውስጥ ባነበባቸው ታሪኮች ውስጥ ባጋጠሙት ጀግኖች ገድል ተውጥሯል ። እኚያም ጀግኖች ጭው ባለ በረሃና ጥቅጥቅ ባለ ደን ውስጥ ጨለማ ለብሰው ፥ ለረዥም ሰዓታት ይጠብቁ እንደ ነበር ታወሰው ። ስለሆነም ዶን ኪኾቴ እንቅልፉ በዐይኑ ሳይዞር ከምሽት እስከ ንጋት በጀግንነት ቁጭ ብሎ እነጋ ።

ሳንቾ ፓንሳ ግን ፥ በእንዲህ ዐይነቱ ጅላ-ጅል ሐሳብና ሥራ ምሽቱን አላሰለፈም ። ቅጠላ - ቅጠሎች ነገ ጉዞ ፥ ሰውነቱን አፍታቶና ተዘረጋግቶ እንቅልፉን ይለጥጥ ጀመር ። እንዲያውም ጌታው ባይቀሰቅሰው ኖሮ ፥ በማግሥቱም እስከ እኩለ ቀን ድረስ ይተኛ ነበር ።

ቁርስ ላይ ምንም ጊዜ አላበከኑም ። ለጀግናው ዶን ኪኾቴ ቀኑ ተስፋ የሚጠቁም በመሆኑ አንዳች ደቂቃ እንኳ ለማባከን አልፈለገም ። ዶን ኪኾቴ ፈረሱን ፥ ሳንቾ አህያውን ፥ ኮርቻ ከጫኑ በኋላ በየእንስሶቻቸው ላይ ተቀምጠው ፥ ፀሐይ ብርሃንዋን ስትፈነጥቅ ጉዞአቸውን ቀጠሉ ። ብዙ ምዕራፍ ከተጓዙ በኋላ በመጨረሻ ወደ አንድ ጋራ ሸንተረር ወደ ሚበዛበት አገር ደረሱ ። ከቀትር በኋላ ድንጋያማ የሆኑ ኮረብታዎችን ዐልፈው በቋጥኞች መኻል ያሉትን መስኮች ሰንጥቀው ፥ ሸለቆዎችን ዐልፈው ‘ ላፒስ ’ ወደ ተባለው መሿለኪያ ገቡ ።

‘‘ይኸውልህ ሳንቾ ! እነሆ ይታይህ የጀግንነት ተግባራችንን የምናሳይበት ምሽግ! ’ አለ ዶን ኪኾቴ በኩራት ።

"ታዲያ ያቺን ደሴት ያኪትን በዚህ አካባቢ የሚ ያገኙልኝ ይመስልዎታል ?" ሳንቾ ፓንሳ ጠየቀ ።

"በርግጥም አገኘለሁ ማለት አልችልም ። ነገር ግን አንድ የተለየ ጉዳይ ልብ እንድትል እሻለሁ ። ይኸውም ከእንግዲህ በማንኛውም ፍልሚያ እኔ ነኝ የምጋፈጠውና የምዋጋው ። ከባድ አደጋዎች ውስጥ ወድቄ በብዙ ጠላቶች ተከብቤ ልታየኝ ትችላለህ ። እና ፣ ታዲያ የምገጥማቸው ተራ ወሮበሎች ካልሆኑ በስተቀር ፣ በምንም ዐይነት ርዳታህን እንዳታደርግልኝ ። የጦረኛ ሕግ እንደሚደነግገው ፣ ጋሻ ጃግሬ ከጦረኛ ጌታው ጐን ሆኖ እንዳይገጥም የተከለከለ ነው" አለ ዶን ኪኾቴ ።

ሳንቾ ፓንሳም ፣ "እሂ ገባኝ ገባኝ ! ያሉትን እፈጽማለሁ ። እንዲያውም ለውጊያ ፍላጐቴ ይህን ያህል ጠንካራ አይደለም ። እጠብ ውስጥ ዘልዬ መግባትም አልፈልግም" አለ ጉዳዩን በማናናቅ ።

"ባንተ ደረጃ ያለ ሰው ማድረግ ያለበት ይህንን በመሆኑ ትክክል ነህ" አለ ዶን ኪኾቴ ።

"ቢሆንም አንድ ጦረኛ አስቀድሞ ቢያንቀኝ ፣ ለማድረጌ ርግጠኛ አደለሁም ፣ ጥቂት ቡጢዎች መሰንዘሬ አይቀርም ! " አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

"ትክክለኛ ሐሳብ ነውና አልከለክልህም ። ነገር ግን ፣ እኔን ለመርዳት ስትል ከማንኛውም ጥሩር-ለባሽ ፈረሰኛ ወይም ፈረሰኞች ጋር ስጋጠም ጠብ ውስጥ እንዳትገባ አደራዬ የጠበቀ ነው" አለ ዶን ኪኾቴ ።

"እሺ ጌታዬ ትእዛዝዎን እፈጽማለሁ" አለና ፣ "እረ እንዲያውም ከጦረኛ ወይም ከጦረኞች ጋር የመጋጠም ፍላጐት ጨርሶ የለኝም" አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

ይህን በመነጋገር ላይ እንዳሉ ፥ ሁለት መነኮሳት በርጋታ እና ዶን ኪኾቴ ወዳሉበት መቿለኪያ አቅጣጫ ሲያመሩ አዩ። መነኮሳቱ የለበሱት ጥቋቁር ካባዎች ሲሆን ፥ ረገቨርም በቅሎዎቻቸው ላይ ተቀምጠው ሲታዩ በግመል የሚጓዙ መንገደኞች ይመስሉ ነበር ። ለአቧራ መከላከያ ጭምብል ፊታቸውን ሸፍነዋል ። ፀሐይም እንዳይመታቸው ድባቸውን (ሰፋፊ ጥላ) ዘርግተው ይዘዋል ።

ከመነኮሳቱ በስተኋላ ፥ ጥቂት እልፍ ብሎ ባለ አራት እግር ተሽከርካሪ ሠረገላ ፥ በሁለት ትናንሽ ፈረሶች እየተጎተተ ይጓዛል ። ከሠረገላው ለጥቆ አራት ወይም አምስት ፈረሰኞችና ሁለት በቅሎ ጫኞች በእግራቸው ይኳትናሉ ። በአሸበረቁ ልብሶች ያጌጠች አንዲት እመቤት ወደ አቅራቢያው ከተማ ለመጓዝ እሠረገላው ውስጥ ትገኛለች ። ይህንን በርቀት ዶን ኪኾቴ ተመለከተና ፥

"አንድ አስደናቂ ታዋቂ ገድል የምንፈጽምበት ወቅት የተቃረበ ይመስለኛል" አለ ፈረሱን በልጓም ቆንጠጥ እያደረገ ።

"እንዴት ሊሆን ይችላል?" ሳንቾ ፓንሳ ጠየቀ ።

"መልካም ። እነዚያ ጥቋቁር የለበሱት አስማተኞች እንደሆኑ እርግጠኛ ነኝ ፤ አንድ የሆነች ልዕልት ጠልፈው በሠረገላ የሚኮበልሉ መሆን አለባቸው ። እንዲህ ዐይነቱን እኩይ ተግባር መግታት የጀግንነት ግዴታዬ ነው" ይል ጀመር ፥ ዶን ኪኾቴ ፈርጠም ብሎ ።

ሳንቾም ፥ "አሃ!" በማለት ትንፋሹን በቅሬታ ድምፅ ካወጣ በኋላ ፥ "ከነፋስ መዘውረ ወፍጮዎች ጋር ከተደረገው ፍልሚያ የባሰ ችግር እንዳያመጣ ነው የኔ ሥጋት" አለ በጭንቀት አገላለጽ ።

ዶን ኪኾቴም ጊዜውን ሳያባክን ፈረሱን ኮርኩሮ ፣ መንኮሳቱ በሚመጡበት አቅጣጫ የመንገዱን መኻከለኛ መሥመር ይዞ ይጋልብ ጀመር ።

"ባላችሁበት ቁሙ ፣ እናንተ ሕገ ወጥ አስማተኞች ! እኒያን ከትልቅ የዘር ሐረግ የሚወለዱትን ልዕልቶች ነጻ እንድትለቋቸው አዝዣችኋለሁ ! እሻፈረን ካላችሁ ግን የሞት ጽዋችሁን ለመጎንጨት ተዘጋጁ " አለ ድምፁን ከፍ አድርጎ ።

መንኮሳቱም በቅሎዎቻቸውን ቆም አደረጉና ፣ ፊታቸውን የሸፈኑበትን ጭምብል (ማስክ) አወለቁ ። 'ምን ዐይነት ሰው ነው ያጋጠመን ' በሚልም አድናቆት በጣም በጣም ተገረሙ ። በእርግጥም የዶን ኪኾቴ አኳኋን ልዩና በጣም የሚገርም ነበር ።

"የተከበሩ ጦረኛ ሆይ ! እኛ አስማተኞች አይደለንም። ስግል ጉዳዮችን የምንጓዝ የማይማኖት ሰዎች ነን እንጂ ! ስለ አንድም ልዕልት የምናውቀው ነገር የለም " አሉት መንኮሳቱ በአክብሮትና በፍርሃት ድምፅ ።

ዶን ኪኾቴም ፣ "እኔን ማታለል አትችሉም ። ደኅና አድርጌ ዐውቃችኋለሁ ። ምንም ያህል ብታወድሱኝ ከሐሳቤ ፍንክች አልልም " አለ ቆጣ ባለ አንደበት ።

ዶን ኪኾቴ ፣ ወዲያው አንዳች ቃል ሳይተነፍስ ጦሩን ሰብቆ ፣ ፈረሱን ኰርኩሮ እጅግ በሚያስፈራ እንቅስቃሴ አቅራቢያው ወደሚገኘው መነኩሴ ተንደረደረ ።

ያም መነኩሴ ከመደንገጡ የተነሣ ፣ ከበቅሎው ላይ ተሽቀንጥሮ ከመንገዱ ባሻገር ተንደባለለ ። በዚህ ዐይነት ዘዴ ሕይወቱን ባያተርፍ ኖሮ ፣ ዶን ኪኾቴ ከትልቁ ዛፍ ቆርጦ ባበጃጀው ሹል ሶማያ ፣ እንዳሰነዘዘሩ ቢሆን

እናቱን ፈጥርቆ በገደለው ነበር ። ሌላኛዉ መንኩሴ ፣ ክፉኛ ከመፍራቱ የተነሣ በቅሎውን በአለንጋ እየገረፈ ልክ ነፋስ ጋር የሚወዳደር ይመስል መሿለኪያውን ፀልፎ መስኩን አቋርጦ እግሬ አውጭኝ ብሎ ፈረጠጠ ።

በዚያን ጊዜ ፣ ሳንቾ ግርግሩ ወደ ተፈጠረበት ቦታ ደረሰ ። ከአህያው ጀርባ ዱብ ብሎ ወረደና ወደ ወደቀው መንኩሴ ቀርቦ ልብሱን መግፈፍ ጀመረ ።

የመነኮሳቱ አሽከሮች የነበሩት ሁለቱ በቅሎ ነጂዎች የሳንቾ ሥራ ገረማቸው ።

“ለምንድን ነው እንዲህ የምታደርገው አንተ ዘራፊ” እያሉ ጮኹበት ።

“እኔ ዘራፊ አይደለሁም ፤ ጌታዬ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ድል ካደረገው ጦርነት የተገኘውን የምርኮ ዕቃ መውሰዴ እንጂ መዝረፌ አይደለም” አለ ሳንቾ ፓንሳ በኩራት አነጋገር ።

እነያ ሁለት ጨካኝ ሰዎች ግን ፣ የሳንቾን ንግግር ከምንም አልቈጠሩም ። በድንገት እላዩ ጉብ ብለው ፣ ያላንዳች ርኅራኄ ወገሩትና ጼመንገዱ አጠገብ ከሚገኘው ጉድባ ውስጥ ጣሉት ። ጭቃ ውስጥ አስተኝተው በርግጫ ከረመረሙት በኋላ ሕይወቱን ስቶ ይንደባለል ጀመር ።

የዶን ኪኾቴን ሽምጥ ግልቢያ መነኩሴው ባየ ጊዜ ፣ ከወደቀበት ከመቅጽበት ተነሥቶ በቅሎው ላይ ጉብ አለ ። በአለንጋ በቅሎውን እየገረፈና በእርካቡ እየኰረኰረ ጓደኛው መነኩሴ ወደ ገሠገሠበት አቅጣጫ ተፈተለከ ። መሿለኪያውን እስኪያልፍ ድረስ ዞሮ ሳያይና ላፍታ እንኳ ሳይቆም ፣ በሰላም ማምለጡን እስካረጋገጠ ድረስ ግልቢያውን ቀጠለ ።

በዚህን ጊዜ ዶን ኪኾቴ ሥረገላውን አስቁሞ ከፈረሱ ላይ ወረደ ። በሠረገላው በር ወደ ውስጥ ከተመለከተ በኋላ ፤ ተቀምጣ ለነበረችው እመቤት ሰላምታውን ያኸጕደጕድ ጀመር ።

‘‘ውቢቱ ልዕልት ሆይ ! የላ ማንቻ ዶን ኪኾቴ የተባልኩ ጥሩር-ለባሽ ፈረሰኛ እኔ ነኝ ። የማረኩሽን ወንበዴዎች ድል አድርጌ እነሆ ከእጃቸው ነጻ ስላወጣሁሽ እጅግ በጣም ደስ ብሎኛል ። ለጀግናዊ ድርጊቴ ግን ዋጋ ይከፈለኝ አልልም ። ነገር ግን አንድ የምለምንሽ ጉዳይ አለ ፤ ይኸውም መንገድሽን ወደ ቶቦሳ አቅንተሽ ፤ ለእመቤቴ ሆይ ዱልሲኒያ ላንቺ ስለ የፈጸምኩትን ጀብዱ በዝርዝር እንድትነግራልኝ ብቻ ነው ።’’

ይህን በመነጋገር ላይ እንዳሉ ፡ ከእመቤቲቱ አንጋቾች አንዱ ፡ በፍጥነት ጋልቦ መጣና ዶን ኪኾቴ ጦሬ ነው ብሎ የያዘውን (ሶማያ) ዕንጨት ጨምዝዞ ቀማው ። በጕልዳፋ የቢስኛ ቋንቋም ፥

‘‘ሒድ ከዚህ ! መረገላውንም ለቀቅ አድርግ ፤ ካለበለዚያ ባልገድልህ እኔ የቢስካያኒቱ ልጅ አይደልሁም ! ’’ አለው የእመቤቲቱ አንጋቹ ፡ በደም ፍላት ።

‘‘ጨዋ ሰው ብትሆን ኖሮ እገሥጽህ ነበር ! ’’አለ ዶን ኪኾቴ ።

‘‘ምን አልክ ? . . .ጨዋ አይደለህም ነው የምትለኝ? ጨዋ ሰው መሆኔን አሳይሃለሁ ። እኔ በባሕር ጨዋ ፥ በየብስና በማንኛውም መስክ ጨዋ ነኝ ’’ አለ የቢስካያኑ ተወላጅ በዛቻ ቃላት ።

‘‘ጨዋ ከሆንክ እንግዲያው ካንተ ጋር ልፋለም ዝግጁ ነኝ ! ’’ አለ ዶን ኪኾቴ ቆጣ ብሎ ።

ይህን ተናግሮ በሚያስደንቅ ፍጥነት ፈረሱ ላይ ጉብ አለና ፣ ጉራዴዉን ነቅንቆ በሚያስፈራ ሁኔታ በቢሳካያኑ ተወላጅ ላይ ተወናጨፈበት ። ያልተገራችው የቢስካያኑ በቅሎ ደንብራ ወደ ሌላ አቅጣጫ ባትመልሰው ኖሮ እንደ እሰንዛዘሩ ከፍተኛንት ከባድ ጉዳት ባደረሰበት ነበር። ሆኖም ፣ ሰውዬው ከወደቀበት ወዲያው ተነሥቶ በግራ እጁ ከሠረገላው ውስጥ የመደገፊያ ትራስ አውጥቶ እንደ ጋሻ መከቶ ፣ ጉራዴዉን በቀኝ እጁ መዘዘ ።

እመቤቲቱ ይህን አይታ ኡኡታዋን አቀለጠችው ። የሠረገላዋ ነጂ ፣ ፈረሶቹን ገራርፎ በፍጥነት ያስጋልባቸው ጀመር ። ለፍልሚያው ያመች ዘንድ ከመንገዱ ላይ ሁሉም ነገር ገለል ተደረገ ።

ዶን ኪኾቴና የቢስኪያኑ ተወላጅ ጉራዴያቸውን ከእናታቸው በላይ እስኪታይ ድረስ እንሥተው ግንባር ለግንባር ተፋጠጡ ። እግረኞቹ በቅሎ ነጋዴዎች ለግ ልግል እየተሯሯጡ ደረሱ ። ዶን ኪኾቴ ግን ፣ ለግልግል የደረሱትን እንዳላየ አይቶ ለፍልሚያው ብቻ ተዘጋጀ ።

‘‘የውበት አበባ የሆንሽው ዱልሲኒያ ሆይ ! ከዚህ አደገኛ ፍልሚያ ጀግናሽ በድል እንዲወጣ ርዳታሽን እንዳ ትነፍጊው’’ እያለ ዶን ኪኾቴ ይማጠን ጀመር ።

ጥቂት እንኳ ሳይቆዩ ፣ የቢስኪያኑ ተወላጅ ጉራዴ በኃይል ተሠንዝሮ በዶን ኪኾቴ ጀርባ ላይ ዐረፈ ። የለ በሰው ጥሩር ጥንት ከልዩ ብረት የተሠራና ጠንካራ ባይ ሆን ኖሮ ፣ የዶን ኪኾቴ ሰውነት ለሁለት ክፍል ባለ ነበር። እንደ ዕድል ሆኖ ዶን ኪኾቴ ምንም ዐይነት ጉዳት ሳይ ደርስበት የቢስኪያኑ ጉራዴ ሜፍ የመታጠፍ ዕድል ደረ ሰበት ። ዶን ኪኾቴ ከጉራዴው ምት እንደ ዳነ ራሱን ጠንክር ፣ ጠና አደረገ ። የራሱን ጉራዴ በእጁ ሙሉ አጥ

ብቃ ጨበጠና ፤ ወደ ሰማይ ከፍ አድርጎ የመጨረሻ ምቱን ለማሳረፍ ኃይሉን ሰበሰበ ።

የሴትዮዋ አሽከሮችና በቅሎ ሜኞች በዶን ኪኾቴ ንዴትና ድርጊት ተደናገጡ ። በሠረገላው ውስጥ የነበረ ችውም እመቤት ራቅ ካለ ቦታ ከግርግሩ ድና ነገር ግን ጋሻ ጃግሬዋን መላዕክት ከተፈጠረው መከራ እንዲያወ ጡላት በጸሎት መማጠኗን ቀጥላለች ።

ይህን የማይረሳ ፍልሚያ ምዕራፍና ውጤቱን ማራ ዘም ለምን ያስፈልጋል? ባጭሩ የቢስኪያኑ ተወላጅ ካል ተገራችው በቅሎ ጋር ሲታገል ፤ ከሠረገላው ውስጥ ባገ ኘው ትራስ ሰውነቱን ሲከላከል ፤ ጉራዴውን መዘዞ ከወ ዲያ ወዲህ ሲያወናጭፍ ይታያችሁ !! የዱላ ማንቻው ጥሩር ለባሽ ፈረሰኛ ኪኾቴም የሰይፉን ስለት እያብለ ጨለጨ ፤ ፈረሱን ወደ ፍልሚያው መድረክ እያስገደደና ሴላም ሴላም .....ሆኗልና ፤ ለማንኛውም ቃላት ሳና በዛ የዚህን ምዕራፍ ማክተሚያ መጋረጃ ብንዘጋው ይበ ጃል ።

የጠፋው ራስ ቅር

ቢዶን ኪኾቴና በቢስኪያኑ ተወላጅ መኻል የተ ፈጸመውን ታላቅ ፍልሚያ ውጤት ምን መልክ እንደ ነበረው ለመገመታችሁ ጥርጥር የለውም ።

ጀግናው ጦረኛ ፤ ዐይኑን ጨፍኖ ወደ ባላጋራው ሲወ ናጨፍ ፤ የቢስኪያኑ ጉራዴ ለሁለተኛ ጊዜ አንገ ብበበት ። በክንዱ መክቶ ባይከላከል ኖሮም ፤ የዶን ኪኾቴ ታሪክ ባከተመ ነበር ። መልኳም አጋጣሚ ሆኖ ፤

ምቱ የዶን ኪኾቴን ጥፍር ጨፍልቆ ግራ ጆሮውን ላሰት (አቁስሎት) ወለፈ ።

ዶን ኪኾቴ ፣ ጥቃቱን ሳይመልስ የቢስኪያኑ ተወላጅ በቅሎ ደነበረች ። በድንገት ወደፊት እመር ብላ በከፍተኛ ፍጥነት ወደ ሜዳው ትሮጥ ጀመር ። እሯሯጧም የእመቤቲቱ ሠረገላ ወደ አለበት አቅጣጫ ሆነ ። እንዲት ፈላሽ ኩሬ ለመሻገር እንጣጥ ብላ ሰውነቷን እጥፍጥፍ ብታደርገው ፣ የተቀመጠባትን ጌታ ከመሬት አደባየችው ።

ምስኪኑ የቢስኪያን ተወላጅ ከበቅሎይቱ ላይ በመውደቁ ሕሊናውን ሳተ ። ተዝለፍልፎ ጭቃና ረግረጉ ላይ ተበረረ ። ዶን ኪኾቴ ከወደቀው ሰውዬ ብዙም አልራቀም ነበርና ፣ የፈረሱን ልጓም ሳብ አድርጎ ከኮርቻው ዱብ አለ ። ከመቅጽበት ርጦ ፣ ከወደቀው ጠላቱ ደረት ላይ የሰይፉን ጫፍ ተክሎ በድል አድራጊነት ቆመና ፣

" በል ድል መሆንክን አምነህ ተቀበል ፤ እሻፈረኝ ካልክም አንገትህን ነው የምቀላው " እያለ ዶን ኪኾቴ ይፎክር ጀመር ። የቢስኪያኑ ተወላጅ ምንም አይሰማውም ፤ ነፍሱን አጥቶ ከዶን ኪኾቴ እግር ሥር ተንጋልሏል ። እመቤቲቱ ከሠረገላዋ ቀፈናጥራ በመውረድ ጋሻ ጃግሬዋን ለማዳን ከሥፍራው ባታደርስ ኖሮ ፣ ይደርስ የነበረውን አሠቃቂ አደጋ ለመግለጽ ያዳግታል ። እንባዋን እያዘራች ዶን ኪኾቴ የታማኝ ጋሻ ጃግሬዋን ሕይወት እንዳያጠፋ ትማጠን ጀመር ።

ዶን ኪኾቴም ፣ " እጅግ የተዋብሽው እመቤት ሆይ ! " አለና ዘና በማለት ፣ " ጥያቄሽን እቀበላለሁ ። ሕይወቱን የምምርልሽ አንድ ቃል የገባሽልኝ እንደሆን ነው " አላት ።

" ግዴታዉ ምንድን ነው ? " እመቤቲቱ ጠየቀች ።

“ ጋሻ ጃግሬሽ ቃል እንዲገባልኝ እፈልጋለሁ ። ከዚህ ሲነግ ፣ በቀጥታ ወደ ‘ ቶቦሳ ’ መሔድ አለበት ። ‘ቶቦሳ’ እንደ ደረሰም በእኔ ስም ወደር ከሌላት እመቤት ዱልሲኒያ ዘንድ ይቀርባል ። እሷም የፈለጋችን ነገር እን ድታዝዘውና እንድትፈጽም መብቱ የራሷ ይሆናል ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

እመቤቲቱም ፣ “ ስለ እርሱ ሆኘ ቃል እገባለሁ ” አለችና ፣ “ እርሱ እንዲያደርግልህ የምትፈልገውን ሁሉ ይፈጽማል ” አለች በትሕትና እንደበት ።

ዶን ኪኾቴም ፣ “እንግዲያውስ ሕይወቱ ትተርፋ ለች ! ” አለና ለእዚያች እመቤት ለጥ ብሎ በምን ሥር ዓት እጅ ነሣ ። ፈረሱ ላይ በኩራት መንፈስ ተቀመጠና ፣ ፈረሱን ከወዲያ ወዲህ በታላቅ ኩራት መለስ ቀለስ አደ ረገና ፣ ምንም ነገር እዚያ ቦታ እንዳልተፈጸመ ቁጥሮ ጉዞውን ቀጠለ ።

ሳንቾ ፓንሳ ብዙም ሳይዘገይ ፣ ዶን ኪኾቴ ዘንድ ቃልቦ ደረሰ ። እንደ ደረሰም የጌታውን እጅ ጨበጠና ፣

“ጀግናው ጌታዬ ዶን ኪኾቴ ሆይ ! መልካም ፈቃ ድህ ይሁንና ፣ በአሁኑ ታላቅ ፍልሚያ ድል ያደረከው ደሴት ላይ እኔን ገዥ ማድረግህን አትዘንጋ ” አለ ሳንቾ ።

“ ወንድሜ ሳንቾ ፣ እነዚህ የደሴት ፍልሚያዎች አይደሉም ። የአሁኑ መጠነኛ የመንገድ ላይ አጋጣሚ ፍልሚያ ነው ። ከነዚህ ሰዎች ያተረፍነው ነገር ቢኖር ፣ ራሰ መፈንከትና ጆሮ መድማት እንጂ ሌላ አይደለም ። ለማንኛውም ትዕግሥት ይኑርህ ! ምናልባት በሚቀጥለው ፍልሚያ የአንድ መንግሥት ግዛት ድል አደርጋለሁ ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

" ያማ እንዴታ ባማረ ነበር ! ……… ግን የጆሮህ ቁስል አያምህም ? » ሳንቾ ጠየቀ ።

" መጠነኛ ጭረት ነው " ካለ በኋላ ዶን ኪኾቴ ፣ « እውነተኛውን ጥሩር ለባሽ ፈረሰኛ ትንሽ ጭረት አታብ ሳጨውም ። ቢሆንም ፣ ማንኛውም ጀግና ቁስሉ እንዲታ ከምለት ይፈቀዳልና ፣ በል ጠጋ በልና ኪሴ ውስጥ በያ ዝኩት መድኃኒትና የቁስል ማሠሪያ አራፊ ጨርቅ አከ መኝ " አለ ።

ከዚያም ፣ አንድ ቅርንጫፉ በተንዠረገገ ዛፍ ጥላ ሥር ሁለቱም ዐረፉ ። ሳንቾ ደም የሚያዘንበው የጌታ ውን የጆሮ ቁስል ሲያክም ፣ ዶን ኪኾቴም ዘና ብሎ ወጉን ቀጠለ ።

" ወንድሜ ሳንቾ ! እንዲያው ለመሆኑ ! መታሰቢ ያነቱ ሲፋቅ የማይችል እንዲህ እንደኔ ታላቅ ተጋድሎ የፈጸመ የጥሩር ለባሽ ፈረሰኛ ታሪክ በሕይወትህ አንብ በህ ታውቃለህ ? »

" በጭራሽ ! " ሲል መለሰ ሳንቾ ፤ " እንዲህ እን ዳንተ ቆፍጣና ጀግና አይቼም አላውቅ ፤ በየትኛውም የታ ሪክ መጽሐፍ ውስጥ ፈጽሞ አላነበብሁም ። ወዲያው ም ኮ ማንበብም ሆነ መጻፍ ጨርሶ እንዳልተማርኩ ልታ ውቅልኝ ይገባል " አለ ። ዶን ኪኾቴ የሳንቾን ንግግር አላጤነም ። ምክንያቱም በዚያን ወቅት መንፈሱን ወጥሮ የያዘው ከቢስኪያኑ ተወላጅ ጋር ፍልሚያ ሲያደርግ የጠ ፋበት የራስ ቍር ጉዳይ ነበር ። በጠፋበት ቍር ምትክ በጉ ዞው ላይ ከሌላ ጦረኛ ጋር ተፋልሞ ድል አድርጎና ማርኮ ፣ አንዷት አዲስ ቍር ከራሱ ላይ እንደሚደፋ ያሰላስላል ።

በፍልሚያው ጊዜ የራስ ቍሩን ይዞበት ስለ ጠፋው አስማተኛም ካሰላሰለ በኋላ ፣ ከርሱም ጋር ቍፋልሞ ቍሩን

አስመልሶ ራሱ ላይ ሲያደርግ እየታየው ፣ ይህን ሁሉ ለሳንቾ ሲያወጋለት ጉቦአቸው ረዥም እንደሚሆን ግልጽ ነው ። ጥሩር-ለባሽ ፈረሰኛ መቼም የራስ ቍሩን ካጣክብ ርና ማዕረጉ ስለሚገፈፍ ፣ ምግብ እንኳ ሲቀርብለት መሶቡ ያለ መሸፈኛ እንደሚሆን በመሥጋት ፣ ዶን ኪኾቴ ሳንቾን ፤

በስሙ ጠራውና ፣ "በመንገዳችን ላይ ቍር የደፋ አንድም ሰው ሳያጋጥመን ነው እንዴ ?" ሲል ሥጋት አዘል ጥያቄ አቀረበለት ።

"እስካሁን ድረስ ጉዞአችን መልካም ነው ። ነገር ግን ፣ ምናልባት ቍር ያልደፋ አንድም ሰው ባያጋጥመን ፣ የሚደርስብንን አሳዛኝ ሁኔታ ማሰብ አለብህ ። በዚህ መንገድ የሚጓዙት ጥቂት ሰዎች ናቸው ። እነዚህም ጋሪ ነጂዎችና በቅሎ ሜኞች ሲሆኑ ፣ እነርሱም ቢሆኑ በጭ ራሽ ቍር አይደፉም" አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

ዶን ኪኾቴም ፣ "ተሳስተሃል ። አሁን ጥቂት ርቀን ሳንሔድ በሕልምህ እንኳ አይተሃቸው የማታውቃቸው መሣሪያ የታጠቁ ሰዎች ያጋጥሙናል" አለ ።

ሳንቾ ምንም መልስ አልሰጠም ። አህያው ላይ ወጣና ፣ ሁለቱም በሳርስ መሺሊኪያ ዐልፈው መንገዳቸውን ቀጠሉ ። በጉዞአቸውም ላይ ስለ ጥሩር-ለባሽ ፈረሰኝነት ገድል ፣ ስለ ልዩ ልዩ ርባን ቢል ጉዳዮች ከመነታረክ በስ ተቀር በአንድም ቁም ነገር አዘል ነጥቦች ላይ ጊዜአቸ ውን አላጠፉም ነበር ።

መሺሊኪያውን ፀልፈው ተራራማውን አገር በገ ግታ እያቋረረጡ ብዙ ተጓዙ ። ማምሻው ላይ ፣ እንደ አጋጣሚ በአንዲት አነስተኛ ሆቴል መስተንግዶው አምሮ

ጠበቃቸውና እዚያው ዕረፍት አደረጉ ። በሚቀጥሉት ቀኖችም ያለ አንዳች ዓላማ ለአዲስ ፍልሚያ በመዘጋጀት ብቻ ከወዲያ ወዲህ ሲናውዙ ከረሙ ።

ለጀግና ሙያ ጀብዱ አያሌ አጋጣሚዎች ነበሩ ። አደጋ የበዛባቸው ፣ ወይም አሥቂኝ የሆኑ ፣ የጥሩር-ለባሽ ፈረሰኝነትን ሙያ የሚያጎበዙ ፣ ብቻ ያልገጠማቸው ሰውና የገድል ዐይነት አልነበረም ። ምን ያደርጋል ፣ ከእነዚህ ሁሉ መኻል አንዱም እንኳ የራስ ቍር ያለበት አልነበረበትም ። ስለሆነም ፣ ጀግናው ዶን ኪኾቴ ያለ ጀግና ቍር ባዶ ራሱን መጓዙና ፣ በባለ ገበታ ልብስ ጠረጴዛ ላይ መብላት ዕጣ ፋንታው ነው ።

በበግ መንጋ ላይ ጦርነት

አንድ ቀን ዶን ኪኾቴና ሳንቾ ፓንሳ በኮረብታ ጫፍ ላይ ሲጓዙ ፣ አቧራ ልክ እንደ ደመና ሲነሣ ቁልቁል ተመለከቱ ። ዶን ኪኾቴ ዐይኑን ጎልጉሎ በአቧራው ላይ በርቀት ካተኮረ በኋላ ፣

“ዕድለኛይቱ ቀን እነሆ ደረሰች ሳንቾ ! ደስታና ሀብት የምታጎናጽፈን ቀን መጣች ! ለዘለዓለም የሚታወስና የሚጠሳ የጀብዱ ሥራ የምፈጽምባት ቀን ዛሬ ናት ። ያንን የሚነሣውን አቧራ ታየዋለህን ፣ ሳንቾ ?”

“አዎን ፤ ይታየኛል ጀግናው ጌታዬ !” አለ ጋሻ ጃግሬው ሳንቾ ።

“መልካም ። የምታየው አቧራ የሚነሣው ወደዚህ አቅጣጫ በሚተም ጦር ሠራዊት ነው ። ይህ ታላቅና ኃይለኛ ሠራዊት ከብዙ ሀገሮች የተውጣጣ ነው ።”

“ነገሩ እንዲህ ከሆነ ፣ በሁለት ቡድን የተከፈለ ጦር ሠራዊት ነው ! ምክንያቱም በስተግራችን በኩልም ሌላ አቧራ ይነሣል ” አለ ሳንቾ ።

ዶን ኪኾቴ አርቆ ተመለከተና ፣ ልቡ በደስታ ፈነደቀ ። ምክንያቱም ፣ እንደ እርሱ ጽኑ እምነት ከሆነ ፣ ሁለቱ ታላላቅ የጦር ሠራዊት የሚተመው ውጊያ ለመግጠም እንደሆነ አድርጎ አሰበ ። መንፈሱ በውጊያ ፣ በጀግና ገድልና በሚያስደንቁ ድርጊቶች ተመልቶ ፣ ባነበባቸው መጻሕፍት ውስጥ እንደ ተፈጸሙት ሁሉ ፣ አሁን የሚገጥሙትም በቀላሉ የሚከናወኑ መስለውና ፣ ፍላጐቱና ምኞቱ እውን ሲሆን ታየው ።

ያ ሁሉ አቧራ የተነሣው በሁለት ተከፍሎ በሚነዳ የበግ መንጋ እንደሆነ እያየም ዐይኖቹን ማመን ትቶ የሚመኘውን ብቻ ያይ ጀመር ። ስለ ሁለቱ ጦር ሠራዊት መቃረብ ርግጠኛ በመሆኑ ፣ ሳንቾ እንኳ ሳይቀር ዶን ኪኾቴ እውነቱን መስሎት ማመን ጀምሯል ።

“ጌታዬ አሁን ምን ማድረግ አለብን ? ” ሲል ሳንቾ ጠየቀ ።

“ማድረግ ያለብን ግልጽ ነው ። ማዳኛችን ምን መሆን አለበት ? ደካሞችን መርዳት ወይስ ከቁስለኞች ጐን መቆም ? ከፊት ለፊታችን የሚገኘው ጦር የሚመራው በታላቁ ሕንድ ደሴት ንጉሠ ነገሥት በታላቁ ‘ አሊፋን ፋሮን ’ ነው ። በእኛ ግራ በኩል የሚገኘው ጦር የሚታዘዘው በአሊፋንፋሮን ጠላት በንጉሠ አጫራቁት ክንዱ ‘ፔንታፖሊን ’ ነው ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

ሳንቾ ፓንሳ ነገሩ ግራ ገባውና ፣ “ ጀግናው ጌታዬ ሆይ ! የዚህ ሁሉ ጣጣ መንሥኤው ምን ይሆን ? እረ እን

ዚያ ታላላቅ ሰዎች ጆሮ ለጆሮ ገጥመው የሚሐሜት ለምንድን ነው ? ” ሲል ጠየቀ ።

“ በጣም የቆየ ታሪካዊ ጉዳይ ነው ፤ ንጉሠ ነገሥት አሊፋንፋሮን አረማዊ ሆኖ ሳለ ፣ ክርስቲያን በሆንችው በንጉሥ ፔንታፖሊን ሴት ልጅ ፍቅር ይነደፋል ። ነገር ግን ፣ ካልተጠመቀና ከንቱ እምነቱን እርግፍ አድርጎ ካልተወ በስተቀር ፣ የፔንታፖሊንን ልጅ ሊያገባት አይችልም ” በማለት ዶን ኪኾቴ ገለጸለት ።

ሳንቾ ፓንሳም ድምፁን ከፍ አድርጎ ፣ “ አይሆንም ! አይደረግም ! ነገሩ እንዲህ ከሆነ ፣ እኔ ከንጉሥ ‘ፔንታፖሊን’ንና ከሴት ልጁ ጐን እሰለፍና በሚቻለኝ ሁሉ እረዳቸዋለሁ ” አለ ።

“ እውነትህ ነው ። በእንዲህ ዐይነቱ ጦርነት ለመካፈል ጥሩር-ለባሽ ፈረሰኛ መሆን አያሻም ። ማንኛውም ሰው በዚህ ዐይነቱ ግጭት ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ አለበት ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

ዶን ኪኾቴ ወደሚነሣው አቧራ በዚያ ረዥም ጣቱ እያመለከተ ፣ እያሌ ጦረኞች ወደ ውጊያው በመጉረፍ ላይ እንዳሉ በሐሳቡ ያወጣ ያወርድ የነበረውን ይተነትን ጀመር ። ሳንቾ ፓንሳም በጥሞና አዳመጠው ። ዐይኖቹን ግራና ቀኝ እያማተረ ፣ ጌታው ስማቸውን ያነሣ የነበሩትን ጀግና ጦረኞች ለማየት ሙከራ አደረገ ።

በመጨረሻም ትዕግሥቱ አለቀና ፣ “ ኧረ በረዶም ጭምር እየወረደ ነው ይበሉኝ እንጂ ፣ በዚህም ሆነ በዚያ በሚነሣው ደመና መሰል አቧራ ውስጥ እንዳችም ሰው ፣ ወይም ጀግና አይታየኝም ” አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

" እንዴታ ! ግን የፈረሶቻቸው ማስካካት ፤ የመ ለከቶቻቸው ኡኡታ ፤ የነጋሪቶቻቸው ጉሰማ አይሰማ ህም ማለት ነው ? " ዶን ኪኾቴ ጠየቀ ።

" በጭራሽ ! እንዲያውም ጆሮዬን በሰፊው ከፍቼ አለሁ ፤ ነገር ግን የበግ መንጋ ጩኸት ብቻ ነው የሚሰ ማኝ ። "

በዚህን ጊዜ በሁለት የተከፈለው የበግ መንጋ ወደ እነ ዶን ኪኾቴ እየተቃረበ መጣ ። ድምፃቸው ከመሰማ ትም ዐልፎ በጐቹ ራሳቸው ይታዩ ጀመር ።

" ሳንቾ ምነው ፈራህ እንዴ ? .... እኔ እንዚ ያን አረማውያን በወኔ ስገጥም ፤ አንተ ግን ሐድና ሥርቻ ውስጥ ተሸሸግ ። "

ዶን ኪኾቴ ፤ ጦሩን ሰብቆ ፤ ፈረሱን ሮሲናንቴን ኰር ኲሮ ፤ እንደ መብረቅ እየጮኸ በመቃረብ ላይ ያለውን የበግ መንጋ ሊገጥም ገሠገሠ ።

ሳንቾ ፓንሳ በመገረም ተመለከተው ። ቀጠል አደ ረገና ፤ " ይቆዩ ጌታዬ ! ይመለሱ .... አበዱ እንዴ ? እኒህኮ በጐች ናቸው ። ርስዎ እንደሚሉት አረማዊ ወይም ክርስቲያን ሰዎች አይደሉም ። ይመለሱ ነው የምልዎት " አለ ድምፁን ከፍ አድርጎ ።

ዶን ኪኾቴ ግን ጨርሶ አልሰማውም ። በሚያስፈራ አኳኋን ወደፊት ጋለበና ፤ " እናንተ ጥሩር-ሰባሽ ፈረሰ ኞች በርቱ ! ወደፊት ገሥግሡ ! ድል አድራጊዎቹ እኛ ነን ! እኔን ተከተሉኝና ጠላቶቻችሁን ተበቀሉ ! " እያለ ዶን ኪኾቴ ድምፁን ከፍ አድርጎ ይጮህ ጀመር ።

በመንጋው መኻል ዘልቆ ገባ ። በቀኝና በግራ በኩል ይጓዙ የነበሩትን ምስኪናን በጐች በጦሩ እየወጋ ልክ

እንደ አባቱ ገዳይ በወኔ ሙሉነት እራወጣቸው ። የበጎቹ እረኞች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ይጣሩ ጀመር ፤ ነገር ግን አልሰማቸውም ፤ ልክ እንደ አበደ ሰው ከወዲያ ወዲህ ተቅነዘነዘ ። በጎቹ በአሞቃቂ ሁኔታ ተረጋገጡ ፤ የተቀሩት ብትንትናቸው ወጣ ።

ዶን ኪኾቴም ፡ "ስመሆኑ የዚህ ጦር ጀኔራል ወዴት ነው ? አንተስ ትዕቢተኛው ' አሊፋንፋሮን ' የት ነህ ? ተመልከት ይህን ብቸኛ ጦረኛ ! ተመልከት በውጊያ የሚቋቋምህንና ባነሣኸውም የግፍ ጦርነት ሲቀጣህ የመጣውን ጀግና " እያለ ለብቻው ሲጮህ ይሰማ ነበር ።

የበጎቹ እረኞች ክፉኛ ተደናገጡ ፤ በጦረኛው ላይ የድንጋይ ናዳ ያወርዱበት ጀመር ። ትላልቅ ቡጢ የሚያኽክለው ድንጋይ በዶን ኪኾቴ ጆሮ ግንድ በኩል ሲያልፍ ፡ ግማሹ ጋሻውን ሲጠልዘው ፡ ሌላዉ የምስኪኑን የሮሲናንቴን ጀርባ ይወግር ነበር ። እንደ በረዶ ለሚወርድበት የድንጋይ እሩምታ ደንታ ሳይኖረው ፡ በድፍረት እየጋለበና እየፎከረ ልክ በተፋፋመ ጦርነት ውስጥ ገብቶ እንደሚዋጋ ጀግና ሁነኛ ጠላቱን ፍለጋ ይቅነዘ ነዝ ጀመር ።

" ወዴት ነህ አሊፋንፋሮን ? " እያለ ዶን ኪኾቴ ድምፁን ከፍ አድርጎ በመጮህ ይጣራ ገባ ። ወዲያው አንድ ድንጋይ ተወርውሮ ወገቡን ቢመታው ፡ የጐድኑን አጥንት ሰብሮት ነበር ።

የሞተ ወይም ክፉኛ የቆሰለ መስሎት ዶን ኪኾቴ ኮርቻው ላይ ተጠመጠመ ። ነገር ግን ፡ ከዚህ ቀደም የትንሿ ሆቴል ባለቤት እንዲይዝ መክሮት የነበረው የቁስል መድኃኒት ትውስ አለውና ፡ ኪሱን መደባበስ ቀጠለ ። የመድኃኒቱን ጠርሙስ ወደ አፉ ሊያስጠጋ ሲል ፡ አንድ ድንጋይ በአየር ላይ ወዲያው ኳ ! የሚል ድምፅ አሰማ ።

ለካንስ የተወረወረው ድንጋይ ጠርሙሱን ሰብሮ ፥ እጁን
አቁስሎ ፥ አፉንም ደኅና አድርጎ ሙቶት ኖሯል ! !

እንዲህ ዐይነቱን ክፉ ምት ጀግናው ጦረኛ ሊቋ
ቋመው አልቻለምና ፥ ከፈረሱ ላይ ወድቆ ልክ እንደ ሞተ
ያህል እመሬት ላይ ተዘረረ ።

እረኞቹም በጉቻቸውን ከተበታተኑበት ሰብስበው
በተቻለ ፍጥነት ሽሽታቸውን ቀጠሉ ፤ ጥሩር-ልባሹ ፈረ
ሰኛውን የገደሉ መሰሏቸውና ፥ ከዚህም ጋር ከሚመጣው
ጦስ ለማምለጥም ጭምር ነበር ሽሽታቸውን የለቀቁት ።

በዚህ አስገራሚ ግጭት ጊዜ ሁሉ ፥ ሳንቾ ፓንሳ
በግራጫ አህያው ላይ ተቀምጦ ፥ ከአንድ ጉብታ ጫፍ
ላይ ሆኖ ፥ ጌታው በሚፈጽማቸው የዕብደት ድርጊቶች
እፍሮና ተደናግጦ ይመለከት ነበር ። በቅሬታ እያጉረ
መረመ ፥ በቁጭትና ተስፋ በመቁረጥ መንፈስ ተውጦ
ራሱን ሲነቀንቅ ቆየ ፤ ነገር ግን ጀግናው ጦረኛ ከፈረሱ
ላይ ተመትቶ መሬት ወድቆ ሲዘረር ባየ ጊዜ ፥ ለእርዳታ
ሮጦ ደረሰበት ።

“ አዩት ጌታዬ ! ይህ ሊደርስ የቻለው ፥ የኔን ምክር
ባለመቀበልዎ ነው ። የበግ መንጋ እንጂ የጦር ሠራዊት
አይደለም ብዬ አልነገርኩዎትምን ? ” እያለ ሳንቾ ድም
ፁን ከፍ አድርጎ ይጠይቅ ጀመር ።

ዶን ኪኾቴ ጥቂት ካጉረመረመ በኋላ ፥ ተመቻችቶ
ተቀመጠና ፥ “ ወዳጄ ሳንቾ ፥ መተተኞች የፈለጉትን
ነገር ቅርጹን ባሰኛቸው መልክ ወዲያው ለመለወጥ አስ
ቸጋሪ አይሆንባቸውም ። አየህ አይደለም ? ልክ እኔ ድል
አድርጌ እንዳበቃሁ ፥ የጥንቱ ጠላቴ ፥ ባልፈኛውን ጦር
ከመቅጽበት ወደ በግ መንጋ በአስማት ለወጠብኝ ! ! ይሆን

ሎሁ ያደረገበት የተገናኛፍኩትን ሞገስና ክብር ለመግ ፈፍ ሲባል ነው .... ”

“ እንዴ ! ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው እኔ ግን ያየሁት የበግ መንጋ ነበር ! ” አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

ዶን ኪኾቴ በብዙ ችግር ከተቀመጠበት ተነሥቶ ፣ በእግሮቹ ቆመ ። አፉን ከፍቶ በጣቶቹ መዳበስ ሲጀምር ፣ በጭካኔ በተወረወረ ድንጋይ የተመቱት ጥርሶቹ መነ ቃነቃቸው ተሰማው ።

“ ወዳጄ ሳንቾ ! ከእኔ ሁሉን ነገር ተማር ። ይህ ሁሉ ችግር በቅርቡ የመልካም ቀኖችን መቃረብ የሚጠቁም ምልክት ነው ። መልካም ዕድልም ሆነ ክፉ አጋጣሚ ዘለዓለማዊ ናቸው ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“ ለማንኛውም ” በማለት ሳንቾ የዶን ኪኾቴን ንግግር አቋረጠና ፣ “ ለማንኛውም ፣ ነገር ቢበዛ በእህያ አይጫንም ፤ እንደሚመስለኝ ፣ እርስዎ ከጥሩር ለባሽ ፈረሰኛ ይልቅ ሰባኪ ይወጣዎታል ” አለው ።

“ ጦረኞች ሁሉን ነገር ማወቅ አለባቸው ። እንዲያውም አንዳንድ ጦረኞች ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደሚሰብኩ መምህራን ከፍተኛ የስብከት ችሎታ የነበራቸው ነበሩ ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“ በጣም ጥሩ ! እንደ አፍህ ይሁንልህ ። ብቻ ይህን ቀውጢ ሥፍራ በፍጥነት ለቅቀን እንሒድና አንድ ማረፊያ ቦታ ፈልገን እህል እንቅመስ ” አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

ሳንቾ ፣ ዶን ኪኾቴን ደጋግፎ ፈረሱ ሮሲናንቴ ላይ እንዲቀመጥ ረዳውና ፣ እሱም ራሱ ግራጫ አህያው ላይ ጉብ አለ ።

ዶን ኪኾቴም ፤ “ ታማኝ የሆንከው የኔው ሳንቾ ፤ በል ቅደምና መንገድህን ቀጥል ፤ እኔ እከተልሃለሁ ” አለ ሙትት ባለ ድምፅ ።

ሳንቾ ፓንሳም ፤ ትእዛዙን ተቀብሎ በተራራው ሜፍ ላይ በሚወስደው መንገድ እየመራው ጉዞአቸውን ቀጠሉ ። ዶን ኪኾቴ በዝግታና በጨዋ ጉዞ ተከተለው ። ከእረኞቹ ጋር ባደረገው ፍልሚያ ሰውነቱ ተቀጥቅጦና ቆስሎ ስለ ነበር ፤ የፈረሱ ንቅናቄም ሕመሙን ስላባባሰበት ነበር ፤ ዶን ኪኾቴ ጉዞውን በዝግታ ያደረገው ።

ከጸጉር አስተካካዩ ጋር ፍልሚያ

ዶን ኪኾቴ ፤ ያለ ራስ ቁር መጓዝ ከጀመረ ቀናት ዐልፈውታል ። ምክንያቱም አሁንም ገና በመንገዱ ላይ አንዱን ጦረኛ ድል አድርጎ አዲስ የራስ ቍር ማርኮ የሚ ያደርግበት ምንም አጋጣሚ አልተፈጠረም ። ቢሆንም ፤ እያንዳንዱ ቀን የራሱ ገድል ፤ እያንዳንዱ ጕዳና ጥሩር ለባሽ ፈረሰኛውንና ጋሻ ጃግሬውን ወደ አዲስ ውጤታማ ድርጅት የሚመራ ነበር ።

አንድ ማለዳ ፤ አውራ ጐዳናውን ይዘው ፤ ከአንስተኛ መንደር ወደ ሌላ ትልቅ መንደር ሲጓዙ ፤ አንድ ፈረሰኛ በብግታ ወደ እነርሱ ሲያመራ አዩ ።

“ ያውልህ ተመልከት ፤ የታላቅነቴን ክብርና ሞገስ ይበልጥ የሚያደስልኝ የጀብዱ ሥራ አሁን ሊገጥመኝ ነው ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“ እንዴት እንዲህ ሊሆን ይችላል ? ” ሳንቾ ጠየቀ ።

“ አንድ ፈረሰኛ አይታይህም ? በራሱ ላይ እንደ ወርቅ የሚያብረቀርቅ አንዳች ነገር አድርጓል ። ባሉሳ

ሏት ‘ የማምብሪኖን ’ የራስ ቍር የደፋ ጦረኛ ነው ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“‘ የማምብሪኖ የራስ ቍር ’ ነው ያሉት ጌታዬ ? የማምብሪኖ ቍር ቢሆንስ ? ” አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

“ ቃል ኪዳኔን ታውቀዋለህ ፤ ሳንቾ ። ታያለህ ነገ የግቢታ ልብስ ባለው ጠረጴዛ መመገቢ የማይቀር ነው ፤ የጀግና ወግ ነው ! ምክንያቱም ያ በተቅበጠበጠ ፈረስ ሆኖ ጥፋር-ለባሽ ፈረሰኛ የወርቅ ቍር ደፍቶ ወደእኛ በመጋለብ ላይ ስለሆነ ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“ ለእኔ እንድም ጥፋር-ለባሽ ፈረሰኛ አይታየኝም ። እንዲያውም የሚታየኝ አንድ ተራ ሰው ልክ የኔት የሚመስል ግራጫ አህያ ተቀምጦ ነው ። በርግጥ በራሱ ላይ የሚያብለጨልጭ ነገር ይታየኛል ፤ የሚያብለጨልጭ ሁሉ ግን ወርቅ አይደለም ” አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

“ ምንው የማምብሪኖ ቍር ነው እያልኩህ ! ደግሞም የወርቅ ነው ! ” አለ ዶን ኪኾቴ በቁጣ ፍላት ።

እውነተኛው ጉዳይ ግን እንዲህ ነው ። ቀደም ሲል ከጠቀስኩላችሁ መንደሮች አነስተኛው ፤ ጸጉር አስተካካይ የለውም ። ስለዚህ የትንሹ መንደር ኅብረተሰብ በትልቁ መንደር ጸጉር አስተካካይ የግድ መጠቀም ነበረበትና ፤ ጸጉር አስተካካይ በተፈለገ ቁጥር በፈረስ ጋልቦ ይሔዳል። አንዳንድ ጊዜ የወንዶችን ሪዝ ለማስተካከል ፤ በሌላ ጊዜ የሴቶችን ጸጉር ለማሸም (ለመሥራት) ነበር ፤ የሚጠራው ። አብዛኛውን ጊዜ ጸጉር አስተካካይ የሚፈለገው ግን ፤ ጤናው የተናጋበትን ሰው በዋግምት ለማገም ነበር ። በዚያን ዘመን አንድ ሰው ሲታመም በዋግምት ሲታገም ፤ የተመረዘው ደም ይወጣና ከሕመሙ ይፈወሳል በሚል

እምነትና ባህላዊ ልማድ ላይ የተመሠረተ ሕክምና ነበር ።

ዶን ኪኾቴ ፣ የጸጉር አስተካካዩን ሁኔታና ሥራ ከተረዳ በኋላ ፣ ሮሲናንቴን ኰርኰሮ ግልቢያውን ቀጠለ ። ጸጉር አስተካካዩም የዶን ኪኾቴን አመጣጥ ተመልክቶ ከአህያው ላይ ተወርውሮ በተረከዞቹ ቆመ ። የመንገዱን ጠርዝ እመር ብሎ ከተሻገረ በኋላ ፣ በድኩላ ፍጥነት ሜዳ ሜዳውን ሸመጠጠ ። ጸጉር አስተካካዩ በዚህን ጊዜ ራሱ ላይ ደፍቶት የነበረው የነሐስ ሣህን ከሩጫው የተነሣ ወድቆ አቧራ ውስጥ ቀረ ።

ዶን ኪኾቴ ፣ የፈረሱን ልጓም ጎታ አደረገና ፣ «ይኸውልህ ሳንቾ ! የራስ ቊሬ ተገኘ ! መጥተህ አንሣልኝ ” በማለት ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ ።

“ እውነትም እንዴት ያለ የእጅ ማስታጠቢያ ሣህን ነው ! ” እያለ ጕንበስ ብሎ አነሣና ለጌታው አቀበለው ።

ዶን ኪኾቴ በታላቅ ደስታ ተሞልቶ ፣ ሣህኑን በራሱ ላይ ደፋውና ከወዲያ ወዲህ እያዟዟረ ፣ ዘምበል ቀና ፣ ወደ ኋላ ወደፊት እንደ ባርኔጣ አሽከረከረው ።

“ በጣም ሰፊ ነው እባክህ ። ጥንቱም ቢሆን የተሠራው ራስ ትልቅ ለሆነ ሰው ነበር ማለት ነው ። ጉድለቱ ደሞ የፊት መከለሊያ የለውም ፤ በዚህ ላይ ግማሽ ክፍሉ ጕድሏል ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

ሳንቾ ፣ በሣቅ ፍርስ አለ ። ጌታው ዶን ኪኾቴም ፣ ‘ ይህ ጅል አሁን ምን የሚያስገለፍጥ ነገር ገጠመው ! ’ በማለት በቊጣ አምባረቀበት ።

"እረ ምንም አላማቀኝም ። ብቻ ፣ በጣም ያሳሰበኝ ይህን የጸጉር አስተካካይ ማህን በራሱ ላይ ይደፋ የነበረው ሰው ምን ያህል ገንቦ-ራስ ኖሯል እያልኩ ነበር" አለ ሳንቾ አሁንም ማቁ እየመጣበት ።

ዶን ኪኾቴም ፣ « መልካም ። የጸጉር አስተካካይ ማህን መምሰሉ እርግጥ ነው ፤ ነገር ግን ይህ ሊሆን የቻ ሰው አንድ አስማተኛ ቅርጹን በመቱት በመሲወጡ ምክ ንያት ነው ። ወደ አንዱ ከተማ ስንደርስ ለአንድ ጦር መሣሪያ አንጥረኛ (ባለ እጅ) እሰጠውና ደንበኛውን የቍር ቅርጽ እንዲያሠሩልኝ አደርጋለሁ ። የስመ ጥሩ (ታዋቂው) ጦረኛ 'የማምብሪኖ' ቍር እንደሆነ ግን ጥርጥር የለውም" አለና ዶን ኪኾቴ ፣ በራሱ ላይ እያ ዟዟረ ወደ ጀርባቹም ዝቅ እያደረገ ይሞክር ጀመር ።

"እረ በዚህ ቅርጹም ቢሆን ምንም አይል ፤ ራሴ ላይ አደርገዋለሁ ።'ከቀዳዳ ይሻላል ጨምዳዳ' እንዲሉ" አለ ዶን ኪኾቴ ።

"የጦረኛዉ ግራጫ ፈረስ ያውና" አለ ሳንቾ ፣ ከመንገዱ ዳር ዳር እየተዘዋወረች ሣር የምትግጠውን የጸጉር አስተካካዩን ግራጫ አህያ በሌባ ጣቱ እያመለከተ ። ቀጠል አደረገና "የኔን ፣ ታማኝ አህያ በዚህች እለውጥለት ዘንድ አሁን ጥሩ ሐሳብ መጣልኝ" አለ ።

"መለዋወጥኮ ዘረፋ አይደለም ። ሆኖም ፣ የምናገኘውን ሁሉ ከዘረፍን ፣ የጦረኝነት ክብራችንን ዝቅ ያደ ርገዋል ። ግራጫው ፈረስ ለባለቤቱ ውድ ንብረቱ እንደ ሚሆን ጥርጥር የለውም ። ሆኖም ኮርቻ እንድትለዋወጡ ፈቅጀልሃለሁ ሳንቾ" አለ ዶን ኪኾቴ ።

“ በእውነቱ ብልህ ነዎት ጌታዬ !” አለና ሳንቾ ፣ ሌላ ምንም ሳይናገር ፣ ከጸጉር አስተካካዩ አህያ ላይ ኮር ቻውን አውርዶ በራሱ አህያ ላይ ሲጭን ፣ የራሱ አህያ በአዲሱ ኮርቻ ሦስት እጥፍ አሸብርቃ ታየች ። በፈጸሙት የዘረፋ ድርጊት ተኩራርተው ፣ ጠረኛዉ ዶን ኪኾቴና ጋሻ ጃግሬው ሳንቾ ፓንሳ ጉዞአቸውን ወደፊት ቀጠሉ ።

ከእስረኞቹ ጋር ፍልሚያ

ከቀን ወደ ቀን ፣ ሁለቱ ተጓዦች ከቦታ ቦታ ያለ አንዳች ውጤት ፣ እንዳሰኛቸውና መንገዱ እንደ መራ ቸው ተዘዋወሩ ። በመጨረሻም በስፓኝ ቋንቋ ፣ ‘ሲይራ ሞሬና’ ተብሎ ወደሚጠራው ጥቁር ተራራ የሚያዘልቀ ውን አባጣ ጎባጣ መንገድ ተያያዙት ።

“ አሁን ጀብዱ ሥራዎች የምናከናውንበት ወቅት ደረሰ ” አለ ዶን ኪኾቴ ድምፁን ከፍ አድርጎ ።

እውነትም አንድ ነገር ሲሆን ነው ። ምክንያቱም ፣ በመጀመሪያ ካዩት ጉብታ ጫፍ ላይ ፣ ቁልቁል እውራ ጎዳ ናውን ይዘው ፣ ፀሥራ ሁለት ሰዎች ወደ እነዶን ኪኾቴ አቅጣጫ በድካም ርምጃ ሲጠጉ አዩ ። ሰዎቹ በተራ ሰልፍ ገብተው ፣ እንደ መቁጠሪያ ተሳስረው ፣ እንዱ ሌላዉን በመከተል ይንቀሳቀሳሉ ። ለካንስ ሰዎቹ እንገታቸው ላይ ሰፋፊ የብረት ቀለበት ገብቶላቸው ፣ በረዥም ሰን ሰለት ተያይዘው የሚጓዙ ነበሩ ።

ከሰልፈኞቹ ቀደም ብለው ሁለት ጠመንጃ ያነገቡ ፈረሰኞች ይጓዛሉ ። በኋላ በኩል ያሉት ሰዎች ቆመጥና ጎራዴ በያዙ በሁለት እግረኞች ታጅበዋል ።

" ጌታዬ ያንን ይመልከቱ ! እነዚያ ምስኪናን የንጉሡን መርከብ እንዲቀዝፉ ተይዘው በመነዳት ላይ ናቸው።"

" ለምንድነው እንዲህ በጭካኔ የሚያሠቃዩዋቸው?" በማለት ጠየቀና ፣ ዶን ኪኾቴ ግርማ ሞገስ በተሞላበት አኳኋን ፈረሱ ላይ ተመቻችቶ ተቀመጠ ።

" መሊቲዎች መሆን አለባቸው ። ሕግና ደንብ ጥሰው እጅ ከፍንጅ የተያዙ ናቸው ። መርከብ እየቀዘፉ ቅጣታቸውን እንዲቀበሉ ወደዚያው በመወሰድ ላይ ናቸው " አለ ሳንቾ ።

" ጉዳዩ ይህ ከሆን ፣ የኔን እርዳታ ማግኘት አለባቸው ። ምክንያቱም ኃይልንና ጭቆናን ለመግታት ቃል ኪዳን ገብቻለሁና " አለ ዶን ኪኾቴ ።

" ግን እኮ ! እነዚህ ርጉሞችና ተንኮለኞች የተጨቆኑ አይደሉም ። ለፈጸሙት ድርጊት ዋጋቸውን እያገኙ ነው እንጂ » ሳንቾ መለሰ ።

ዶን ኪኾቴ በሳንቾ አባባል አልረካም ነበርና ፣ " ለማንኛውም ሥቃይ ውስጥ ናቸው " ሲል መለሰ ።

ወዲያው በሰንሰለት የተቆራኙት እስረኞች ወደ ዶን ኪኾቴ ተጠጉ ። ዶን ኪኾቴም ከሁለት ፈረሰኛ መኮንኖች አንዱን ፣ " ይቅርታዎን ጌታዬ ፣ እኚህ ሰዎች በምን ምክንያት ነው በዚህ ዐይነት ሁኔታ ታጅበው የሚነዱት ? » ሲል ጠበቅ አድርጎ ጠየቀው ።

" ወንጀለኞች ናቸው ። " አንዱ መኮንን መለሰ ። " የንጉሡን መርከብ እንዲቀዝፉ የተበየነባቸው ናቸው ። ሌላ የምገልጽልዎ ነገር የለኝም " ሲል ጨምሮ ተናገረ ።

“ እያንዳንዱ ምን ፀይነት ጥፋት እንደ ፈጸመ ለማወቅ እፈልጋለሁ » አለ ዶን ኪኾቴ ።

“ ከእርስዎ ጋር የምንጋገርበት ምክንያት የለኝም ። ነገር ግን ከዚህ ጉብታ ጫፍ ላይ ዕረፍት በሚያደርጉበት ጊዜ ራሳቸውን መሊቲዎቹን መጠየቅ ይችላሉ ። ታማኞችና እውነተኞች ከመሆናቸው የተነሣ ያደረጉትን ለመግለጽ በጭራሽ የሚያፍሩ አይደሉም ። ”

ዶን ኪኾቴ በጣም ደስ አለው ። በሰንሰለት ወደ ታሰሩት ሰዎች ተጠግቶ ጥያቄውን ያጐርፍ ጀመር ።

“ ኧረ በምን ሰበብ ነው መርከብ እንድትቀዝፍ የተበየነብህ ! ንገረኝ የኔ ወንድም ? » በማለት አንዱን ጠየቀው ።

“ አ ! በፍቅር ስለ ተጠመድኩ ብቻ ነው ። ” እንደ ዋዛ መለሰለት ።

“ እውነትክን ነው ! ? በፍቅር የሚጠመዱ ሁሉ የንጉሡን መርከብ እንዲቀዝፉ የሚፈረድባቸው ከሆነ ፤ ምን ሊውጠን ሁላችንንም ? ” ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ ዶን ኪኾቴ ።

“ እውነትዎን ነው ! ” እስረኛው ጮክ ብሎ ተናገረ …… “ ሆኖም የኔ ፍቅር ተራ ፀይነቱ አይደለም ። አንድ ቅርጫት ሙሉ ልብስ አፈቀርኩና በክንዴ አንጠልጥዬ ወደ ቤቴ በመውሰዴ ሰርቀሃል ‘ ተብዬ ስለ ተከሰስኩ ፤ እነሆ እዚህ እገኛለሁ ። ”

ዶን ኪኾቴ ፤ ፊቱን ወደ ሌላው ሰው አዞረና ፤ “ አንተስ ታማኙ ወዳጄ ምን አጥፍተህ ነው ፤ በዚህ አሳዛኝ ነገር ውስጥ የገባኸው ? ” ሲል ጠየቀ ።

“ እንዲህ ነው ፡፡ በእምነት የመሰድኩትን ዕዳ ለመ ክፈል ሁለት ወቄት ወርቅ ማግኘት አቅቶኝ ፡፡ ”

“ ይኸ ከሆነማ በርግጥ ስሕተት ነው ፡፡ እኔ አራት ወቄት ወርቅ እሰጥሀና በነጻ እንድትለቀቅ አደርጋለሁ ” አለ ዶን ኪኾቴ ፡፡

“ ጌታዬ አመሰግንዎታለሁ ፡፡ የርስዎ እርዳታ ግን ፣ በባሕር ላይ ላለ አንድ ረሃብተኛ ሰው እህሉ ሳይኖር መጣጥ እንደ መስጠት ዐይነት ነው ፡፡ ፍርዱ ከመወሰኑ በፊት ወቄት ወርቅ ኖሮኝ ቢሆን ኖሮ እዚህ ቦታ ባል ተገኘሁ ነበር ” አለ እስረኛው በምጸታዊ አነጋገር ፡፡

እንዲህ እንዲህ እያለ ዶን ኪኾቴ ፣ ከአንዱ እስረኛ ወደ ሌላው እየሔደ ታሪካቸውን እንዲነግሩት ሲጠያይቅ ቆየ ፡፡

በሰንሰለት ከታሰሩት ሰዎች መኻል የመጨረሻው ፣ ሰውነቱ የተደላደለ የሠላሳ ዓመት ጐልማሳ ነበር – አንድ ፀይኑ ጠንጋራ የሆነና ከሌሎቹ ሁሉ የከፋ አተያይ ያለው ፡፡

ለዶን ኪኾቴም ይህ ሰው በሰንሰለቱ ከብደት ከፉኛ የተጐዳ መስሎ ታየው ፡፡ አንገቱ በሁለት ዙር ሰንሰለት ታብቷል ፤ እንዲሁም እጆቹ ተጠፍረው ቁልቁል ከብረት ስለ ተያያዙ ፣ እጆቹን አፉ ማድረስ አይቻለውም ነበር ፡፡

ጠረኛው ዶን ኪኾቴም ወደ አንዱ እግረኛ ዘበኛ ፊቱን መለሰና ፣ “ ይህ ሰው በምን ምክንያት ነው በብ ረታ ብረት እንዲመቃይ የተደረገው ? ” ሲል ጠየቀ ፡፡

“ ምክንያቱም እሱ ከሁሉም የባሰ እርጉም በመ ሆኑ ነው ፡፡ በዚህም ላይ ፣ ከድፍረቱና ከብልጠቱ የተነሣ ፣ ምንም ዐይነት ወህኒ ቤትና ሰንሰለት ሊያግደው አልቻ

ለም ። በስንት ብረት እንደ ተጨፈረ ማየት ይችላሉ ፤ እንዲያም ሆኖ በእጃችን እንዳለ አድርገን አንቈጥረውም ” የሚል መልስ አገኘ ።

“ ግን ምን አድርጎ ነው ? ” ዶን ኪኾቴ ጠየቀ ።

“ ምን አድርጎ ነው ነው የሚሉት ! ? ምን ያላደረገው ነገር አለ ? እሱኮ ሴባና ዘራፊ ገርን ዲ ፓሳሞንቴ ነው ። ”

ከዚያም እስረኛው ራሱ ፈጠን ብሎ ፥ “ጌታዬ የሚ ሰጡን ነገር እንዳለ ቶሎ ይስጡንና በፈረስዎ ሆነው ጉዞ ዎን ይቀጥሉ ። ለጥያቄዎችም ምንም መልስ የለኝም ” አለ ።

ዶን ኪኾቴም ፥ “ ወዳጄ ሆይ ! አንተ ከባድ ሰው ትመስላለህና ፥ ታሪክህን ለማወቅ እፈልጋለሁ ” አለ ።

“ ሁሉም ነገር ተጽፎ ያገኙታልና ፥ ያንን ገዝተው ያንብቡት ” አለ ገርን ።

“ እውነቱን ነው የሚነግርዎት ፤ የሕይወት ታሪኩን በሙሉ በመጽሐፍ ጽፎታል ” አለው የእስረኞቹ ጠባቂ ።

“ የመጽሐፉ ርዕስ ምን ይባላል ? ለማንበብ እፈል ጋለሁ ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

...... ‘ የገርን ዴ ፖሳሞንቴ የሕይወት ታሪክ ’ ይባላል ። የመጽሐፉ ታሪክ በሙሉ እውነትን የተላበሰ ሆኖ ፥ በብልጫ ብልጥ ታሪኩና በገድሉ የሚወዳደረው የተረት መጽሐፍ አይገኝም ” በማለት እስረኛው መለሰ ።

ዶን ኪኾቴም ፥ “ እውነትም ልዩ ሰው ነህ ” በማ ለት አደነቀው ።

በዚህን ጊዜ ጠባቂዎቹ ትእዛዝ ሰጡ ፤ በሰንሰለት ተጠላልፈው የታሰሩት እስረኞች በዝግታ ወደ ኮረብ

ታው ጫፍ ማዘገም ቀጠሉ ። ዶን ኪኾቴ አሁንም የእስረኞቹን ታሪክ ሰምቶ አልረካም ። ረዥም ንግግር እያደረገ እስረኞቹን በመጀመሪያ ፤ ቀጥሎ ጠባቂዎቹን ይለቀል ጀመር ። በመጨረሻም ፤ ርካቡ ላይ ቀጥ ብሎ ቆመና በጩኸት ድምፅ ፤

« ክቡራት ዘበኞች ሆይ ! እኔ የታወቅሁት ጀግና ዶን ኪኾቴ ዴ ላ ማንቻ እባላለሁ ። እነዚህን ምስኪን ሰዎች ፈትታችሁ እንድትለቋቸው አዝዛለሁ ። እሻፈረን ብትሉ ግን ይህ ጦር ፤ ይህ ጎራዴና ይህ የማይበገረው ጥሩር ትእዛዜን እንድትቀበሉ ያስገድዳችኋል ። »

የጠባቂዎቹ አለቃም ፤ “ ይህችስ ጥሩ ጨዋታ ናት ። ይልቅስ አሁን የእጅ ማስታጠቢያ ሣህንህን ባዶ ጭንቅላትህ ላይ ደፍተህ ፤ ወደ ጉዳይህ ብትሔድ ይሻላል ። በእኛ ሥራ ገብተህ አትፈትፍት ። ‘ አይጥ ሞቷን ስትሻ ፤ ስታበዛ ፉጫ ፤ ሔዳ ታሸታለች የድመት አፍንጫ ’ እንዳይሆን ነገሩ ” አለ ኰስተር ብሎ ።

ይህ አነጋገር ዶን ኪኾቴ በጣም አናደደውና ፤ “ ድመቱም አይጡም አንተ ነህ ። ፈሪ ቡከኑም አንተ ነህ ! ” አለና ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ ፤ የዘበኞቹ አለቃ ራሱን ሊመከላከል ጊዜ አግኝቶ ሳይዘጋጅ ፤ ድንገት ዶን ኪኾቴ ከነፈረሱ አጠገቡ ከተፍ አላለበት ፤ በጭንቅላቱ ጭቃ ውስጥ ተተከለ ። ሌሎቹ ዘበኞች ለርዳታ ወደ አለቃቸው ሮጠው ፤ ዶን ኪኾቴ ፤ በጎራዴና በቆመጥ ሲረባረቡበት ፤ እሱም ሮሲናንቴን ከወዲያ ወዲህ በልጓም እያዘዋወረ ፤ ጦሩን አሹሎ ከንዱን መክቶ ይከላከል ገባ ። በግርግር እስረኞቹ ሁካታ ፈጥረው ሰንሰለታቸውን መበጣጠስ ባይጀምሩ ኖሮ ፤ ዶን ኪኾቴ ክፉኛ ጉዳት ይደረስበት ነበር ።

ይህን ሁሉ ትርምስ ሳንቾ ፓንሳ ከተመለከተ በኋላ ፣ ከአህያው ላይ ዱብ ብሎ ለጌታው ርዳታ ለመስጠት ወደ ዠርን ዶ ፓሳሞንቴ ተንደርድሮ የታሰረበትን ሰንሰለት ይፈታለት ጀመር ። እንደ አጀማመሩ ቢሆን ፣ የሚቀጥ ለው ግጭት የባሰ የሚያስፈራ ነበር ። እስረኞቹ ከዶን ኪኾቴ ዋጋ ቢስ ጦር የላቀ ራሳቸውን የመከላከል በቂ ችሎታ ነበራቸው ። ከሁካታው የተነሣ ሁሉም የሚያ ደርጉትን ማወቅ ተሳናቸው ።

እስረኞቹ ከታሠሩበት ሰንሰለት ራሳቸውን ነጻ አው ጥተው አካባቢውን በቁጥጥራቸው ሥር አደረጉና ጠባ ቂዎቻቸውንም ከበቡ ። ጠባቂዎቹም ከእስረኞቹ ከሚ ወርድባቸው የድንጋይ ውርጅብኝ ለማምለጥ ፣ እግሬ አውጭኝ ብለው አውራ ጐዳና ገብተው ፈረጠጡ ። እሬ ታቸው ከሚገኘው መንደርተኛ ርዳታ እንኳ እንዳያገኙ ፣ አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ስለሚርቅ የነፍስ ነፍሳቸውን ተፈተለኩ ።

ሳንቾ ፓንሳ አህያው ላይ ወጣና ፣ ወደ ጌታው ጠጋ ብሎ ፣ “ ይስሙኝ ጌታዬ ! የንጉሡ መኳንንቶች አሁኑ ያሳድዱናልና ፣ ፈጥነን ጫካ ውስጥ ገብተን ብንሸሸግ ይበጃል ” አለ ።

“ ዝም በል ! ምን ማድረግ እንዳለብኝ ጠንቅቄ ዐው ቃለሁ ” አለ ዶን ኪኾቴ በቍጣ ! ከዚያም እስረኞቹን በዙሪያው ሰበሰበና አጠር ያለ ንግግር ማድረግ ጀመረ ።

“ ክቡራን ሆይ ! ምን ዐይነት ርዳታ እንዳበረከትሁ ሁላችሁ ከእናንተ የተሰወረ አይደለም ። ለዚህም ወሮታ እንድትከፍሉኝ አልሻም ። ነገር ግን ፣ እያንዳንድህ በቀጥታ ‘ ቶቦሶ ’ ወደ ተባለው ከተማ ትጉዘህ ፣ የዶን ጆዎች ቆንጆ በሆነችው ወደር የለሽ እመቤት ዱልሲኒያ

ዘንድ እንድትገኙ እፈልጋለሁ ። ይህንን ታላቅ የጀብዱ ሥራ ውጤት በትክክል ግለጹላትና ለወደፊት ምን እንደምትፈልጉ ከርሷ ፈቃድ ካገኛችሁ በኋላ ፣ ዕድላችሁ ወደመራችሁ ቦታ ትሔዳላችሁ ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

እስረኞቹም በንቀት መልክ ፈገግ ካሉ በኋላ ፣ ዢን ዶ ፓሳሞንቴ ምላሹን ንግግር አደረገ ።

“ እጅግ የተከበራችሁትና ከችግር ያዳናችሁን ጌቶች ሆይ ! እንድንፈጽም የተጠየቅነው ጉዳይ የማይሞከር ነው ። አሁኑኑ ከዚህ ሥፍራ ፈጥነን መሔድ አለብን ። አንዳንዶቻችን በአንዱ መንገድ ፣ ሌሎቻችን በሌላ መንገድ ማምለጥ አለብን ። በየጥሻው ፣ በየቋጥኙና በየጉድባው መሸሸግ ይኖርብናል ። እኛን የሚያሳድዱ ሰዎች ዱካችንን አሁኑኑ ተከትለው እንዳይዙን መታየት የለብንም ። እመቤት ዱልሲኒያ የተባለችውን ቶቦሶ ድረስ ሔዶ መጎብኘቱ ግን ፋይዳ የሌለው ሥራ ነው ” አለና ንግግሩን ባቃ አደረገ ።

ይህ አባባል የዶን ኪኾቴን መንፈስ አስቆጣ ። “ ስማኝ ጌታ ሆይ ! ጊርን ወይም ማንትስ የምትባለው አንተ በፍርሃት ጭራውን የሸጎጠ ውሻ መስለህ አንተው ራስህ ወደ ቶቦሶ ትሔዳለህ ። መላው አካላትህ በሰንሰለት ተጠፍሮ ፣ አንተው ራስህ ነህ ወደ ቶቦሶ ሔደህ በትእዛዙ መሠረት መልዕክቱን ለዱልሲኒያ የምታደርሰው ” ይለው ጀመር ።

ጊርን በዶን ኪኾቴ የድፍረት ዛቻ ፈገግ ከማለት በስተቀር ምንም መልስ አልሰጠም ። ነገር ግን ፣ ባልደረቦቹ በደቦ ሆነው ድንገት ጦረኛዉ ላይ ተረባረቡበትና ከፈረሱ ላይ ጎትተው እመሬት ላይ ዘረሩት ።

ጥሩሩን እና ፣ ከእግር እስከ ወገቡ እንዲ ሱሪ አጥ ልቆት የነበረውን ጥቁር ሹራብም ገፍፈው ወሰዱበት ። ራሱ ላይ ደፍቶት የነበረውን ሣህን አንዱ አንሥቶ ከቋ ጥኝ ጋር ቢያላትመው ፣ በአሳፋሪ ሁኔታ ጭርምትምቱ ወጣ ። ሌላዉ ያንን ረዥም ጦሩን ለሁለት አንክቶና ጥቅ ጥቅ ወዳለው እሾማማ ቁጥቋጦ ወረወረው ።

ከዚህ ሁሉ አደጋ ሳንቾን ጥቂት ሳይተርፈው አል ቀረም ። ኮቱን ብቻ ገፍፈው ስደሪያውን ትተውለታል ። አርጌና እማይረባ ሆነባቸው እንጂ ሜማውንም ሊያወል ቁበት ዳድቷቸው ነበር ።

ወሮበሎቹ በእንዲህ ዐይነት ዘረፋ ለጥቂት ደቂቃ ዎች ራሳቸውን ከአስደሰቱ በኋላ ፣ መንገዳቸውን ቀጠሉ ። እያንዳንዳቸው የተለያየ አቅጣጫ ይዘው ተበታተኑ ። ከሕግ አስከባሪ መኮንኖች እጅ በማምለጣቸው እጅግ ተደሰቱ እንጂ ፣ የቶብሶዋን እመቤት ዱልሲኒያን የመገ ናኘቱን ጉዳይ ከቁም ነገርም አላስገቡት ።

ስለሆነም ፣ በመጨረሻው ግራሚዋ አህያ ፣ ሳንቾ ፓንሳና ዶን ኪኾቴ ብቻ የአውላላው ሜዳ ጌቶች ሆነው ዐረፉት ። ያውም በኃፍረት ቅስማቸው የተሰበረ ጌቶች !

“ ወዳጄ ሳንቾ ” አለ ዶን ኪኾቴ ከወደቀበት ጭቃ ላይ እየተነሣ ። “ አንድ ምሳሌያዊ አባባል ላስታውስህ እፈልጋለሁ ። ይኸውም ፣ ‘ እጸድቅ ብዬ ባዝላች ተንጠ ልጥላ ቀረች ’ የሚለውን ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

የተሰባበረውን ጦር ፍለጋ ሔዶ ግማሹን ቁጥቋጦ ውስጥ አገኘና ፣ ወዲያው ተመልሶ ሮሲናንቴ ላይ ጉብ አለ ። ቀኑ እየመሸ ቢሔድም ዶን ኪኾቴ በሐሳብ ተውጦ ፣ በጸጥታ መንፈሱ ወደ ጥቁር ተራራዉ አምብርት ገሠገሠ ። ሳንቾ ፓንሳም ግራሜ አህያው ላይ ተቀምጦ ጌታውን ይከተል ጀመር ።

በጥቁር ተራሮች

የሴሲቱ ጨለማ ሁለቱን ተጓዦቻችንን ምቹ ሆቴል ከማይገኝበትና ራቅ ካለው ተራራ መኻል አስቀራቸው ። ቢሆንም ፡ ሰማዩ የጠራ ነበርና ከዛፎች አናት ላይ ጨረቃዋ ሙሉ ሆና ብርሃንዋን በመለገስ ላይ ነች ። ጠረኛውና ጋባ ጀግሬው ፥ በረዥሙ ጉዞ ከመድከማቸውም በላይ ፡ በእነዚያ ውለታቢስ ሴቦች የተደበደበው ሰውነታቸው ቆስሏል ፤ ዝሏልም ።

በመጨረሻም ሳንቾ ፡ "እነሆ ደርሰናል" አለና በመሙሁ ፡ አፀያፊውን እየመራ ወደ አንድ ግዙፍ ዳጥኝ ተጠጋ ። "ጌታዬ ይኸውልዎ ፤ በመጨረሻ እዚፀ ደረስን ። ይህ ግፋም መጠለያ ነው ። እስከሚነጋ ድረስ እዚህ ዐረፍ እንበል" አለ ሳንቾ ።

"በእውነት እዚህ ለማረፍ ፈቃደኛ ነኝ" አለ ዶን ኪኾቴ ። ሁለቱም በጣም ተዳክመው ነበርና ፡ ከእንሰሶቻቸው ለመውረድ እንኳ ተሳናቸው ። ሁለቱም በየኮርቻቸው ላይ ፥ በጸጥታ እንደ ተቀመጡ በሐሳብ ባሕር ይዋኙ ጀመር ፤ እና .... ወዲያው ከባድ እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ወሰዳቸው ።

ዶን ኪኾቴ ፡ ወርበሎቹ ሰባብረው ጥለውት በነበረው ሰማያ ጉማጅ ኮርቻው ላይ ቁደግፎ ሲቀመጥ ፡ ሳንቾ ግን ፡ አህያው ኮርቻ ቀዳማይ ላይ ተደፍቶ ልክ ምቹ አልጋ ላይ እንደ ተኛ ያህል ሰላማዊ እንቅልፉን እየለጠጠ ግን

ኳረፉን ቀጠለ ። ሮሲናንቴና ተንኘር ግራጫትም ከጌቶ ቻቸው ያላነሰ ድካም ስለ ተሰማቸው ተግትረው ቆመው ነበርና ፣ ለፀመል ያህል ነካ ቢያደርጓቸው እንኳ ይወድቁ ነበር ።

እንደ አጋጣሚ ሆኖ እኩል ሌሊት ገደማ ፣ ሌባው ዢን ዶ ቻሳሞንቄ ጥሻ ለጥሻ እያለ ለማምለጥ ደኅና መንገድ ሲፈልግ ፣ እነ ዶን ኪኾቴ አሉበት ሥፍራ ደረሰ ። በትልቁ ቋጥኝ በኩል ሲያልፍ ፣ ሁለቱ እንስሳትና ጌቶቻቸው በጥላው ሥር ጸጥ ብለው ዕረፍት ላይ እንዳሉ ተመለከተ ። ከእንቅልፋቸው እንዳይቀሰቅሳቸው በዝግታ ወደ እነርሱ እየዳኸ ተጠጋ ።

'እኛ!' ብሎ ለራሱ ካጉመተመተ በኋላ ፣ 'እንቅልፍ ድብን አድርጎ ወስዷቸዋል ! እኒህ ሁለት ጅሎች ያላንዳች ሥጋት ማንንም ሳይፈሩ ፣ ሕዝብ በሚመላለስበት ጐዳና በሰላም ይጓዛሉ ። እኔ ግን ፣ በዚህ ምሽትና በጭር በገደሉ ፣ በዲሾሁ በቁንጥቁ ውስጥ ከመሔድ የተነሣ ፣ እነሆ ልምት ደርሻለሁ ። ከእነዚህ ከሁለት ፈረሶች አንዱ እንዲኖረኝ ያስፈልጋል ' አለ ወሮበላዉ ለራሱ ።

ሮሲናንቴን እየተዘዋወረ ጉድኖቹን ለስለስ አድርጎ ከዳበሰና ራሱንም መታ መታ ካደረገ በኋላ ፣ 'ይህስ አጥንቱ የወጣ ፈረስ ነው ። መቼ ወድቆ እንደሚሰባበር መትንበይ ያስቸግራል ፤ ለማንኛውም የራሴ ሳደርገውና ፣ ትንሽ ትንሽ ልንዝበበት ብችልም ፣ በመጨረሻ ግን የማልሸጠው ወይ ለሰው የማልሰጠው እንደሆን ግልጽ ነው ' አለ ወሮበላዉ ። ወደ ግራጫው የሳንቾ አህያ ተጠግቶ ፣ ከአፍንጫው እስከ ጅራቱ ድረስ መረመረው ።

'ይህ እንስሳ እንደሚችለኝ እርግጠኛ ነኝ ። በመጨረሻም በአንድ ወይ በሁለት ብር ልሸጠው እችላለሁ ፤ ነገር ግን እንዴት አድርጌ ልውሰደው ?'

ቋጥኙን ደገፍ ብሎ በጉዳዩ አጥብቆ ሲያስብ ፤ የሳ
ንቾ ፓንሳ ማንኮራፋት በጫካው ውስጥ ያስተጋባ ነበር ።

‘ ከአህያው ላይ ገፍቶ ጥሎ እንስሳውን በጉልበት
መውሰድ ይቀላል ’ እያለ ገርን ፤ አሁንም ለብቻው ማጉ
ተምተሙን ቀጠለ ። ‘ማን ይህ ሰው ዛሬ ውሰታ ውሎል
ኛልና ከእንቅልፉ ልቀሰቅሰው አልሻም ’ አለ በኀዘኔታ ።

ወዲያው ከኪሱ ውስጥ ጩቤውን ላጥ አድርጎ
አወጣና ፤ በሴባ አካሔድ እየተራመደ ከመንገዱ ዳር ወደ
ሚገኘው ቁጥቋጦ ውስጥ ገባ ። ከቁጥቋጦ ውስጥም ልክ
እንደ ክንዱ ጠንካራ ፤ እንደ ሰውነቱ ግዙፍ የሆኑ አራት
ረዣዥም አጣናዎች ቆራረጠ ።

የቆራረጠውን ይዞ ወደ አህያው ተመለሰና በዝ
ግታ ኮርቻውን ፈታ ። ሳንቾ ፓንሳ እግሮቹን አርካብ
ውስጥ አስገብቶ አጭር ሰውነቱን አህያው ጋማ ላይ ደፍቶ
እንቅልፉን ይለጥጣል ። በከባድ እንቅልፍ ተውጦና በማ
ንኮራፋት ላይም ስለሚገኝ ሌላ ምንም ድምፅ ሊሰማ
አይችልም ነበር ።

ብልጡ ገርን ፤ ራሱ በሚሠራው ብልሃት ተደንቆ
ፈገግ አለ ። አራቱንም የባላ ዕንጨቶች ከኮርቻው ሥር
እንደ አልጋ እግር አድርጎ ከመሬት ላይ ደጎና አድርጎ
አቆማቸው ። በጥንቃቄና በዝግታ ዕንጨቶቹን እየገፋ
በአህያው እግሮች አኳያ ተከላቸው ። ይህ አድራጎቱ ኮርቻ
ውን ጥቂት ከአህያው ጀርባ ላይ ከፍ አደረገው ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ሳንቾ መድፍ እንኳ ቢተኮስ አይ
ሰማም ነበር ።

ገርን እያንዳንዱ ባላ ቀጥ ብሎ እንደ ቆመና እንደ
ምሰሶ መጠንከሩንም ከአረጋገጠ በኋላ ፤ ከኮርቻው ሥር

ጉትቶ ሲያወጣ ፡ ኮርቻው ሳንቾን እንደ ተሸከመ በባላ ዎቹ ተወጥሮ አየር ላይ ተንጠልጥሎ ቀረ ።

ወለል ባለ የጨረቃ ብርሃን ድርጊቱን ለተመለከቱ አጅግ የማያስደንቅ ነበርና ፡ ዝርን ዶን ፓሳሞንቴ ራሱ በገዛ ሥራው በጣቅ ፍርስ አለ ። ይህ ሁሉ ሲሆን ሳንቾ ፓንሳ እንቅልፍ ዓለም ገብቶእያንኮራፋ ንቅንቅ አይልም ነበር ። ዝርን ዶን ፓሳሞንቴ መለስ ብሎ የሳንቾ ፓንሳን በባላ ባልቾ መንጠልጠል ተመለከተና ፡ አሁንም በጣቅ ፍርስ አለ ። ከዚያም አህያው ጀርባ ላይ ዘሎ ወጣና በሴ ጣው ላይ ተቀምጦ በደስታ ጉዞውን ቀጠለ ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ፡ ሳንቾ ፓንሳ ከተኛበት ሥፍራ አን ዱት ስንዝር እንኳ ሳይንቀሳቀስ ኩርፊያውን ቀጠለ ። ሌሊቱ በጸጥታ ዐለፈ ። ጨረቃና ከዋክብትም ፀዝግታ ጉዞአቸውን ወደ ምዕራብ ሰማይ አመሩ ፤ በመጨረሻም ጐህ ቀደደ ። የፀሐይ ውጋጋንም በየዛፉ ውስጥ ጭልጭል ይል ጀመር ።

አብዛኛውን ጊዜ ሳንቾ ማልዶ ነበርና የሚነሣው ሲነጋጋ ሲል ኩርፊያውን አቆመ ። ዐይኖቹን ከፍቶ ፡ አጆቹን ዘርግቶ አዛጋ ። የሰውነቱ እንቅስቃሴ ባላዎቹን ስለ ነቀነቃቸው እጥፍጥፍ እያሉ ሲወድቁ ፡ ኮርቻውም ከሥሩ ከዳውና ሳንቾ አመሬት ወርዶ ተዘረፈጠ ።

ሳንቾ ሲወድቅ የተፈጠረው ድንገተኛ ድምፅ ዶን ኪ ኾቴን ከእንቅልፍ ቀሰቀሰውና ፡ “ አህያው የት አለ ወዳጄ ሳንቾ ? ” በማለት ዙሪያ ገባውን በመቃኘት ጠየ ቀው ።

“ ‘ አህያው ወዴት ነው ? ’ ብሎ መጠየቅ አይከ ፋም ። አህያዬ ጠፍቷል ። አንድ ሌባ ሌሊት ይዞብኝ

ነጉዷል ። ለእኔ ግን ከአራት አጠናዎችና ከጸጉር አስተ
ካካዩ በለውጥ ወስጄበት ከነበረው ኮርቻ በስተቀር ምንም
ነገር አልተወለኝም ” አለ ሳንቾ ።

« የምን ሌባ ? ” አለና ዶን ኪኾቴ ፡ “ ሌላ አይደ
ለም ፤ ይህንን ያደረጉት እነዚያው ተንኮለኞች አስማተ
ኞቹ ናቸው ፤ ምስኪኑን እንስሳ ወደ አራት አጠና ዕን
ጨት ለውጠውታል ። እና ፡ አሁን እኛ አጠናዎቹን ከእ
ነርሱ አስማት አላቀን መልሰን ወደ አህያ እስክንለው
ጣቸው ድረስ እንደ ፈረደብህ በእግርህ መጓዝ ሊኖር
ብህ ነው ” አለው ።

ሳንቾ ፓንሳ ተጨነቀ ፡ ተጠበበ ። እንዴ ወደ ኮር
ቻው እንዴ ወደ እንጨቶቹ ፡ ከዚያም አህያው የተጓ
ዘበትን አቧራማ መንገድ በኀዘን ተመለከተ ። ዐይኖቹ
እንባ አቀረሩ ፤ በከፍተኛ የሐዘን ድምጽ መሪር ልቅሶ
ውን አሰማ ።

“ ወይኔ ግራጫዬ ! ወይኔ አህያዬ ! የምወድህ አህ
ያዬ በራሴው ቤት ተወልደህ ያደግህ ! የልጆቼ አጫዋች ፡
የባለቤቴ አጽናኝ ፡ የጐረቤቶቼ መቅኛ ፡ የሸክሜ አቃላይ ፡
የሕይወቴ አለኝታ አንተ ነበርክ !!! ግራጫዬ ተወሰድ
ክብኝ ፤ ግራጫዬ የኔ አህያ ! ካላንተ እንዴት አድርጌ እኖ
ራለሁ ? ” እያለ ሳንቾ ሙሾውን ያወርድ ጀመር ።

የዶን ኪኾቴ ርኅሩኅ ልብ ተነካ ። “ ውድ ወዳጄ
ሳንቾ ! እንባህን ጥረግ ፤ ግድ የለም አታስብ ፤ እቤቴ አም
ስት አህዮች ስላሉኝ ሦስቱን እንድትሰጥህ ለእኅቴ ልጅ
ትእዛዝ አስተላልፋለሁ ። መጀመሪያ በምናገኘው ብዕ
ርና ቀለም ደብዳቤ እጽፍላታለሁ ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

ይህ ደግነት ከልብ የተመላበት ገጸ በረከት ፡ የሳ
ንቾን መሪር ሐዘን ከመቅጽበት ወደ ደስታ ለወጠው ፤

እንባውን አደረቀለት ። ዋይታውን ጸጥ አደረገለት ። ሐዘኑ ወደ ፍሥሓ ተለውጦ ምስጋናውን ለዶን ኪኾቴ ያጕርፍለት ጀመር ።

“ እርስዎ ምን ጊዜም ቢሆን መልካም ጌታ ነዎት ። እና አሁን ፤ ብዙ ጥሩር-ለባሽ ፈረሰኛ ከሚያጋጥመን ይልቅ ብዕርና ቀለም ብናገኝ እመርጣለሁ » አለ በፈገግታ ።

ጦረኛዉና ጋሻ ጃግሬዉ ከመሬት ላይ ተቀምጠው ጥቂት ደረቅ ዳቦ ለወጉ ያህል ፤ ቁርስ አደረግን ለማለት ያህል አፋቸውን አሟሹ ። ሮሲናንቴ በየመንገዱ ዳር ያገ ኘውን ጨሌ ሣር ከጋጠ በኋላ ፤ የተረፈውን መኻከለኛ ሥፍራ እያቆራረጡ ጉዞአቸውን ተያያዙት ። ዶን ኪኾቴ ከፊት ፤ ሳንቾ ፓንሳ የአህያውን ኮርቻ በጫንቃው ላይ ተሸክሞ ከኋላ ሆኖ በዝግታ እየተከተለው ይጓዙ ጀመር ።

ለዱልሲኒያ የተላከ መልእክት

አንድ ቀን ዶን ኪኾቴ ጋሻ ጃግሬውን አስከትሎ ፤ ያለ አንዳች ዓላማ በአባጣ ጐርባጣማ ተራራ ሲጓዙ ፤ በድ ንገት ጨዋታውን አቁሞ ጸጥ አለ ።

“ ወዳጄ ሳንቾ ፤ ለሕይወትህ እንደምትሳሳላት ሁሉ እባክህን እኔ እስካልፈቀድኩልህ ድረስ አንድም ቃል እንዳትተነፍስልኝ እጠይቃለሁ ” አለ ዶን ኪኾቴ ከረ ጅም ጸጥታ በኋላ ።

አእምሮው በሙሉ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ተወጥሯል ። ምክንያቶቹን በቀጡ በማይገልጻቸው ምኞቶች መንፈሱ ይዋዠቃል ። አዲስና ከበድ ያሉ ሐሳቦች ውስጥ ገብቶ በማውጣት በማውረድ ላይ እንዳለ ሆኖ ይታያል ። በዚህ

ፀደንት ቀኑን ሙሉ ሳይነጋገሩ በዝግታ ርምጃ ይከምከሙ ቆለው ሲገዙ ዋሉ ።

በመጨረሻም ፣ ሳንቾ ፓንሳ ደከመ ። ጨለማታና ቀልድ ከመጠን በላይ ፈለገ ። አሁንም የአህያውን ኮርቻ በጉ ከሻው ላይ እንዳደረገ ፣ የሮሲናንቴን ዱካ እየተከተለ ሐሳቡን ከራሱ ጋር ያመላልስ ጀመር ። በመጨረሻው ግን ፣ ሐሳቡ ስላስጨነቀው ሊታገሥ አልቻለም ። እግሩን ነጠቀ አድርጎ ከጌታው ጉን እስኪደርስ ርምጃውን አፋጠነ ። እጆቹን በዶን ኪኾቴ ጉልበት ላይ ጣል አድርጎና ንግ ግሩን ጀመረ ።

“ ደጉ ጌታ ሆይ ! ይመርቁኝና ወደ ባለቤቴና ወደ ልጆቼ ዘንድ ልመለስ ። በቤቴ ውስጥ እስኪደክመኝ ብለ ፈልፍ ከልክይ የለብኝም ። እውነቱ ነው የምነግርዎት ፣ ሌት ተቀን አፈን ዘግቼ ተራራ መውጣትን ፣ ቁልቁለት መውረዱን ልክ ራሴን እንደ መግደል እቈጥረዋለሁ ። እንገሽግሾኛልና ለዘለቄው አልችልም ” አለ ሳንቾ በምሬት እንጋገር ።

“ ወዳጄ ሳንቾ ! ምን እንደምትል ይገባኛል ። ምላ ስህን ነጻ ልቀቀውና በዚህ ተራራ ውስጥ አብረን በምንን ዝበት ጊዜ ሁሉ እንደ ፈለግህ እንድትናገር ፈቅጀልሃለሁ ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“ እንግዲያውስ ‘ ፀሐይ ሳለ እሩጥ አባት ሳለ አጊጥ ’ እንደሚባለው ፣ መናገር ከቻልኩኝ አሁኑኑ ልናገር ! በኋላ ምን እንደሚደርስብኝ ማንም ሊተነብይ አይችል ምና ፡ እንዳንዱ ሰው ለራሱ ፣ እግዚአብሔር ግን ለሁላ ችን ነው እላለሁ ። ጥቂት አባባል ቁም ነገር አለው ። የሰ ዎችን አፍ መቆለፍ አይቻልም ። ‘ ዝም ባለ አፍ ዝንብ አይገባበትም ’ ቢባልም ቅሉ ” አለ ሳንቾ ።

"እባክህን ተረትህን አቁምና ፣ ይልቅስ ለእኔ የወደፊት ጉዞዬ ፣ እንዲሁም ላንተ የሚበጅ ዕቅድ አውጥቻለሁና አድምጠኝ ፣ ውድ ሳንቾ" አሏ ዶን ኪኾቴ ።

ከዚያም ፣ ዶን ኪኾቴ ለእመቤት ዱልሲኒያ ደብዳቤ ያደርስ ዘንድ ጋሻ ጃግሬውን ቶቦሳ ሊልከው በዝርዝር ያስረዳዋል ።

"በሦስት ቀን ውስጥ ጉዞህን ብትጀምር ፈቃዴ ነው ። አካሔድህ በጣም ቀርፋፋ በመሆኑ ፣ ፈጥነቱም ሆነ ለምቾቱ ሮሲናንቴ ይጠቅምሃልና እሰጥሃለሁ ። "

" መልካም ነው ጌታዬ ። እኔ ከሔድኩ በኋላ እና ስዎ ብቻዎን ምን ይሠራሉ ? "

"ምን ትሠራለህ ? ምን እንደማደርግ ነው የምትጠይቀኝ ? የታወቀውን ጥሩር-ለባሽ ፈረሰኛ አርላንዶን ለመምሰል የሚያስችል ግሩም ጥንቅሳት አለኝ ። ማለትም ልክ እንደ እሱ ዕብድ እሆናለሁ ። ጥሩሬን አሽቀንጥሬ እጥላለሁ ፤ ልብሶቼን እቦጫጭቃለሁ ፤ ዛፎችን ከነሥራቸው እነቅላለሁ ፤ እነቅላለሁ ፤ ራሴን ከአለት ጋር አላትማለሁ ፤ ይህንና የመሳሰሉትን በሺህ የሚቈጠሩ አስገራሚ ድርጊቶችን እፈጽማለሁ ። እንዲያውም ሳንቾ ፣ ጥቂት ጊዜ ጠብቀኝና አንዳንዶቹን ድርጊቶች ስፈጽም ከተመለከትክ በኋላ ለዱልሲኒያ በዐይንህ በብሌኑ ያየኸውን ታስረዳታለህ ። "

" ጌታዬ ይህን ያህል መቸገር አያስፈልግዎትም ። ያሉኝን ሁሉ ልክ እንደ ተደረገ አስመስዬ እነግራታለሁ ። በሺህ የሚቈጠሩትን ዕብደታዊ ድርጊቶችን በዝርዝር ከገለጽኩላት በኋላ ፣ ጣፋጭ የሆኑትን የእመቤቴን ቃላት ይዤ እመለሳለሁ ። "

“ ዕብደታዊ ድርጊቶች ያልኳቸውን ፣ ግን ቁም ነገር አዘል የሆኑትን በዝግታ እፈጽማቸዋለሁ ፤ ምክንያቱም ጦረኛ መዋሸት ስለሌለበት ነው ። ለማንኛውም ፣ አሁን በፍጥነት ደብዳቤ እጽፍለሁና ማለዳ ፀሐይ ስትወጣ ይዘህ መሔድ አለብህ ። ”

“ እባክዎን ጌታዬ ! ” አለና ሳንቾ ፣ “እስጥሃለሁ ያሉኝን የምስቱን አህዮች ጉዳይ እንዳይዘነጉብኝ ! ከዚያ ጋር አብሮ ይጻፍልኝ ” ሲል ምጋቱን አሳየ ።

በአንድ ለምለም ቁጥቋጦ ውስጥ ዐረፍ አሉና ፣ ከብዙ ችግር በኋላ ደብዳቤዉ ተጻፈ ። አህዮቹም ለሳንቾ እንዲሰጡት ትእዛዝ አብሮ ተከተበ ። ደብዳቤዉ የተጻፈው ከዶን ኪኾቴ ኪስ በተገኘ ቁራጭ ማስታወሻ ወረቀት ሲሆን ቀለሙም የከሰል ስባሪ ነበር ።

“ ሳንቾ ፡ ደብዳቤዉ በወጉ ያልተጻፈ ነው ። ቢሆንም ፡ በጉዞህ ላይ መጀመሪያ ትደርስበት መንደር መምህር በደንብ ገልብጦ ይሰጥሃል ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

ሳንቾ የማስታወሻ ደብተሩን ተቀብሎ በጥንቃቄ ሰደርያ ኪሱ ውስጥ አስቀመጠና ፡ « አሁን ዐይኔን ጨፍኜ በችኮላ ለመሔድ ተዘጋጅቻለሁ ። ሮሲናንቴ ላይ ገብቼ እከንፋለሁ ። መልእክተኛ መዘግየት የለበትም ። ውድ ጌታዬ ሆይ ! ይመርቁኝና ጉዞዬን ልጀምር ። ገና እርስዎ ዕብደታዊ ምትሃትዎን እስኪያሳዩኝ ድረስ መዘግየት የለብኝም ! »

“ አትቸኩል ጥቂት ቆየት በልና ኻያ ወይም ሠላሳ ዐይነት የቡረቃ ድርጊቶችን ፤ ግንባሬን ከአለት ጋር ላላትምና የመሳሰሉትን ስፈጽም ማየት አለብህ ። በግማሽ ሰዓት ውስጥ ልፈጽመው እችላለሁ ። ”

“ ይህን ባይነግሩኝ ይሻላል ። እርስዎ የዕብድ፡ ሥራ ሲፈጽሙ ማየት እጅግ ልቤን የሚያሳዝነው ይሆናል ። ዐይኔ እስኪጠፋ ነው የማለቅሰው ፤ እንዲያውም ቀደም ሲል አህያዬ በመጥፋቱ ዐይኔ እስኪጠፋ ድረስ ነበር ያነባሁት ። ቢሆንም ፣ ጌታዬ ለእመቤት ዱልሲኒያ ሁሉንም ተአምራዊ ድርጊትዎን በዐይኔ እንዳየሁኝ አድርጌ እነግራቸዋለሁ ። ”

“ እንግዲያውስ ልመርቅህና ጉዞህን ቀጥል ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“ ግን እኮ ጌታዬ ! እኔ ከሔድኩ በኋላ ምግብዎን እንዴት አድርገው ሊመገቡ ነው ? በየአውራ ጐዳናው ከሚያጋጥምዎ መንገደኛ ሊዘርፉ ነው ወይስ የእረኞችን ምግብ ከያለበት ቦታ ሊሠርቁ ነው ? ”

“ ሳንቾ ስለ ምግቤ ጉዳይ አታስብ ! የዱር ቅጠልና ፍራፍሬ እመገባለሁ ። ሌላ ምንም አልሻ ። ደምፆኮ ጠረኛ ጥቂት መብላትና መራብ ተግባሩ ናቸው ። አይዞህ ስትመለስ ደኅና ሆኜ ታገኘኛለህ ። ”

“ ነገር ግን ፣ አሁን አንድ ሐሳብ መጣልኝ ። ይህን ጉራንጉር ቦታ ስመለስ እንዴት ላውቀው እችላለሁ ? እንዴትስ ይህን ጥቅጥቅ ያለ ዱር ላገኝ እችላለሁ ? ”

“ በመንገዱ ላይ ለምለም ቅጠሎች እየበተንክ ሒድ ሳንቾ ! ዋናው አውራ ጐዳና እስከትደርስ ድረስ ቅጠሎቹን እየበተንክ መጓዝ ነው ። ወዲህ ስትመለስ ምልክት ሆነው ያገለግሉሃል ፤ ምናልባት መንገዱ ቢጠፋህ ለማለት ነው ። ”

“ አሁኑኑ ቅርንጫፎቹን ቆራርጬ እመጣለሁ ” አለ ሳንቾ ።

ሳንቾ እሜካ ውስጥ ገባና አንድ እቅፍ ሙሉ ቅጠል ከነቅርንጫፎቻቸው ተሸክሞ መጣ ። እንዲያሰናብተው ጌታውን ምርቃት ጠየቀ ። ሁለቱም እንባቸውን አዘነቡ ትና ሳንቾ ሮሲናንቴ ላይ ጉብ አለ ።

" ጨዋዋ ፈረሴን በጥንቃቄ ያዝልኝ ሳንቾ ፤ ለኔ ለጌታው ደግ እንደ ነበርክ ለርሱም ደግ ሁንለት ። "

" የነገሩኝን ሁሉ የምዘነጋው ጉዳይ አይደለም " አለና ሳንቾ በየጐዳናው የቆረጣቸውን ቅጠሎች እየበተነ ግልቢያውን ቀጠለ ።

ዶን ኪኾቴም ፣ ጋሻ ጃግሬው ከዐይኑ እስኪርቅና ቃጫፊ መንገድ ላይ እጥፍ እስኪልበት ድረስ ቆሞ ተመለከተው ። ከዚያም ዶን ኪኾቴ ደኑ ውስጥ ዘልቆ ገብቶ ፣ ከቦታ ቦታ ይዘዋወር ጀመር ። እንብቦት ከሚያውቀው የዕብዶች ዕብድ ከሆነ ጥሩር-ለባሽ ፈረሰኛ ፣ እርሱ የባሰ ዐመሆን ልዩ ልዩ ድርጊቶች መፈጸሙን ቀጠለ ።

ሳንቾ ፓንሳ በጉዞ ላይ

በማግሥቱ ፣ ሳንቾ ፓንሳ በዝግታና በድካም ሲጓዝ ውሎ በመጨረሻው ወደ አንድ ትንሽ ሆቴል ደረሰ ። ይህ ችን ሆቴልና አካባቢዋን በቅጡ ያውቃታል ፤ ምክንያቱም እሱና ጌታው ከአንድ ወር በፊት እዚሁ ሆቴል ውስጥ ተስተናግደው እንደ ነበር ያስታውሳልና ።

የራት ሰዓት ስለ ነበር ከወጥ ቤቱ የሚወጣው የትኩስ ምግብ ሽታ አየሩን ሞልቶታል ። ሳንቾ ፓንሳ "ትንሽ ትንሽ የበግ ጥብስ በበላሁ" እያለ ከመከጀሉ የተነሣ ፣ ምራቁን ዐምሬ ይውጥ ጀመር ። ለብዙ ቀናት ክድርቆሽ በስ

ተቀር ምንም ዐይነት ደኅና ምግብ አላገኘም ነበርና ፤ ጉጉቱ ከፍተኛ ሆነ ።

እስከ ሆቴሉ በር ድረስ በፈረሱ ቀረበና ቆም አለ ። በቀድሞ ጉብኝቱ ጊዜ ከሆቴሏ ባለቤት ሠራተኞች ጋር ጭቅጭቅ ፈጥሮ ነበርና ፤ ዛሬ ምን መስተንግዶ እንደ ሚጠብቀው እርግጠኛ አልነበረም ። እና ፤ ከግቢው በር ፈንጠር ብሎ ተቀመጠና በመስኮት በኩል የሚወጣውን የጣፋጭ ምግብ ሽታ እየሳበ ይረካ ጀመር ።

ይህ በዚህ እንዳለ ፤ ድንገት ሁለት ሰዎች ከዚያው ሆቴል ግቢ ወጥተው ቆም አሉና ፤ ሳንቾን ትክ ብለው ይመለከቱ ጀመር ። አንደኛው ሊሴሳዉ እንዲህ አለው ።

“ ጌታዬ ዶክተር ፤ ምን ይመለከቱ ! ሳንቾ ፓንሳ አይደለም እንዴ ? ”

« ያለ ጥርጥር እሱ ራሱ ነው ። ከዚህም በላይ የዶን ኪኾቴን ፈረስ ነው የሚነው ” አለ ሌላዉ ።

እነዚህ ሁለት ሰዎች ፤ የዶን ኪኾቴ መንደር ነዋሪ የሆኑት የነፍስ አባትዩጠጫ ጸጉር አስተካካዩ ነበሩ ። እነዚህ ሁለት ሰዎች ፤ በዶን ኪኾቴ መጻሕፍት ላይ ፍርድ ሰጥ ተው እንዲጋዩ ያደረጉና ፤ የምስኪኑን ጦረኛ ‘ ሕክ ፍት ’ ከማንም ሰው ይበልጥ የሚያውቁ ናቸው ።

የእንሱም ዓላማ ዶን ኪኾቴን ፍለጋ በየአገሩ መሄ ዚር ከመሆኑም በላይ ፤ ሲያገኙትም ወደ ቀድሞው ሕይ ወቱ እንዲመለስና ፤ ወደ ወዳጅ ዘመድ እንክብካቤ እንዲ መለስ ለማሳመን ቆርጠው የተነሡ ነበሩ ። ሳንቾን ጠጋ ብለው ሲያናግሩት ፤ እሱ ግን ለምን እነዚህ ሰዎች ከዚህ አካ ባቢ ሊገኙ ቻሉ ብሎ እጅግ በጣም ገረመው ።

« ጌታህ ወዴት ነው ፣ ሳንቾ ? ዶን ኪኾቴ ወዴት ነው ያለው ? » ሁሉቱም ጠየቁት ።

« ጌታዬ በከባድና እጅግ ጠቃሚ በሆነ ሥራ ተጠምዶ ይገኛል » በማለት ሳንቾ ፓንሳ በኩራት መንፈስ መለሰ ።

« እና የት ነው ያለው ? » የነፍስ አባቱ ጠየቀ ።

«ያለበትን ልነግራችሁም አልችልም » ሳንቾ መለሰ ።

« ስማ ሳንቾ ፓንሳ ! በዝባዝንኬ ወሬህ አታስልቺን ። ዶን ኪኾቴ የት እንደሚገኝ ካልነገርከን ፣ እሱን ገድለህ ፈረሱን እንደ ሰረቅህበት ነው የሚሰማን ። ስለ ዚሀ እውነቱን ተናገር ። ፈቱን ግለጽልን ፣ ካለበለዚያ አጋድመን እንገርፍህና ዋጋህን ታገኛለህ ፡ እሰ ጸጉር አስተካካዩ ።

« እንዴ ! ምን ነካችሁ ጎረቤቶቼ ! ሰምን ታስፈራሩኛላችሁ ? ጌታዬ አሁን በዚህች ደቂቃ ውስጥ የሚገኝበትን ሥፍራ ማወቅ አልችልም ። ሆኖም ባሻገር ከሚገኘው ተራራ ትቼው መጥቻለሁ ። እሱም ራሱን ከግንዶች ጋር እያላተመ ፣ ቁጥጥቹን እየሰነጠቀና ብዙ ሺህ ተአምራዊ ድርጊቶች በመፈጸም ላይ በመሆኑ ፣ እንዳንዶቹንም ላገልጻቸው አልሻም ። »

የዶን ኪኾቴን ገድል በዝርዝር ሲገልጽላቸው ፣ ራሱ የፈጠራቸውን ፍሬ ከርስኪ ወሬዎችንም ጨማምሮና እየቀባባ ነበር ።

« እና ፣ ይኸውላችሁ ! አሁን የጌታዬን ደብዳቤ ለእመቤት ሆይ ዱልሲኒያ ለማቅረብ ወደ ቶቦሶ በመጓዝ ላይ እገኛለሁ » አላቸው ።

“ እስቲ ዶብዳቢጪን አሳየን ” ጸጉር አስተካካዩ ጠየቀ ።

ሳንቾ ፓንሳም የማስታወሻ ደብተሩን ፍለጋ እጁን ኪሱ ውስጥ ከተተ ። ቢፈልግ ቢፈልግ ሊያገኘው አል ቻለም ። ከአንዱ ኪስ ወደ ሌላዉ እጆቹን ቢያስገባና ቢያወጣ፣ ብብቱ ውስጥ፣ ባርኔጣው ውስጥ ቢፈልግ፣ እስከ መጨረሻው ቢደክም ሊያገኝ አልቻለም ። ለካንስ ዶብዳ ቢዉ በቀዳዳ ኪሱ በኩል ሾልኮ በተጓዘበት መንገድ ላይ ጠፍቶበት ኖሯል !

ፊቱ ከሰል መሰለ ፤ እጆቹም ይንቀጠቀጡ ጀመር ። እንደ ፅብድ በመቀባጠርና ጢሙን በመንጨትና፣ ፊቱን እየጠፈጠፈ ብስጭቱን ቀጠለ ።

« ምን ሆነሃል ሳንቾ ? ለምን እንዲህ ትበሳጫለህ ? » ሲል ጠየቀ ።

“ ለምን አልበሳጭም ? መበሳጨት ይነሰኝ እንዴ ? ልክ እንደ ሦስት ዶብር የሚቆጠሩ ሦስት አህዮች ጥያለሁ ። በዓለም ላይ ተደርጎ የማያውቅ ድብደባና ቅጣት ይገ ባኛል ” አለ ሳንቾ ።

“ ምን ማለትህ ነው ? በኪስህ ውስጥ አህዮች አስቀ ምጠህ ነበር እንዴ ? ” ሲል የንሥሐ አባትየው ጠየቀ ።

“ እንዲህ አይደለም ጉዳዩ ! ለዱልሲኒያ የተጻፈው ዶብዳቤ ብቻ ሳይሆን ፣ ለዶን ኪኾቴ የእኅት ልጅ የተጻ ፈም ትእዛዝ አብሮ ጠፍቷል ። ጌታዬ ካሉት አምስት አህዮች ሦስቱን እንቷ ልጅ ለኔ እንድትሰጠኝ የታዘዘ በት ማስታወሻ ዶብተር ነው የጠፋብኝ ። ”

ሳንቾ እንባውን እያዘራ ፣ ከዚህ ቀደም አንድ ግራጫ አህያው እንደ ጠፋበት ፣ ያም ግራጫ አህያው ፣

ልቡቱ፣ ለልጆቹ ደስታ ፤ ለሕይወቱ ተስፋ እንደ ነበር እየሮጡኝ በለቅሶ ይገልጽ ጀመር ።

የዶን ኪኾቴም የንስሐ አባት ፤ « አይዞህ ሳንቾ እኔ እረዳሃለሁ ። እኛ የመጣነውም ጌታህን ዶን ኪኾቴን ፈልገን ልናገኘው ነውና ፤ ከዚህ ቀደም ከጻፈልህ የተሻለ ማዘዣ እንዲጽፍልህ አደርጋለሁ ” አለው ።

ሳንቾ ፊቱ ፈካ ፤ በደስታ ባሕር ገብቶ ይዋኝ ጀመር ። በእርግጥ ይህን ታደርግልኛለህ ? እንግዲያውስ የደብዳቤው መጥፋት ምንም አይደለም ። በበኩሉ የዱልሲኔያን ደብዳቤ ከቁም ነገር አልቈጠረውም ። “ በደብዳቤው ውስጥ የሰፈረውን መልእክት በሙሉ በቃሌ ስለማውቀው ራሴ በሌላ እንግራታለሁ ። ዝርዝሩንም ከፈለገች ፤ ልክ እንደ ጽሑፍ ቃል በቃል ሳንብላት ስለምችል የዚ ደብዳቤ ጉዳይ ቀላል ነው ። ከፈለጋችሁ ቃሉን ለእናንተ ልተር ክላችሁ እችላለሁ ። ”

“ ንግግርህ በሙሉ የብልህ ሰው ነው ። አሁን እኛን የሚያሳስበን ጌታህን የማግኘቱ ጉዳይ ነው ። ቅብጥብጥ የጀብደኝነት ባሕርዩን ሁሉ እርግጥ አድርጎ እንዲያቆም ፤ ከዕብደት ሥራው እንድንመልሰው ብቻ ነው የኛ ጥረት ። አንተ ከእኛ ጋር ወደ ሆቴል ቤቱ ውስጥ ግባና ፤ ምሳችንን እየበላን በጉዳዩ ላይ እንወያይበት ” አለ የንሥሐ አባት ዬው ።

“ እናንተ ሁላችሁ ወደ ሆቴል ቤቱ ግቡ ፤ ለእኔ የሚሻለኝ ግን ፤ እዚሁ ነፋስ እየመታኝ እንደ ልቤ ሆኘ ስመገብ ነው ፤ ደስታ የሚሰማኝ ። ፈቃዳችሁ ይሁንና ፤ ትኩስ ምግብ በሳህን አድርጋችሁ እዚሁ ድረስ ብትል ኩልኝ እየበላሁ እጠብቃችኋለሁ ። የፈረስ ቤቱ ልጅም

አንድ ሸክም ድርቆሽ ለሮሲናንቴ እንዲያመጣለት ንገ ሩት ” አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

ጸጉር አስተካካዩና የንስሐ አባትዬው ወደ ሆቴሉ ውስጥ ሲገቡ ፤ ሳንቾ ግን ከአጥሩ ውጭ ተቀምጦ ትክስ ቅቅል ሥጋ በሳህን ተደርጎ ወዲያው ተሳከለት ። ለብዙ ቀናት ከደኅና ምግብ ተለይቶ ነበርና ፤ ሳንቾ ደስታውን አልቻለውም ። የጥሩ ምግቡ መጣፈጥና ጣዕም ስሜቱን አስፈነደቀው ። ከምግቡ በኋላ ዶን ኪኾቴ ወደሚገኝበት ተራራ ሲመለስ ዝግጅቱን ቀጠለ ፤ በራሱ በዶን ኪኾቴ እጅ የተጻፈ ሦስት አህዮች ሲያስጠው የሚያስችል ማዘዣ እንደገና ለመቀበል ቸኩሏል ።

የንስሐ አባትዬዉና ጸጉር አስተካካዩ ከሆቴሉ ቅጥር ግቢ ከብቶቻቸውን ጭነው ለጉዞው ተዘጋጅተው ሲወጡ ፤ ሳንቾ ፓንሳ ምሳውን እንደ ዘበት ገና መጨረሱ ነበር ። ጊዜ ሳያባክኑ ጉዞአቸውን ቀጠሉና ፤ ከቀትር በኋላ መንገድ እንዳይጠፋው በማለት ሳንቾ ፓንሳ በየ ጉዳናው ካንጠባጠባቸው ቅጠላ ቅጠሎች አካባቢ ደረሱ ።

“ ከጌታዬ ጋር የተለያየነው እዚህ ገደማ ይመስለ ኛል ” ሲል ሳንቾ ተናገረ ፤ እንደ አጋጣሚ ሆኖ ጀግናው ጦረኛ ከአንድ ትልቅ ቋጥኝ ላይ ተቀምጦና ወደ ሰማይ አንጋጦ ሲመለከት አገኙት ። ዶን ኪኾቴ ሰውነቱ ገር ጥቶ በረሃብ አንጀቱ ተጣጥፎ ቢያገኙትም ፤ እሱ ግን “ የእመቤት ዱልሲኒያ ጉዳይ እምን ደረሰ ? ” እያለ ትን ፋሹን ቁርጥ ቁርጥ ሲያደርግ ፤ ሳንቾ ጠጋ ብሎ አዳመጠ ።

ዶን ኪኾቴ ፤ በቋጥኙ ላይ ቆሞ በምን ፀይነት መን ገድ ጉረቤቶቹን እንደ ተቀበላቸው ፤ እነሱም ልብሳቸ ውን በመለወጥ ገጻቸውን በጭምብል (ማስክ) በመሸ

ፈን ሌላ ሰዎች መስለው ስለ ሐዱበት ፣ ማንነታቸውን ለይቶ አላወቀም ነበር ።

ዶን ኪኾቴ ፣ የቀድሞ ጥሩሩን ለብሶ ፣ በፈረሱ በሮ ሲናንቴ ላይ ወጥቶ ፣ ከዚያ እልም ካለው ደን ውስጥ እን ዲወጣ ለማድረግ ፣ የንሥሐ አባቱና ጸጉር አስተካካዩ (አሁን ገጻቸውን ለውጠው — ሌላ ሰው ናቸው ለዶን ኪኾቴ) በምን ዐይነት ጥበብ እንደ ቀረቡትና በዘዴ ሊታዘዛቸው እንደቻለ በዝርዝር ማውሳቱ ጊዜ ይፈጃል ። ዶን ኪኾቴ ሁለቱ ጐረቤቶቹ ሊያታልሉት የበቁት ፣ እሱ ራሱ የሚፈልገውን ዐይነት ጉዳይ በማንሣት ነበር ። ይኸውም ፣ ‘ እንዲቷን ደካማ ልዕልት አንዱ ጉልበተኛ ከሥልጣኗ ሳላወረዳት ፣ ካባንተ በስተቀር ይህንን ሰው የሚቋቋም የለም ብለን ርዳታህን ልንሻ መጥተናል በማ ለት ይደልሉታል ።

ዶን ኪኾቴ ፣ በፈረሱ ላይ ገብ ብሎ ከተመቻቸ በኋላ ፣ “ ተከተሉኝ ! ሁላችንም በአንድነት ሔደን የዚህችን ዕድለ ቢስ እመቤት መከራ በደም እንወጣላታለን ” እያለ ይጮኽ ጀመር ። ንሥሐ አባትየውና ጸጉር አስተካካዩ መልካቸውና ልብሳቸው ፍጹም ተለውጧልና ፣ ዶን ኪኾቴ ማንነታቸውን ሳያውቅ እርዳታ ጥየቃ የመጡ መስለውት ፣ ሁሉም ጉዞአቸውን በአንድ ላይ ቀጠሉ ። ዶን ኪኾቴና ጐረቤቶቹ በከብቶቻቸው ላይ ሆነው ሲጓዙ ፣ ሳንቾ ፓንሳ ግን ፣ በእግሩ ከኋላቸው ሆኖ መከተል ዕጣ ፋንታው ሆነ ። ቢሆንም ፣ ስውነቱን እዝናንቶ መንፈሱን በደስታ ሞልቶት ነበር ። በጉዞው ላይ ሳንቾ ሦስቱን አህዮች እንዴት እንደሚያገኝ ፣ ዶን ኪኾቴ የሚሰጠውን ደሴት የሚያ ገኝበትን ቀን ከማሰላሰል በስተቀር ፣ እንዳችም ሌላ ሐሳብ አልገባውም ነበር ።

በማግሥቱ ፣ መንገደኞቹ ከነበሩበት ተራራማ አካባቢ በደኅና ጉዞአቸውን በመቀጠል ላይ እንዳሉ ፣ በድንገት ዘወር ሲሉ አንድ በልዩ አለባበስ የተጀቦነ ሰው ፣ በከብት ጀርባ ላይ በዝግታ ሲጓዝ ተመለከቱ ። ሰውዬው ከሁኔታው መላ ቅጡ የጠፋበት ሆኖ ፣ በአንዲት አጭር አህያ የተቀመጠ ነበር ። አህያይቱ ከቅንድ - አጠማ ጋር እንኳ ለመሸቀዳደም የማትችል ሙትቻ እንስሳ ነች ። ሳንቾ ፓንሳ ሰውዬውን እንደ ተመለከተ ዐይኖቹ ተከፈቱ ፤ ገጹ በራ ። ይህ መላቅጡ የጠፋው በአለባበስ የተጂያጂያለው ሰውዬ ፣ የታወቀው ሌባ ዢን ዴ ፓሳሞንቴ መሆኑን ሳንቾ ፓንሳ ጠንቅቆ ዐወቀ ። አህያዋም ለብዙ ጊዜ ያገለገለው ግራጭ መሆኗንም ወዲያው እንዳየው አረጋገጠ ። ከዚያም ሰውዬውንና አህያውን በአንድነት ለመያዝ ይሮጥ ጀመር ፤ ምንም እንኳ ዴ ፓሳሞንቴ አህያውን እየገረፈ ሊያስጋልብ ቢሞክርም ፣ ሳንቾ ፓንሳ ደረሰበት ።

" አንተ ሌባ ደርሼብሃለሁ ። ከውድ አህያዬ ጀርባ ላይ ውረድ ! መጽናኛዬ ከሆነው አህያዬ ውረድና በእግርህ ጉዞህን ቀጥል ብዬሃለሁ " እያለ ሳንቾ ፓንሳ ይጮኽበት ጀመር ።

ዢን ዴ ፓሳሞንቴ ፣ ከኋላው ሰዎች በጩኸትና ቢተረማመሱ ጉዳዩ አልነበረም ። እንዲያውም ብዙ ሰዎች ሲሯሯጡና ሲጠጉት ባየ ጊዜ ፣ ከአህያው ላይ ዱብ ብሎ በሰመደው እግሩ ሩጫውን ቀጠለ ። የሮጠበትም ምክንያት ይከታተሉት የነበሩት ፣ እነዚያ የንጉሡ መኰንኖች የደረሱበት መስሎት እንደሆነ የማይጠረጠር ነው ። እስካሁን ባደረገው ሽሽት ዱር ውስጥ ገብቶ ይጓዝ ስለ ነበር ፣ በየት ወጥቶ በየት እንደሚገባ ሊደረስበት ባለ መቻሉ ሰላሙን አግኝቶ ነበር ። አሁን ግን ፣ ሳይታሰብ ሰዎች

ስለ ደረሱበት ነው አህያውን ጥሎ እግሬ አውጭኝ ብሎ የፈረጠጠው ።

የሳንቾ ፓንሳን ደስታ ይህ ነው ብሎ በቃላት ለመ ግለጽ ያዳግታል ። በአህያው አንገት ላይ ተጠምጥሞ እየሳመ ከሚገባዉ በላይ ያሞጋግሰዉ ጀመር ።

" ፍቅሬ ! የምወድህ ግራጫዬ ፣ ገንዘቤ ንብረቴ ! እውነት አሁን ተመልሰህ በእጄ ገባህ ? እኔ አላምንም ። ከተለያየንበት ቀን ጀምሮ እንደምን ከረምህልኝ ? " እያለ ሳንቾ ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ ። አህያው ግን ከማ ንኛውም አህያ ይበልጥ ጸጥ ብሎና ፈዝዞ ከማንቀላፋት በስተቀር እንቅስቃሴ አይታይበትም ። ለሳንቾ ጥያቄና መቀበጣጠር አንዳችም መልስ ሳይሰጥ አፍንጫውን — ግንባሩን ሲስመው በዝምታ መቆም ብቻ ሆነ ።

አብረውት የነበሩት ሰዎች ሁሉ ፣ በዶን ኪኾቴ ጋሻ ጃግሬ ዕድለኛነት ተደሰቱ ።

" የጠፋብህን እንስሳ መልሰህ በማግኘትህ ደስ ብሎኛል ። ሆኖም ወደ እኅቴ ልጅ የተጻፈውን የትእዛዝ ደብዳቤ የሚሽር ትእምር አይፈጠርም ። ሦስቱንም አህ ዮች በትእዛዜ መሠረት እንድትሰጥህ አሁንም ቃሌ የጸና ፣ ትእዛዜ የተጠበቀ ነው " አለ ዶን ኪኾቴ በኩራት መንፈስ።

ሳንቾ ፓንሳም ፣ "እመሰግናለሁ ጌታዬ ! እኔም ምንም ጊዜ ቢሆን እርስዎን የሚመስል ጌታ አይገኝም ያልኩት ቃል አሁንም ጽኑ ነው " አሉና ሁሉም ጉዞአቸውን ቀጠሉ ።

ጉዞ በበሬ ሠረገላ

የንስሐ አባትዬው ፣ ጸጉር አስተካካዩና ሳንቾ ፓንሳ ዶን ኪኾቴን አጅበው ጉዞአቸውን በመቀጠል ላይ ቢሆኑም ፣ ከሀገራቸው ወረዳ ገና አልደረሱም ። የዶን ኪኾቴ መንፈስ አልተረጋጋም ። በልዩ ልዩ ጉዳዮች መንፈሱ ስለ ተጠመደ ፣ ሐሳቡ ሁሉ ውሉ እንደ ጠፋበት ድር ይዝረከረክበት ጀመር ። የፈረሱን የሮሲናንቴን ልጓም በወጉ ይዞ መንገዱን ተከትሎ ፈረሱን መምራት ባለ መቻሉ ፣ የንስሐ አባትዬዉና ጸጉር አስተካካዩ ዶን ኪኾቴን ወደ አገሩና ወደ ቤቱ በቀጥታ የሚወስዱበትን ዘዴ ይፈልጉ ጀመር ።

እንደ አጋጣሚ ሆኖና ፣ አንድ ሆቴል አቅራቢያ ደርሰው ዕረፍት ሲያደርጉ ፣ አንድ የበሬ ሠረገላ ነጂ በሬዎቹን ይዞ አንዳች ነገር ሲፈልግ አገኙት ። ሰውዬውም ማንኛውንም ዐይነት ሥራ ቢያገኝ ሲሠራ ዝግጁ ነበር ። የዶን ኪኾቴ የንስሐ አባት ከዚህ ሰውዬ ተቀራርቦ በጥቂት ጊዜ ተወዳጀ ፤ የሰውዬዉ ሠረገላ በበሬ የሚሳብ ፣ ለነጂው ምቾት እንዲሰጥ ሆኖ የተሠራ እንደ መሆኑ መጠን በብዙ ጥንቃቄ የተያዘ ሠረገላ ነበር ። ጎጆ—መሰል የሠረገላው አካል ፣ በዕንጨት የተማገረ ሲሆን ፣ ከነጂው ሠረገላ ጋር የሚታሰርና የሚዘጋ ነበር ። የትራሱ ምቾት ከፍታው የክፍሉ ስፋት ፣ አንድ ሰው ቢፈልግ ሊቀመጥበት ፣ ወይም ሠረገላው ተዘግቶ ሊተኛበት የሚያስችል ዐይነት ‘ ጎጆ ’ ነበር ። ዶን ኪኾቴ ወዳጆቹ ምን ዐይነት

ነገር በማካሔድ ላይ እንዳሉ አላወቀም ። እነርሱ ከሠረገላው ነጂ ጋር ፣ ዝግጅታቸውን ሲያጣድፉ ዶን ኪኾቴ በሆቴል ውስጥ ተቀምጦ ፣ በአካባቢው ለተሰበሰቡት ሁሉ ስለ ጦረኛና ስለ ጀብዱ ሥራ ወጉን ይጠርቅ ነበር ።

መሽትሽት ሲል ፣ ዶን ኪኾቴ በሆቴሉ መኝታ ክፍል በጸጥታ ተጋድሞ እንዳለ ፣ ልዩ ዐይነት ልብስ የለበሱ ፣ ልዩ ፍጡር የሚመስሉ ሰዎች በቀጥታ ወደ መኝታ ክፍሉ ሲገቡ ታዩ ። ፊታቸው ተሸፋፍኗል ። ልብሶቻቸው ረግኸርም ቀሚስና ነጫጭ የአንገት ልብስ ሲሆኑ ፣ ሁኔታቸው ግን በጣም የሚያስፈራ ነበር ። እነዚህ ሰዎች የዶን ኪኾቴ የንስሐ አባትና ጸጉር አስተካካዩ ሲሆኑ ፣ አብረዋቸውም የነበሩት የሆቴሉ ሠራተኞች ናቸው ። መልካቸውን ለውጠው ስለ ነበር ፣ ሳንቾ ፓንሳ እንኳ እነርሱ መሆናቸውን ለማወቅ ተሳነው ። የመኝታ ክፍሉን ድንገት ከፍተው ዘው አሉበት ። ዶን ኪኾቴም ብድግ ብሎ ሲቀመጥ ታየ ። በመገረም ተመለከታቸው እንጂ ፣ የፍርሃት መንፈስ አላሳደረበትም ። በነጫጭ መጎናጸፊያቸው ተሸፋፍነው በአልጋው ዙሪያ ሲርመሰመሱ ፣ ተቀምጦ ከማየት በስተቀር አንድም ቃል አልተነፈሰም ። በመተተኞች የተከበበና ፣ እነዚህ ርኩስ መንፈሶች ሊወጉት የመጡ ስለ መሰለው ፣ ከመተተኞች ጋር መዋጋት ዋጋ ቢስ መሆኑንና ፣ ከመተተኛ ጋር የሚዋጋ መተተኛ ብቻ ነው ብሎ ስለሚያምን ፣ በጸጥታ ድርጊታቸውን ከማየት በስተቀር አልተንቀሳቀሰም ።

ርኩስ መንፈስ ናቸው ያሏቸው ሰዎችም ፣ ዶን ኪኾቴን ለቀም አድርገው ከመኝታው አንሡና ፣ ልብሱን አለበሱት ፣ ተሸክመው ወደ በሬዎ ከወሰዱት በኋላ ፣ ተዘጋጅቶ ይጠባበቅ በነበረው የማገር ጐጆ ውስጥ አስገቡት ። በሩንም በህግታ ዘጉት ። በማገር የተሠራውን

ጐጆ ፣ ዶን ኪኾቴ እውስጡ እንዳለ ተሸክመው በተሽከ
ርካሪው ሠረገላ ላይ ካስቀመጡት በኋላ ፣ ዙሪያውን ጥፍር
አድርገው አሰሩት ፤ ነጂው አለንጋውን በበሬዎቹ ላይ
በዝግታ እያሳረፈ ሠረገላው ከሆቴሉ ዋና በር ለመውጣት
ሲያዘግም ታየ ።

ዶን ኪኾቴ እምብዛም አልከፋውም ፤ እንዲያውም
በጨረቃ ብርሃን በበሬ ሠረገላ ላይ ፣ በዕንጨት ጐጆ ውስጥ
ሆኖ ሲጓዝ ለማየት ፣ ሰዎች ከሆቴል ቤቱ ዙሪያ ተሰብ
ስበው ስለ ነበር በማገሩ ቀዳዳ ያጫውታቸው ጀመር ።

“ ባነበብኳቸው መጻሕፍት ውስጥ ፣ አንድም ጦረኛ
በበሬ በሚነዳ ሠረገላ ላይ ተቀምጦ ሲጓዝ አላጋጠመ
ኝም ፤ ኧረ ጨርሶ አንብቤም አላውቅ ! ” ሲል ተናገረ ።
ቀጠል አደረገና ፣ « ጥሩር-ለባሽ ፈረሰኛ ሲባል ፣ ክንፍ
እንዳለው ነገር በሚበርሩ ፈረሶች ወይም በሌላ አውሬ
ላይ ተቀምጦ ሲጓዝ ብቻ ነው ያነበብሁት ። ሆኖም ፣ የኔ
በበሬ ሠረገላ ላይ ተቀምጦ መጓዝ ፣ ለክፉ የማይሰጥ ስለ
ሆነ አልቃወምም ” ይል ጀመር ። ከዚህ ንግግሩ በኋላ
ለብዙ ጊዜ በጸጥታ ቆየ ።

የማግሥቱ ጉዞአቸው ለጥ ባለ ሜዳ ላይ ሆኖ ፣ አያሌ
መንገደኞች የበዙበት ስለ ነበር ፣ የሠረገላውን ውገዝ
ዋዜ ሰው እንደ ድንቅ እየተከተለ ሲያየው ዋለ ። እስረ
ኛውን ጦረኛ ፣ የሠረገላው ነጂ በሬዎቹን እየነዳ ፊት ፊት
መንገድ ይመራል ።

ከሠረገላዉ ግራና ቀኝ ፣ የዶን ኪኾቴ የንስሐ አባ
ትና በሆቴሉ ውስጥ የነበሩት ሰዎች እንደ ጠባቂ መኮን
ኖች ተመስለው ያጅቡት ጀመር ። ከሠረገላው በስተጀ
ርባ በጣም ተጠግቶ ፣ ሳንቾ ፓንሳ በግራጫ አህያው ላይ
ጉብ ብሎ ፣ ሮሲናንቴን እየጐተተ ተከትሏል ። የንሥሐ

አባትዬውና ጸጉር አስተካካዩ ገጾቻቸውን ሸፍነው ፣ በየበቅሎቻቸው ላይ አጐንብሰው ይጓዛሉ ፤ ዶን ኪኾቴ ሠረገላው ላይ ካለው ጐጆ ውስጥ ቢቀመጥም ፣ እንደ ልቡ መንቀሳቀስና መተኛትም ይቻለው ነበር ። ሆኖም ፣ ዶን ኪኾቴ ያላንዳች እንቅስቃሴ ተቀምጦ ሲታይ ሐውልት እንጂ እስትንፋስ ያለው ፍጡር አይመስልም ነበር ። እና ፣ በዚህ ዐይነት ጕዳናውን እያቋረጡ ፣ ዋናውን መንገድ እየዘለቁ ጉዞአቸውን ተያያዙት ።

ጉዞው በቀጠለ ቍጥር ፣ ጦረኛው ጌታ አንገቱን ደፍቶና ፈገዞ በመታየቱ የሳንቾ ልብ በሐዘን ተነካ ። ጦረኛ ጌታው እንደ አውሬ በጐጆ ውስጥ ታፍኖ ፣ ያለ ፈቃዱ ከቦታ ቦታ ሲንከራተት ማየቱን ሊቋቋም አልቻለም ። ስለሆነም ፣ ጠባቂዎቹ ምሳቸውን በሚበሉበት ጊዜ ሳንቾ ከጌታው ጋር በመነጋገርና በማጽናናት ጊዜውን ያሳልፍ ነበር ። ታዲያ ፣ ጦረኛውም እውነተኛ ጀግና በመምሰል ከጋሻ ጃግሬው ጋር በደስታ መንፈስ ይነጋገራል ።

“ በርታ ሳንቾ ! ግድ የለም ! ሁሉም ነገር ጥሩ ነው ። ከእነዚህ የተረገሙ መተተኞች እጅ በቅርብ ጊዜ ውስጥ እንደምናመልጥ የታወቀ ነው ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“ እሺ ጌታዬ ! እንዲያውም የዚህን የመተት ጉዳይ እውነቱን በዝርዝር እገልጽልዎታለሁ ። እኒህ ፊታቸውን ሸፍነው ከኋላችን በበቅሎ ላይ ተቀምጠው የሚጓዙት ሁለት ሰዎች እነማን እንደሆኑ ያውቃሉን ? ” ሳንቾ ጠየቀ ።

“ እንዴታ ! ያለ አንዳች ጥርጥር መተተኞቹ ናቸዋ ! ማናቸው ልትለኝ ነው ታዲያ ? ” አለ ዶን ኪኾቴ ቆጣ ብሎ ።

“ በፍጹም መተተኞች አይደሉም ። እኒህ ሰዎች ከሀገራችን መንደር የመጡት የንስሐ አባትዎና ጸጉር

አስተካካዩ ናቸው ። እነሱም የርስዎ ሙያና ዝና እንዳይ ጋንንና እንዳይበልጢቸው ፈርተው የሚያደርጉት የቅናት ሥራ ነው ። ምንም ለዘወትር ቢማስኑ ፣ እርስዎ ከደረሱ በት ደረጃ ላይ እንደማይደርሱ ስላወቁ ፣ በምቀኝነት ሐሳብዎ ሁሉ እንዳይሳካ ለማድረግ የተነሣሡ ናቸው ። እንደ ሚመስለኝ መተት ሆኖ አይደለም ፤ ነገር ግን እርስዎ የባጡን የቆጡን ስለሚቀባጥሩ እነርሱም መንገድ አግኝተው ዓላማዎን ሊያደናቅፉ ተነሣሥብዎ ” አለ ሳንቾ በቅሬታ ።

“ ወዳጄ ሳንቾ ሆይ ! ይህ ጉዳይ የመተት ነው ብዬ ሃለው ። በእንተ ሐሳብ እኒህ እኛን የሚጠብቁ ዘበኞች የቀድሞ ወዳጆቻችን ፣ የንጉሡ አባቴና ጸገር አስተካካዩ ናቸው ፣ ብለህ ያሰብከው ፣ የፍርሃትህ ውጤት ነው ። መተት ታላቅ ኃይል ነው ። እኒህ መተተኞች በአለባበስ ወዳጆቼን የመሰሉ ቢሆንም ፣ መተተኞች በችሎታቸው የፈለጉትን ከመፈጸም የሚያግዳቸው ነገር እንደማይኖር ያስገነዝባል ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

ብዙ ከተጓዙ በኋላ ፣ በንጉሡ አባትዮው ፈቃድ ሳንቾ በሠረገላው ላይ የተጫነውን ጎጆ በር ከፍቶ ፣ የምስኪኑ ጌታው እግር ለመጀመሪያ ጊዜ መሬት እንዲነካ አደረገ ።

“ ይምጡ ጌታዬ ! ከዚህ ወህኒ ቤት በነጻ እንዲወጡ ላድርግ ” ሲል ከተነፈሰ በኋላ ፣ “ ቢታማኝ ፈረስዎ በሮሲናንቴ ጀርባ ተቀምጠው ዓለምዎን ይቅጩ ! ” አለ ሳንቾ ።

ምስኪኑ ፈረስም እንዲያው ነፍስ ስላለችበት ብቻ ይንከላወሳል እንጂ ፣ እሱም በመተት እንደታሰረ ሁሉ እንገቱን ደፍቶ ሲንቀሳቀስ ካሁን አሁን ወደቀ ያሰኛል ።

ዶን ኪኾቴ "ሳንቾ በል አንተ እንዳልከው ይሁን ፤ ከእኒህ ክቡራን ሰዎች ለማምለጥ እንደማልሞክር በልበ ሙሉነት ማሳየትና ቃሌን መስጠት አለብኝ ። ደግሞም ልክ እንደ እውነተኛ ጥሩር - ለባሽ ፈረሰኛ ፤ በፈረሴ ላይ ወጥቼ የምጓዝና ፤ ለዚህም ችሎታና ብቃት ያለኝ መሆኔን ማሳየት አለብኝ ? " እያለ ይለፈልፍ ጀመር ።

"አንተ ተፈረስ ጋር የተፈጠርክ ፤ ነገር ግን አበባና የክብር አክሊል የሆንክ ፤ አይዞህ እንደገና ተመልሰን ራሳ ችንን እንደምንችል እምነቴ የጸና ነው" እያለ ዶን ኪኾቴ ፈረሱን ያናግረው ጀመር ።

ዶን ኪኾቴ ፍጹም ተዳክሞ ስለ ነበር ፤ ከኮርቻው ላይ ዶጋግፈው ቢያወጡትም ፤ ሰውነቱ ተዝለፍልፎ ነበ ርና በወግ መቀመጥ ተሳነው ። በዚህም ላይ ጸጥታ የሠ ፈነበት መኖሪያ ቤቱና ተወዳጅ ጉረቤቶቹ እየታወሱት በናፍቆት ይጨነቅ ጀመር ። ሳንቾ ፓንሳን ጠራውና ፤

"በፈረሴ ጀርባ ላይ መቀመጥ ተስኖኛልና ፤ እንደ ምንም ብለህ በእስማተኞቹ ሠረገላ ውስጥ ደግፈህ አስ ገባኝ" አለው ።

"በደስታ ትእዛዝዎን እፈጽማለሁ ጌታዬ ። የምመ ክርዎት ከእነዚህ ሰዎች ጋር በቀጥታ አገራችን ከገባን በኋላ ፤ እስካሁን ካከናወነው ጉዞ የበለጠና ሌላ ጠቃሚ

ጉዞ የምናቅድበትን ዘዴ በሰፊው ለመመካከር እንችላለን ። ”

“ ምክርህ መልካም ነው ። ነገር ግን ፥ እኒህ ሙሉቶኞችና ሥራቸው ካለቀቀኝ ፤ እንዴ ምን ያልከውን ልፈጽም ይቻለኛል ? ” ሲል በጥርጣሬ ጥያቄውን ሠርወር አደረገ ።

የሠረገላው ነጂ በጐጆዉ ውስጥ ጥቂት ድርቆሽ ሣር ጉዝጉዞ ፥ ጀግናውን ጦረኛ ተረዳድተው በቀስታ ከፈረሱ ላይ አንሥተው ፤ ለምለም ሣር ላይና ሽታው ደስ በሚያሰኝ አልጋ ላይ አስተኙት ፤ ካስተኙትም በኋላ ፥ በሩን ሳይዘጉ ገርበብ አድርገው ተዉለት ። ምክንያታቸውም ዶን ኪኾቴ የእስረኝነት መንፈስ እንዳይሰማው አስበው ነበር ።

ሠረገላ ነጂዉ ፡ እስንጋዉን በከብቶቹ ላይ ሲያሳርፍ እጀቡ እንደ ቀድሞ ሆነና ጉዞው ቀጠለ ። ሁሉም በአውራ ጎዳናው በትራ ግብተው ትራራውን ዐልፈው ሜዳውን ስንጥቀው ይጓዙ ጀመር ።

ከስድስት ቀን ጉዞ በኋላ ፥ ቀትር ላይ ሀገራቸው መኻል ወደምትገኘው መንደራቸው ደረሱ ። እንደ አጋጣሚ ቀኑ ሰንበት (እሑድ) በመሆኑ ፡ የአገሬው ሕዝብ ሁሉ በየመንገዱ ላይ ይንሸራሸር ነበር ። በበሬዎች ይነዳ የነበረው ሠረገላ በሕዝቡ መካከል ሲደርስና በላዩ ላይም የተሠራው ቆጥ መሰል ጐጆ ሲታይ ፥ ብዙ ሕዝብና ሕፃናት ሠረገላዉን ከመቅጽበት ከበቡት ። ሕዝቡ በሙሉ፡ በዚህ ጐጆ ውስጥ የተጠመደው አውሬ ለመካኑ-አራዊት የተያዘ ግዙፍ አውሬ እንደሆነና ማን ይዞትና ወደ አገራቸው የመጣበትንም ምክንያት ለማወቅ ይጣደፍ ጀመር ። የሆነ ሆኖ በመጨረሻ በጐጆው ውስጥ ያዩት ፡ አውሬ ላይ

ሆን ፡ የተከበረው ጐረቤታቸውና ወዳጃቸው የነበረው ፤ ስሙንም አቶ ኪሻና ብለው ይጠሩት የነበረው ሆኖ አገኙት ። በሣር ድርቆሽ ላይ ተጋድሞ ዙሪያውን ከበው የሚመለከቱትን ሁሉ ከጉዳዩ ሳይቆጥር ለጥ ብሎ ይታይ ነበር ። የሚያውቀው መንደር አዲስ ሆነበት ። የጐረቤቶቹና የዘመዶቹ መልክ ተለዋወጠበት ።

የሀገሩ ሕዝብ ሲገረምና ሲደነቅ ሳለ ፡ አንድ ልጅ ከሕዝቡ መኻል ተፈትልኮ በመሮጥ ወደ ዶን ኪኾቴ ቤት አመራ ። በቀጥታ ወደ ቤቱ ውስጥ ተንደርድሮ ገባና ፤ ለዶን ኪኾቴ የእኅት ልጅና ለቤት ሠራተኛዋ ፡ ዶን ኪኾቴ ተመልሶ የመጣ መሆኑንና ፤ ከደጃፋቸው አቅራቢያ የደረሰ መሆኑንም ጭምር ቁና ቁና እየተነፈሰ ነገራቸው ።

“ ምን ያህል እንደ ከሣና እንደ ገረጣ ባያችሁት ! ! የሣር ድርቆሽ ተጐዝጉዞበት ፤ በዚያ ላይ ለምለም ሣር ተነጥፎለት በትልቅ ሠረገላ ውስጥ ተኝቷል ። ሠረገላውም በበሬ የሚሳብ ነው ። ራሳችሁ ቶሎ ወጥታችሁ ልታዩት ትችላላችሁ ” አለ ልጁ ትንፋሽ እያጠረው ።

የእኅቱ ልጅና የቤት ሠራተኛው ወሬውን እንደ ሰሙ እንባቸውን ያፈስሱት ጀመር ።

“ ይህ ሁሉ ሊደርስበት የቻለው ፡ እነዚያን መጻሕፍት በማንበቡ ብቻ ነው ” እያለች የእኅቱ ልጅ እንባዋን ዘራችው ።

“ ይህ ሁሉ ከመምጣቱ በፊት እነዚያን መጻሕፍት ባጠፋናቸው ኖሮ እንዲህ ያለ ጉድ ባልደረሰ ነበር ” ትላለች የቤት ሠራተኛዋ እሷም እንባዋን እያፈሰሰች ።

ሠረገላው ከክብር መንገደኛው ጋር ታማኝ ዘቦቹን አስከትሎ ፤ በዝግታ አውራ ጐዳናውን ይዞ አዘቅዝቆ

ሲዳዝና የአገሬዉ ሕዝብ በአድናቆት እየተንጫጫ ሲዋርፍ ለጉድ ይታይ ነበር ።

የሚንጫጫውን ሕዝብ ለማየት አንዲት ሴት በድንገት ከአንድ ጐጆ ውስጥ እመር ብላ ስትወጣ ታየች ። ይህችም ሴት ፡ ‘ዩዋና’ የምትሰኘው የሳንቾ ፓንሳ ሚስት ኖራለች ።

እሷም ሳንቾን እንዳየች በደስታ ፈንድቃ ፡ “ እንኳን ደኅና ገባህ ሳንቾ ! ያስ ውድ አህያችን እንደ ምን ከርሟል ? ” ስትል ድምጿን ከፍ አድርጋ ጠየቀችው ።

“ አህያዉ ከጌታዉ ይልቅ ጤነኛ ነው ” ሲል ሳንቾ ድምፁን ጐላ አድርጎ መለሰላት ።

“ እንግዲያውስ ተመስገን አላለሁ ። የሆነ ሆኖ ለቤታችን ምን ይዘህልን መጣህ ? ለኔ የሚሆን ልብስና ለልጆቻችን ጫማና ምናምን አላመጣህልን ? ” ስትል ዩዋና ጠየቀች ።

“ የማፈቅርሽ ባለቤቴ ሆይ ! እውነቱን ለመናገር ከሆነ ከጠየቅሽኝ ነገሮች ሁሉ አንዱን እንኳን አላመጣሁላችሁም ” ሲል ሳንቾ በተሰባበረ ድምፁ መለሰላት ። “ ሆኖም በሚቀጥለው ጊዜ በምናደርገው ጉዞ ተመልሼ የአንዲት ደሴት ገዥ ልሆን ታይኛለሽ ” አላት ።

“ ይህንንስ ከልቤ ነው የምመኘው ፤ ለቤታችን በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው ። ነገር ግን ፡ ይህች ደሴት ያልካት ምንድን ናት ? ከዚህ ቀደም ደሴት ሲባል ሰምቼ አላውቅም ፤ ምን ዐይነት ዕቃ እንደ ሆነ ሊገባኝ አልቻለም ” አለች ዩዋና ወደ ሳንቾ በጣም እየተጠጋች ።

“ ሁሉም ነገር በጊዜው ይደርሳል ። ‘ ለአህያ ማር አይጥማትም ’ እንዲሉ ። የጠየቅሽኝ ምን ዐይነት ነገር

እንደሆኑ በቅርቡ ታገኚዋለሽ ። ለአንድ ጥሩር ለባሽ ፈረ ሰኛ ጋሻ ጃግሬ ሆኖ መጓዝን የመሰለ ቁም ነገር ለእንደኔ ያለ ታማኝ ሰው የሚገኝ አይመስለኝም ” አለ ሳንቾ በኩራት ።

“ ይህ ጉዳይ ከመሰለህ ደስ ይለኛል ” አለች ዩዋና ።

“ መስሎ መታየት ብቻ ሳይሆን ስለማውቀውም ጭምር ነው ። ስሚኝ ፣ ተራራ መውጣትን የመሰለ ልዩ ስፖርት አይገኝም ፤ ቋጥኝ ለቋጥኝ መዝለሉን ፣ ከዱን ውስጥ መሽሎክሎኩን ፣ ትላልቅ ቤተ—ግንብን መጎብኘትንና ፣ ቤሳ ቤስቲን ሳይዙ በየሆቴሉ ቤት መዝናናትን የመሰለ ዓለም ማግኘት ቀላል አይምሰልሽ ” ይላት ጀመር ሳንቾ ፓንሳ ።

በበሬ የሚሳበው ሠረገላ በአያሌ የመንደሩ ሰዎች ታጅቦ ፣ በዘበኞች እየተጠበቀ ከዶን ኪኾቴ መኖሪያ ቤት ደጃፍ ላይ ደረሰ ። የንስሐ አባትዬዉና ጸጉር አስ ተካካዩ ፣ ጠረኛውን ከተጋደመበት የግር ጉዝጓዝ ላይ በቀስታ ተንከባክበው ካነሡት በኋላ ፣ ወደ መኝታ ክፍሉ አስገቡት ። አፉን ዘግቶ ሰውነቱን አኮራምቶ ልክ እንደ ሕፃን ልጅ የሚያሳዝን ፍጡር ሆነ ። የቤት ሠራተኛዋና የእኅቱ ልጅ ልብሱን አወላልቀውለት በቀድሞው አል ጋው ላይ አጋደሙት ። በአልጋው ላይ ተንጋሎ ትክ ብሎ ቢመለከታቸውም ፣ ማንነታቸውን ለማወቅ ግን ተስኖ ታል ። መልካቸውና አጠቃላይ ቁመናቸው ፍጹም አዲስ ሆነበት ። ዶን ኪኾቴ የት እንደ ነበረና ፣ አሁንም የት እንዳለ ሊታሰበው አልቻለም ።

የንስሐ አባትዬዉ ለዶን ኪኾቴ የእኅት ልጅ ትእ ዛዝና መመሪያ ሰጠ ። እጅግ በጣም እንዲጠነቀቁለትና እንክብካቤም እንዲያደርጉለት መከራቸው ። “ በምንም

ዐይነት ቢሆን ካጠገቡ እንዳትለዩ ። ይህንን ባታደርጉ ለሦስተኛ ጊዜ በፈረሱ ያመልጣችሁና እንደ ልማዱ ለጀብዱ ሥራ ፍለጋ ይጠፋባችኋል ” አለ የንስሐ አባትዬው ።

የዚህ መልካም ሰው ጐረቤቶችና ዘመዶች አንድ በአንድ ወደየቤታቸው ተመልሰው ሔዱ ። ሳንች ፓንሳም አህያውን ይዞ የግል ጕጆው ወደ ምትገኝበት ኰመራ ። ዶን ኪኾቴ በገዛ ቤቱ ውስጥ የእምሮና የአካል ዕረፍት ማድረጉን ተያያዘው ።

ከጓደኞቹና ጐረቤቶቹ ጋር

ለአንድ፣ ወር ያህል ፣ ዶን ኪኾቴ ከእኅቱ ልጅና ከቤት ሠራተኛው በስተቀር ከማንም ጋር ሳይገናኝ ሰነበተ ። የንስሐ አባትዬውና ጸጉር አስተካካዩ ፣ በየዕለቱ እየመጡ ስለ ጤንነቱ ይጠይቁታል ። ይህም ሲሆን ጀግናው ጦረኛ እንዳያያቸው ጥንቃቄ እያደረጉ ነው—ምናልባት እንርሱን ካየ እንዳያገረሽበት በማሰብ ።

በመጨረሻም ፣ የዶን ኪኾቴ የእኅት ልጅ ጦረኛው ጤናው የተመለሰ ፣ አእምሮው የተረጋጋ መሆኑን ለንስሐ አባትዬውና ለጸጉር አስተካካዩ ገለጸችላቸው ። እነርሱም ሊጐበኙት መጡ ።

“ ገብተን ለመጠየቅ ደስታውን እንችለውም ” አለ ጸጉር አስተካካዩ ። ወዲያው ወደ መኝታ ክፍሉ ተያይዘው ገቡ ። ምስኪኑን ጀግና አልጋው ላይ ተቀምጠ አገኙት ። አረንጓዴ ሰደርያ ለብሶ ፣ ቀይ ኮፍያ ራሱ ላይ ደፍቷል ። ዐይኖቹ ብሩህ ፣ ድምፁ ጉልህ ነበር ። ገጹና መላ ሰውነቱ ገርጥቶና ጠውልጎ አፅም መስሏል ።

ዶን ኪኾቴ ቃሉቱን የጥንት ጓደኞቹን ለማግኘቱ
ተደሰተ ። አሊጋው አጠገብ ተቀመጡና ፤ ብዙ ዐይነት
ጨዋታ እያመጡ አወጉት ። በጭውውታቸው ውስጥ
ስለ ጥሩር-ለባሽ ፈረሰኝነትና ስለ ጀግንነት አንዲት ቃል
አልተነፈሱም ። ቢሆንም ፤ ጉዳዩ በመጨረሻ ላይ በእ
ርሱ በራሱ ይነሣ ጀመር ።

ዶን ኪኾቴ፣እንደበተ ርቱዕ በመሆን ወጉን እያጣ
ፈጠ ተረከላቸው ። ስለ ጥሩር-ለባሽ ፈረሰኞች ፣ ስለ ጭራ
ቆች ፣ ስለ ስመ ጥር ጀግኖች ፣ የንስሐ አባትዬው እንኳ
ቃል እንዳይተነፍስ ፋታ ነሥቶ ፣ ጣፋጭ ወጉን ያዥጎ
ደጉደው ጀመር ።

የንስሐ አባትዬውና ዘመዶቹ እጅግ በጣም አዘኑ ፤
አሁንም አእምሮው እንደ በፊቱ ወደዚያ ቃሳቅ ጭንቀት
ውስጥ ተመልሶ ለመግባቱ በሐዘን ልባቸው ተነካ ። በቅ
ርብ ጊዜ ወይም ሲመቻቸው ፣ ዶን ኪኾቴ ፈረሱን ጭኖ
እንደገና አዲስ የጀግና ገድል ሊፈጽም ዕቅድ እንዳለው
ተረዱ ። እና ፤ በመጨረሻው ተሰናብተውት ሲወጡ ሲሉ
የንሥሐ አባትዬው ለዶን ኪኾቴ የእኅት ልጅ የማስጠን
ቀቂያ ቃል በሹክሹክታ ነገራት ።

" ደኅና አድርገሽ ጠብቂው ። በዙሪያው ጸጥታ
ይስፈንበት ። ከቤት ወጥቶ የመሔድ ሐሳብ ጨርሶ እን
ዳይመጣበት ይሁን " አለ የንስሐ አባትዬው ።

ዶን ኪኾቴ ጉልበቱ ጠና ብሎ ፣ በቤት ውስጥ መዟ
ዟር ሲጀምር ፣ ሌሎች ጐረቤቶቹና ወዳጆቹ እየመጡ ይጠ
ይቁት ጀመር ። እያንዳንዱን እንግዳ ፣ ‘ እንኳን ደኅና
መጣችሁ ’ እያለ በአክብሮትና በደስታ ከመቀበል ጋር ፣
ስለ ጥሩር - ለባሽ ፈረሰኞች ወግና ውዳሴ ጥቂት እንኳ
ሳይናገር ፀልፎ አያውቅም ። ጉብኝዎቹ ግን ፣ አስቀድሞ

በንስሐ አባትየው ማስጠንቀቂያ ስለ ተሰማቸው ፣ ስለ አየር ልውጥ ፣ ስለ ዘመኑ መከር ፣ ስለ ሌላ ሌላ ጉዳይ አንሥተው ካጫወቱት በኋላ ፣ ተሰናብተውት ይወጣሉ ። በእንዲህ ዐይነት ሁኔታ ቀስ በቀስ ምስኪኑ ጦረኛ ጤንነቱ እየተሟላ ፣ ሰውነቱ እየጠነከረ በመሔዱ ደስታ ይሰማው ጀመር ።

አንድ ቀን ጥዋት የዶን ኪኾቴ በር በማን ይንኳኳል መሰላችሁ ! በሳንቾ ፓንሳ ! !

“ ጀግናውን ዶን ኪኾቴን ልጠይቀው ነው የመጣሁት ” አለ ሳንቾ ፓንሳ፤ የዶን ኪኾቴ የእኅት ልጅ በሩን ልትከፍትለት ።

እሷም በሩን ጥርቅም አድርጋ እንዳይገባ ከያዘች በኋላ ፣ « ማንንም መጠየቅ አትችልም » አለችው በሩን ወደ ውጭ እየገፋች ።

« ሒድ ከዚህ ! ይህ ሁሉ መንከራተት ዓለምን መዞርና መንገላታት የደረሰው በአንተ ከንቱ ግፊት እንጂ በሌላ ሰው አይደለም » አለች የዶን ኪኾቴ የቤት ሠራተኛ ደም ፍላት ይዟት ።

“ በጭራሽ እንደሱ አይደለም ! እኔ ነኝ በከንቱ ግፊት ተመርቼ የተንከራተትሁት እንጂ ፣ ጌታሽ አይደለም ። እንዲያውም እሱ ራሱ ነው ከቤቱና ከንብረቱ ሊፈናቅለኝ ፣ አንዲት ደሴት እሰጥሃለሁ ብሎ ያወጣኝ ፤ አሁንም ይቺን ደሴት በመጠባበቅ ላይ እገኛለሁ ” አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

“ ደሴት ! የምን ደሴት ? የሚበላ ነገር ከሆነ እንደ ሚያንቅህ ተስፋ አደርጋለሁ » አለች የዶን ኪኾቴ እኅት ልጅ ።

“ እዚህ ላይ ተሳስተሻል ! ደሴቶች አይበሉም ፤ ግዛት ይሆናሉ እንጂ ” አላት ሳንቾ ።

“ ምንም ይሁን ምንም አንተ እንደሆንክ እዚች ቤት አትገባም ። ሒድና የራስህን ቤት አስተዳድር ፤ መሬትህን እረስ ፤ እና ስለ ሰዎች ደሴትና መሬት እያሰብክ ራስህን አታስጨንቅ ። ላንተ ምንም አይረቡህምና በመዘላበድ ጊዜህን አታባክን ! ” አለች የዶን ኪኾቴ የእኅት ልጅ ።

የንስሐ አባትዬውና ጸጉር አስተካካዩ ፣ ዶን ኪኾቴን ጠይቀው ሲመለሱ ፣ በሳንቾና በልጅቷ መካል የተነሣውን መጠነኛ ውዝግብ ጥቂት ቆም ብለው አዳመጡ ። በተነሣውም ውዝግብ በጣም ተደነቁ ። እነሱም በሐሳብ ልጅቷን ለመርዳት በዝግጅት ላይ እንዳሉ ፣ ዶን ኪኾቴ ራሱ ወደ በሩ ሲመጣ ታየ ።

“ እንኳን ደኅና መጣህ ታማኙ ወዳጄ ” አለና ሳንቾ ፓንሳን ወደ ቤት እያስገባ ፣ በእኅቱ ልጅ ላይ ጮኸባት ።

“ ጕረቤታችን እንደገና ለዙረት ተነሥቶ ካልንገደ ታዘበኝ ፣ ብቻ እኛ ቀድመን አንድ ነገር ማድረግ አለብን ” አለ የንስሐ አባትየው ፣ ከጸጉር አስተካካዩ ጋር እንደ ቆሙ ፣ በሹክሹክታ ።

ዶን ኪኾቴ ጋሻ ጃግሬውን ወደ መኝታ ክፍሉ ካስገባው በኋላ ፣ በሩን ጥርቅም አድርጎ ዘጋው ። ሁለቱም ጕን ለጕን ተቀመጡና ፣ በጕዞአቸው ጊዜ ስለ ገጠማቸው የሕይወት ፈተናና ፣ በጀግንነት ስለ ተቀዳጁት ድል በሰፊው ያወጉ ጀመር ።

“ ምን ታስባለህ ወዳጄ ፣ ሳንቾ ! ወደ ጋሻ ጃግሬነት ሥራህ ትመለሳለህን ? ውዷ ባለቤትህስ ምን አለችህ ? ” ዶን ኪኾቴ ጠየቀ ።

“ እሷማ የምትለው ፤ ሰው ግትር መሆን የለበትም። እርግጠኛ መሆንም መልካም ነው ትላለች ። ይህም ፤ ‘ ከእጇ በጉንጯ ’ እንዳለችው ዝንጀሮ ሲሆን ፤ ነገ ሁለት ከሚሰጥህ ፤ ዛሬ አንዱን ያስጨብጥህ ማለት ነው ። ምንም እንኳ የሴት ምክር ባያዋጣም ፤ ‘ ምክሯን የናቀ ፤ ከችግር ላይ ወደቀ ’ የሚባለውን ያሳስበናል ” አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

“ እኔም የምለው ይኸንኑ ነው ። የዛሬው ንግግርህ ወርቅ ነው ፤ ነገር ግን ምን ለማለት ፈልገህ እንደሆን አል ገባኝም ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“ እንዲያ ጌታዬ ! የወር ቀለቤን አስበው ቢሰጡኝ ደስ ይለኛል ። ሌሎቹ ሽልማቶች በኋላ ሲመጡ ይችላሉ ፤ ወይም ጨርሶ ላይገኙ ይችላሉ ። ‘ በጅ የገባ ጥቂት ነገር ፤ በጅ ካልገባ ብዙ ይመረጣል ’ እንደሚባለው ማለት ነው ። ‘ ዶሮህ እንድትፈለፍል ፤ እንቁላሎች ላይ ትዋል ’ እን ደሚባለው ። ‘ የወሻ ጠብታ ኩሬ ይሆናል ’ ይባላልኮ ! ” አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

“ ብልህ ነህኮ ሳንቾ ! የተረቶችህን ቁም ነገር በሙሉ ተረድቼልሃለሁ ። ”

“ እውነትዎን ነው ። እና ፤ እኔም ስለማገኘው ነገር ቁርጤን ማወቅ አለብኝ ። ወደፊት ያቺን ደሴት የሚሰ ጡኝም ከሆነ ፤ ዛሬ ከማገኘው ደሞዝ ተቀናሽ ላደርግልዎ ፈቃደኛ ነኝ ። ”

“ ስለ ደሞዝህ ከነጣህ ፤ የጥሩር-ለባሽ ፈረሰኛነት ደንብ የሚፈቅድ ቢሆን ኖሮ ልከፍልህ ዝግጁ ነበርሁ ። ነገር ግን ባነበብኳቸው የጦረኞች ገድል ውስጥ አንዱም እንኳ ለጋሻ ጃግሬው ደሞዝ ሲከፍል የሚያወሳ አላጋጠመኝም ። የጦረኛ አሽከር የሚሰጠው ነገር ቢኖር ደሴት

ወይም የመሳሰለውን ሆኖ ፣ ታሪኩም በዚሁ ያከትማል ።”

“ ግን ምናልባት ደፄቷ ያልተገኘች እንደሆነስ ፣ ጌታዬ ! ” ሳንቾ ጠየቀ ።

“ እኔ በጀግኖች ሕግ የጸናሁና ሕጉንም አክባሪ ነኝ ። እኔን የሚገጥመኝን መልክምም ሆነ ክፉ ዕድል ፊት ጋራ ካልፈለግህ በል ደኅና ሁን ፤ ፈጣሪ ይርዳህ ። ካንተ የተሻለ ታማኝና ጠንቃቃ ጋሻ ጃግሬ ባገኝ እችላለሁ ፤ ያውም እንዳንተ ዘላባጅ ያልሆነ ” አለ ዶን ኪኾቴ ኰስተር ብሎ ።

ሳንቾን ድንጋጤ ልቡን ነካው ። እንዲህ ዐይነት መልስ ጨርሶ አልጠበቀም ነበር ። እንደ ሳንቾ አስተሳሰብ ከሆነ ፣ ዶን ኪኾቴ ያለሱ ድጋፍና ርዳታ አንዳችም ነገር የማያከናውን መስሎት ነበር ። ከመደንገጡ የተነሣ ምን ማድረግና ፣ ምን ማለት እንዳለበት መላ ቅጡ ጠፋው።

ልክ በዚያን ጊዜ በሩ ተንኳኳ ። በሩ እንደ ተከፈተ ፣ የዶን ኪኾቴ የቤት ሠራተኛና የእኅቱ ልጅ ፣ ሳምሶን ካራስኮ ከተባለው ጐበዝ ጋር ወደ ክፍሉ ገቡ ።

ይህ ወጣት ፣ ሳላማንካ ከተሰኘው ኮሌጅ ዲግሪውን አግኝቶ ገና ወደ አገሩ መመለሱ ነበር ። ሰውነቱ ይህን ያህል ግዙፍ ያለ ባይሆንም ፣ በመሣቅ ችሎታውና ቀልደኛነቱ የታወቀ ነው ። ዕድሜው ኻያ አራት ገደማ ደርሷል ። ፊቱ ክብ ፣ አፉ ሰፊ ሆኖ ፣ ዐይኖቹ ቁልጭልጭ የሚሉና ቀልደኛነቱን የሚያሳዩ ነበሩ ።

“ መቼም አንተ ምሁር እንደ መሆንህ መጠን ፣ የጀግንነት ሙያ እያለ ዳግመኛ ከቤት ወጥቶ እንዳይሔድ በደንብ አግባባው ” አለች የዶን ኪኾቴ የእኅት ልጅ በሩን ዐልፍ ሲሉ — በሹክሹክታ ።

ነገር ግን ፣ ሳምሶን ስፖርትና ቀልድ እንጂ ሌላ የሚወደው አልነበረም ። ተንደርድሮ ዶን ኪኾቴ እግር ሥር ተንበረከከና ፣ በውብ ቃላት እያወደሰ የድለላ ንግግሩን ያወርደው ጀመር ።

“አንተ የጦረኞች አበባ ! የመሣሪያዎች ጌታ ፣ የስፓኝ መመኪያ ! ለሦስተኛ ጊዜ ወደ ጀግንነት ሙያ እንዳትሠማራ የሚከላከሉህ ሁሉ ከከንቱ ምኞታቸው ጋር ይውደሙ ” አለ ድምፁን ከፍ አድርጎ ።

ፊቱን ወደ ዶን ኪኾቴ የቤት ሠራተኛ መለስ አደረገና ፣ “ ጀግናውን ልታስሩት አይገባም ፤ ምክንያቱም እዚህ ሥራ ፈት ሆኖ ሲቀመጥ ስንት ድሆች ረዳት ያጣሉ ! አባት እናት የሞቱባቸው ዘመድ አልባ ይሆናሉ ፤ ጭቁኖች እሚታደጋቸው ያጣሉ ፤ ዓለማችንም እንደ ታላቅ ጥሩር-ለባሽ ፈረሰኛ በማጣት ባዶ ትሆናለች ” አለ አሁንም በከፍተኛ ድምፅ ።

ለሳምሶን ንግግር የዶን ኪኾቴ የቤት ሠራተኛ ምንም መልስ መስጠት አልቻለችም ። አሁንም ሳምሶን ፊቱን ወደ ኪኾቴ መለሰና ፣

“ አንተ ባለ ግርማ ሞገስ ጀግና ! አንተ ፍርሃት የማይነካህ ጦረኛ ! ጉዞህን ቀጥል ! ታላቅነትህ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ ይናኝ ! ያንተን ምኞትና ፍላጎት ለማሟላት ካስፈለገ ፣ ወይም የምትሻው ርዳታ ካለ ፣ እነሆ ለማንኛውም ከጐንህ ሆኘ ላገለግልህ ዝግጁ ነኝ ። አዎን ላገለግልህ ቆርጬ ተነሥቻለሁ ። ታማኝ ጋሻ ጃግሬህና አሽከርህ ልሆንም ወስኛለሁ ” አለ ሳምሶን ። ከወዲያ ወዲህ እየተንጐራደደና እጆቹን እንደ ተዋናይ እያወናጨፈ ።

ዶን ኪኾቴ ልቡ ተነካ ። ወጣቱን እጁን ጐትቶ እቅፍ አደረገውና ፣ “ ወዳጄ ሆይ ! አይደረግም ! ሳምሶን ካራስኮን የመሰለ በቤተ መንግሥት ተወዳጅ ፣ የሳላማንካው-ት/ቤት ተወዳሽ ልዩ ስጦታውን ለእንዲህ ያለው የጋሻ ጃግሬነት ተግባር ማዋል የለበትም ። በበኩሌ እቃወማለሁ፣ በአገርህ ውስጥ ተቀምጠህ ለሲፓኝ ክብሯ ሁንላት ! እንዲሁም ለወላጆችህ ። ምንም እንኳን ሳንቾ ከእኔ ጋር ባለመሔድ ቢፈልግም ፣ የኔ ጋሻ ጃግሬ ለመሆንና ግልጋሎታቸውንም ሊያበረክቱልኝ በደስታ የሚጠባበቁ እያሌ ብቁ ሰዎች አሉ ” አለ ዶን ኪኾቴ ጕርደድ ጕርደድ እያለ ።

ይህን ንግግር እንደ ሰማ ሳንቾ ፓንሳ እንባ ፍንቅል አድርጎት ፣ “ ጌታዬ ሆይ ! ከአንተ ጋር እሔዳለሁ ! እሔዳለሁ ! ካንተ ተለይቼ ጨክኘ የምቀርበት አንጀት የለኝም ። ስለ ደሞዝ ጉዳይ አንሥቼ ከሆነ ሚስቴን ለማስደሰት ስል ብቻ የተናገርኩትን ነው ” እያለ ይንሰቀሰቅ ጀመር ። ሳንቾና ዶን ኪኾቴ ተቃቀፉና እንደ ቀድሞው ወዳጅነታቸውን ቀጠሉ ። በሳምሶን ካራስኮ ምክር መሠረት በሦስተኛው ቀን ለአዲስ የጀብዱ ሥራ ጉዞ እንዲጀምሩ ተወሰነ ።

የዶን ኪኾቴ የእኅት ልጅና የቤት ሠራተኛው በመረር ሐዘን ተንጫጩ ፤ ጸጕራቸውን ነጩ ፤ ፊታቸውን ቧጠጡ ። ተማጸኑ ፤ እንባቸውንም አንገፍገፉት ። የሆና ሆኖ የጀግናውን ውሳኔ ውጥን ሊለውጥ የሚችል ነገር ከቶ ሊገኝ አልቻለም ።

የንስሐ አባትየው ፣ ጸጕር አስተካካዩ ፣ ሌሎቹና ሌሎችም ሳምሶን ካራስኮን በድርጊቱ አወገዙት ። ሆኖም ከእነርሱ ይልቅ እርሱ ሁኔታውን ጠንቅቆ ተረድቶታል ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ፣ ሳንቾ ዱልሲኒያን በጭራሽ አይቷት አያውቅም ። ነገር ግን ፣ ከዚህ ቀደም ጌታው ደብዳቤ አድርስልኝ ብሎ ልኮት የነበረውን በማስታወስ የተገናኘ ለማስመሰል ነበር የዘባረቀው ።

አውራ ጐዳናውን ይዘው በዝግታ በመጓዝ ላይ እን ዳሉ ፣ አንድ ትልቅ ግንብ ቤት አጠገብ ደረሱ ። በጨረቃዋ ውጋጋን ሕንፃው በጣም ግዙፍ ፣ ረዝሞና ጠቁሮ ይታያቸው ጀመር ።

« ይኸውልህ ! የእመቤቴ ሆይ ዱልሲኒያ ቤተ መንግሥት ይህ ነው ። እኔም ለሌላት ውብ እመቤት ፣ መቼም ከእዚህ ያነሰ ቤተ መንግሥት ሊኖር አይችልም » አለና ጉዞውን ቀጠለ ።

«ተሳስተናል ፣ ሳንቾ ። ይህ የርሷ መኖሪያ ስላል ሆነ ፍለጋችንን መቀጠል አለብን ! » አለ ደከም ባለ ድምፅ ።

እስከ መንገዱ ማብቂያ ድረስ ጉዞአቸውን ቀጠሉ ። መለስ ቀለስ እያሉ በመንደር ውስጥ መንገዶች ፍለጋ ቸውን ቢቀጥሉም ፣ ቤተ መንግሥት የሚመስል መኖ ሪያ ሊያገኙ አልቻሉም ።

ሌሊቱ እየገፋ ፣ ብርሃን ከበስተምሥራቅ ቢፈነጥቅ ታየ ። ብርሃኑ እየፈካ አካባቢውን አደመቀው ። ሰማዩም ጥርት አለ ። ወፎች ከጐጆዎቻቸው ብቅ እያሉ ዝማሬ ያቸውን ማሰማት ጀመሩ ። ንጋት ወለል ብሎ ቅርፀ ገፅታው ታየ ።

አሁንም ከዚያም የከተማው ቤቶች በር ሲከፈት ይሰማል ። የልዩ ልዩ ድምፆች ኃይል የከተማውን ጸጥታ እየጣሰ ይሰማ ጀመር ። ሕዝቡም ሲንቀሳቀስ ይታያል ።

ጆግናዉ ጦረኛና ጋሻ ጃግሬዉ አውራ ጐዳናው ላይ ፈዘውና መዳፉ ጨፍቋቸው እንደ ቆሙ ፣ አንድ የባላገር ወጣት ሁለት በቅሎዎች እየነዳና ፣ የጆግናው ሮላንድን ታዋቂ መዝሙር እየዘመረ ፣ ወደ እነዶን ኪኾቴ መጣ ።

"እንደ ምን አደርክ፤ ታማኝ ወዳጄ ? ወደር የሌላትን ልዕልት ፣ የቶቦሶ እመቤት ፣ የዱልሲኒያ ሆይ ቤተ መንግሥት የት እንደሆነ እንድታሳየኝ እለምንሃለሁ" አለ ዶን ኪኾቴ በትሕትና ።

"ጌታዬ ሆይ! እኔ ለከተማው እንግዳ ነኝና ፣ አንድም ቤተ መንግሥት አላውቅም ። የከተማዉ ቄስ ገዘዝ እዚሁ ቤት ውስጥ ይኖራሉና ፣ እሳቸውን ጠይቋቸው ። ስለ ልዕልታትና ስለ ቤተ መንግሥታት ርሳቸው ይበልጥ ያውቃሉ" አለ ወጣቱ ባላገር ።

ይህን ተናግሮ በቅሎዎቹን ቀስቅሶ ዜማውን ከቀድሞ የበለጠ እያሰማ መንገዱን ቀጠለ ። ዶን ኪኾቴ ፈረሱ ሮሲናንቴ ላይ ጸጥ ብሎ ተቀምጦ የቄሱ ገበሬና ቤት ትክ ብሎ ከመመልከት በስተቀር ፣ ለጊዜው የሚያደርገው ነገር ጠፍቶታል ። ቄሶችና የሃይማኖት ሰዎች እምብዛም ስለማይደግፉና ፣ ለጆግና ገድል ቁብ ስለ ሌላቸው እኒህም ቄስ ፣ ይህ ጆግና ምንም እንኳ ታላቅ ቢሆንም እንደማይፈሩለት የታወቀ ነው ።

ጊዜው ረፈድ ፈድ ብሏል ። የፀሐይዋ ጨረር በዛፎች አናት ላይ ቁልቁል ይወርዳል ። ዐላፊ አግዳሚው በጐዳናው ላይ ይዋባል ። ሳንቾ ፓንሳ ይጨነቅ ጀመር ።

"ጌታዬ እዚህ በከንቱ ተቀምጠን ፣ ሰው ዐልኝ ባያየን ይሻላል ። እንዲያውም ቀስ ብለን ከዚህ ወጥተን አንድ ቁጥቋጦ ውስጥ ገብተን ከተደበቅን በኋላ ቆይቶ ለብ

ቻዬ ተመልሼ እመቤት ሆይ ዱልሲኒያን የመንደሩ ሰፈር ሳይቀር እፈልጋታለሁ ። እንዳገኘኋትም ፣ እርስዎ ጌታዬ በቅርብ እዚሁ እንደሚገኙና የሷን ትእዛዝ ለመፈጸም ዝግጁ መሆንዎንም ጭምር ገልጨ እነግራታለሁ ። ይህ ደግሞ በርግጥ እርስዎን ሊመቀበል ይበልጥ ዝግጁ ያደርጋታል ” አለ ሳንቾ ።

« ውድ ሳንቾ ! መቼም አንተ ዘወትር ብልህ መሆንህ የታወቀ ነው ። አንድ ሺህ ዐረፍተ ነገሮች በጥቂት ቃላት ገልጸሃልና ፣ እኔም ልክ አንተ እንዳልከው ልፈጽም ዝግጁ ነኝ ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

ብዙ ጊዜ ሳያባክኑ እንስሶቻቸውን አዘጋጁና ከከተ ሙማው ሁለት ኪሎ ሜትር ያህል ወጣ ብለው ወደ አንድ ቁጥቋጦ ደረሱ ። ዶን ኪኾቴ ትእዛዝ ከሰጠ በኋላ ፣ በቁ ጥቋጦዎቹ ውስጥ ተሸሽጐ ሲቆይ ፣ ሳንቾ ፓንሳ ግን ፣ ዱልሲኒያ የምትገኝበትን ሥፍራ አስሶ ለመመለስ ገሠ ገሠ ።

“ጠንክር ጠና በል ጌታዬ! አፍታ እንኳ ሳልቆይ እመለሳለሁ ። ጥንቸል ሳንጠብቃት ነው ከጫካው ውስጥ ውልብ የምትለውና እኔም ፈጥኜ አደርሳለሁ ። ‘ልብ ሙት ፣ መልከም ቆንጆን አያገኛት ! ይባል የለ ” አለ ሳንቾ ።

“ሳንቾ ! ምሳሌዎችን ጠቅሶ የመናገር ልዩ ስጦታ አለህ ” ብሎ ዶን ኪኾቴ ንግግሩን ሳይጨርስ ፣ ሳንቾ ፓንሳ ከመቅጽበት አህያው ላይ ወጥቶ ወደ ከተማዋ ተፈ ተለከ ።

ሆኖም ሳንቾ ፓንሳ ብዙ አልተጓዘም ። እንዲቅ ተራራ ግርጌ ሲደርስ ቆም አለና ወደ ኋላ ተመለከተ ። ከጌታው መራቁን እንዳወቀ ፣ እመንገዱ አጠገብ ከሚ

ገኘው ዛፍ ጥላ ሥር ዐረፍ አልና ብቻውን መቀባጠር ጀመረ.....

‘ ወዳጄ ሳንቾ ! ወዴት ትሔዳለህ ? በቅሎ ፍለጋ ነው የምትዘዋወረው ? ’ ‘አይደለም ። በቅሎ አልሻም ።’...

‘ ታዲያን ምን ታደርጋለህ?’

‘‘የቆንጆዎች ቆንጆ የሆነች ልዕልት በመፈለግ ላይ ነኝ ።’

‘ የት የምታገኛት ይመስልሃል ? ’

‘ የት? ምነው ? በታላቁ የቶቦሶ ከተማ ነዋ ! ብቻ መርፌ ገለባ ክምር ውስጥ እንደ መፈለግ ይቈጠራል ።’

‘ ታዲያ እንዲህ አድካሚ መሆኑን ስታውቅ ለምን አስቀድመህ ፍለጋ ጀመርክ ? ’

‘ ለምን ትደክማለህ ? የምደክመውማ ዕብዱ ጌታዬን ለማስደሰት እንደሆነ አይጠረጠርም ። ግን ዕብደኑቱ ከታወቀና ወፍጮ ቤቶችን በጭራቅ የሚመስል ከሆነ ማንኛዋንም የባላገር ልጃገረድ ጉትቶ ‘እመቤት ሆይ ዱል ሲኒያ ማለት ይህች ናት’ ብሎ ማሳመን ከባድ አይሆንም። ’

‘ እውነትም ከባድ አይደለም ’

‘ እኔም ልክ ይህንኑ ነው የማደርገው ! ከዚህ እስ ቸጋሪ ሥራ ለመላቀቅ ያሁኑ ሐሳብ ቀላል ዘዴ ይመስ ለኛል ። ’

ጥላው ተስማሚ ነበርና ዘና ማለት ሲጀምር ፡ በአቀ ፋዳጡ ውስጥ እጭቆት የነበረው ስንቅ ትውስ አለው ። ሳንቾ ጥስቅ አድርጎ ቁርሱን ከበላ በኋላ ፡ ጋደም እንዳለ እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ስለ ወሰደው ከማግሽ ቀን በላይ ተኛ ።

በመጨረሻ ፣ ሰውነቱን አፍታቶና ተደስቶ ከእንቅ ልፉ ነቃና ፣ 'የዱልሲኒያን ቤተ መንግሥት ፍለጋ በቶ ሎ ከተማ ከመንከራተት ይልቅ ፣ እንዲህ ወፍራም እን ቅልፍ ለጥጦ መተኛት ይሻላል !' አለ ።

አህያዉ ላይ ወጥቶ ቂልቂል ጉዳናውን ሲያያዝ ፣ ሦስት የባላገር ልጃገረዶች ከከተማው ሲወጡ ተመለ ከተ ። ልጃገረዶቹም መልከ ጥፉዎች ከመሆናቸው በላይ ፣ አይኖፋፍ ጭምርም ናቸው ። እያንዳንዳቸው በየአህያ ቻቸው ተቀምጠው በዝግታ ነበር የሚጓዙት ።

ሳንቾ ደቂቃ ሳይቆይ ፣ አህያውን እዚያ ጌታው ወደ ሚገኝበት ሥፍራ ይጋልብ ጀመር ። ጌታውም ሳንቾን እንዳየ ፣ " ወዳጄ ሳንቾ ምን የሚያስደስት የምሥራች ይዘህ መጣህ ? የዛሬውን ቀን በደስታ ነው ወይስ በሐዘን የምናስታውሰው ? » አለ ጦረኛዉ ፣ የሳንቾን መልስ በጉጉት እየጠበቀ ።

" በደስታ እናስታውሰው ጌታዬ ! ! እመቤት ዱል ሲኒያ ከሁለት ደንገጡሮቿ ጋር ሆና ከጌታዩ ጋር ልትገናኝ በመምጣት ላይ ነች ። እንዲያውም እዚህ አጠገባችን ደርሳለች ። ስለዚህ ፣ ፈረስዎ ፈረስዎ ሮሲናንቴ ላይ ይውጡና ወደ መንገዱ ብቅ በማለት ፣ ሊቀበሏት እንደ ተዘጋጁ መስለው መታየት አለብዎ ። መምጣቷንም በዐይን ማየት ይችላሉ ። "

" ይህን ወሬ ጨርሶ አላምንም ሳንቾ ። ' በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ' እንዲሉ ፣ በሐዘኔ ላይ ሌላ የማታለያ ቃል አትንገረኝ ። "

" ጌታዬ እኔ እርስዎን ላታልል ? ለምን ብዬ ነው የምጫወትብዎ ? ይምጡ ይከተሉኝና ፣ ልዕልቷንም ስት

መጣ ያይዋታል ። እርሷና ደንገጡሮቿ እንደ ወርቅ የሚያንጸባርቁ ፡ ሁሉም ዕንቁዎች ፡ ሁሉም አልማዞች ፡ ሁሉም የሚንተገተጉ ፈርጦች ናቸው ። እነሱን የሚስተካከል ቆንጆ በመላው ስፓኝ ታይቶ አያውቅም ። »

“እንግዲያውስ ፈጠን እንበል ፡ ሳንቾ ” አለና ዶን ኪኾቴ ባልተለመደ ፍጥነት ፈረሱ ላይ ፊጥ አለ ። “ለቸር ወሬህ እሸልምሃለው ። ለዚህም ቃል እገባለሁ ። ከሚቀጥለው የጀብዱ ሥራችን የሚገኘው ከፍተኛ የምርኮ ውጤት በሙሉ ላንተ ይሆናል ። ያም የማይበቃህ ከሆነ እቤት ያሉኝን ሦስት ውርንጭላዎች እጨምርልሃለሁ ። ”

“ውርንጭላዎቹን ባገኝ ለደስታዬ ወሰን የለውም ጌታዬ ። ለችሮታዎ ምስጋናዬ የላቀ ነው ። የምርኮ ዕቃዎቹን በሚመለከት ግን ስለሚያንሱኝ ይሆን ያህል አል ጨነቅባቸውም ” አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

ከሸለቆው ፈጥነው ወጡና አውራ ጐዳናውን ዘለቀው ከጋራው አፋፍ ላይ ብቅ አሉ ። ቁልቁል ወደ ከተማው ሲመለከቱ ፡ ሦስት የባላገር ልጃገረዶች በአህዮቻቸው ተቀምጠው ሲያዘግሙ ተመለከቱ ።

የዶን ኪኾቴ ገጽ ልውጥውጥ አለና ፡ ልቡ በሐዘን ተሰበረ ። ግራና ቀኝ እየተዘዋወረ ፡ መለስ ቀለስ እያለ ቃኘ ።

“ የት አለች ዱልሲኒያ ፡ ሳንቾ ? ከከተማው ወጥታ ለመምጣቷ ርግጠኛ ነህን ? ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“ምነው ጌታዬ? ዐይንዎን ምን ነካው? ከተዋቡትና ከሚያማምሩት ደንገጡሮች ጋር እዚህ አጠገባችን እንዷለች እንዴት ማየት ተሳነዎ ? ”

“ሦስት የባላገር ልጃገረዶች በሦስት የኮሰመኑ አህ
ዮቹ ላይ ተቀምጠው ይታዩኛል እንጂ ፡ አንተ እንደም
ትለው አይደለም ።”

“ እንዴ ! እንዴ ! ልዕልቷን እንዴት አድርገው ከአ
ንዲት ወጭማዳ የባላገር ልጃገረድ ጋር ያመሳስሏታል?
ቆንጆ የኮርቻ ፈረስ ከደቃቃ አህያ እንዴት መለየት አቃ
ተዎት ?”

“እውነት ለመናገር ካስፈለገ ፡ ሦስት ኮስማና አህ
ዮች ፡ ፀይናፋር የባላገር ልጃገረዶች ተሸክመው ከሚታ
የኝ በስተቀር ሌላ ምንም ነገር የለም ። ወደ እኛ በመም
ጣት ላይ መሆናቸው በግልጽ ይታየኛል ፤ ነገር ግን ልዕ
ልቴ የት አለች ?”

“ጌታዬ ! ጌታዬ ለካንስ እንዴት ያለ ዕውር ኖረ
ዋል ! የገጠር ልጃገረድ ያሏት ጨርሶ አትታይም ። ልዕ
ልቲቷን ነውኮ እርስዎ የሚያዩት ። እሷም እነሆ በየደ
ቂቃው እየቀረበችን ነው ። እኛም ፈጠን ብለን ቀር
በን እናነጋግራት” አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

ሳንቾ ይህን ተናግሮ ፡ አህያውን ኮረኮረና ከኮረብ
ታው አፋፍ ተንሥቶ ቁልቁል ሲጋልብ ታየ ። እንደ ደረ
ሰም ከአህያው ላይ ዱብ ብሎ ፡ ከልጃገረዶቹ ፊት ለፊት
አመኻኟ መንገዱ ላይ ቆመ ። ከሦስቱም ተንጋና ቀውላላ
ከሆነችው ልጃገረድ ፊት ሔዶ ተንቻረ ። ባርኔጣውን አወ
ለቀና በጉልበቱ ተንበረከከ ።

“የቆንጆዎች ቆንጆ የሆንሽው ንግሥትና ልዕልት
ሆይ ልመናዬን ስሚኝ” በማለት ንግግሩን ጀመረ ።
“የልዕልትነትሽ መልካም ፈቃድና ክብር ታክሎበት ፤ የፍ
ቅርሽ ምርኮኛ ሆኖ አንቺን በመፈለግ ላይ የሚገኘው ጀግ

ናዉ ጦረኛ ፣ እነሆ ቀርቧልና ተቀበይው ። እኔም ሳንቾ ፓንሳ የጀግናው ጋሻ ጃግሬ ስሆን ፣ እሱም እንቺን በመፈለግ የተንገላታው ጦረኛ ዶን ኪኾቴ ዴ ላ ማንቻ ይባላል” አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

በዚህን ጊዜ ዶን ኪኾቴ ከፈረሱ ላይ ወርዶ ፣ ከመንገዱ መኻል ተንበረከከ ። ይህች መልከ‑ጥፉ የባላገር ሴት እመቤት ሆይ ዱልሲኒያ ናት ብሎ ማመን አልቻለም ። ምክንያቱም ይህች የባላገር ሴት አፍንጫዋ ደፍጣጣ ፣ ጉንጮችዋ ያበጡ ፣ በጸባይም ሆነ በአጠቃላይ ሁኔታዋ የማትማርክ ሆንችበት ። ቢሆንም ፣ አስማተኞች ጸባይዋንና መልኳን ቢለውጡባት እንጂ ፣ እሷስ ቆንጆ ነበረች ብሎ ያስብ ጀመር ።

“ከመንገዳችን ላይ ወግዱ! አቤታችን ለመድረስ ስለምንቸኩል መንገዱን ልቀቁልን” ቢሉም ልጃገረዶቹ አህዮች በሚያልፉበት መንገድ ላይ እንደ ተንበረከከ ሳይነሣ ቀረ ። “ከዓለሙ ሁሉ ውብ የሆንሽው እመቤት ሆይ! ይህ ሁሉ ልመና ልብሽን አያራራውምን? ያውልሽ ያንን ተመልከቺ! የጦረኞች ጦረኛ ፣ የወንዶች ወንድ የሆነው ጀግና ሳንቺ የሚገባሽን ክብርና ሰላምታ በማቅረብ ላይ ነው” አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

“ሐይዶይ መላ‑ቅጥ የሌለው ቅብጥርጥር ንግግሩን ስሚልኝ!” አለች አንዷ ልጃገረድ ለጓደኛዋ ።

“መንገዱን ልቀቅልን!” ብላ ጮኸች ፣ ረዥሟ ልጃገረድ ።

“እውነቷን ነው ! መንገዱን ልቀቅልንና እንሒድበት” አምባረቀች ሦስተኛዋ ።

እንዲህ እንዲህ እያሉ አህዮቻቸውን ገረፉና በአን ድነት ፈጥነው በዘዴ እነ ሳንቾ ፓንሳን ፀለፏቸውና ሽምጥ ጋልበው አቧራውን እያነሡ ሽቅብ ዳገቱን ወጡ ።

ዶን ኪኾቴ ከተንበረከከበት ተነሥቶ ፥ ልጃገረዶቹ ወደ መጡበት አቅጣጫ ይመለከት ጀመር ። ከዐይኑ ርቀው ወደ ሌላ አቅጣጫ እስኪታጠፉ ድረስ ዶንኪኾ ቴ በቅሬታ ተውጦ ይመለከታቸው ነበር ። ከዚያም ወደ ጋሻ ጃግሬው ፊቱን መልስ አደረገና ፥ "ሳንቾ ይህ ነገር የምን ይመስልሃል? እኒህ አስማተኞች በዓለም የተረገሙ ፍጡ ራን አይመስሉህም? ውዷ ዱልሲኔያን ወደ አንድ ቀርፋፋ የባላገር ልጅ በመለወጣቸው እንኳ የረኩ አልመሰለ ኝም ። መዓዛ የተመላበትን ጣፋጭ ጽጌ ረዳዊ ሽታዋን ገፈዋታል ። በአጠገባችን ስታልፍ የነጭ ሽንኩርት ሽታ እንዳወደኝ ተሰምቶኛል ። የሽታው ኃይል አፍንጫዬን ዝግት አድርጎት ነበር" አለው ።

"ጉድ ነው የእኒያ አስማተኞች ሥራ! ማናቸውንም ክፋት ከመሥራት አይመለሱም ማለት ነው ። ምነው ሁሉም በገመድ እንደ ቋንጣ ተሰቅለውና ደርቀው ባየ ኋቸው!" አለ ሳንቾ ።

"ወይ ነዶ! ግድ የለም ። በፊትም ተናግሬአለሁ ። አሁንም ቢሆን ሺህ ጊዜ የምናገረው ጉዳይ ነው ። በዓ ለም ያልታደልኩ ከንቱ ፍጡር እኔ ነኝ"! አለና ክፉኛ አዘነ ፥ ዶን ኪኾቴ ።

ሮሲናንቴ ላይ ወጥቶ ፥ በሐዘን ልቡ ተሰብሮ ፥ በጸ ጥታ ረዥም ጉዞውን ቀጠለ ። ወዴት እንደሚሔድ ሳያ ልም ከተማውን አቋርጦ ፥ አቧራማ በሆነው አውራ ጎዳና በኩል መንገዱን ተያያዘው ። ሳንቾ ፓንሳ ከኋላ ሆኖ ፥ ጌታውን ተከተለ ።

ከተጓዥ ትርዒተኞች ጋር

ከጥቂት ቀናት በኋላ ፣ ዶን ኪኾቴ በዕድለ - ቢስ ኑቱ እያማረረ ጉዞውን በመቀጠል ላይ እንዳለ ፣ድንገት አንድ ትልቅ ሠረገላ ልዩ የሆኑ ተጓዥ ሰዎች አጭቆ ወደ እርሱ አቅጣጫ ሲመጣ ተገናኘ ።

የሠረገላው ነጂ አለባበሱ ያልተለመደ ዐይነት ሆኖ በእግሩ ከፈረሶቹ ጐን ጐን ነበር ፣ የሚራመደው ። ኮትና ሱሪው በደማቁ ቀለማ- ቀለማት ያሸበረቀ ሆኖ ፣ ፈርጥ በሚመስሉ ቁልፎች የተዋበ ነው ። በራሱ ላይ ሁለት ቀንዶች ያሉት ቆብ ደፍቶ ፣ ኮቱም ባለ ጅራታም ጌጥ ነበር ።

"ይኸስ አንድ እኩይ ጋኔን ይመስላል" በማለት ሳንቾ ፓንሳ ለጌታው በሹክሹክታ ነገረው ። በሠረገላዉ ውስጥ ጣዕረ-ሞት የመሰለ ፍጡር ተቀምጧል ። ከጣረ ሞቱ አጠገብ መልአክ የመሰለ ነገር ረዣዥምና ፣ ነጫጭ ክንፎቹን አጣጥፎ ቆሟል ። በአንደኛዉ ጐን በኩል የወርቅ ዘውድ ደፍቶ ንጉሥ ተቀምጧል ። ከእነዚሁ በስ ተጀርባ ፣ ቀስት የያዘ አንድ ሰው ቆሟል ። ከእርሱ አጠ ገብ ፣ አንድ ጦረኛ ጥሩሩን የለበሰ በቁር ፋንታ ለስላሳ ባርኔጣ የደፋ ይገኛል ። ሠረገላውን ከኋላ በእግር አጅቦ አንድ ተጫዋች (ኮሚክ) ባርኔጣ ደፍቶ ደወሎች ይዞ ይከተላል ። ከእዚሁ ተጫዋች ጋር አራት ወይም ሦስት ሰዎች በልዩና በደማቅ ልብሶች አሸብርቀው ይከተላሉ ።

ጦረኛዉም ሆነ ጋሻ ጃግሬዉ እንዲህ ዐይነት ልዩ ተጓገዦች አይተው አያውቁ ነበርና ፤ ዶን ኪኾቴ በአድናቆት ፈዝዞ ቆመና ፤ ሰዎቹን በእዚያ ብቸኛ ሥፍራ በማግኘቱ ይገረም ጀመር ። ሳንቾ ፓንሳ ግን ፤ እጅግ በጣም ፈርቶ ነበር ። ምክንያቱም ጌታው ዘወትር የሚያወራለት አስማተኞች እኚህ መሆን አለባቸው በማለት ያለ ጥርጥር አምኗልና ።

ትንሽ እንደ ቆዩ ፤ የዶን ኪኾቴ ገጽ ብሩህ ይሆን ጀመር ፤ ድንገት የጀግንነት ወኔና አዲስ የጀብዱ ሥራ ሐሳብ ብልጭ አለበት ። ሮሲናንቴን ወደ ፊት እንዲሔድ ኮረኮረና ፤

“ምናልባት ይህ የዛሬው የጀብዱ ሥራችን ከሁሉም የላቀና ልዩ ይሆናል” አለው ሳንቾ ፓንሳን ። ወደ እርሱ አቅጣጫ በሚጕረፉት ሰዎች እንዲያ እመኻል መንገድ ላይ ተገትሮ ፤ “እናንተ ጋሪ ነጂዎችና ባለሠረገላዎች ማንም ሁኑ ማንም ባላችሁበት ቁሙ! እዚያው ቁሙና ለጥያቄዬ እጥጋቢ መልስ ስጡኝ ። ለመሆኑ እናንተ ማናችሁ ? ከወዴት ነው የምትመጡት ? ወዴትስ ነው የምትጓዙት? ሥራችሁስ ምንድነው?”

ሠረገላ ነጂው ጋሪውን ድንገት ቀጥ አድርጎ አቆመና ፤ ይኸን እንግዳ አለባበስ የሚታይበትን ሊፈታተናቸው ከፊታቸው የተገተረውን ፈረሰኛ በመገረም አስተዋለው ።

“ጌታዉ . . . . .እኛ የአንድ ተጓዥ ተጫዋች ቡድን አባላት ነን ። ከዚያ ማዶ ተራራ ባሻገር ካለው ከተማ መምጣታችን ነው ። እዚያም ፤ ‘የሞት ዳንስ’ የተሰኘውን አሠቃቂ ድራማ ስናሳይ ሰንብተን ፤ አሁን ጨርሰን መሔዳችን ነው ። ዛሬ ከሰዓት በኋላ ፤ ይህንኑ ጨዋታ ከፊታችን ከሚገኘው ከተማ ልናሳይ ተዘጋጅተናል ። ይፀ

ጨዋታ የማሳያ ልብሳችን ሲሆን ፡ በማውለቅና በጣም ልቅ ጊዜአችንን ላለማባከን ብለን ነው ፡ ለብሰን የምንኀዘው ። ”

“ምንም እንኳ ልዩ ዐይነት ነገር መስለህ ብትታይም ፡ አነጋገርህ የታማኝ ሰው ይመስላል” አሉ ዶን ኪኾቴ።

“በበኩሌ የዲያብሎስን ሚና ፡ ማለት ተግባር ወክዬና መስዬ ነው የምጫወተው ። እና ከሁሉም ተጫዋች የላቀው ድርሻ የኔ መሆኑን የምታውቀው ነው ። ሠረገላው ውስጥ ያለው ወጣት እንደ ሞት ሲመስል ፡ አጠገቡ የቆመው ደሞ እንደ መልአክ ሆኖ ይጫወታል ። በጨዋታው ውስጥ ንጉሥ አለ ፤ ወታደር አለ ፤ ባጠቃላይ ከሠረገላው በስተጀርባ ያሉትን አጃቢዎች ሁሉ ማየት ይችላሉ ” አለ በተዋናይ እንቅስቃሴ ።

“መልካም ሰዎች ስለ ሆናችሁ በበኩሌ መልካሙን እምኝላችኋለሁ ። ሠረገላችሁን ንዱና ጨዋታችሁንም ቀጥሉ ። የምረዳችሁ ነገር ካለ ደስታውን አልችለውም ። እኔም በሕፃንነቴ የትያትር ጥበብ ጨዋታ በጣም እወድ ነበር ” አሉ ዶን ኪኾቴ ከተጉተረበት መኻል መንገድ ገለል እያሉ ።

በዚህን ጊዜ ‘ኮሚኩ ሰውዬ’ ከሠረገላው ፊት ለፊት ምን እንደሚደረግ ለማወቅ ጥምልምል እያለና እያቃጨለ መጣ ፤ ብዙ ትናንሽ ቃጭሎች በኩቱ ላይ ተንጠልጥለዋል ። አንድ ረዥም ዕንጨት ላይ ሦስት ፊኛዎች ታስረዋል ። ፊኛዎቹን እያውለበለበ አስገራሚ እንቅስቃሴዎች ያሳይ ጀመር ።

የመጀመሪያው ጨዋታው ፊኛዎቹን ከሮሲናንቴ አፍንጫ ጋር ማጋጨትና ማውለብለብ ነበር ። ይህን ያደረገበት ምክንያት ምስኪኑን ሮሲናንቴን እንደ ነብር አድርጐ ወደ

ፊት እመር እመር እያለ የተሻለ ግልቢያ እንዲያሳይ ነበር ። ሮሲናንቴ ግን ፣ ድንብሮ ከጌታዉ ልጓሙን አሸንፎ ወደ ሜዳው ፈረጠጠ ።

ሳንቾ ፣ ዶን ኪኾቴ ከፈረሱ ላይ ወድቆ ከባድ አደጋ ይደርስበት ይሆናል በማለት ይጨነቅ ጀመር ። ከአህያው ላይ ወርዶ ፈረሱን ለማረጋጋት ሩጫውን ተያያዘው ። ቢቻለው ፈረሱን ለመያዝ ፣ ካልሆነም ጌታውን እንዳይጥልበት ፍጥነቱን ለማስቀነስ ነበር ፣ የሩጫው ዓላማ ። ሆኖም መቶ ሜትር ያህል እንኳ ሩጦ ሳይደርስባቸው ፣ ፈረሱና የፈረሱ ጌታ አብረው ወድቀው ከአቧራው ውስጥ ሲንከባለሉ አገኛቸው ።

ኮሚኩ ሰውዬ ፣ ሳንቾ ከአህያዉ ላይ ወርዶ ጌታውን ለመርዳት መሮጡን ሲረዳ ፣ እሱም ተንደርድሮ ግራሟ ላይ ጉብ አለ ። የያዘውንም ፊኛ በአህያዉ ጀሮ አካባቢ ማስጮኽ ሲጀምር ፣ ግራሚም እጅግ ከመፍራቱ የተነሣ ደንብሮ ጨዋታው ወደሚታይበት ከተማ ኮሚኩን ተሸክሞ ከነፈ ።

ሳንቾ ታንሳ የአህያውን መፈርጠጥ አይቶ የሚያደርገው ነገር ጠፋው ። ጌታውን ይረዳ ወይስ ግራሚ አህያውን ለማስጣል ኮሚኩን ይከተል? ከወዲያ ወዲህ ዐይኖቹን እያቁለጨለጨ ግራ ተጋባ ። በእጥሩ ላይ ዘሎ ገባ ፤ ወዲያው ተመልሶ ወጣ ። በመጨረሻም ጠረኛ ጌታውን ለመርዳት ፈጥኖ ወደ ዶን ኪኾቴ ዘንድ ሔዶና ደጋግሞ አነሣው ።

"ጌታዬ ሆይ ! አንዱ ከይሲ ተወዳጁ ግሪሚዬን ይዞብኝ ነጉደ ” አለ ሳንቾ ።

"የምን ከይሲ ? ” ዶን ኪኾቴ ጠየቀ ።

"እንዴ ! ያ ፊኛዎች ያሸከረክር የነበረው ነዋ !”

"ስለ አህያህ መወሰድ ምንም አትዘን ። እኔ ኮሚኩ እንስላውን እንዲመልስ አደርጋለሁና ፡ አንተ ብቻ ተከተለኝ ።"

" ጌታዬ ባልከተልዎ ይሻላል ። ለማንኛውም ጉዳይ መቸኮል አያስፈልግም ። እንዲያውም ኮሚኩ አህያዉን ጥሎልኝ ወደ ሥራው እንደሚሔድ ይታየኛል ።"

ሳንቾ የተናገረው በመጨረሻ እውነት ሆነ ። አህያዉ መንገድ ላይ ኮሚኩን ስውዬ ከመሬት ላይ ወቅቶ ታል ። ኮሚኩ ስውዬም ምንም ጉዳት ሳይደርስበት ከወደቀበት ተነሥቶ ጉዞውን ወደ ከተማ ቀጥሏል ። አህያውም ከተንጋለለበት ተነሥቶ አካባቢውን ከቃኘ በኋላ በዝግታ ወደ ጌታው ወደ ሳንቾ ዘንድ ተመለሰ ።

" አንተ ዕድለኛ ነህ ። እኔ ግን ማንነቴን ለእኒህ ሰዎች ከማሳወቅ አልቦዝንም " አለ ዶን ኪኾቴ ።

ዶን ኪኾቴም ከሳንቾ ምክር ወጥቶ በግልቢያ ሠረገላውን ተከተለና ፤ "አቁም ! አቁም ብያለሁ ! እናንት ጽጌረዳ የምትመስሉ ቆንጆዎች ባላችሁበት ቁሙ ! መንገደኞችንና ባይታዋሮችን ስታገኙ ፍጹም ትሑትና ስላማዊ እንድትሆኑ ትምህርት እሰጣችኋለሁ " እያለ ዶን ኪኾቴ ድምፁን ከፍ አድርጎ ይናገር ጀመር ።

ተጓዥ ተጫዋቾቹ ሠረገላቸውን አቆሙ ። ምናልባት ግጭት ቢነሣ ራሳቸውን ለመከላከልና ካስፈለገም ዶን ኪኾቴን ለመውጋር ድንጋይ ለቃቅመው ጠበቁት ። ዶን ኪኾቴም ሁኔታቸውን አይቶ የፈረሱን ፍጥነት ቀነሰና ፣ እኒህ ፍርሃት የማይነካካቸውን ተጓዥ ተጫዋቾች እንዴት አድርጎ እንደሚገጥማቸው ያወጣ ያወርድ ጀመር ። ጦሩን ወደ ጠላቶቹ ቀስሮ ሁሉንም በአንድነት ወግቶና ቀስፎ

ሊያጠቃ መነሣቱን ሳንቾ ተረዳና ከመቅጽበት እጁን ለቀም አደረገው ።

“ስለ ፈጠረዎ ይሁንብዎና ጌታዬ ይንገሩኝ—አበዱ እንዴ ? ወይስ ጤነኛ ነዎት ? እኒህ ሰዎችኮ ዘፋኞች ናቸው ! ከመኻከላቸው አንድም ጦረኛ ስለሌለ እባክዎን ምክሬን ይቀበሉና ይመለሱ ” አለ ሳንቾ ፓንሳ የጌታውን ጦር አጥብቆ እንደ ያዘ ።

“እውነትክን ነው ! ያልከው ሁሉ እውነት ነው ፤ ከእነርሱ ጋር መፋለም ለክብሬ የማይበጅ መሆኑን ተገንዝበህ ስለ ገላገልከኝ ፡ የጋሻ ጃግሬነት ተግባርህን ተወጥተሃልና ተባረክ ። እንደ ወጉማ ቢሆን እኔ መፋለም ያለብኝ እንቻዬ ከሆነ ጦረኛ ጋር ብቻ መሆን ነበረበት እንጂ ፡ ከማንም ኩታራ መንገደኛ ጋር አልነበረም ። ከተጫዋቾቹ መፋለም ያለብህ አንተ ነህ ። ተግባርህ ስለሆነ ግጥሚያውን አሁኑኑ ቀጥል ። እኔ ግን እዚሁ ቁሜ በተቻለኝ መጠን ምክሬን እለግስሃለሁ ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“በላሰቡልኝ በጣም አመሰግንዎታለሁ ። ግጥሚያው እኔን ስለማይመለከተኝ አላደርገውም ። ይህንንም በታላቅ አክብሮት እየገለጽኩልዎ ፡ ለሰዎቹም ቢሆን ይቅርታ አድርጌላቸዋለሁ ። እንዲያውም አልፈልጋቸውም ፤ እኔ ሰላምና ጸጥታ የምሻ ስለሆንኩ ሌላ ምንም መጥፎ ነገር እንዲገጥመኝ አልመኝም ። እስካሁን ይህ ሁሉ ትእምር ሲፈጸም እህያዬ አልተጐዳምና ፡ እንዴት ያለ ምክንያት ሰዎቹን ነካክቼ ፡ የነገር እሳት ልጫር !” አለ ሳንቾ ፓንሳ ኩስተር ብሎ ።

“ሐሳብህ እንዲህ ከሆነ ተጫዋቾቹን እንተዋቸውና መንገዳችንን እንቀጥል ። ይልቅስ የበለጠ ዕድል ወደሚ

ገጥመን አቅጣጫ እናምራና ፥ የጀግንነት ግዳጃችንን እን
ወጣ ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

ይህን ተናግሮ እንዳበቃ ፈረሱ ሮሲናንቴ ላይ ወጥቶ
በዝግታ ርምጃ መንገድ ቀጠለ ። ሳንቾ ፓንሳም ለስዎቹ
የራራ መሆኑን ጌታው ስለ ተረዳለት ፥ በጣም ተደስቶ
ግራጫ አህያው ላይ እንጣጥ ብሎ ወጣ ። ጦረኛዉና ጋሻ ጃግ
ሬዉ ሌላ የጀግና ገድል ፍለጋ ረዥሙን ጎዳና ተያያዙት ።

ብልጭልጭ ለባሹ ጦረኛ

ዶን ኪኾቴና ሳንቾ ፥ ከተጓዥ ተጫዋቾች ቡድን እንደ
ተለዩ ሲጓዙ ውለው ፥ የማታ ማታ ከመንገድ ዳርቻ ከሚ
ገኝ ትልቅ ዛፍ ሥር ዐረፉ ። ሳንቾ የአህያውን ኮርቻ ፈታቶ ፥
ግራጭ በየሙጃውና በየዛፉ ሥር እየተዘዋወረ ሣር እን
ዲግጥ ለቀቀውና ፥ እርሱ ከአንድ ዋርካ ሥር ተዘረጋግቶ
እንቅልፉን ይለጥጥ ጀመር ።

ምስኪኑ ሮሲናንቴ ግን ኮርቻዉ ሳይፀርድለት ፥ ሌሊ
ቱን ሙሉ እንደ ተገተረ አሳለፈ ። ይህ የሆነበት ያለ ምክ
ንያት አይደለም ። ጌታው ዶን ኪኾቴ በድንገት አስቦ እንደ
ተረዳው ከሆነ ፥ ጦረኛ ሲባል በዱር በገደሉ መሸቶበት
በሚያድርበት ጊዜ ፥ ‘ የፈረሱን ልጓም እንጂ የፊሉን ትጥቅ
መፍታት የለበትም ’ በሚል ጽኑ የጦረኛ ዓላማ ተመ
ርቶ ነው ።

ዶን ኪኾቴ ፍሬው በተንገርረገገ ፥ ቅርንጫፉ በተን
ሰራፋ አንድ ሾላ ሥር ዕረፍት ለማድረግ ወሰነ ። ጋደም
አለና በጠራው ሰማይ ላይ የሚንቆጉቆጉትን ከዋክብት
ይቃኝ ጀመር ። ጦረኞች ሁሉ ፥ እንዲህ በዱር በገደሉ ሲጓዙ

ይህን በመሳሰለ ዛፍ ሥር ዕረፍት ያደርጉ እንደነበር ታሪካቸው ትውስ አለው ። የጦረኞችን ገድልና ዝርዝር ሥራቸውን በሚያሰላስልበት ወቅት ፣ ከአቅራቢያው አንድ ድምፅ ሰማ ። እንደ መባነን ቃጣውና ቀንሥቶ ተቀመጠ ፣ የድምፁንም አቅጣጫ በጆሮው ይፈልግ ጀመር ። ድምፁ ከመንገድ አካባቢ ትንሥቶ በባሮች ውስጥ እየበለቀና እየቀረበ ተሰማው ።

ከፈረስ ኮቴ ድምፅ በኋላ ሁለት ሰዎች እርሱ ወደ ተቀመጠበት ሸላ አካባቢ መቃረባቸውን አረጋገጠ ። ወራቱ በጋ ስለ ነበር ፣ በጨለማው ውስጥ ሰዎቹ ወደ እርሱ ሲጠጉ ፣ ከጨረቃ ጨረቃን ጋር ወለል ብለው ታዩት ። ከማየት ዐልፎ ንግግራቸው ሁሉ ጥርት ብሎ ተሰማው ።

"እዚህ ጥሩ ቦታ እንረፍ እንጂ ወዳጄ ! ሌሊቱን በጸጥታ ለማሳለፍ ከሁሉም የተሻለ ቦታ ይህ ይመስለኛል" አለ ከሁለቱ ሰዎች አንዱ ።

ዶን ኪኾቴ ፣ በሾላው ግንድ ከለላ ሆኖ ሲጠባበቅ ፣ አንዱ ከፈረሱ ላይ በዝግታ ወርዶ በለምለሙ ሣር ላይ ሲንጠፍ ተመለከተ ። የጥሩር ወይንች ድምፅ ሲንኳኳ ሰማ ፤ ዶን ኪኾቴ እንደ እርሱ ያለ ጦረኛ ያጋጠመው መስሎት ልቡ የደስታ ከበሮ ይመታ ጀመር ። 'ይህ እንግዳ ሰው ፣ እንደኔው ጀግና ጦረኛ ሳይሆን አይቀርም' እያለ ዶን ኪኾቴ ጥቂት አሰበ ። ለልቡ ልብ ሰጠና በዝግታ ወደ ሳንቾ ጎንሳ ተራምዶ ከእንቅልፉ ቀሰቀሰው ።

"ሳንቾ ! የጠበቅነው የጀብዱ ሥራና ድል እነሆ ዛሬ እውን ሊሆን ነው" አለ ዶን ኪኾቴ በሹክሹክታ ።

"አንድ በጎ ነገር እንዲያጋጥመን እመኛለሁ ። ነገር ግን ይህ ድል የሚባለው ወዴት ነው ያለው ?" ሳንቾ ቀና ብሎ ጠየቀ ።

“ድል ወዶት ነው ብለህ ትጠይቀኛለህ? ምን ነካህ ሳንቾ! ዘወር ብለህ ያንን ሥፍራ ተመልከት። አንድ ጦረኛ በሜዳ ላይ ተጋድሟል ። ብስጩ ይመስለኛል ፤ ምክንያቱም ከፈረሱ ሲወርድ የብሽቀት ድምፅ አሰምቷል ።”

“ታዲያ ይህ ምን ማለት ነው ? የፈለገውን የብሽቀት ድምፅ ቢያሰማ ፡ ከዚህ ሰው ምን የጀብዱ ሥራ ይጠ ብቃናል ?”

“ለጀብዱ ሥራዉ እንኳ አርግጠኛ አይደለሁም ። ግን ፡ ነገር ነገሩ ይመስላል ። እሽሽ ! ይኸውልህ ተቀምጠ ክራሩን ይቃኝ ጀመር ። የፍቅር ዜማ ሲያንጎራጉር ነው መሰለኝ ” አለ ዶን ኪኾቴ ፡ ለውዬውን በርቀት ፀጉሩን ጎልጉሎ እየተመለከተ ።

ዶን ኪኾቴና ሳንቾ ፓንሳ ጎን ለጎን ተቀምጠው ሲመለከቱት ፡ ፋኖው ክራሩን እየገረፈ ከድምፁ ጋር አስማምቶ ሲያንጎራጉር ተሰማ ።

“ሰማኸው ! ፀፍቅር ስላጠመደችው ሴትና ስለ ጭካኔዋ ነው የሚያንጎራጉረው ። ብስጩ ፀይኑት ሰው ነው አላልኩህም ነበር አለው?” ዶን ኪኾቴ በሹክሹክታ ።

ፋኖዉም እንጉርጉሮውን ሲጨርስ በሐዘን ስሜት ደጋግሞ ተነፈሰ ። እንዲያውም ከተቀመጠበት ተነሣና ዛፉን ተደግፎ ፡ ድምፁን ከፍ አድርጎ “እንቺ የቆንጆዎች ቆንጆ የሆንሽው ካስሊዲያ ዴ ባንዲሊያ ! በዓለም ከሚገኙት ቆንጆጆች ሁሉ የላቅሽ እመቤት ነሽ ብንልሽ አይበቃሽምን? ምክንያቱስ ቢሉ የካስቲሊ ፡ የሊዮንና የላማንቻ ጦረኞች ሁሉ ፎደር የሌለሽ የንግሥትነት ጸጋ የተላበሽ እመቤት መሆንሽን መስክረውልሻልና ነው ” አለ ፋኖዉ ለራሱ ።

“ ይህ አባባሉ ልክ አይደለም ። እንዴ ! የላማንቻዉ ጀግናና ጦረኛ እኔ ብቻ ነኝ ። በዚህም ላይ አንዳችም ቆንጆ ሴት ብትሆን ከኔዋ ዱልሲኒያ ትበልጣለች ያልኩበት ቀን የለም ፤ ወደፊትም ቢሆን ጨርሶ እንደማይወጣኝ ርግጠኛ ነኝ ። ይህ ፋኖ እእምሮውን የሳተ ፡ ወይ ልቡን የነሣው ለመሆኑ ካነጋገሩ ይታወቃል ። ቢሆንም ፡ ገና ብዙ ይናገራልና እስቲ በትዕግሥት እናድምጠው ” አለ ዶን ኪኾቴ ድምፁን በጣም ዝቅ አድርጐ ።

“ እረ ሰውዬዉ አንድ ወር ያህል በእንጉርጉሮው ብቻ የሚዘላብድ ሳይሆን አይቀርም ። እስኪበቃን ድረስ የሚያሰማን ይመስለኛል ” ሲል ሳንቾ መለሰለት ።

የሳንቾ ንግግር ጕላ ባለ ድምፅ ነበርና ፡ ፋኖዉ ሰምቶ ከነበረበት ጥላ ሥር ወጣ ።

“ማነህ አንተ!” ብሎ ዙሪያ ገባውን ቃኝቶ ተናገረ።

“ዘመድ አዝማድ ! ” ሳንቾ መለሰለት ።

“ከደስተኞቹ ፡ወይስ ከብስጩዎቹ ወገን ናችሁ ?” ፋኖዉ ጠየቀ ።

“ከብስጩዎቹ ! ከብስጩዎቹ !” ዶን ኪኾቴ ቃሉን መላለሰለት ።

“ እንግዲያውስ እንኳን ደኅና መጣችሁ ?” አለ እንግዳው ሰውዬ ፡ ጊታሩን በእጁ አጥብቆ እንደያዘ ። “ እኔ ዘንድ ቅረቡና እንወያይ ” በማለት ፍኖዉ ድምፁን ለስለስ አደረገ ። ዶን ኪኾቴ ወደ ፋኖዉ ቀረበና ተጨባበጡ ። ፋኖዉም እጅግ ደስ አለው ።

“እኔ ጀግና ጦረኛ ነኝ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“እኔም እንዳንተው ጦረኛ ጀግና ነኝ ። ” ፋኖዉ መለሰለት ።

ሁሉቱም ከለመለመው ሣር ላይ ተቀመጡና ወጋቸውን በሰፊው ዘረጉ ። በሰላምና በፍቅር ቢጨዋወቱ እንጂ ፣ ለፍልሚያ ጦር የሚማዘዙ ሁለት የተለያዩ ጀግኖች ጨርሶ አልመሰሉም ።

ሻንቅ ፓንሳ በበኩሉ መንገዱን አቋርጦ ፣ የፋኖዉ ጋሻ ጃግሬ የጌታውን ፈረስ ከሚጠብቅበት ሥፍራ ሔደ ። እንደ ደረሰም ፣

“ እንደምን ሰንብተሃል እንግዳው ? ” አለ ።

“ አንተስ እንደምን ሰንብተሃል!አጠገቤ ተቀመጥና ልክ ጋሻ ጃግሬዎች ሁሉ በወትር እንደሚያደርጉት እኔና አንተም ነጻነት ተሰምቶን በሰፊው እናውጋ ።”

“ሐሳብክን በሙሉ ልብ እቀበላለሁ ። ካንተ ጋር ማውጋት እፈልጋለሁ ፤ በዚሁ ላይ እኔ ማንና ምን እንደ ሆንኩም በዝርዝር እገልጽልሃለሁ ። ታዲያ ከጭውውታችን በኋላ ለጋሻ ጃግሬነት ብቁ መሆን አለመሆኔን ልታውቅ ትችላለህ ” አለ ሻንቾ ፓንሳ እየተጉማለለ ።

ሁለቱም ጋሻ ጃግሬዎች የወደቀ ግንድ ላይ ተቀመጡና ለረዥም ጊዜ የቂላ - ቂሉ ወሬያቸውን ሲሰልቁ ፣ ጌቶቻቸውም ስለ ጀግኖች ውግ በሰፊው ቁም ነገር ዘርግተው ያወሩ ጀመር ።

በጨረቃ ብርሃናዊ ምሽት ፣ ሌሊቱ በሰላም ዐለፈ ። ሁለቱ ጋሻ ጃግሬዎች ጐን ለጐን ሆነው ሙቀት በሚሰጥ ፀፉር ላይ ተጋድመው እያንኮራፉ እንቅልፋቸውን ለጠጡት፤ ሁለቱ ጦረኛ ጀግኖች ግን ፣ እንቅልፍ ፀዐይናቸው ሳይዞር ሌሊቱን በሙሉ ሲያወጉ ነጋላቸው ። ወጋቸው በሙሉ ስለ ጀብዱ ፣ ስለ ፍልሚያና ስለ ወንድነት ነበር ።

ፋኖዉ ወይም አዲሱ ጀግና በጣም ጉረኛ ነበር ። እንደ አነጋገሩ ከሆነ ፣ እርሱ ያልተዋጋበት ጦር ሜዳ ፣ ያልሞከረው የጦር መማሪያና ድል ያላደረገበት ሥፍራ አይገኝም ።

“ እንደማስታውሰው ከሆነ ፣ ክሰማይ በታች ድል ያል ነሣሁት ጀግና ጦረኛ የሚገኝ አይመስለኝም ። እንዲያውም አንድ ጊዜ ክታወቀው ጦረኛ ከጀግናው ዶን ኪኾ ዴ ላ ማንቻ ጋር ፊት ለፊት ተጋጥመን ድል አድርጌዋለሁ ” አለ ፋኖዉ ኩራት በተመላበት አነጋገር ።

ዶን ኪኾቴ ቁጣ በተቀላቀለ አድናቆት ፣ “ አቁም ! ዝጋ ! እንዲህ አትበል ! በመላ ስፓኝ የሚገኙትን ጦረኞች ከአንድ ሰው በስተቀር ድል መትተህ ሊሆን ይችላል ። ነገር ግን ፣ ዶን ኪኾቴን ጨርሶ አልገጠምከውም ። ”

“ ተጋጥመን ድል አድርጌዋለሁ እያልኩዎት ” እንግዳዉ መለሰ ።

“ምናልባት እርሱን ከሚመስል ጦረኛ ጋር ገጥመህ ይሆን ይሆናል ። ነገር ግን ሰውዬዉ ራሱን ዶን ኪኾቴን ገጥመኸው ቢሆን ኖሮ ፣ ስለ ግጥሚያዉ እንዶታህ ለኔ እን ዲህ አትጨክርም ነበር ። ”

“ ምን ማለትዎ ነዎ? ራሱን ዶን ኪኾቴን ነው ድባቅ የመታሁት ። እርሱን መሰል ሰው ጨርሶ አልተፈጠረም ፤ መልኩና ጠቅላላ አቋሙን ልግለጽልዎ ፤ ቁመናው ቀው ላላ ፣ ፊቱ ሞጣጣ ፣ አገጫም ፍጡር ነው ። ጸጉሩ ሽበት ጣል ጣል ያደረገበት ፣ አፍንጫው ሰልካካና ረዥም ነው ፤ የጋሻ ጃግሬዉ ስምም ሳንቾ ፓንሳ ይባላል ። በፍቅሯ የተ ነደፈላት ውብ ሴት ዶንያ የቶቦሳዋ እመቤት ዱልሲኒያ ትባላለች ። ይህን ካላመኑኝ አሁኑኑ ጉራዴዬን ታጥቄ እንዲያምኑኝ ላደርግ እችላለሁ ። ”

“ጌታው ጦረኛ አትቻኩል ። አሁን ከገለጽክልኝ ታላቅ ጀግና ፡ ከላ ማንቻዉ ጦረኛ ጋር እኔ ፣ ራሴ ተዋውቄ አለሁ ። እንደ እውነቱ ከሆነ በዓለም ላይ ያለኝ አንድ የልብ ወዳጅ እሱ ነው ። ራሴን የምወደውን ያህል ነው ፣ እርሱንም የምወደው ። ሁኔታውን ዶግና አድርገፀ ገል ጿሃል ፤ ነገር ግን ከእርሱ ጋር በፍጹም አልተዋጋህም ! አስማተኞች ስለሚፈታተኑት ምናልባት ሌላዉን ጦረኛ በመተታቸው ዶን ኪኾቴን አስመስለውብህ ሊሆን ይች ላል ለውጠውት ማለቴ ነው ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

እንግዳዉ ፋኖ ራሱን ነቀነቀ ፣ ዶን ኪኾቴም ንግግሩን በመቀጠል ፡ “ አሁን ያልኩህ ሰው እውነት ነው ። እኒሁ አስማተኞች አሁን በቅርብ ቀን እንኳ ውቢቷን የቶቦሳ ዋን እመቤት ዱልሲኒያን ወደ ቀርፋፋና አስቀያሚ የባ ላገር ልጃገረድነት ለውጠዋት ነበር ። የሆነ ሆኖ ፣ አሁንም አንተ ‘ ዶን ኪኾቴን ድል መትቸዋለሁ ’ በሚለው ቃልህ የምትጸና ከሆንክ ፥ አንድ ቁም ነገር ብቻ ልንገርህ ። እነሆ ስሙጥርና ጀግናዉ ጦረኛ ራሱ ቃሉን በተግባር ለመፈ ጸም በጨበጣም ሆነ በፈረስ ላይ ፣ ወይም ላንተ በሚመ ችህ ፣ ወንድነቱን ሊያሳይህ ተዘጋጅቷል !” አለ ዶን ኪኾቴ በደም ፍላት ድምፁን ከፍ አድርጐ ።

ይህን ትናግሮ ሮሲናንቴ ላይ ዘሎ ወጣና ፣ ጉራዴዉን ጨብጦ ለፍልሚያ ተዘጋጀ ። ፋኖዉ ግን ምንም ነገር እንዳልተፈጸመ ሆኖ ቀዝቀዝ ባለ መንፈስ እዚያው ከተ ቀመጠበት መሬት ሳይነሣ ቀረ ።

“ጌታው ! ያ ያሸነፍኩት ጦረኛ በአስማት የተለወ ጠው ዶን ኪኾቴ ከሆነ ፣ በአካል በኤምሳል ባገኘው ምን የሚያስፈራኝ ነገር አለ? ሆኖም ጦረኞች በድቅድቅ ጨለማ ጨርሶ አይጋጠሙም ። እስኪነጋ ጠብቀን ንጋት ምስክ

ራችን ስትሆን የጀብዱ ተግባራችንን እንያያዘዋለን ''አለ ፀዝቄቃ ።

"መልካም ብለሃል ። እኔም እስኪነጋ ለመጠበቅ ፈቃደኛ ነኝ ።"

ሁለቱም ጦረኞች ስምምነት ላይ ከደረሱ በኋላ ፡ ጋሻ ጃግሬዎቻቸውን ፍለጋ መንገዱን አጽርጠው ግራና ቀኝ ተለያይተው ሄዱ ። ከብዙ ፍለጋ በኋላ ሁለቱም ጋሻ ጃግሬዎች መሬት ላይ ተዘርግተው በእንቅልፍ ዓለም ገብተው ሲያንኰራፉ አገኟቸው ። ቀሰቀሷቸውና ሁለቱም የጌቶቻቸውን ፈረሶች እንዲጭኑ ትእዛዝ ሰጧቸው ። ምክንያቱስ ቢሉ ፡ ግለዱ ፀሐይ ብርሃንዋን ስትፈነጥቅ በጀግኖች መኻል ፍልሚያው ይጀመራልና ነው ።

ሳንቾ ፓንሳ ፡ የሚለዳውን ፍልሚያ ወሬ ሲሰማ እጅግ ተገረመ እንጂ እንዳችም ቃል አልተነፈሰም ። ከተኙበት ቦታ ከመቀስቀሳቸው ትንሾ ቆ ከእንግዳው ጋሻ ጃግሬ ጋር ፈረሶቹን ፍለጋ ተያይዘው ሄዱ ።

የእንግዳው ጦረኛ ጋሻ ጃግሬ ንግግሩን ጠረግረግ አደረገና ፡ "ስማ ጓዴ ! እንግዲህ ጌቶቻችን ጦር መማዘዛቸው መፋለማቸው አልቀረምና እኛና እንትም መጕሸሸም ሊኖርብን ነው ። በእኛገሬ በአንዳሉሲያ ፡ ጋሻ ጃግሬዎች የሚያደርጉትም ይህንኑ ነው ። አሽከሮች ወይም ጋሻ ጃግሬዎች የሆኑ ሁሉ ጌቶቻቸው ፍልሚያ ሲገጥሙ ዝም ብለው አይመለከቱም" አለ ።

"ያህንን ባህል በአንዳሉሲያ ሊሠሩበት ይችላሉ ! ነገር ግን እኔ በበኩሌ አላደርገውም ። ለጦርነያ ይሆን ያህል ክንዴ የፈረጠመ አይደለም ። በእጆቻቸሁ መሉ ቀላሉ በእጄ ጨብጬውም አላውቅ" አለ ሳንቾ ፓንሳ ፍርሃት በተመላበት ድምፅ ።

“እ! ለስ ጉራዴ እያያዝ ይህን ያህል አታስብ ። አንድ ሁለት ክረጢቶች አሉኝ ። አንተ አንዱን ያዝ ፤ እኔ ሌላዉን እይዛለሁ ። ከዚያም አንተ ስትወረውርብኝ ፣ መልሼ ለሰጥህ ፤ እኔ ስወረውርብህ ፣ መልሰህ ስትሰጠኝ — በዚህ ዐይነት ፍልሚያዉ ይፋፋማል !”

“ድንቅ ሐሳብ ነው ። በመጨረሻም የልብሶቻችንን አቧራ ከማራገፍ በስተቀር የሚደርስብን ጉዳት አይኖርም !” ሳንቾ በደስታ ፈንድቆ ተናገረ ።

“አንተ እንዳልከው ይህን ያህል ቀላል አይደለም ፤ አሁን እንግዲህ ክረጢቶቻችንን በግማሽ ድንጋይ እንሞ ጅርባቸው ። ፍልሚያዉ የተሻለ የሚሆነው በእንዲህ ዐይነት ዘዴ ስንጠቀም ነው ። ”

“ነገሩ እንዲህ ከሆነ ፣ አሁንም በድጋሚ ቃሌን ለሰጥህና ፣ እኔ የውጊያ ነገር አይሆንልኝም ብያለሁ ፤ የውጊያ ስሜት የለኝም ። ጌታዬስ ዕድሜያችን እስከፈቀደልን ድረስ በደስታ እንዚጋጅ ፣ ማለት እንደሰት ። ካንተ ጋር የሚያፋልመኝ ምንም ጠብ የለኝም ፣ በዚህ ላይ ሳልቆጣና ደሜ ሳይፈላ እንዲያው በዘፈቀደ የምጣላበት ምክንያት አይኖርም ።”

እንግዳዉ ጋሻ ጃግሬው ፣ “አይዞህ ጓደኛዬ ፣ ይህ ከሆነ ችግርህ ፣ አሁኑኑ ደምህን አፈላዋለሁ ። እንዴት አድርጌ መሰለህ የማፈላው ? በጨዋ ያንብ ቀበ ብዬ እጠጋህና ሦስት ጥፊ አለሰዋለሁ ፤ ከዚያም ፊትህን ስገጭህ ትዝረራለህ ። ታዲያ ወዲያው ደምህ ይፈላል ፤ አይፈላም ነው የምትለው ?”

“ደሜ ቢፈላም ባይፈላም ይህን ያልከውን ሲታደርግ እንተያያለን ። እናትህን ነው በቆመጥ የምፀጠርቀው ፤

ማንም ለማንም አያነስም ። ብዙዎች ሊያጭዱ ይመጡና ታጭደው ይመለሳሉ ። የጩኸቶች ድምጽ ያንበሳን ያህል ታስፈራለች ። ስማ ! ደሟ ሲፈላ የማያደርገውን ነገር የሚያውቅ ሰው የለም ” እያለ ሳንቾ ፓንሳ ፣ ንዴቱን መቈጣጠር አቅቶት የቃላት ናዳ ያወርድ ጀመር ።

ንትርካቸው ጋብ እንዳለ ፣ ፈረሶቻቸውን ፈላልገው የባልደራስነት ሙያቸውን ተያያዙት ። ፈረሶቹ ለጌቶቻቸው ግጥሚያ ተጭነው መሰናዳት ነበረባቸውና እንደ ድንጉላ ፈረስ ያቁነጠንጣቸው ጀመር ።

“ምንነው ይህች ፀሐይ ቶሎ በወጣች ! ፍልሚያውን ለማየት በጣም ጓጉቻለሁ ” አለ እንግዳዉ ጋሻ ጃግሬ ።

በእርግጥም ብዙ ሳይቆዩ ጎሕ ቀደደ ። ሳንቾ ፓንሳ ፀወጋግኑ ብልጭታ ቀስ ብሎ እያየውን ጋሻ ጃግሬ ተመለከተ ። ልቡ በፍርሃት መታ ፤ ሰውነቱም ከመጠን በላይ ተንቀጠቀጠ ። ይህም የሆነበት ምክንያት ፣ የእንግዳዉ ጋሻ ጃግሬ አፍንጫ አስገራሚና ከዚህም በላይ በጣም የሚያስፈራ በመሆኑ ነበር ። እንዲህ ያለ ልዩ የሰው አፍንጫ ሳንቾ በሕይወቱ ሙሉ አይቶ አያውቅም ። ከአፍንጫው ትልቅነትና ርዝማኔ የተነሣ ፤ ፊቱን በሙሉ ሸፍኖት ነበር ፤ የሰውዬው አፍንጫ እንደ ዶሮ እመኘቱ ላይ ጉብ እንደ ቲማቲም ቀልቶ ሊያዩት ይዘገንናል ።

ሳንቾ ፓንሳ የሰውዬውን አፍንጫ እሁንም ትክ ብሎ ተመለከተና ፣ “ ከእዚህ አፍንጫ ጋር ከምናፈልም ፣ ሺህ ጊዜ ቢፈጠጠኝ እመርጣለሁ ” አለ ሳንቾ ለራሱ ፍርሃት ገብቶት ።

ዶን ኪኾቴ በበኩሉ ፣ ከሚፋለመው ጠላት ጋር ትመ ፍጠጥ በስተቀር ምንክቸ አላለም ። ፍልሚያውንም በወኔ ይጠባበቅ ጀመር ። ነገር ግን የፊቱ ፊት በጆሮና ቀኖር ሙሉ

በሙሉ ስለ ተሸፈኑ የባላጋራውን ገጽ ለማየት ባለ መቻሉ ቅሬታ ተሰምቶታል ። ተፋላሚዉ የለበሰው ጥሩር በዐይነቱ ከፍተኛ ሲሆን ፣ በወርቅ የተለበጠ ፣ ያማረ የደመቀ ነበር ። በኩቱም ላይ ከመስተዋት የተሠሩ ፈርጦች ፣ ልክ ጨረቃ ይመስላሉ ።

በቆብሩ ላይ የሰካቸው ፣ ቢጫ ፣ አረንጓዴና ነጭ ላባዎች ኅብረ ቀለማቸው ልብ ይሰርቃል ። የያዘው ጦር ወፍራምና ረዥምም ነው ። ፋኖዉ ቁመናው ለጋ ቀጠን ያለ ሙሉ መሳይና ፈጣን ነው ።

“ጌታዉ ባለ ብልጭልጭ ፣ ቍርህን ትንሽ ከፍ አድርግልኝ ፣ ገጽህን በቅጡ እንዳየው” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“አይቻልም ! አሁን ትግሉትህንና ፍላጐትህን ላሟላልህ ፈቃደኛ አይደለሁም ። ክፍልሚያችን በኋላ በቂ ጊዜ ስላለን ያኔ ገጼን እስኪበቃህ ማየት ትችላለህ ። ይልቅስ ነጥቋልና ፣ፍልሚያችንን እንቀጥል” አለ ፋኖዉ ጦረኛ።

“ዝግጁ ነኝ ። ሆኖም በፈረሶቻችን ላይ ስንወጣ ፣ምን ‘ትጋጥሜ ድባቅ መትቸዋለሁ’ ያልከውን ዶን ኪኾቴን እመስል እንደሆን እባክህን ንገረኝ? ‘ፊት ለፊት ገጥሜው በትክክለኛ ፍልሚያ ነው ድል ያደረግሁት’ ብለኸኛል” አለ ዶን ኪኾቴ ምጸት በተመላበት አነጋገር ።

“እንዴታ! ጥርጥር የለውም ። እንዲያውም አምላኮች ናችሁ” አለ ብልጭልጭ ጥሩር-ለባሹ ጦረኛ ።

“ ፍልሚያዉን እንጀምራ ! አንተ የምታውቀው ኪኾቴን አለመሆኔን አሁኑኑ ላሳይህ ዝግጁ ሆኛለሁ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

ቃላት ሳያበዙ በየፈረሶቻቸው ላይ ወጡ ። ጥቂት ተራርቀው ሶምሶማ ጋልበው ፣ ተሟሙቀውና ልበ ሙሉ

ሆነው ፤ አንዱ ሌላዉን ሲያጠቃ እነሆ የመጨረሻዋ ደቂቃ ደረሰች ።

በዚያ ቅጽበታዊ ወቅት ዶን ኪኾቴ የእንግዳውን ጦረኛ አፍንጫ አትኩሮ ለማየት ቻለ ። ሳንቾ ፓንሳም ጌታው የሰውዬውን አፍንጫ በአድናቆት መመልከቱን አይቶ በሩጫ ቀረበውና ፤ እርካቡን በሁለት እጁ ይዞ ፤ “ ውዱ ጌታዬ ሆይ ! ከጠላትዎ ጋር ከመጋጠምዎ በፊት አባክዎን እዚህ ዛፍ ላይ እንድወጣ ይርዱኝ ። በዛፉ ላይ ሆኘ ሁለታችሁም የምታደርጉትን ከፍተኛ ፍልሚያ ለማየት ያመቸኛል ” አለ ሳንቾ ።

“ሰበብ ከምታበዛ ፤ ‘ ከአዲጋው ንፍሴን ለማዳን ፈልጌ ነው’ ብትል አይሻልህም ? ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“ ጌታዬ እውነተኛውን ነገር ልንገርዎት ፤ ያንን አፍንጫ ፈርቼኮ ነው ” አለ ሳንቾ ወደ ሰውዬው በጣቱ እየጠቆመ ።

“አልፈርድብህም ። የዚህ ሰው አፍንጫ ከእኔ በስተቀር የማንንም ወንድ ልብ የሚያስፈራራ መሆኑ ግልጽ ነው። አሁን እግርህን እዚህ እርካብ ውስጥ አስገባና ፤ በዝግታ ከዛፉ ቅርንጫፍ ላይ ተንጠልጥለህ ወደላይ ውጣ ” አለ ዶን ኪኾቴ በአንድ ዐይኑ ባላጋራውን እያየ ።

ሩኖዉ ፈረሱን እንደገና ከወዲያ ወዲህ ሶምሶማ እያስጋለበ ፤ ለማጥሚያ ተጨድሮ ትዕግሥቱ ዐልቆ ወደ አልተዘጋጀው ዶን ኪኾቴ ጋለበ ። ሆኖም ፤ ፈረሱ ከሮሲናንቴ የባሰ መጋኛ ስለሆነ የተኮረኮረውን ያህል ሊከንፍ አልቻለም ነበርና፤በየቦታው ሲወላከፍ ጌታው ተደናግጦ ልጓሙን ግታበት ።

ዶን ኪኾቴ ቀና ብሎ ባላጋራውን ተመለከተ ። በአቅራቢያው እንደ ደረሰ ባየ ጊዜ ሮሲናንቴን ኰረኰ

ፈው ። ምስኪኑ እንስሳ ሲሮጥ ላየው በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የፈረስ ወግ ደርሶት ሽምጥ መጋለቡ ነበር ።

ፋኖዉ ፈረሱን እንደገና ኰርኩሮ ግልቢያውን ከመቀጠሉ በፊት ፤ ዶን ኪኾቴ ዐይኑን ጨፍኖ ወጣበት ። ፋኖዉ ጦሩ ከእጁ ላይ ተፈናጥሮ ወደቀበት ፤ እርሱ ራሱም ከኮርቻው ላይ ተፈንግሎ በአቧራው ላይ ተነጠፈ ። አደገኛ አወዳደቅ ስለ ነበረ ፤ ለጥቂት ጊዜ ትንፋሹን አጥቶ ሕይወቱ ያለፈች መስሎ ታየ ።

ሳንቾ ፤ ከተንጠለጠለበት ዛፍ ላይ በፍጥነት ወርዶ ጌታውን ለመርዳት ከመሮጡ በፊት ፤ ቅጽበታዊውን ፍልሚያ በድንጋጤ ነበር የተመለከተው ። ዶን ኪኾቴ ፈረሱን አረጋግቶ ካቆመ በኋላ ፤ ከኮርቻው ላይ ዱብ ብሎ ወረደ ። መሬት ተንጋሎ ትንፋሽ ወዳጣው ባላጋራው ዘንድ ሔደ ። አጠገቡ ቆም ካለ በኋላ ፤ እየሮር ያገኘ ዘንድ ቊሩን በዝግታና በጩዋ ደንብ ከአናቱ ላይ አነሣለት ። ዶን ኪኾቴ በእጁ የወደቀ ጉረኛ ጠላቱን መልክ በአድናቆት ይመለከት ጀመር ። ይህ መልክ ፤ አስተያየትና ቁመና የወዳጁና የጐረቤቱ የማንቻዉ የሳምሶን ካራስኮ መልክ ሆነበት ! !

"ሳንቾ ወዲህ ተመልከት ። እኒህ ምትሃተኞች ዛሬም የሚያደርጉትን መተት ተመልከት ብቻ ! " እያለ ዶን ኪኾቴ ድምፁን ከፍ አድርጎ ይጮኽ ጀመር ። ሳንቾ ፓንሳ በድንጋጤ መልኩ ተለዋወጠ ።

"ጌታዬ ሆይ ምክሬን ይስሙኝ ። ይህ የወደቀው ዘውትር የሚፈታተንዎ አስማተኛ ነው ። እዩት ! ብሎ ብሎ የወዳጃችንን የሳምሶን ካራስኮን መልክ ወስዶ ዐረፈው ። እርስዎንና ሳምሶንን ለማቆራረጥ ሆን ብሎ ያደረገው ደባ ነውኮ ! ! አሁኑኑ ጉራዴዎን ጉሮሮው ውስጥ ይቀርቅሩ

በትና ዓለም በመላ ጀግንነትዎን እንዲያደንቅ ፣ ስምዎንም እንዲያወድስ ያድርጉ ! " ሲል ሳንቾ ፓንሳ በዶን ኪኾቴ ጆሮ አንሾካሾከለት ።

"ምክርህ ጠቃሚ ነው፤ያልከኝን አሁን ባደርግ ፣የሚፈታተኑን ጠላቶቻችን እየተቀናቡ ይሔዳሉ " አለና ዶን ኪኾቴ ፣ ጐራዴውን መዝዞ የጠላቱን አንገት ሊቀላ ክንዱን ሲያነሣ ፣ ከበስተጀርባው አንድ ከፍተኛ ድምፅ ፣

"አቁም ዶን ኪኾቴ ! " ሲል ተሰማ ። ዶን ኪኾቴ ዘወር ብሎ ቢመለከት እንግዳው ጋሻ ጃግሬ ነበር ፣ ከበስተጀርባው የቆመው ። አስፈሪ አፍንጫው ግን የለም ። ድምፁ እንደገና አምባረቀ ።

" ተጠንቀቅ ዶን ኪኾቴ ! ይህ ወድቆ የሚታየው ወዳጅህ ሳምሶን ካራስኮ ሲሆን ፣ እኔ ደግሞ ጋሻ ጃግሬው መሆኔ ነው ። "

ሳንቾ ግራ ተጋባና ፣

"የቅድሙ አፍንጫህ የት ደረሰ ? " ሲል በአድናቆት አፉን ከፍቶ ጠየቀ ።

" በኪሴ ውስጥ አስቀምጬዋለሁ " ሲል መለሰ ትና በአፍንጫ ቅርጽ የተሠራ ፣ ቀለም የተቀባ የክርታስ አፍንጫ ከኪሱ ውስጥ ብቅ አደረገ ።

ሳንቾ የሰውዬውን ገጽ ትክ ብሎ ተመለከተና ፣ "ወይ ጉድ ! ጉድ ነው ! ስመሆኑ አንተ ማነህ ? የጥንቱ ወዳጄና ጐረቤቴ ቶማስ ሴሲያል አይደለህም ? ነህ እንጂ ! የኔ ጓደኛዬ ቶም ! " እያለ ይደነቅ ጀመር ።

"እኔው ራሴ ቶም ነኝ ። ከላ ማንቻ ጀምረን እነሆ እናንተኑ እንደ ተከተልን ነን ። ይህ ዑሱ ፍልሚያ ፣ ክፎ

ክርና ውዝግብ ዶን ኪኾቴን በማስፈራራት ወደ ሀገሩና ወደ መንደሩ በሰላም እንዲመለስ ለማድረግ የወጠንነው ብልሃት ነበር ” አለ እንግዳዉ ጋሻ ጃግሬ ።

“እንግዲያውስ አስማተኛ አይደለህማ ! ” አሉ ሳንቾ ።

“እኔ ወዳጅህና ጐረቤትህ ቶማስ ሴሲያል ነኝና ፥ በቅጡ ተመልከተኝ ። ”

በዚህን ወቅት መሬት ላይ ተዘርሮ የነበረው ብል ጭልጭ ለባሹ ፋኖ ንፍስ እየዘራ ፥ ትንፋሹ እየተመለሰ መጣና ዙሪያውን ቃኝቶ ፥ ከወደቀበት ተነሥቶ ፥ ተቀመጠ ።

ዶን ኪኾቴ ድምፁን ከፍ አድርጎ ፥ የጐራዴውን ጫፍ ግንባሩ ላይ ተክሎ ፤

“የቶቦሳዋ ዱልሲኒያ ፥ በዓለም ከሚገኙት እመቤ ቶች ሁሉ የላቀች ቆንጆ መሆንዋን ካማመን ወይም ከሞ ትህ አንዱን ምረጥ ! ” አለ ዶን ኪኾቴ በቁጣ ።

“አምናለሁ ! ! የእመቤት ዱልሲኒያ አሮጌ ጫማ እንኳ ከእኔዋ እመቤት ከካሲልዲያ አጅግ በጣም ብልጫ ያለው ነው ! ” አለ ብልጭልጭ ለባሹ ፋኖ ።

“እንግዲያውስ ፥ አሁኑኑ ወደ ቶቦሳ በመሔድ ይህንኑ ቃልህን ለኔዋ ዱልሲኒያ ለራሷ ትገልጽላታለህ ወይ ? ” ዶን ኪኾቴ ጠየቀ ።

“ ትእዛዝህን በሙሉ ልፈጽም ዝግጁ ነኝ ። ”

“እንዲሁም እውነተኛውን ዶን ኪኾቴን ሳይሆን አምሳያውን ገጥመህ ድል ማድረግህን ብቻ ትናዘዝላታ ለህን ? ”

“እመኑኝ ያልከውን ሁሉ በሙሉ ልቤ ሐጂ እናዘዝ ላታለሁ ” አለ ድል የተመታው ጦረኛ ። ዶን ኪኾቴ ደጋግሮ አነሣው ፤ እጁንም ጨብጦ ልባዊ ሰላምታ ሰጠው።

“ ወዳጄ ሳምሶን ካራስኮንን ትመስላለህ ፡፡ግን እንዳ ልሆንክ ዐውቃለሁ ፡፡ አንተ ሌላ ሰው ነህ ፡፡ ምትሃተኞች ግን እኔን ለማታለል ብለው መልክህ ሳምሶንን እንዲመ ስል ለወጡህ ፡፡ ቢሆንም አልታለልም ፤ ከንቱ ድርጊታቸ ውን ጠንቅቄ ዐውቃለሁ ፡፡ በምንም ሊያሞኙኝ አይች ሉም ” አለ ዶን ኪኾቴ ፡፡

ሳምሶን ካራስኮ በጣም ተደናገጠ ፡፡ ጉረቤቱን ጥበብ በተመላበት ዘዴ አታሎ ወደ ቤቱ ለመመለስ ያቀደው ሁሉ ገና ከጅምሩ እንደ ከሸፈበት ተረዳ፡፡ ዶን ኪኾቴ ሳም ሶንን ሊያምነውና ሊቀበለው አልቻለም ፡፡ ዶን ኪኾቴ ‘ ሳምሶን መተተኞች የሚጫወቱበት አንድ ምስኪን ጦረኛ ፤ ወይም የነርሱ አገልጋይ የሆነ ነሆለል ነው ’ የሚል ነው እምነቱ ፡፡

በመጨረሻም ፤ ሳምሶን በደረሰበት ምት ሰውነቱ ተቀ ጥቅጦ ፤ ልቡ በሽንፈት ቆስሎ ፤ ውርደቱን ተከናንቦ ፤ በዚያ መጋኛ ፈረሱ ላይ ወጣ ፡፡ ጋሻ ጃግሬውን ከጐኑ ሆኖ እንዲ ጠብቀውና እንዲደግፈው በማድረግ እያቃሰተ ፤ ለቁስሉ ማከሚያ ፋሻና መድኃኒት ለማግኘት በአቅራቢያው ወደ ሚገኘው ከተማ አመራ ፡፡

“ወዳጃችን ሳምሶን ካራስኮ ይሆናል የሚል ጥር ጣሬ በመጠኑ አለኝ ” አለ ሳንቾ ፓንሳ ጌታውን እየተ መለከተ ፡፡

“ በመልክና በአቋም አትታለል ወዳጄ ሳንቾ ” አለ ጌታው ዶን ኪኾቴ ፡፡ እና . . . . .እንስሶቻቸው ላይ ወጥተው የተነሡበትን የጀግንነት ዓላማ ከግቡ ለማድረስ መንገዳቸውን ወደፊት ቀጠሉ ፡፡

ከአንበሶች ጋር

ፀሐይዋ ከፍ ብላ ከአድማስ እስከ አድማስ ብርሃንዋን ፈንጥቃለች ። ዶን ኪኾቴም በለስ ቀንቶት ፣ በደስታ ተሞልቶ ፣ በወኔ ተኩራርቶ ለሌላ ገድል ጉዞውን ቀጥሏል ። ብልጭልጭ ለባሹን ጦረኛ ድል በማድረጉ የልብ ሐሴት ተሰምቶታል ።

በዓለም ከሚገኙት ጦረኞች ሁሉ የላቀ ጀግና መሆኑንም በልቡ አረጋግጧል ። አስማተኛም ሆነ አስማት ከእንግዲህ አያስፈራውም ። እውነትም ይሁን ሐሰት ምንም ነገር ሊያስበረግገው እንደማይችል አረጋገጠ ።

"ከእንግዲህ የፈለገው ይምጣ ። ዝግጁ ነኝ ። ሞገደኛ የሆነ ጠላት እንኳ ቢገጥመኝ ልደቁሰው በበኩሌ ዝግጁ ሆኜአለሁ" አለ ዶን ኪኾቴ ድምፁን ከፍ አድርጎ ።

በጉዞው ላይ እንዳለ ፣ ከቀትር በኋላ አንድ ሠረገላ በርቀት ወደ እርሱ አቅጣጫ ቁልቁል አውራ ጎዳናውን ይዞ ሲገሰግስ ታየ ። ሠረገላው እየተቃረበ ሲመጣ ፣ በሁለት በቅሎዎች የሚጎተትና አናቱም ላይ ትናንሽ ሰንደቅ ዓላማዎች ሲውለበለቡ ዶን ኪኾቴ ተመለከተ ።

" ያውልህ! ተመልከት ሳንቾ ። እነሆ የጀግና ሙያ ሊያጋጥመን ወቅቱ ደረሰ " አለ ዶን ኪኾቴ በደስታ ፈንድቆ ። ሳንቾ ግን በጥርጣሬ ተውጦ ራሱን ነቀነቀ ።

"እንዚያኮ የንጉሡ ሰንደቅ - ዓላማዎች ናቸው ። ሰንደቅ ዓላማ የሚያውለበልቡበትም ምክንያት ፣ ሠረገላው

ሠረገላው ቆመ ። የዶን ኪኾቴ ትዕግሥት እያለቀ በመምጣቱ እጅግ ተቅበጠበጠ ።

“ አንተ ደደብ ! አትሰማኝም እንዴ ? የአንበሶቹን ጎጆ ቶሎ ብለህ ክፈትልኝ ። ካለበለዚያ ከሠረገላው ጋር ነው በጦሬ የምቀብቅብህ ” አለ ዶን ኪኾቴ ክፉኛ ደሙ ፈልቶ ።

ሠረገላው ነጂው በተፈጥሮው ቡከን ነበርና ፣ ዘሎ መሬት ከወረደ በኋላ በፍርሃት ሰውነቱ ይናጥ ጀመር ።

“ይማሩኝ ጌታዬ ! በቅሎዎቼን ከሠረገላው እስክፈታ ድረስ ይታገሡኝ ፤ ሠረገላውን ከመክፈትዎ በፊት ፣ እባክ ዎን በቅሎዎቼን ላሸሻቸው ! በዓለም ላይ ያሉኝ አንጡራ ሀብቶቼና ቅርሶቼ እኒህ በቅሎዎች ብቻ ናቸው ” እያለ ሠረገላ ነጂዉ መሬት እየሧጠጠ ዶን ኪኾቴን ይለምን ጀመር ።

“ አንተ አቅመ-ቢስ ! እኒህን የዋህ እንስሳት ፍታና ይዘሃቸው ጥፋ ! አንበሶቹን ግን በቁጥጥሬ ሥር እንደማደ ርጋቸው አሳይሃለሁ ” አለ ዶን ኪኾቴ በኃይሉ ተመ ክቶ ።

ሠረገላ ነጂው ፈጥኖ ትእዛዙን ተቀበለ ። በቅሎዎ ቹን ከሠረገላዉ ላይ ፈታና ፣ በከፍተኛ ፍጥነት እያስሮጠ ሩብ ኪሎ ሜትር ካሸሸ በኋላ ፣ አንድ ኮረብታ ጫፍ ላይ ደረሰ ። ትንፋሹን ውጦ ፣ ተረጋግቶ ፣ አደጋ እንደማይደር ስበት ካረጋገጠ በኋላ ፣ ሠረገላዉ አካባቢ ምን እንደሚ ፈጠር ቁልቁል አርቆ ይመለከት ጀመር ።

ዶን ኪኾቴ አጠገቡ የቀረውን ያንበሶቹን ጠባቂ ጣራና ፥

"ብሊ ! ሳታመነታ ትእዛዜን መፈጸም አለብህ ። እሻ ፈረኝ ካልኸ ግን ዋጋህን ታገኛለህ " ! ብሎ እንደ ብራቅ ጮኸበት ።

የእንበሶቹ ጠባቂ የዶን ኪኾቴ ጦር ደረቱን ገና ሲገናው ሲሰነጥቀው ተሰማው ፤ እሱም በተፈጥሮው ወኔ-ቢስ ብመ ሆኑ በደረሰበት ዱብ ዕዳ ተደናግጦ ፊቱ አመድ ለበሰ ።

"ጌታዬ ትእዛዝዎን እፈጽማለሁ ። ሆኖም ተገድጄ እንበሶቹን ለመልቀቄ እርስዎ ብቻ ይወቁልኝ " አለ እየተርበተበተ ።

ጠባቂዉ ፡ ዶን ኪኾቴ እንዳዘዘው ከሠረገላው በስ ተጀርባ ዞሮ ፡ የመጨረሻውን የአንበሳ መጠበቂያ ሽቦ በር ይከፍት ጀመር ። "ገለል በሉ ፡ ራሳችሁን አድኑ ! እንበሶች እኔን ስለ ለመዱኝና ስለሚያውቁኝ አይጐዱኝም ። በእና ንተ ላይ ስለሚያደርሱት አደጋ ኃላፊነት የለብኝም " እያለ ጠባቂዉ ፡ ማስጠንቀቂያውን ፈጠን ብሎ ተናገረ።

ጠባቂዉ ፊቱን ወደ ዶን ኪኾቴ መልሶ በተጠየቅ ወጥሮ ያዘው ፡ " ጌታዬ ራስዎን ለአደጋ አጋልጠው በመ ስጠት ፈጣሪዎን በመፈታተን ላይ ይገኛሉ " አለ ።

"አንተ ደደብ ! አንተ መታዘዝ ብቻ እንጂ ማማከር ራህ አይደለም ። ቶሎ ብለህ የአንበሶቹን ጐጆ በር ፈክተ ብዬሃለሁ " አለ ዶን ኪኾቴ በቁጣ ! !

ሳንቾ ፓንዛ መናገር ፈለገና ፡ "ደግ ጌታዬ ሆይ ! ይህ የአስማተኞች ሙቱት እንዳይመስልዎት ፤ እውነተኛው ነገር ነው ። ቀስ ብዬ በሽቦው አጥር ውስጥ አጮንቁሬ ስመለከት የአንበሳውን ጥፍር ለማየት ችያለሁ ። ትልቅና የሚያስፈራ ነው ። ያን ያህል ጥፍር ያለው አውሬ ትልቅ ተራራ የሚያህል መሆን አለበት " አለ ሳንቾ ።

"ያንተ ፍርሃት ብቻ አውሬዉን የዓለምን ያህል ያተልቀዋል" አልና ዶን ኪኾቴ፣ "ወዳጄ ሳንቾ ሆይ! ይህን ለኔ ተውልኝና አንተ ነፍስህን ወደ ምታድንበት ሥፍራ ተሸሸግ ። በግጥሚያዉ ብረታ ተግባርህን በደንብ ታውቀዋለህና ፣ ዜናውን ለዱልሲኒያ አድርስልኝ፤ ቤታ የምለው የለኝም" አለ ዶን ኪኾቴ ።

ምስኪኑ ሳንቾ ዐይኖቹ ዕንባ አቀረሩ፤ የጌታው ሕይወት ማክተሚያ ቀን ዛሬ መሆኑን አረጋገጠ፤ ያንን አህያውን ኰርኲሮ፣ የግልቢያ ፍጥነቱን ጨምሮ፣ ቀደም ሲል የሠረገላው ነጂ ነፍሴ አውጭኝ ብሎ ከበቅሎዎቹ ጋር ወደ ተሸሸገበት ኮረብታ ጫፍ ሸመጠጠ ።

የአንበሶቹ ጠባቂ እጁን በሽቦው አጥር ላይ አድርጐ ያንበሳ ጐጆውን ሊከፍት ተሰናድቷል ። ዶን ኪኾቴ ግን ስለ ፍልሚያው ዐይነት በሐሳብ ይዋዥቅ ጀመር ።
አንበሳዉን በጨበጣ ወይስ በፈረስ ላይ ሆኖ እንደሚገጥመው ርግጠኛ አልሆነም ።

'ሮሲናንቴ ከአንበሶች ጋር ትውውቅ የለውምና ምናልባት ሥርዐት ላይጠብቅ ይችላል ። እኔው ራሴ በእግሬ ሆኘ ብጋጠም ይበጃል' አለ ዶን ኪኾቴ ለራሱ ።

ከፈረሱ ላይ ወረደና ሮሲናንቴን ከአንድ ዛፍ ላይ ሸብ አደረገው ። ጦሩን ወደ ጐን አስቀመጠና ጐራዴውን መዘዘ ።

የአንበሶቹ ጠባቂ፣ በታላቅ ጥንቃቄ ወደ አንበሶቹ ጎጆ ተራመደና በሩን ድንገት በረገደው፤ ዶን ኪኾቴም በሚያስደንቅ ድፍረት ተንደርድሮ ከበሩ ፊት ለፊት ተገተረና፣

"አንተ ቁጫጭ የምታህል አውሬ ና ውጣ! ውጣ በል እንጂ! በዓለም የታወቀው ጦረኛ ጀግና ምን እንደሚሠራ አሳይሃለሁ አለ!!"

አንበሳዉ በመጠበቂያው ውስጥ ከወዲያ ወዲህ ተጕማለለ ። መዳፉን ዘርግቶ አፉን ከፍቶ ከአዛጋ በኋላ፣ ክንድ የሚያህል ምላሱን መዘዘ ።

ጦረኛዉ ደረቱን ገልብጦ ፣ ልቡን ነፍቶ ፣ ከአንበሳዉ ፊት ለፊት ተገተረና ፣ "እንጋጠም ነውኮ የምልህ ! ፊት ለፊት እንድንገጥም እጠይቃለሁ ። ከሰማይ በታች በማ ንም ያልተሸነፈውን ጦረኛ ፣ በግንባር መግጠም አለብህ ! በታዋቂዉ ጦረኛ በዶን ኪኾቴ ዴላማንቻ እንኳ ፣ ድል ያልተመታው ጦረኛ ነው ዛሬ ሊገጥምህ እዚህ የቆመው" እያለ ዶን ኪኾቴ ፉከራውን ደጋገመው ።

አንበሳዉ ፍም መስለው በሚያስፈሩ ትላልቅ ዐይ ኖቹ ከመጠበቂያው ውስጥ ሆኖ ፣ ዶን ኪኾቴን በጥንቃቄ ያስተውለው ጀመር ። ያንበሳው አስተያየት የማንንም ወንድ ልብ የሚያሸብር ነበር ፤ ጀግናው ዶን ኪኾቴ ግን ፍንክች አላለም !

"ልገጥምህ ዝግጁ ነኝኮ !" እያለ ዶን ኪኾቴ አም ባረቀ ።

ሆኖም ፣ ግራሙ አንበሳ የዶን ኪኾቴን እንቅስቃሴ ከምንም ሳይቆጥር ደጋግሞ ካዛጋ በኋላ ፣ ዘንፈል ብሎ እንደ መተኛት ከጀለው ።

"ጉዳዩ ገባዎት ጌታዬ ?" አለ ያንበሳዉ ጠባቂ ፣ "እዩት ኩራት ሊሰማዎ ይገባል እዉሬውን ! አስገብረ ውታል ። አንበሳዉ በጣም ስላፈረዎ መረታቱን ሳይጋ ጠም በመተኛት አመነልዎ" አለ ።

"ሐቅ ነው" አለ ዶን ኪኾቴ ።

"ከዚህ የበለጠ ምን ይፈልጋሉ ? ታላቅነትዎን በማ ይበገር ወኔ አስመስክረዋል ። ማንም ጀግና ቢሆን ጠላ

ቱን በግንባር ለመፋለም ፣ ከመመከትና ብሎም ከመግጠም ሌላ የሚያደርገው ነገር አይኖርም ።”

“ጌታው ጠባቂ ልክ ነህ ። በሩን ዝጋና የፈጸምኩትን የጀግንነት ሙያ የሚገልጽ የምስክርነት ቃልህ ማረጋገጫ የሠፈረበት ደብዳቤ ጻፍልኝ ፤ በሩን ዝጋው ። ነፍሳቸውን ለማዳን የፈረጠጡትንም እጠራቸዋለሁ ። የምስክርነት ቃልህንና የኔንም የጀብዱ ሥራ መስማት አለባቸው ” አለ ዶን ኪኾቴ ተኩራርቶ ።

ጠባቂዉ የአንበሳዉን መጠበቂያ በር ዘጋ ፡፡ ዶን ኪኾቴ መሐረም ጦሩ ጫፍ ላይ አስሮ ያውለበልብ ጀመር።

ሳንቾ ፓንሳ፣የመሐረሙን ምልክትነት ከሩቅ ለማየት የመጀመሪያው ሆነ። “ ተመልከት ! ተመልከት ! ጌታዬ እኒያን አንበሶች በሙሉ አሸንፏል ፣ ካልሆነ ግን ጀርባዩን ለጅራፍ እሰጣለሁ” አለና በሠረገላ ነጂዉ ላይ ፎከረበት ።

ሳንቾና ሠረገላ ነጂው ጥቂት ቆይተው ሁሉም ነገር መረጋጋቱን ካረጋገጡ በኋላ በዝግታ ወደዚያው አመሩ ።

ዶን ኪኾቴ ፣ የሠረገላውን ነጂ በፈገግታ ተመለከተና ፣ “ወዲህ ቀረብ በል ወዳጄ ! በቅሎዎችህን እንደገና ጫናቸው ። አንተ ሳንቾ ! አንተ ደግሞ ፣ ቦርሳህን ክፍትህ ለያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ወቄት ወርቅ ስጣቸው ፤ እዚህ ከእኛ ጋር የሥራ ጊዜአቸውን አባክነዋልና ” አለ ጦረኛዉ ወገቡን ይዞ ።

“ትእዛዝዎን በሙሉ ልብና ደስታ እፈጽማለሁ ። ግን ጌታዬ ! አንበሶቹ ወዴት ደረሱ ? ሞቱ ወይስ በሕይወት ይገኛሉ ? ” ሳንቾ ጠየቀ ።

የአንበሶች ጠባቂ ፣ በዶን ኪኾቴና በአንበሶቹ መኻል ስለ ተፈጸመው ፍልሚያ ዝርዝር መግለጫ በሥፍራው ላልነበሩት ሰጠ ። “አንበሳዉ ጀግናው ዶን ኪኾቴን ፣ ገና

ሲያየው ፣ በቆራጥነቱና በድፍረቱ ተደናግጦ ፣ ከመጨበጫ
ያው ጡቡጥ ውልፍች ሳይል መሸነፉን ቅስሙን ሰብሮ
በመግለጽ ተንበርክኳል ” እያለ ሞቅ ያለ የግጥሚያ
ውጤት ማብራሪያ አቀረበ ።

“ ታዲያስ ሳንቾ ይህ ምን ይመስልሃል ? እየው ወዳጄ
ከአስማቅ ይልቃል ” አለ ልብ-ሙሉው ጦረኛ ።

ለሁለቱ ሰዎች ወቂት ወርቅ ተሰጣቸው ። ሠረገላ
ነጂዉም በቅሎዎቹን ጫናቸው ። እንበሶቹም በሰዓቱ ምግ
ባቸው ቀርቦላቸው ተመገቡ ። የእንበሶቹ ጠባቂ ዛሬ ዒጋ
ጠመው መልካም ዕድል ፈንድቆ ሠረገላው እናት ላይ
ወጥቶ ፈጭ አለ ።

“ጌታዩ በደኅና ይሰንብቱ ! ምስጋና ይግባዎት ። ስለ
አስደናቂዉ የጀብዱ ሥራዎ ለንጉሡ በዝርዝር አስረዳቸ
ዋለሁ ” አለ ባርኔጣውን እንሥቶ ለዶን ኪኾቴ እያው
ለበለበ ።

“ ያየኸውን በሙሉ ግለጽላቸው ። ምናልባት ፣ ‘አንበ
ሶችን ሊያንበረክክ የቻለው ጀግና ማነው ? ’ ብለው ንጉሡ
ቢጠይቁህ ‘የአንበሶች ሁሉ አንበሳ ፣ የጦረኞች ሁሉ ጦረኛ
ነው’ በላቸው ፤ እኔም ዓለም በዚሁ ስም እንዲጠራኝ እፈ
ልጋለሁ ” አለ ታላቁ ጦረኛ ዶን ኪኾቴ ድምፁን ከፍ
አድርጐ ።

ሠረገላ ነጂዉ ፣ በቅሎዎቹን በአለንጋ ሾጥ ሾጥ አደ
ረጋቸውና ፣ በድምፁ ምልክት ሰጠ ። በቅሎዎቹም መን
ገዳቸውን ጀመሩ ። ሠረገላው በዝግታ ዘምበል ቀና እያለ
መንከባለሉን ቀጠለ ።

ዶን ኪኾቴና ሳንቾ ፓንሳም ለሌላ የጀብዱ ሥራ
ጉዞአቸውን ተያያዙት ።

ምትሐታዊ ጀልባ

ዶን ኪኾቴና ጋሻ ጃግሬዉ ሳንቾ ፓንሳ፣ በጸጥታና በርጋታ ቀስ በቀስ ሜዳውን ዘልቀው፣ሜካውን አጽር ጠው፣ መንደሮችን ሰንጥቀው፣ጉዞአቸውን በረዥሙ ቀፆ ይዘውታል ። ጉዞአቸው ሁሉ በሐዩና አስገራሚ ገጾሎች የተሞላ፣ ፀርግጥም እስደናቂነቱን ሁሉ መተረክ ቀርቶ፣ ግማሹን እንኳ እንዲህ ነበር ብሎ ጨልፎ ለማውሳት ያዳ ግታል ።

ዶን ኪኾቴና ሳንቾ ፓንሳ አንድ ቀን የቀትር ፀሐይ በገረረበት ወቅት ወደ ኤብሮ ወንዝ ይመጣሉ ። ጦረኛዉ ጀግና ፈረሱ ሮሲናንቴ ላይ ጉብ ብሎ የሚፈስውን ታላቅ ጅረት፣ በወንዙ ዳርቻ ያለውን ለምለም ጨፌና ሜካ ሲመ ለከት፣ልቡ የደስታ ክበር ይመታ ጀመር ። ጋሻ ጃግሬዉ ግን ደስ እንዳላለውና እንደ ቀፈፈው ከገጹ ይነበባል ። ምክንያቱም ባለፉት ቀናት መከራና ችግር ስለ ተፈራረ ቁበት በጣም ደክክሞታልና ነው ።

ወንዝ አጠገብ እንደ ደረሱ፣ ዶን ኪኾቴ አንዲት ጀልባ ከውሃው ውስጥ ይመለከታል ። ጀልባዋ ከግንድ ጋር በገመድ ተጠፍራለች ። ጀልባይቱ መቅዘፊያም ሆነ ኬላይ አጐብር አልነበራትምና በምትፈጥረው እንቅስቃሴ ተን ሳፈፉብኝ ብላ የምታስጐመጅ ዐይነት ናት ።

ጀግናው ከፈረሱ ዱብ ብሎ ጋሻ ጃግሬውም ከአህ ያው እንዲወርድ ትእዛዝ ሰጠ ።

"እንግዲህ ሳንቾ እንስሶቻችንን እዚህኛው ዛፍ ቅርንጫፍ ላይ እንሠራቸው " አለ ዶን ኪኾቴ ።

" ለምንድን ነው እዚህ የምንወርደው ጌታዬ ? " ትእዛዙን ተቀበለና ጥያቄ አቀረበ ።

" ይህች ጀልባ ተዘጋጅታ የምትጠብቀው እኛን መሆኑን ዕወቅ ፤ ጀልባዋም እኔ አንድ ሣፈርባትና አን ዱን ምርኮ ጦረኛ ወይም አንዱን ባለ ማዕረግ ሰው ከችግር ለማዳን ትገፋፋኛለች ፤ እንዲያውም ለዚህ…እን ዲያውም ለዚህ ዓላማ የምትጠብቀኝ ናት !! " አለ ዶን ኪኾቴ ።

" ለዚህ ከሆነ ጀልባዋ የምትጠብቅን ተደንቄም አላበራ ! " አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

"ነው እንጂ! ባነበብኳቸው መጻሕፍት ሁሉ ምት ሐተኞች እንዲህ ማድረግ የዘልዓለም ልማዳቸው ነው ። አንድ ጦረኛ በአደጋ ላይ ሲወድቅ ፣ ሌላዉ ጦረኛ ሕይ ወቱን ማትረፍ አለበት ። ስለሆነም ለአዳኙ ጀግና ጀልባ ይዘጋጅለትና ከመቅጽበት ችግሩ ከደረሰበት ሥፍራ ይዳ ዛል ፤ ምንም እንኳ መንገዱ ሦስት ሺህ ምዕራፍ ቢሆንም መሔድ አለበት ። "

" የሚያስደንቅ ነው " አለ ሳንቾ ።

"አይጠረጠርም ። እና ፣ ስለዚህም ነው ይህች ምት ሐታዊ ጀልባ እዚህ የቆመችው ። ከብቶቻችንን እዚህ ጥላው ሥር አስረን ጀልባዋን እንሳፈር " አለ ዶን ኪኾቴ ።

" እንዴታ ! እንዴታ ! የጌታዬን ትእዛዝ መፈጸም አለብኝ ። ግን'ኮ ይህች ጀልባ ምትሐታዊ ጀልባ አይደለ ችም ። የአንድ ዓሣ አስጋሪ ጀልባ መሆን አለባት ።

" በርግጥ እንዲህ ዐይነቶቹ አብዛኛውን ጊዜ የዓማ አጥማጆች ጀልባዎች ናቸው ። ስለሆነም ፈጥነን እንሳ ፈርና ጉዞአችንን እንጀምር " አለ ዶን ኪኾቴ ።

ጦረኛዉ ዘሎ ጀልባዋ ላይ ተቀመጠ ። ሳንቾም ተከተለውና ጀልባዋ የታሠረችበትን መልሕቅ ፈታታ ፤ ጀልባዋ በውሃው ላይ በዝግታ መንሳፈፍ ቀጠለች ። ጀል ባዋ ወደቡን ለቅቃ መጓዝ ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ፣ርቃ ከመሔድ በስተቀር ወደ ኋላ ለመመለስ የሚያስችላት ዘዴ አለመኖሩን ሲረዳ፣ ሳንቾ በፍርሃት ይንቀጠቀጥ ጀመር ።

" ውድና ቅርሶቻችን የሆኑትን ምርጥ እንስሶቻችንን ዳግመኛ እናያቸውም ማለት ነው ። ጥለናቸው በመራቃ ችን ምስኪኑ አህያዬ ሲያናፋና ሲያላዝን ይሰሙ ጌታዬ ! ሮሲናንቴም ከልጓሙ ጋር እልህ ይዞት እንዴት እንደ ሚታገል ይመልከቱ ! እናንተ ምስኪናን ውድ ወዳጆቼ ! በሉ ደኅና ሰንብቱ ! " እያለ ሳንቾ ፓንሳ ያለቅስ ጀመር ።

በሳንቾ ልቅሶና ጩኸት ዶን ኪኾቴ ትዕግሥቱ አለቀ ።

"ፈሪ! ምን ያስፈራሃል ? ማን ነው ከኋላህ የሚያ ባርርህ? ማን ነካው ? ምነው ! እነሆ እስካሁን ድረስ ሰባት ወይም ስምንት መቶ ምዕራፍ ተጉዘናል ። ባልሳሳት አሁን በቅርብ ዓለምን ሁለት ላይ የሚከፍላትን መሥመር እናል ፋለን ። "

" አሁን ካሉኝ መሥመር ላይ ከደረስን በኋላ ምን ያህል ምዕራፍ መጓዛችን ነው ? "

"የትዬ የለሌ !"

ጀልባዋ ጅረቱ ፣ ቁልቁል እየተወረወረ ከሚፈስበት አካባቢ ደረሰች ፤ ከበታች ሁለት ትላልቅ የውሃ ወፍጮ ቤቶች ጅረቱ መኻል ጉች ጉች ብለዋል ።

"ተመልከት! ተመልከት የኔ ሳንቾ! ያ፤ኩ-ተማ ወይም ቤተ-ግንብ ይታይሃል? እዚያ ነው የሆነ ጦረኛ እስረኛ ሆኖ ያለበት ወይም የሆኑ ልዕልት ያለውድ በግድ ተግዘው የሚገኙበት።"

"ምን ማለትዎ ነው? እነዚያ ቤተ-ግንብ አለመሆናቸውን መለየት አይችሉም እንዴ? እህል ለመፍጨያ የሚያገለግሉ የውሃ ወፍጮዎች ናቸው'ኮ" ሳንቾ መለሰ።

"ቃገሥ ሳንቾ! በእርግጥ ወፍጮ እንደሚመስሉዐውቃለሁ፤ ይህ ሁሉ የመተተኞች ደባ ውጤት ነው። እኒያ እርኩሶች ሁሉን ነገር ከተፈጥሮ ቅርጹ ወደ ሌላ መልክ መለወጥ እንደሚችሉ ሊዘነጋህ አይገባም። የኔዋን ዱልሲኒያን እንኳ እንዴት እንደ ለወጧት የምታውቀው ጉዳይና በዐይንህም ያየኸው ነው።"

ድንገት ጀልባዋ በከፍተኛ ፍጥነት ቁልቁል ተምዘገዘገች። ወፍጮ ቤቶቹ ውስጥ የነበሩት ሰዎች ሁሉ፣ ይህን አደጋ ሊያስከትል የመጣውን ተንሳፋፊ ተመለከቱና፣ ረጃጅም እጠናዎች ይዘው፣ ወፍጮው ማሽከርከሪያ ውስጥ ከመግባቱ በፊት፣ አሽቀንጥረው ለማውጣት ተዘጋጁ። እህል አስፈጭዎች በመሆናቸው መላ ሰውነታቸው በዱቄት የተሸፈነ በመሆኑ፣ ፍጥረታቸው ልዩና አስፈሪ ይመስላል።

"እንዴት ነው ነገሩ! በጀልባዋ ውስጥ ያላችሁት እብዶች ናችሁ፣ ወይስ ጤነኞች? ዘላችሁ በፍጥነት ካልወረዳችሁ የወፍጮው ማሽከርከሪያ ይጉማምዳችኋል!" እያሉ ይጮኹ ጀመር።

" ቀደም ሲል ነግሬህ አልነበረም ሳንቾ፣ ይህ ቦታ ኃይሌንና ማንነቴን የማሳይበት ነው አላልኩህም ነበር? ተመ

ልክት እኒህ ጉግማንጉኞች ሊያጠቁን ሲመጡ ! እኔ ግን ማንነቱን አሳያቸዋለሁ ” አለ ዶን ኪኾቴ በደም ፍላት ።

ዶን ኪኾቴ ጀልባዋ ውስጥ ቆመና ፤ በወፍጮ ቤቱ ሠራተኞች ላይ የስድብ ናዳ ያወርድባቸው ጀመር ።

“ የማትረቡ ፈሪዎች ናችሁ ! በቤተ-ግንባችሁ ውስጥ ፀምርኮ ያስቀመጣችኋቸውን እስረኞቻችሁን በአስቸኳይ ነጻ ልቀቋቸው ። እኔም ዶን ኪኾቴ ዴ ላ ማንቻ የአንበሶች ጀግና ፤ እነዚህ እስረኞቹን ነጻ እንዲወጣ የተላኩ መሆኔንም ዕወቁ ! ” እያለ ዶን ኪኾቴ ይፎክር ጀመር ።

ጉራዴውን መዝዞ ፣ ከጠላቶቹ ጋር እንደሚጋጠም በአየር ላይ ደጋግሞ አወናጨፈው ። የወፍጮ ቤቱ ሠራ ተኞች ግን ፣ ድርጊቱን ከምንም ሳይቈጥሩ አጠናቸውን ጨብጠው ጀልባዋ ተሽከርካሪው ውስጥ እንዳትገባ ተዘ ጋጅተው ይጠብቁ ጀመር ።

ሳንቾ ፓንሳ ፣ ጀልባዋ ውስጥ ተደፍቶና ተንበርክኮ ከዚህ መዓት እንዲያወጣው ጸሎቱን ተያይዞታል ። እው ነትም ጀልባዋ ወደ ተሽከርካሪው በቀጥታ በመጠጋቷ የዕልፈት ቀናቸው የተቃረበ ይመስላል ። የወፍጮ ቤቱ ሠራተኞች በእርዳ ተረዳዳ ብያዙት አጠና ጀልባዋን ሰቅ ሰቀው ገለበጧት ።

ዶን ኪኾቴና ሳንቾ ፓንሳ ውሃ ውስጥ ሰጠሙ ። ሆኖም ሁለቱም ዋና ይችሉ ነበርና ፣ ከወዲያ ወዲህ ሲን በጫረቁ ፣ የጦረኛው ጥሩር ክብደት ሁለት ጊዜ ወደታች ሲደፍቀው ፣ አጋጣሚ ሆኖ የወፍጮ ቤቱ ሠራተኞች ዘለው ጅረቱ ውስጥ በመግባት በአሳር በመከራ ጐትተው ባያ ወጧቸው ኖሮ ፣ የጌታውና የጋሻ ጃግሬው የመጨረሻ ቀን ትሆን ነበር ።

ሁለቱ ጀግኖች በስንት መከራ ትንፋሻቸው ተመ ልሶ ነፍሳቸውን ዘርተው እንዳበቁ ፣ የጀልባዋ ባለቤት የሆ ነው ዓሣ አስጋሪ ጅረቱን ተከትሎ ሲከንፍ ደረሰ ። ያቺ ብቸኛ ንብረቱ የሆነች ጀልባ እንኩትኩቷ መውጣቱን ባየ ጊዜ እጅግ በጣም በገነ ። ሳንቾ ፓንሳ ላይ ጉብ አለና በክርን ይደቁሰው ጀመር ።

"የጀልባዬን ዋጋ ትከፍለኛለህ !" እያለ በንዴት ዶጋግሞ ጮኸ ።

"የጀልባህን ዋጋ ልከፍልህ ዝግጁ ነኝ ። ነገር ግን እኚህ ሰዎች ያለ አግባብ ያሰሯቸውን ሰዎች በአስቸኳይ ከቤተ-ግንቡ ውስጥ ነጻ መልቀቅ ይኖርባቸዋል ። አሁን የጠየቅሁት ሁሉ ካልተሟላ ፣ የጀልባህ ክፍያ ጉዳይ ያጠ ያይቃል" አለ ዶን ኪኾቴ ።

"የምን ቤተ-ግንብ ነው የምትለው? የምን እስረኞች? አስረዳን እንጂ ጌታው ምን እንደምትል ሲገባን አልቻ ለም ።" የወፍጮ ቤቱ ሠራተኞች ጠየቁ ።

"ለእናንተ መንገር በድንጋይ ላይ ውሃ እንደ ማፍ ሰስ ይቈጠራል ። መልካም ሥራ እንድታከናውኑ እናን ተን ከማሳመን ይልቅ ከድንጋይ ጋር መሟተሙ ይሻላል" አለና ዶን ኪኾቴ ፣ "እንደሚገባኝ ከሆነ ሁለት ተፎካካሪ አስማተኞች ናቸው በዚህ ጀብዱ ሥራ ውስጥ የተጋጩት። አንዱ ጀልባ ለእኔ ላከልኝ ፤ ሌላው ተቀናቃኝ ጀልባዋን ወንዙ ውስጥ ገለበጣት ። ጉዳዩ ግልጽ ነው ።በሤራ ላይ ሌላ ሤራ ሲፈጸም እኔ ምንም ማድረግ አልችልም" አለ ዶን ኪኾቴ እጅግ በጣም በሽቆ ።

ፊቱን ወደ ወፍጮ ቤቱ መለሰና ዐይኑን ከወፍጮ ማሽከርከሪያዉ በላይ ከሚገኘው መስኮት ላይ ተክለ ።

“ወዳጆቼ ሆይ!” እያለ ድምፁን በጣም ከፍ አድርጎ
መጣራት ጀመረ ።

“ወዳጆቼ ሆይ! ማንም ይሁን ማንም እዚያ እስር
ቤቱ ውስጥ በመሠቃየት ላይ ያላችሁ ሁሉ — እባካችሁን
አድምጡኝ!! በደረሰብኝ መጥፎ አጋጣሚ ይቅርታች
ሁን እጠይቃለሁ፤ ምነው ቢሉ ነጻ ላወጣችሁ አልቻል
ኩም ። ሌላ ጠረኛ ጀግና መጥቶ ይህን የጀብዱ ሥራ እስኪ
ፈጽም ድረስ የመልካም ዕድላችሁን ቀን ተጠባበቁ” አለ
ዶን ኪኾቴ በተሰባበረ ድምፅ ።

ይህን ተናግሮ ሲፈጽም ፣ ለዓሣ አሥጋሪው ሻምሳ
ሪያል (ዱካት) እንዲከፍለው ሳንቾን አዘዘው ። ሳንቾ ቅር
እያለው ትእዛዙን ተቀበለ፤ ምክንያቱም ሳንቾ በምንም
ዐይነት መንገድ ከገንዘቡ መለየት አይወድም ።

“እንዲህ ዐይነት ሁለት ጉዞ ካደረግን ግምጃ ቤታችንን
በሙሉ ሊያራቁተው ይችላል” አለና ሳንቾ አጉረመረመ ።

ዓሣ አሥጋሪውና የወፍጮ ቤቱ ሠራተኞች አፋቸ
ውን ከፍተው ፣ ሳንቾንና ጌታውን እንደ ጉድ ይመለከቷ
ቸው ጀመር ። እኒህ ሁለት ተአምረኛ ጌታና ጋሻ ጃግሬ፣
እንዴት እመኻላቸው ሊገኙ እንደ ቻሉ ነገሩ ግራ ገብቷ
ቸው ከመፋጠጥ በስተቀር መልስ ሊያገኙ አልቻሉም ።
በመጨረሻም ፣ ‘እኒህ ሁለት እንግዳ ነገሮች አእምሮአቸ
ውን የሳቱ እብዶች መሆን አለባቸው’ ብለው ከደመ
ደሙ በኋላ ፣ የወፍጮ ቤቱ ሠራተኞች ወደ ሙያቸው ፣
ዓሣ አሥጋሪውም ወደ ደሳሳ ጎጆው ፣ ጌታና ጋሻ ጃግሬን
ጥለው መለስ አሉ ።

ዶን ኪኾቴና ሳንቾ ፓንሳ ግን ፣ ደክመው ፣ አዝነውና
ተንሳቅለው ፣ ወደ እንስሶቻቸው ረዥሙን መንገድ ፣ ጅረ
ቷን ተከትለው ሽቅብ በዝግታ ተመለሱ ። እነሆ የምታሐ
ታዊ ጀልባዋ ታሪክም በዚሁ ያከትማል ።

ከመስፍኑና ከሰፋኒቱ ጋር

ብሩህ ቀን ነበር ። ፀሐይዋ የዕለት ጉዞዋን ፈጽማ ልትጠልቅ አካባቢ ፣ ሁለት ተጓዦቻችን በምስት አቅጣጫ ቃጥሮ ወደ አማረ ለምለም ሜዳ ድንገት ደረሱ ። በሜዳዉም ውስጥ ፣ ለዶን ኪኾቴ ዶጋግ የመሰሉ ለአደን የወጡ ሰዎች በሩቅ ተመለከቱ ። ዶን ኪኾቴ በማንነታቸው ግምቱ ምንም አልተሳሳተም ።

ቆም ብለው ከሩቅ ተመለከቷቸው ። የቡድኑ አለቃ አንዲት እመቤት ስትሆን ፣ እጅግ በጣም በተዋበ አረንጓዴ ልብስ ተሽሞንሙናለች ። በነጭ ድንጉላ ፈረስ ላይ ተቀምጣለች፤ኮርቻው በብርማ ግላስ ያጌጠ ፣ ዕቃዉ በሙሉ በልዩ ጌጣ ጌጥ የተንቆጠቆጠ ነበር ። በግራ እጅዋ ላይ አንድ ለማዳ አሞራ ተቀምጦ ስለ ነበር ፣ በዚህ ምልክት ሴቲቱ የቡድኑ መሪ ወይም እመቤት መሆንዋን ዶን ኪኾቴ ተረዳ።

ዶን ኪኾቴ በዝግታ ጋሻ ጃግሬውን ጠራና ፣ “ ወዳጄ ሳንቾ ፣ ፈጥነህ ወደዚያች ነጭ ድንጉላ ፈረስ እመቤት ሒድና የአንበሶች ጀግና እጅግ ትሕትና በተመላበት አክብሮት ወደር ለሌለው ቁንጅናዎ ተገቢውን ክብርና ሰላምታ ያቀርባል ” ብለህ ንገራት ። ነገር ግን ፣ አንድ የማስጠንቀቅህ ጉዳይ አለ ፤ ይኸውም የተለመደውን ተረትና የምሳሌያዊ አባባሎችህን እያዥጎደጎድህ ጉራህን በመንዛት ልታወቅ ልታወቅ እንዳትል ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“ ትእዛዝዎ ተፈጻሚ ይሆናል ” አለና ሳንቾ ፣ ግራጫ አህያው ሊጋልብ በሚችልበት ፍጥነት መንገዱን ወደ

ሰዎቹ ዘንድ ሊቀና ፤ አዳኟዋ እመቤት ካለችበት ሊደርስ ፣ ከአህያው ወርዶ እፊቷ ተንበረከከ ።

" ውብ የሆንሽው እመቤት ሆይ ! እዚያ ማዶ የም ታይው ጦረኛ ፣ የአንበሶች አንበሳ የተባለ ነው ፤ እሱም ጌታዬ ነው ። እኔን የላከኝ ፣ እርሱ አንቺን ውቢ ቷን እመቤት ከማገልገል ሌላ ፍላጎት እንደሌለው እን ድነግርሽ ነው ፤ እና . . . እመቤቴ . . . .እና . . . . " አለ ሳንቾ ።

"መልካሙ ጋሻ ጃግሬ ሆይ! ከተንበረከክበት እንድ ትነሣ እጠይቃለሁ ። የአንበሶችን አንበሳ ወይም የጦረኛዉን ማንነት ሰምቻለው ። እና ፣ የርሱ ጋሻ ጃግሬ ሆነህ መንበ ርከክህ ተገቢ አይደለምና ትነሣ . . . . . ትነሣ ! " አለች እመቤቲቱ ።

ሳንቾ ከተንበረከከበት ተነሣ ። በእመቤቲቱ ቁንጅና እጅግ በጣም ተደነቀ ። የጌታዉን ዝና የሰማች መሆንዋን በማወቁም በጣም ተገረመ ። ትእዛዝዋን ለመቀበል አፉን ከፍቶ ፣ እንደ ዕንጨት ተገትሮ ቀረ ።

" እባክህን ንገረኝ እስቲ ይህ ፣ ጌታህ የታወቀው ጀግናና ሊቅ 'ዶን ኪኾቴ ዴላ ማንቻ' የሚባለው አይደለ ምን ?" ስትል ጠየቀች ።

" እመቤት ምስጋና ይግባዎትና ፣ ልክ ነዎት ፤ እሱዉ ነው ። የጋሻ ጃግሬውም ስም ሳንቾ ፓንሳ ይባ ላል ፤ ያ ጋሻ ጃግሬም እኔ ራሴዉ ነኝ ፣ እመቤት ።"

"ይህን ሁሉ መስማቴ ደስ ብሎኛል " አለች እመ ቤቲቱ ።

" እኔም እጅግ ደስ ብሎኛል " አለ ሳንቾ ።

"ወዳጄ ሳንቾ ! አሁን ወደ ጌታህ ተመለስና ፡ ወደ ግዛቴ በመምጣቱ ደስ ያለኝና ፡ ልቀበለውም ዝግጁ መሆኔን ግለጽለት ። እርሱን ከማስተናገድ የበለጠ ደስታ እንደሌለኝም ይወቀው" አለች እመቤቲቱ ።

ሳንቾ በደስታ ፈነደቀ ። ወደ ጌታውም ፈጥኖ ተመለሰና ፡ እመቤቲቱ ያለችውን በሙሉ ፡ ቃል በቃል መልሶ ነገረው ።

ዶን ኪኾቴም በጸጥታ አደመጠው ። ኮርቻው ላይ ተመቻችቶ ተቀመጠና የጥሩሩን አለባበስ አበጃጀ ። ሮሲናንቴን አስነቃና ግርማ ሞገስ ባለው አረማመድ ፈረሱን እየመራ የአዳኝቿን እመቤት እጅ ለመሳም ገሠገሠ ።

ሴቲቱ ሰፋኒት ነበረችና ፡ ዶን ኪኾቴ እርሷ ዘንድ ከመድረሱ በፊት ፡ ባሏ ወዳለበት ተጠግታ ፡ ሁለቱም ጦረኛዉን በጉጉት ይጠባበቁ ጀመር ። ስለ ዶን ኪኾቴ መከራ ፡ ድካምና ገድል በሰፊው ሰምተውነበርና ፡ ተገናኝተው በአካል ፡ በአምሳል ሊያውቁት መፈለጋቸው ይታወቅባቸዋል።

ዶን ኪኾቴ ርምጃውን አፋጥኖ እቦታው ከደረሰ በኋላ ሊወርድ ሲል ፡ ሳንቾ ፓንሳ ቀርቦ ርካቡን ሊይዝለት ግልቢያውን አፋጠነ ። ነገር ግን ልክ ከአህያው ሊወርድ ሲል ተረከዙ ኮርቻው ውስጥ ተሰንቅሮ በመያዙ ተገለበጠና ራሱ መሬት ሲነካ ሰውነቱ የተሰቀለ ይምስል ቁልቁል ተንጠለጠለ ።

ሁኔታው አሥቂኝ ቢሆንም ፡ ሁሉም ሰው ትኩረቱ ዶን ኪኾቴ ላይ በመሆኑ ፡ በዚህን ጊዜ የሳንቾን ግብግብ ማንም አላጤነለትም ።

እንደ ወጉ ዶን ኪኾቴ ከፈረሱ ሊወርድ ርካቡን ዘወትር ጋሻ ጃግሬው እንደሚይዝለት ቢያውቅም ፡ ልጓ

ሙን ገታ አድርጎ ያለ ረዳት ሲወርድ ተዘጋጀ ። ድንገት ከሙሉ ኃይሉና ክብደቱ ጋር ወደ ርካቡ እግሩን ዘረጋ ። ርካቡ በሰው ባለመያዙ የሮሲናንቴ ኮርቻ ዛብ ላልቶ ፣ ጦረኛዉን እፈረሱ እግሮች መኻል ገለበጠው ።

የመስፍኑ አገልጋዮችም ተንደርድረው ዶን ኪኾቴን ከወደቀበት ሊያነሡት ሮጡ ። ብዙ አልተጎዳም ። አባ ራውን ከእጆቹ ላይ አራገፈና ፣ እንክስ እያለ ሰፋኒቱና መስፍኑ ወደ ሚጠብቁት ሥፍራ አመራ ።

መስፍኑ ቀረበውና በወዳጅነት መንፈስ ከዐቀፈው በኋላ ፣ “ ይህን የመሰለ መጥፎ አጋጣሚ በግዛቴ ውስጥ ስለ ደረሰብህ አዝናለሁ ” አለ መስፍኑ ።

“ ገናናው መስፍን ሆይ ! አሁን የደረሰብኝን እንደ መጥፎ አጋጣሚ አልቈጥረውም ፤ ግርማ ሞገስ ከተጎናጸ ፈው ፣ ከመስፍንነትዎ ጋር ስመገናኘት በመቻሌ ከፍተኛ ኩራትና ደስታ ተሰምቶኛል ። ጋሻ ጃግሬዬ የፈረሴን ዛብና ርካብ ከማጥበቅ ይልቅ አፉን መክፈት ይቀናዋል ። እፈ ረስ ጀርባ ላይም ሆነ ፣ ወይም በእግሬ ፣ ወይም መሬት ላይ ተንጋልዬ ። ትልቁ ቁም ነገር ትእዛዝዎን ለፈጸም ዝግጁ መሆኔን ይወቁልኝ ” አለ ጦረኛዉ ዶን ኪኾቴ በተጠንቀቅ ቁሞ ።

ጥቂት ቆየት ብሎ ለሰፋኒቱ ተገቢውን ሰላምታ ሊሰ ጣት ፣ ስለ ውበቷና ጥበቧ ውዳሴ ለማበርከት በቀጥታ ወደ ርሷ ተራመደ ።

የጠቅላላው ጉዳይ መቋጫ የሆነው ፣ ጀግናው ጦረኛ በመስፍኑ ቤተ-ግንብ እንዲሰነብት ስለ ተጋበዘ በአቅራቢ ያው ከሚገኘው ቤተ-ግንብ እንዲቆይ መሆኑ ነው ።

“የአንበሶች ጀግና የሆንከውን ዝነኛዉን ጦረኛ ፣ በቤተ-ግንባችን ስናስተናግድህ ክብርና ኩራት ይሰማናል ።

አንተን ለሚያህል ታላቅ ጀግና ክብርና ድል ሲባል የተዘጋጀ ልዩ የደስታ በዓል ነውና ፤ የክብር እንግዳችን በመሆንህ ደስታ ይሰማናል ” አለ መስፍኑ ።

ዶን ኪኾቴ ፈረሱ ሮሲናንቴ ላይ ጉብ አለ ። መስፍኑም ለክብሩ በተዘጋጀለት ፈረስ ተቀመጠ ። ልፍኒቷ በዶን ኪኾቴና በመስፍኑ መኻል ሆና፣ በፈረሶቻቸው ተጉዘው ኮረብታ ላይ ወደ ተሠራው ቤተ-ግንባቸው ብዙ ሳይቆዩ ደረሱ ።

ሰፍኒቱ በሳንቾ ሁኔታ እጅግ በጣም ተደሰተች ። ለጥቃቅን ጉዳዮች ሁሉ ይቅርታ መጠየቁ ፤ ተረትና ምሳሌዎችን ቀላቅሎ ጨዋታ አጣፍጦ በማቅረብ ችሎታ ከልክ በላይ አስደሰታት ።

“ጋሻ ጃግሬህ ከእኛ ጎን ሆኖ እንዲጓዝ ለምን አትፈቅድለትም ?” ስትል ሰፍኒቱ ዶን ኪኾቴን ጠየቀችው ።

ሳንቾ ይህን ሰምቶ ፤ የማንንም ግብዣና ትእዛዝ ሳይጠብቅ በሰፍኒቱና በመስፍኑ መኻል ገብቶ ፤ አራተኛ ተጓዥ ሆነ ። ሥነ ሥርዓቱን በመጠበቅ ሁሉም ከአጃቢዎቻቸው ጋር ወደ ቤተ-ግንቡ ተመሙ ።

ቤተ-ግንቡ ሲደርሱ ትንሽ ሲቀራቸው ፤ መስፍኑ ፈረሱን ኮርኩሮ ቀድሞአቸው ሸመጠጠ ። መስፍኑ ቀድሞ ወደ ቤተ-ግንቡ የጋለበበትም በምክንያት ነበር ። ለዛሬው እንግዳ መስተንግዶ ለማዘጋጀት ፤ ሠራተኞቹ ሁሉ ጀግናው ጦረኛ ዶን ኪኾቴ በሚመጣበት ጊዜ ጨዋ እንዲሆኑና ተገቢውን ክብር እንዲሰጡት ለማስጠንቀቅ ፤ ነበር መስፍኑ ቀድሞ የጋለበው ።

በመጨረሻም፣ አጀቡ እንዳለ ከቤተ-ግንቡ ዋና በር ላይ ሲደርስ ፤ የመስፍኑ አገልጋዮች አደግድገው ተቀበ

ኗቸው ። ጃኖና ፈገግታም እጀ-ጠባብ አጥልቀው ሲታዩ በሌሊት ልብስ ያጌጡ ይመስሉ ነበር ።

አገልጋዮቹ በቀጥታ ወደ ዶን ኪኾቴ አመሩ ። ትከሻውን ደጋግፈው ፤ ርካቡንና ዛቡን ወጥረውለት ከኮርቻው ላይ በሥነ-ሥርዓት አወረዱት ።

“ታላቁና ኃያሉ ጌታ ሆይ ! ሰፋኒቷን ከፈረሷ እንዲያወርዷት እንጠይቃለን ” አሉት ፍጹም ትሕትናን ተላብሰው ።

ዶን ኪኾቴም ፈጥኖ ትእዛዛቸውን ተቀበለና ፤ ሲዘገጃጅ ፤ እመቤቲቱ ግን እምቢ አሻፈረኝ አለች ። ዶን ኪኾቴ በውዳሴ ቃላት ቢወተውታትም ፤ ውብ የምስጋና ቃላት ቢያዘንብም ፤ ሰፋኒቷ ከፈረሷ ላይ ንቅንቅ ሳትል ቀረች ።

“ በባለቤቴ ትከሻ ካልሆነ ፤ በጭራሽ አልወርድም” አለች ።

መስፍኑ መጥቶ በሥነ-ሥርዓት አወረዳት ። ዶን ኪኾቴም ለጥ ብሎ ይቅርታ ከጠየቀ በኋላ ፤ እጇን እንደያዘ እየተራመደ ዋናውን በር ዘለቁ ። ከመስፍኑ እልፍኝ ሲደርሱ ፤ ሁለቱ ቆንጆጆች ልጃገረዶች የተዋበ ካባ በዶን ኪኾቴ ትከሻ ላይ ደረቡለት ። በመስፍኑ ቅጽር ግቢ ውስጥ የተገኘው ሕዝብና ሠራተኛ ፤ ወንዱ ሴቱ ድምፁን ከፍ አድርጎ ፤ “ እንኳን ደኅና ገቡ ! እንኳን ደኅና መጡ ! የጦረኞች አበባና አለኝታ ታላቁ ጀግና ! እንኳን ደኅና ገቡ ! ” እያሉ በሆታና በዕልልታ ፤ በደማቅ ጭብጨባ ተቀበሏቸው ።

ይህ ሁሉ ሁኔታ ፤ ዶን ኪኾቴን ከልብ አስደሰተው ፤ ምክንያቱም እንዲህ በሕይወቱ ሙሉ ገና ነበር እውነተኛው

ጦረኛ መሆኑን ያረጋገጠው ። እንደ አንድ ስመ-ጥር ጦረኛ የተደረገለት ክብር ፣ ባነበባቸው የጦረኞች ገድል ውስጥ እንደተጻፈው ሆኖ ስላገኘው መንፈሱ በደስታ ረካ ።

ለታላላቅ የክብር እንግዶች ማስተናገጃ ተብሎ ወደ ተዘጋጀዉ አዳራሽ አጅበው ወሰዱት ። አዳራሹ በወርቅ ምንጣፍ ጌጦች የተንቈጠቈጠ ነበር ።

ዶን ኪኾቴ ጥሩሩን አውልቆ ለተመለከተው ፣ የሚ ያሳዝን ምስኪን ፍጡር ኖሯል ! አጥንቱ የሚቈጠር ፣ ከሲታ ረዥም አገዳማ ፣ ሞጋጋ አገጫምና ጥርስ-የለሽ ፣ እንዲ ያው ባጠቃላይ ማስፈራሪያ ይመስላል ። የሚያስተና ግዱት ልጃገረዶች ይህን ጣዕረ-ሞት የመሰለ ፍጡር ሲመ ለከቱ ሣቅ እፍን አድርጐ ያስጨንቃቸው ጀመር ።

ዶን ኪኾቴም ፣ በታላቅ ግርማ - ሞገስ ወደ ማረፊያ ክፍሉ አምርቶ ፣ ለራት ጊዜ የሚሆነውን ልብስ ለብሰ ። ዝናሩን ወገቡ ላይ ሸብ አድርጐ ፣ ጐራዴውን ታጥቆ ካባ ውን ትክሻው ላይ ደርቦ ፣ እንፋሮ በራሱ ላይ ደፋ ። በእ ንዲህ ዐይነት አለባበስ አምሮና አጊጦ ወደ አዳራሹ ሲመ ለስ ፣ በርግጥ ዶን ኪኾቴ ለመሆኑ ያጠራጥር ነበር ።

ዐሥራ ሁለት የአልፍኝ አሽከሮች ፈጥነው ቀረቡና፣ ወደ ምግብ አዳራሽ መንገዳቸውን አቀኑ ። ግማሹ ከፊት ግማሹ ከኋላ - ሁሉም በክብር አጅበውና አዳምቀው ተፈመዱ ።

የምግብ ገበታዉ ለአራት ሰዎች ብቻ ነበር የተሰና ዳው ። እዚያም ፣ መስፍኑ ፣ ሰፋኒቱና አንድ ቄስ ለዶን ኪኾቴ የክብር አቀባበል አደረጉለት ። በአራት ላይ ሲፈ ጸም የሚገባው ሥርዓት በወጉ ከተፈጸመ በኋላ ፣ ሁሉም በገበታዉ ዙሪያ ፣ በአራቱም ማዕዘን ተቀመጡ ።

ይህ ለዶን ኪኾቴ የተደረገለት መልካም ምግባር የተመላበት ሥነ-ሥርዓት በቂ ምክንያት አለው ። መስፍኑና ስፋኒቱ የሚሠሩት ቁምነገር ስላልነበራቸው ፣ ጊዜያቸውን የሚያጠፉበት የዋዛ ፈዛዛ ነገር ነበር የሚሹት ። ይህን ለዶን ኪኾቴ ያደረጉትን የክብር አቀባበልና መስተንግዶ እንደ ታላቅ ሥራና መዝናኛ ስለ ቆጠሩት ደስታውን አልቻሉትም ። መስፍኑና ስፋኒቱ አደን ሰልችቷቸዋል ፤ ዳማ መጫወት አንገሽግሿቸዋል ፤ አሽከሮቻቸውን ማሠራት አድክሟቸዋል ፣ ሙዚቃ መስማት፣.. ሁሉም ነገር ሰልችቷቸዋል ።

'ሕይወት ጣዕመ-ቢስና አድካሚ ናት ! ሕይወት የደስታና የፈንጠዝያ እንድትሆን ማድረግ አይቻልምን? ' ይሉ ነበር—መስፍኑና ስፋኒቱ ፣ ከዚህ ቀደም ደስታ ሲናፍቃቸው ።

ስለሆነም ፣ የዶን ኪኾቴና የጋሻ ጃግሬው ድንገት ከተፍ ማለት፣ለመስፍኑና ለስፋኒቱ የዓለም፣የደስታ ወቅት ፈጠረላቸው ። 'ከእኒህ ከፅሁለት ብርቅዬ ሰዎች ጋር ታላላቅ ስፖርታዊ ጨዋታዎች እናደርጋለን ። ዕድሜ ልካችንን በሙሉ የምንሥቅበት ትዝታ እናገኛለን ።' አለ መስፍኑ ደስ ደስ እያለው ።

ስፋኒቱም በመስፍኑ ሐሳብ ተስማማች ። ዶን ኪኾቴ ማረፊያውን እዚያው መስፍኑና ስፋኒቱ ቅጥር ግቢ ከሚገኘው ቤተ-መንግሥት እንዲያደርግ ጋበዙት ። ማንኛውም ሥልጣንና የንጉሥ አጫዋች ከሚሰጣቸው ደስታ ይልቅ ፣ከዶን ኪኾቴ የሚያገኙት ቀልድና ጨዋታ እጅግ የላቀ እንደሚሆን ዐወቁ ። ዶን ኪኾቴ በሰንበቱ ቁጥር ፣ በየዕለቱ መስፍኑና ስፋኒቱ በእሱና በጋሻ ጃግሬው ላይ አዳዲስ ቀልድና ጨዋታ ፣ አሥቂኝ ድርጊቶች በመፍጠር የደስታ

ጭላንጭታቸውን ያረኩ ጀመር ። ቀልድና ጨዋታው ሁሉ የማንንም ስሜት ሳይነካና መንፈስ ሳያስቆጣ ፡ ይኼናወን ነበር ። አንዳንዶቹን የጨዋታ ዐይነቶች በዝርዝር መግለጹ ጊዜና ቦታ ይወስዳል፤ቢሆንም ፡ ለአብነት ያህል አንድ ሁለቱን እናወሳለን ።

የእንጨት ፈረስ

አንድ ቀን ፡ መስፍኑና ሰፋኒቱዋ የዶን ኪኾቴን የገ ድል ዜና በመስማት ፊታቸውን ያዝናኑ ነበር ።

“በየዋህነቱ ዝናቱ የተረሰበት ልጡ ታውቃላችሁ እንዴ ? እኔ እበቀልለታለሁ ። እኩይ ድርጊቱን ለመዋጋት ቤል ዓለምን እዳርሳለሁ ። ጭራቆችንም ሆነ አስማተኞችን ጨርሶ አልፈራም ። አንድ በአንድ ወይም ሁሉ ንም ስለ እውነት ፡ ስለ ጥቅር ብዬ እዋጋቸዋለሁ ” አለ ዶን ኪኾቴ ደልቦ መሐሉን ።

ዶን ኪኾቴ ይህን ገድላዊ ንግግሩን በሚያሰማበት ወቅት ፡ እምቢልታና መለከት እየተነፋ ፡ ነጋሪት እየ ተጎሰመ ፡ የመንኮላኩሉ ልብስ የለበሱ ሰዎች ሁለት ባለ ቁቅሮች ወደ አዳራሹ ገቡ ። ከመንኮላኩሉ በጥቁ አንዲት የተ ከበረች ሴት ወይዘሮ ቅጹ ቃለቃ ላይ የተከፈለ ረዥም ካባ እንዝርፋ ፡ ፊቷን ተሸፋፍና ብቅ አለች ።

ሰዎች ሁለቱ ሴትዮ በሁለት ረድፍ ተሰልፈው፥ ሴት ወይዘሮዋ መኻላቸው በኩራት መስፍኑንና ሰፋኒቱን እንድ ቀኝና እቅጣጫቸውን አመቻቸላት ። ተከትሏት ይራመድ የነበረው ጋሻ ጃግሬዋ ፡ ይቺች ወይዘሮ የትሪፋልዲን ግዛት እመቤት የነበረችና ዛሬ ግዜ ጥቂት ረዥም ገዳና ፡ የደረ

ሰበትን ግፍ መከራና በደል ልትገልጽ ፣ መምጣቷን ዘር ዝሮ ተናገረ ።

መስፍኑ ፣ ወይዘሮዪቱን በታላቅ ክብር ተቀበሏት ። እጇዋን ይዞ ከሰፉኒቱ ጎን በወንበር ላይ አስቀመጣት ። ዶን ኪኾቴና ሳንቾ ፓንሳ ተሸፋፍና የገባችውን እመቤት ገጽ ለማየት በጉጉት ቆመው ይጠባበቁ ነበር ።

የሰላምታው ፣ የውዳሴውና የአቀባበሉ ሥነ ሥር ዓት ከተገባደደ በኋላ ፣ እንግዳዋ እመቤት ፣ “እዚህ የተከ በራችሁት ሕዝቦች መኻል ፣ ዶን ኪኾቴ ዴ ላ ማንቻሲማ የተሰኘ ጦረኛ ከዋና ጋሻ ጃግሬዉ ሲማ ኔሳንቾ ፓንሳ ጋር ይገኝ እንደሆን ብትገልጹልኝ ? ” ስትል የጥያቄ ዱብ ዕዳዋን አወረደችው ።

“ ፓንሳ ማለቱ እኔ ነኝ ። ዶን ኪኾቴም እዚሁ ይገ ኛል ። ክብርትና ንጽሕት እመቤት ሆይ ! እባክሽን እስ ገራሚ ወግሽን አውጊን ፣ እኛም ልናገለግልሽ ዝግጁ ሆነን በመጠባበቅ ላይ ነን ” በማለት ሳንቾ በአደባባዩ ከሚገኙት ሰዎች ሁሉ ቀድሞ ተናገረ ።

ቀጥሎም ዶን ኪኾቴ ፣ “ ዝነኛዉ ዶን ኪኾቴ ዴ ላ ማንቻ ይሉዎታል እኔ ነኝ ። ሙያዬና ተግባሬም የተጨቆኑ ትን መርዳት ስለሆነ ፣ አገልግሎቴ ለርስዎም ይደርስዎት ዘንድ ዝግጁ ሆኜ እጠባበቃለሁ ። ችግርዎን ይግለጹልን ፣ መፍትሔ ለመሻት ቢሳነን እንኳ ፣ የሐዘንዎ ተካፋይ እን ሆናለን ” አለ ቀኩራርቶ ።

ሽፍንፍኗ እመቤትም ፣ አዛማጋ ቅንፋዃን ከዋጠች በኋላ ፣ በኃይለ-ቃላት ወጓን መተርተር ጀመረች ።

ራቅ ብሎ ከሚገኘው ከካንዳያ ግዛት መምጣቷን ገለጸች ። እዚያም በአንድ ወቅት ክቡር እምክቡራን ከነ

በሩት ታላላቆች እንዲ እንደ ነበረችም ተናገረች ። እንዴ ማላምብሩና የተባለ ጠንቋይ ፣ በሚርቱ ፣ በመተቴና በም ትሐቱ ከክብሯና ከማዕረግ እንዳወረዳት ፣ እሷም ባፍዝ አደ ንግዝ እንደ ተጠመደች ፣ ታብራራለች ። ይህን አፍዝ አደ ንግዝና ሟርት የሚያረክስ ታላቅ ጀግናና ድል አድራጊ እስካልተገኘ ድረስ ፣ እሷንም ወደ ክብሯና ማዕረግ የሚ መልሳት ኃያል ሰው እስካላጋጠማት ድረስ ፣ ዕድሟ ልኳን ተዋርዳ ዓለምን እንደምትኖር በዝርዝር ታነበንብ ጀመር ።

"እሜቴ ! ሙያውን ለኔ ይተዉልኝ ። እርስዎ የሀ ገርዎን መንገድ ብቻ ይምሩን ። እስከ ዓለም ዳርቻ እን ኳን ቢሆን ሔጄ ልረዳዎ ዝግጁ ነኝ" አለ ዶን ኪኾቴ ።

እመቤቲቱም የካንዳያ ግዛት ብዙ ሺህ ምዕራፍ የሚ ያስኬድ መሆኑንና ፣ ከዚህ እስከዚያ በተራ መንገድ ለመድ ረስ ዓመታት እንደሚፈጅ ገለጸችለት ። እመቤቲቱ ንግግ ሯን በመቀጠል ፣

"ቢሆንም ጠንቋዩ ማላምብሩና ላንተ ግሩም ፈረስ ይልክልሃል ። ምትሐታዊ ፈረስ ነው የሚልክልህ ። ፈረ ሱም ከመቀመጫው ከንፎ ያላንዳች ችግር ፣ አፍታ እንኳ ሳይቆይ ፣ ካንዳያ ግዛት ሊያደርስ የሚችል ከነፋስ የፈጠነ ነው ። እስማተኛው ያንቱን ቆራጥ ጀግንነት ስለ ሰማ ፣ ግንባር ለግንባር ገጥሞህ የሞት ሽረት ፍልሚያ ለማድ ረግ ይፈልጋል" አለች ።

"እረ ለመሆኑ እኔን ለማጓጓዝ የሚላክልኝ ፈረስ ተፈጥሮው ምን ዐይነት እንደሆነ እባክዎን ግለጡልኝ ?" አለ ዶን ኪኾቴ ።

"ክላቪሌኞ የተባለ ፈረስ ሲሆን ፣ ፈረሱም ከዕን ጨት የተሠራ ሆኖ ፣ ጠንቋዩ ሜርሊን ለወዳጁ ለጴጥሮስ

አውሶት የነበረው ነው ። በእርግጥም ድንቅ ፈረስ ነው። ምግብ አምጡ አይል ፥ እንቅልፍ በዐይኑ አይዞር ፤ የፈረስ ጫማ የማይፈልግ ልዩ ፍጥረት ነው ። ክንፍ የለውም ፤ ቢሆንም አየሩን ሰንጥቆ ሲክንፍ ከምቾቱ የተነሣ በኩባያ የጨበጥከው ወሃ እንኳ ጠብ አይልም ። ይህን ፈረስ ለመጋለብ ድፍረት ካለህ እና . . . ” ንግግሯን ሳትጨርስ —

“ ድፍረት ካለህ ? ” በማለት ንግግሯን አቋረጠና ፡ “ ማነው ድፍረቴን ጠያቂ ? ፈረሱን ብቻ አምጡልኝ ፡ ፍንክች የማልል መሆኔን ታያላችሁ ” አለ ዶን ኪኾቴ ደረቱን ነፍቶ ።

“እንግዲያውስ ፈረሱ ማለዳ ተዘጋጅቶ ይጠብቅሃል” አለች እመቤቲቱ ።

በማግሥቱ ፡ ሲንጋጋ መስፍኑ ከነመላ ቤተሰቡ ፡ እንግዶቹና ወዳጆቹ ጋር የታቀደውን ምሥጢራዊ ገድል በዐይኑ ለማየት ወደ አትክልት ሥፍራው አመራ ። ሁሉም በደስታ ፈንድቀዋል ። ምክንያቱም የጠነሰሱት ጉዳይ ከፍተኛ ሐሴት ሊያስገኝላቸው ተቃርቧልና ።

ዶን ኪኾቴ ከዝግጅቱ ቦታ ፈጥኖ ደረሰ ። ጥሩሩን ለብሷል ፤ ጉራዴውን አንገንድሯል ፤ ጋሻውን ለማከናወን በወኔ ይቅበጠበጣል ። ሳንቾ ፓንሳ ፡ ከጌታው ጉን በመሆን ለሚመጣው ሁሉ ዝግጁ ቢመስልም ፡ በጉዞው ለመካፈል ግን ፈቃደኛ አልነበረም ።

ረፋዱ ላይ መለከት ተነፋ ። አራት ደን ጠባቂዎች አትክልት ሥፍራዉ መጡ ። ቅጠልያ ልብስ ተጐናጽፈው በራሳቸው ላይ የሐረግ ጉንጉን ደፍተዋል ። ቅርጹ ቢስ ፡ ቅልጥማም ከዕንጨት የተሠራ ፈረስ ተሸክመው ካመጡ በኋላ ከመሬት ላይ ቸከሉት ።

“ክላቪሌኞ፣ የተሰኘው ዝነኛው ፈረስ ማለት ይህ ነው” አለ የደን ጠባቂዎቹ አሲቃ። በዓለም ላይ እሱን የሚያህል እስካሁን አልተፈጠረም። ይህን ፈረስ መጋለብ እያስፈራኝም የሚል ወንድ እንዳለ ይሞክርና፣ ከመቅጽበት ወደ ካንዲያ ግዛት ሊበርር ይችላል። እኔ ነኝ የሚል ደፋር ጀግናም፣ ጋሻ ጃግሬ እንዳለው፣ አብሮት ይፈናጠጥ፤ ፈረሱ ይበልጥ የሚከንፈው ክብደት ሲበዛበት መሆኑንም ማወቅ ያስፈልጋል” አለ የደን ጠባቂዎቹ አሲቃ።

“ልጓም የት አለው? ልጓም ከሌለው ይህ ታላቅ ፈረስ በምን ይመራል? በምንስ ይገታል?” አለ ሳንቾ ፓንሳ።

“ግንባሩ ላይ ያለውን ብሎን በማዞር በቀላሉ ሊመራም ሆነ ሊገታ ይችላል። ፈረስ ወደ ግራም ሆነ ወደ ቀኝ በቀላሉ መምራት ይህን ያህል አዳጋች አይሆንም። ነገር ግን ጦረኛውና ጋሻ ጃግሬው ዐይኖቻቸውን በጨርቅ መሸፈን አለበት፤ ካለበለዚያ ከፈረሱ ፍጥነት የተነሣ አየር ዐይናቸው ውስጥ ይገባና ከሰማይ ላይ በአፍንጫቸው ተዘቅዝቀው መሬት ላይ ይተክላሉ” አለ በገለጻው ተኩራርቶ።

ዶን ኪኾቴ ጥቂት እንኳ አላመነታም። ኮርቻው ላይ ዘሎ ጉብ አለ። መሐረም ከኪሱ መዝዞ ከሴቶቹ አንዷ ዐይኑን ጥርቅም አድርጋ እንድታስርለት ጠየቀ። ሳንቾ መፍራቱንና ማፈግፈጉን ተመልክቶና፣

“ምን! አንተ ደደብ! ካንተ የተሻሉ ብዙ ሰዎች ከተቀመጡበት ፈረስ ላይ መቀመጥ ነው የሚያስፈራህ? ቅረብና ዐይንህን ተሸፍነህ ቦታህን ተቀበል። እንዳች የምሬት ቃል ካንተ መስማት አልፈልግም” እያለ ዶን ኪኾቴ በሳንቾ ላይ የቁጣ መዓት አወረደበት።

ጦረኛውና ጋሻ ጃግሬው ባለ ዕንጨቱ ፈረስ ላይ ወጥ
ተው ፤ ዐይኖቻቸው በመሐረም ተጠፍረው በቆራጥነት
ወደ ካንዳያ ግዛት ለመብረር ተዘጋጁ ። መስፍኑና ሰሩ
ኒቱ ከነቤተሰቦቻቸው ከበው በደኅና ግቡ ለማለት ይጠ
ባበቃሉ ። ዶን ኪኾቴ ወደ ፊት ጕንበስ ብሎ በፈረሱ ግን
ባር ላይ የተተከለውን ብሎን ያሽከረክር ጀመር ። ከመ
ሬት ተነሥቶ ወደ ላይ በአየር ተንሳፎ በቀጥታ ወደ ሰማይ
የሚከንፍ መስሎት በደስታ ይፍነከነክ ጀመር ። በአካባ
ቢው ተሰባስቦ ይመለከት የነበረው ሕዝብ ፤ “ መልካም
ፍጥነትና በረራ ይሁንልህ ጀግናው ጦረኛ ! መላክት
መሪህ ይሁኑ ደፋሩ ጋሻ ጃግሬ ! ” እያሉ በከፍተኛ ድምፅ
በጕ ምኞታቸውን ገለጹላቸው ።

በደማቅ ጭብጨባ እያታጀቡ ፤ “ ወደ ሰማይ ተጠ
ግታችኋል ! እንደ ተወርዋሪ ኮከብ በሰማያት ላይ በመወ
ናጨፍ ላይ ናችሁ ! ሳንቾ ጠበቅ አድርገህ ጌታህን ያዝ !
እጥብቀህ ካልያዝክ ከዚያ ርቀት ወርደህ ትንኮታኮታለህ ”
እያለ ሕዝቡ በደቦ ጨኸቱን ይለቀው ጀመር ።

“ ጌታዬ ! ” አለ ሳንቾ ጌታውን ተጠግቶና ሙጭጭ
አድርጎ ከያዘ በኋላ ፤ “ ጌታዬ እኛ በሰማየ - ሰማያት ላይ
እየበረርን ሳለ እንዴት የሰዎች ሁካታ በቅርባችን እንዲህ
ሆኖ ሊሰማን ይችላል ? ልክ ጎናችን አጠገባችን የቆሙ
ይመስላል ? ኮ ” አለ ሳንቾ ።

“ይህ የታወቀ ነው ። ይህን በመሰለ ከፍተኛ የአየር
ላይ በረራ ፤ ብዙ ሺህ ምዕራፍ እንኳ የራቀ ነገር ይሰማሃል፤
ማየትም ትችላለህ ። የሆን ሆኖ ፤ እንዲህ አጥብቀህ አትያ
ዘኝ ፥ተንከባልዬ ልወድቅ እችላለሁ ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“አጥብቄ የያዝኩህ እንዳትወድቅ ’ ኮ ነው” አለ ሳንቾ።

“መልካም፤ግን ምን ይሁን ያህል ያንቀጠቅጠኛል! በበኩሌ እንዲህ በቀላሉ የጋለብኩበት ጊዜ በሕይወቴ ውስጥ የለም ። ፈረሱ እንደ አሞራ ነው የሚከንፈው፤የሚንቀሳቀስ አይመስልም ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ፡ “ እንደሚመስለኝ አሁን የምንገኘው ከሁለተኛው ቀጣና የአየር ክልል ውስጥ ነው። እዚህም ክልል ውስጥ የበረዶ ግግር የሚፈጠርበትና ቅዝቃዜም ከፍተኛ የሆነበት ነው ። በአሁኑ ፍጥነታችን ከቀጠልን ከሦስተኛው ቀጣና በፍጥነት እንደርሳለን ። ይህም ክልል መብረቅና ነጎድጓድ የሚፈጠርበትና ተምዘግዝጎ ወደ መሬት የሚወረወርበት ነው ። ወደ ፀሐይ እንደማን ጠጋ ተስፋ አለኝ!!ለምን ቢሉ ሙቀቷ እንዳያንጨረጭረን ነዋ !” አለ ዶን ኪኾቴ ።

በዚህን ጊዜ ፡ ከመሰፍኑ ባለሟሎች አንዱ ፡ በአንድ ረዥም ዕንጨት እሳት ለኩሰና ከዶን ኪኾቴና ከሳንቾ ፓንሳ ፊት ዙሪያ እንቦግቦገው፤ ነበልባሉ ተሰማቸው ።

“እንዴ ! እንዴ ! እሳት ወደ ሚነድበት ቀጣና ገብተናል፤የጢሜን እኩሌታ እሳቱ ባስ አደረገብኝኮ ። የዐይኔን ሽፋን በመጠኑ ገለጥ አድርጌ ለመመልከት እእምሮዬ እየገፋፋኝ ነው ” እያለ ሳንቾ ይወተውት ጀመር ።

“ለንፍስህ ከሳሳህ ዐይንህን ባትገልጥ ይሻላል ። የዚህ ጀብዱ ሥራ ቁም ነገር የሚለካው በትእዛዝ አክባሪነት ጭምር ነው።በርታ!ብቻ ትዕግሥቱን ይስጥህ!ከፍ እያልን የምንበርበት ምክንያት ወደ ካንዳያ ግዛት በቀጥታ ቁልቁል እንደ ፍላፃ ተስፈንጥረን ለማረፍ እንዲያመቸን ነው ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“ለመሆኑ በቅርብ ጊዜ ልንደርስ እንችላለን ? ” ሳንቾ ጠየቀ ።

«የማውቀው ነገር የለኝም ፤ ነገር ግን ፡ አብዛኛውን ጉዞ እንዳገባደድን ርግጠኛ ነኝ ” ነበር የዶን ኪኾቴ መልስ ።

“ ልስላሳ ኮርቻ ባገኝ በበኩሌ ጉዞውን በጣም ወድ ጀዋለሁ ” አለ ሳንቾ ።

መስፍኑና ሰፋኒቱ የፈጠሩት ቀልዳ ቀልድ ጨዋታ በመሳካቱ ፡ ለደስታቸው ወሰን አጡ ። ትልቁ ጥያቄ ይህን የፈጠሩትን ጨዋታ በምን ዐይነት ብልሃት አፈጻጸሙን የማሳመሩ ጉዳይ ነበር ።

ከመስፍኑ አሽከሮች አንዱ ዕንጨታማውን ፈረስ የክላቪሊኛን ጭራ እሳት ለኮሰው ። የዕንጨቱ ፈረስ በእ ሳት ተያይዞ እንደ መብረቅ ጮኾ ፈነዳ ። ዶን ኪኾቴና ጋሻ ጃግሬው ተወርውረው ከመሬት ላይ ተንደባለሉ ። ከእንስቶኛ ጭረትና ግጭት በስተቀር ይህን ያህል ጉዳት አላገኛቸውም ነበር ።

ጥቂት ከዳሁ በኋላ ፡ የዐይናቸውን ሽፋን መሐረጮን ገላለጡ ። ፀሩያ ግባውን ሲቃኙ ቀድሞ በረራ ሲጀምሩ ከነበሩበት የመስፍኑ አትክልት ቦታ በመሆናቸው እጅግ ተገረሙ ። ከድንጋጤአቸው ጋብ ብለው ትንሽ ነፍስ ከዘሩ በኋላ ፡ ዘወርወር ብለው ቢያዩ አንድ ጦር መሬት ላይ ተተ ክሎ በጦሩም ላይ በእረንግዳ ጥብጣብ የታሰረ ነጭ ብራና ተመለከቱ ።

ዶን ኪኾቴ የተጠቀለለውን ብራና አትኩሮ ሲመለ ከት የራሱ ስም ተጽፎበታል ። ብራናውን ከጦሩ ላይ ፈትቶ ማንበብ ጀመረ ። ብራናዉ ላይ በወርቅ ቀለም የተ ጻተበው ጽሑፍ እንዲህ የሚል ነበር ።

“ዝነኛው ጦረኛ ዶን ኪኾቴ

የዚህ ገድል ባለቤት ሲሆን

የቻለውና በአሸናፊነት የተወጣው
በጽኑ ዓላማ ግዳጁን በመከወኑ ነው ፤ ማላምብሩ
ኖም ከመጠን በላይ ረክቷል ። እስከ ዛሬ በአስ
ማት የተተበተቡ ሁሉ ነጻ ሆነዋል ። ይህ ትእዛዝ
የተሰጠው " በየእስማተኞች
ሜርሊን "

"ምን ዐይነት ዕድለኞች ነን !" አለ ዶን ኪኾቴ ጽሑ
ፉን አንብቦ ከጨረሰ በኋላ ። "ከእንግዲህ ድፍረት ይኑ
ረን ። የጀብዱ ሥራችን ፍጻሜ ሆነ ። የገድሉን ምዕራፍ
የዘጋነው በማንም ላይ አንድም ጉዳት ሳናደርስ ነው "
አለ ዶን ኪኾቴ ፤ ድምፁን ከፍ አድርጎ ።

መስፍኑ ወደ ዶን ኪኾቴ ቀረበና ፣ በዓለም ውስጥ
ተፈጥሮ በማይታወቅ ጀግናና አስደናቂ ተግባሩ ፣ በታላቅ
ክብር ሰላምታ አቀረበለት ። ሰፉኒቱም በፈገግታ መልክ
ወደ ዶን ኪኾቴ ቀርባ ጦረኛውንና ጋሻ ጃግሬውን የእጅ
ሰላምታ ሰጠቻቸው ።

"አደገኛውንና ረዥሙን ጉዞአችሁን እንዴት ተወ
ጣችሁት ? " ሰፉኒቱ ጠየቀች ።

"በደስታ ተወጣነው ፣ እመቤት ! ከተፈጠርኩ ጀምሮ
እንዲህ ያለ አስገራሚና ድንቅ የተፈጥሮ ትዕይንት አይ
ቼም አላውቅ ። በእሳት ቀጣና ውስጥ ስንጥቅን ስናልፍ ፣
ከዐይኔ ላይ መሐረሙን ትንሽ ዝቅ አድርጌ ቆሌቁል ተመ
ለከትኩ ። እቤት ! መቼም ዐይንን የሚማርክ ትዕይንት
ነበር ። ይህችን ዓለማችንን ከእኛ በታች ርቃ አየኋትና
ታዘብኳት ፤ ከሰናፍጭ ቅንጣት የማትበልጥ ሆና አገኘኋት"
አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

"ያላንዳች ጥርጥር አስደናቂ መሆን አለበት ፤ ያየ
ኸው ይመሰ " አለች ሰፉኒቷ ።

“ይህን ያህል የሚያስደንቅ አልነበረም ። ለምን ቢባል ፤ ሰዎች በምድር ላይ ሲረማመዱ በዐይኔ አይቻለሁ ። እውነት እውነት እላችኋለሁ ፤ ከሸንብራ ፍሬ በልጠው እንኳ አልታዩኝም ። ”

ሰፋኒቷ በሣቅ ፍርስ አለችና ፤ “ የሸንብራ ፍሬ የሚያህሉ ሰዎች የሰናፍጭ ቅንጣት በማታህል መሬት ላይ ሲረማመዱ ማየት እጅግ በጣም የሚያስደንቅ መሆን አለበት ! ” አለች ።

“ በእውነት የሚያስደንቅ ነው ” ካለ በኋላ ፤ “ አንድ ጊዜማ በቅንድቦቼ ውስጥ ስመለከት ፤ ሰማዩ አጠገቤ ተጠግቶ ስለ ነበር በእጄ ልነካው ምንም አልቀረኝም ነበር ! ቀጥሎም ሰዓቱ ከዋክብት ያሉበትን ሥፍራ ስናልፍ ፤ ሰባት የፍየል ጠጠጤዎች በሥራ መስክ ላይ ተሠማርተው ተመለከትኩ ። ምን አደረግሁ መሰላችሁ ? ከክላቪሌኛ ቀስ ብዬ ወረድኩና ፤ ለሩብ ሰዓት ያህል ከፍየሎቹ ጋር ስቦርቅ ቆየሁ ” አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

“ አንተና ፍየሎቹ ስትቦርቁ ፈረሱና ጌታህ የት ደረሱን ? ” ሰፋኒቷ ጠየቀች ።

ሳንቾ የሚናገረው ጠፋውና ፤ ራሱን ማከክ ጀመረ ። ቀጥሎም ፤ “ እዩት እመቤቴ ! እኔ ! እእ እኔ ..... ማለት እኔ .... እእ ... ” እያለ እንደበቱ ተሳሰረ ።

“ ተናገርና ይውጣልህ ። ያ ጨዋ ፈረስ አንዲት ጋት እንኳ ሳይላወስ ያንተና የፍየሎቹ ጨዋታ እስኪያበቃ ድረስ በትዕግሥት ይጠብቅ ነበር በል እንጂ! ” አለ መስፍኑ የሳንቾን ዐይን ትክ ብሎ እየተመለከተ ።

“ በእውነት እርስዎ አሁን ያሉትን ነው ፈረሱ ያደረገው ” አለ ሳንቾ ።

መስፍንና አሽከሮቹ ማቃቸው ሊያባራ አልቻለም ። ሆኖም ሳንቾ የምሩን ይሆን ወይም ውሸቱን ርግጠኛ ሊሆኑ አልቻሉም ። ምናልባት የእነርሱን ብልጣ ብልጥ የሆነች አነስተኛ ጨዋታ ንቅቶባቸው እንደሆነና ፥ በራሳቸው ቀልድ መልሶ እነርሱኑ በማታለል ላይ እንደሆነስ ማን ያውቃል ?

ዶን ኪኾቴ ቢናገርም ፥ ይህን ያህል አልነበረም ፤ሆኖም በፈጸመው የጀብዱ ሥራ ኩራት ተሰምቶት ባገኘው ድል የረካ ለመሆኑ ከአኳኋኑ ያስታውቅ ነበር ። እና ፥ የዕንጨቲቃማው ፈረስ ታዋቂና አሥቂኝ ገድል በዚሁ አከተመ ።

ሳንቾ በደሴቱ ላይ

መስፍንና ሰፋኒቱ በፈጠሩት የቀልዳ ቀልድ ዝግጅትና በውጤቱም በጣም ስለ ተደሰቱ ሌላ የመጫወቻ ነገር አቀዱ ። በአሁኑ ቀልዳቸው ዐቢዩ ተዋናይ ሳንቾ ፓንሳ እንዲሆን ተስማሙ ።

“ ሳንቾ ፓንሳ ! ” አለ መስፍኑ አንድ ቀን ፥ “ ጌታህ የአንድ ደሴት ገዥ ሊያደርግህ ቃል ገብቶልህ ነበር እንዴ ? ” በማለት ጠየቀው ።

“እንዴታ! ቃል ገብቶልኝ ነበር ። ከማንም ይልቅ እኔ ነኝ ለዚያ ሙያ ብቁ የሆንኩና ሹመቱም የሚገባኝ ! ጌታዬን ለብዙ ወራት በመከተል አገልግያለሁ ። ሕይወታችን ይኑር እንጂ የማስተዳድረው ደሴት ይህን ያህል አይገድም ” አለ ሳንቾ ።

“መልካም ! የኔ የሆኑ ጥቂት ትርፍ ደሴቶች በቅርቡ ይገኛሉ ። ለወዳጄ ለዶን ኪኾቴ ፍቅር ስል አንዱን ደሴት ላንተ እሰጥሃለሁ ” አለ መስፍኑ ።

“እጅ ንሣ ! ተንበርከክና እጅ ንሣ ሳንቾ ! ለውለታቸው ጫማ ሳም ፤ አመስግን ! ” አለ ዶን ኪኾቴ ፤ ድምፁን ከፍ አድርጎ ። ሳንቾም የተባለውን በሙሉ ፈጸመ ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ፤ መስፍኑ ሳንቾን ፤ “ሳንቾ ቃል ገብቼልህ ስለ ነበረው ደሴት ታስታውሳለህን ? ” አለው ።

“ያላንዳች ጥርጥር አስታውሳለሁ ። የሚረሳኝ አይደለም ” አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

“እንግዲያውስ ከነገ ጀምሮ ግዛትህን ተረክበህ ለማስተዳደር ተዘጋጅ ! ገበሬ የክረምት ዝናብ እንደሚጠባበቅ ሁሉ ፤ የደሴቲቱ ነዋሪዎችም አንተን በናፍቆት በመጠባበቅ ላይ ናቸው ። ከእንግዲህ ብዙ ሊጠብቁህ የሚችሉ አይመስለኝም ” አለ መስፍኑ ።

ሳንቾ በትሕትና እጅ ንሣና ፤ “እንግዲህ የሚቻለኝን ሁሉ ለማድረግ እሞክራለሁ ። የሆነ ሆኖ በዚያን ሰሞን ሰማይ ላይ ሆኘ ምድርን ቁልቁል ስመለከታት አንሳ ታይታኛለች ። ታዲያ ከዚህ አንጻር ፤ ገዥ ለመሆን ይህን ያህል የሚያጓጓኝ ጉዳይ አይደለም ። ከሽምብራ ፍሬ የማይበልጡ ግማሽ ደርዘን ሰዎች ማስተዳደር ይህን ያህል ቁም ነገር ይሆናል እንዴ ? ” አለ ሳንቾ ።

“ አይ ያንተ ነገር ! እየህ ሳንቾ ፤ የመግዛትን ጣዕም አንድ ጊዜ ከቀመስከው ፤ ልትለቀው አትፈልግም ፤ እንዲያውም ጥሩ ምግብ በልተህ ጣትህን እንደ መምጠጥ ያህል ማዘዝ ይጥማል ፤ ያስደስታልም ” አለ መስፍኑ ።

"በእርግጥ ግዘዝ ይጥማል ፤ ያስደስታልም ። እስደ ሳችነቱን ልረዳ የቻልኩት ፣ አንድ ሰሞን የበግ መንጋ አዛዥ ሆኘ ነበር " አለ ሳንቾ ።

"ጥሩ እረኛ የሆንከውን ያህል ፣ ጥሩ አስተዳዳሪ እንደ ሚወጣህ ተስፋ አለኝ ። እንግዲህ ነገ ጠዋት ወደ ደሴት ግዛትህ ለመጓዝ ተዘጋጅ ። አሽከሮቹ ለክብርህና ለማዕረግህ ተስማሚ ልብስ ያለብሱሃል ። "

"የፈለጉትን ባለጌጥ ልብስ ያልብሱኝ እንጂ ፣ እኔ እንደሆንኩ ያው ሳንቾ ፓንሳ ነኝ " አለ ጋሻ ጃግሬ ሳንቾ።

ዶን ኪኾቴ የሳንቾ ፓንሳን ወደ ደሴት ግዛቱ የመሔድ ወሬ ሲሰማ ፣ ለረዥም ጊዜ አብረው ተቀመጡና ብዙ ጠቃሚ ምክሮች ለገሠው ። ከብዙ ሺህ ጠቃሚ ምክሮቹ መካል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ነበሩ ።

"ከሁሉ በፊት ፣ ከሕሊናህ ተማገት ፤ ሕሊና የጥበብ ምንጭ ነውና ።

"ሁለተኛ፣ራስህን ጠንቅቀህ" ማወቅ ተግባርህ ይሁን።

"ኩራተኛና ክፉ ከመሆን ፣ ሕሊና ያለው ትሑትና ቀጥተኛ መሆን ጠቃሚ ነው ።

"ድሀ ዘመዶችህን አትናቅ ።

"ከከበርቴዎች ምስጋናና ምስክርነት ይልቅ የድሆች እንባ ይበልጥ ይሰማህ ። ባደረሰው ጥፋት በሕግ ልትቀጣው የሚገባህን ሰው በቃል ዘለፋ ብቻ እንዳታልፈው ።

"ወንጀለኛን ስትቀጣ ፣ ደካማ ፍጡር መሆናችንን ተገንዝበህ ርኅራኄና ምሕረት አድራጊ ሁን ።

"አስተዳዳሪ ስትሆን የመጀመሪያው ትእዛዝ ንጽሕና ነው ። ንጹሕ በአእምሮ ፤ ንጹሕ በአካል ።

"ጥፍርህን አታሳድግ ።

"አለባበስህን ከሰውነትህ ጋር አስማማው ።

"ሽንኩርት በልተህ በሰው ላይ አታግሳ ።

"አረማመድህ ዝግ ያለ ፤ ንግግርህም መቋጫ ይኑረው ።

"በመጠኑ ጠጣ ።

"በሁለቱ መንጋጋህ ምልተህ አታኝክ ።

"እንቅልፍ አታብዛ ።

"በአለባበስ ረገድ ጠባብ ሱሪ ፣ ረዥም ኮትና ካባ ደርብ ።

"በመጨረሻም ከንቱ ቱረት አታብዛ ፤ ጥበብ ሳላል ሆነ አይጠቅምህምና ። "

ሳንቾ በጸጥታ ሆኖ የዶን ኪኾቴን ምክር በሙሉ ክልቡ አዳመጠና ፤ በተቻለው መጠን ሁሉንም በተግባር እንደሚያውል ቃል ገባለት ።

"የማስታወስ ችሎታዬ ደካማ በመሆኑ ፤ እባክዎን የነገሩኝን በወረቀት ጽፈው ይስጡኝ ። እውነት ለመናገር ከሆነ ፤ ማንበብም ሆነ መጻፍ አልችልም ። በግዛቴ ውስጥ ለማገኘው ቄስ ጽሑፉን እሰጠውና ፤ እሱም በአእምሮዬ ውስጥ ከጠቀጠቀልኝ በኋላ ፣ በፈለግሁት ጊዜ እያወጣሁ እጠቀምበታለሁ ። »

"አ ! እንዴት ያለሁ ኃጢአተኛ ኖሬአለሁ ለካ ! " አለና ዶን ኪኾቴ ራሱን ይዞ ከጮኸ በኋላ ፣ "የማያነብና የማይጽፍ አስተዳዳሪ ጉደኛ ነው ! ሌላው ቢቀር እንኳ ስምህን እንድትጽፍ አስተምርሃለሁ " አለው ።

ሥልሜንማ እጽፋለሁ ። ይህንንም ለማጥናት የቻል ኩትቁጥቋጦ ፈደሎች ስምነሜሜር ያዩኝ ሰዎች ስምህ ነው ብለው ስለነገሩኝ ነው ። ከዚህ በተረፈ፥ለፈርማው እጄን ያመኛል እያልኩ ሰበብ ፈጥሬ ሌላ ሰው እንዲፈርምልኝ አደርጋለሁ ። አዩት ! ከሞት በስተቀር ለሁሉም ነገርመፍ ትሔ ይገኝለታል ። ሰዎች እፊቴ ሆነው ቢፈልጉ በሐሜት ይቦጭቁኝ ፤ ሐሜተኞችን መልሼ እኔ እቦጭቃቸዋለሁ፤ አትርፍ ብለው ይመጡና እንድለው ይሔዱታል ! የሀብ ታም መዝካበድ እንደ ሰውቀት ይቆጠራል ። ‘ ሰው ያለውን ያህል ያህላል ’ ትል ነበር አያቴ ።”

“በቃህ ! በቃህ ! ተረትህ ሰለቸቶኛል ። የተረትህ መብዛት በደሴትህ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ያንገፈገፍና አድ መው ከሥልጣንህ ያወርዱሃል !” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“እባክዎን ይማሩኝ ጌታዬ ! በገዛ ዕቃዬ እንደ ፈለ ገኝ ብጠቀምበት እርስዎ አይቸገሩ ። የኔ ዋናው ሀብቴ ተረቴ ። ድንጋይ በጋን ላይ ቢወድቅ ወይም ጋን በድንጋይ ላይ ቢወድቅ ምንጊዜም ተጐጂው ጋኑ ነው” አለ ሳንቾ።

“ጥሩ ነው ። ዛሬ ደረጃና ዕድገት ስላገኘህ፣ንግግር ህም መጣፈጥ ጀምሯል ። አሁን ወደ እራት እናምራ ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

በማግሥቱ ሳንቾ ወደ ደሴት ግዛቱ ተጓዘ ። በመጣብር የተንቆጠቆጠች ሰጋር በቅሎ ተቀምጦ ገሥገሠ ። ከበስተ ኋላው የእርሱ ግራጫ አህያ እንደ ፈረስ የክብር ልብስ ለብሶ የመሳፍንት ፈረስ ፀመምሰል ያዘጠዝጣል ።

ሳንቾ የመስፍኑንና የሰፋኒቱን እጅ ክሳመ በኋላ፣ ከጌታው ምርቃት ለመቀበል ጐንበስ አለ ። ከሥነ ሥር ዓቱ በኋላ፥እንባውን እያፈሰሰ፥በሠለጠኑ አሽከሮች ታጅቦ

ጉዞውን ቀጠለ ። አጃቢዎቹ በክብር እንዲጠብቁትና ትዕዛዝ እንዲሆኑለት በምስጢር ትእዛዝ ተሰጥቷቸዋል ።

ጉዞው ረዥምም አልነበረም ። ብዙም ሳይቆዩ የመስፍኑ ግዛት ከሆነችው ከአንዲት ከተማ ደረሱ ። የተሾመበት ደሴት መሆንዋን ለሳንቾ ነገሩት ፤ የከተማይቱም ስም ባራታሪያ ይባላል ።

በከተማዋ መግቢያ በር ላይ ታላላቅ ሹማምንት የክብር አቀባበል አደረጉለት ፤ የየአድባራቱ ደወሎች ድምፃቸውን አሰተጋቡ ፤ ሕዝቡም በሆታና በእልልታ ደስታውን ገለጸ ። ወደ ቤተ ክርስቲያን አጅበው ከወሰዱት በኋላ፣ የከተማይቱን ቁልፍ አስረከቡት ።

"ክብርና ምስጋና ለተከበሩት ገዥያችን ይሁን!" እያለ ቤቱ፣ ወንዱ፣ ወጣቱና ሽማግሌዉ ደስታውን በይፋ ገለጸ ። ሳንቾም የልብ ልብ ተሰማውና ደረቱን ነፋ አደረገ ።

ሳንቾ በጣም አጭር፣ ወፍራምና አምቢኛ መላይ በመሆኑ፣ ከለበሰው የክብር ልብስ ጋር ሲያዩት፣ ግራ የሚያጋባ ዐይነት ሰው ሆነባቸው ። መስፍኑ ለቀልድ የፈጠረው ጉዳይ መሆኑን ሕዝቡ ሳያውቅ፣ በሁኔታው ይገረም ጀመር ፤ ቢሆንም ሕዝቡ ሆታና እልልታውን በመቀጠል፣ "ጌታችን ዶን ሳንቾ ፓንሳ ለዘለዓለም ይኑር !" ከማለት አልተቆጠበም ።

ሳንቾ ወደ ግል ጸሐፊው ፊቱን መለስ አደረገና፣ "ማንን ነው ዶን ሳንቾ ፓንሳ የሚሉት ?" ሲል ጠየቀ ።

"እንዴ ! ክቡርነትዎን ነዋ ! እርስዎ ራስዎን !" ጸሐፊው በመገረም መለሰ ።

"እሺ ወዳጄ ! 'ዶን' የተሰኘው መጠሪያ ለኔ የሚገባኝ ሆኖ መሆኑን አሁኑኑ ማስታወቅ ያገባኛል ። የኔ ስም በግልጽ እንደሚታወቀው ሳንቾ ፓንሳ ነው ። አባቴ፣ አያቴ፣

ቤተሰባችን በሙሉ ‘ዶን’ ወይም ‘ዶና’ የሚል ቅጽል በስማቸው ላይ ሳያክሉ ‘ፓንሳዎች’ እየተባልን ነው የምንጠራው ፤ ‘ዶኖች’ ልክ እንደዚህ ደሴት ድንጋዮች መዓት ይመስሉኛል ። የገዥነት ዕድሜዬ አራት ቀን እንኳ ቢሆን ፤ እንደ ዝንብ መንጋ ጠራርጌ ነው የማባርራቸው ” አለ ሳንቾ ።

ከቤቱ ክርስቲያን በታላቅ ሥነ-ሥርዓት ታጅቦ ወደ ችሎት አዳራሽ ተወሰደ ። በአዳራሹም ውስጥ በተሰናዳለት መንበር ላይ ተቀመጠ ። ፍትሕና ርትዕ የሚሹ ሁሉ ቀርበው በዝርዝር ችግራቸውን ያስረዱ ጀመር ።

በመጀመሪያ ከቀረቡት መካከል አንዱ እንደ ባላገር የለበሰ ሲሆን ፤ ሌላው እንደ ልብስ ሰፊ ነበር ።

“ክቡር ገዥያችን ሆይ ! እኔና ይህ ገበሬ በመካከላችን የተፈጠረውን ውዝግብ እርስዎ ዘንድ አቅርበን ከዳር እንዲያደርሱልን መጥተናል ። ይህ ገበሬ ትናንት ቁራጭ ጨርቅ ይዞ እኔ ሱቅ መጣ ። አንድ ኮፊያ ለመስፋት ጨርቁ ይበቃ እንደሆነ ጠየቀኝ። እኔም ጨርቁን ከመተርኩ በኋላ እንደሚበቃ ገለጽኩለት ፤ እንደገና ለሁለት ኮፊያ ይበቃ እንደሆን ቢጠይቀኝ ለእሱ እንደሚበቃ ነገርኩት ፤ በመጨረሻም ፣ እኔው ራሴ ጨርቁ ለአምስት ኮፊያዎች እንደሚበቃ አስረዳሁት ። እነሆ ዛሬ ጥዋት ቆቦቹን ሊረከበኝ መጣ ። ሥራውን አጠናቅቄ ነበርና በሙሉ አስረከብኩት ፤ ሆኖም የሰፋሁትን ዋጋ አልከፈለኝም ። እሱ የሚለው ፣ ጨርቁን እንድመልስለት ወይም ዋጋውን እንድከፍለው ይፈልጋል ” አለ ልብስ ሰፊው ።

ሳንቾ ፊቱን ወደ ገበሬው መለሰና ፣ “ወዳጄ ሆይ ! ይህ ሰው የተናገረው እውነት ነውን ?” ሲል ጠየቀ ።

“እውነት ነው ! ነገር ግን ፣ የሰፋቸውን ቆቦች አምስቱንም ለርስዎ አቅርቦ ያሳይዎት ።”

“ በደስታ !” አለና ልብስ ሰፊው በአራቱ ጣቶቹ ላይ አራት ትናንሽ ቆቦች ሰካካ ! በአውራ ጣቱ ላይ አም ስተኛውን አስቀመጠና ፤ “እነሆ አምስቱንም ኮፊያዎች በጠየቀኝ መሠረት ሰፍቼለታለሁ ፤ አንዲት ቁራጭ ጨርቅ እንኳ ለራሴ አላስቀረሁም ” አለ ልብስ ሰፊው ።

አዳራሹ ውስጥ የነበረው ሕዝብ ሁሉ በኮፊያዎቹ ጥቃቅንነት በጣም አለቀ ። ሳንቾ አገጩን በእጁ ደግፎ ጥቂት አሰላሰለ ። ቀጥሎ ፤ እንዲህ ሲል ተናገረ ።“ ይህ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ልብስ ሰፊው የልፋቱን ዋጋ እንዳያገኝ ፤ ገበሬውም ጨርቁን እንዳያጣ ወስኗል ። ኮፊያዎቹም ተወርሰው ወህኒ ቤት ውስጥ ለሚገኙ እስ ረኞች እንዲሰጡና ጉዳዩም በዚህ እንዲያበቃ ይሁን ” አለ ሳንቾ ።

የፍርዱን ውሳኔ የሰሙ ሁሉ በትክክለኛነቱ እጅግ ተደሰቱ ። ቀጥሎ ሁለት የዕድሜ ባለጸጋ አዛውንት አገረ ገዥው ሳንቾ ዘንድ ቀረቡ ። አንደኛው የሚመረኰዝበት ከዘራ ይዟል ።

“ጌታዬ ! ከጥቂት ወራት በፊት ለዚህ ሰው ዐሥር ወቄት ወርቅ አበድሬው ነበር ። ደግ የሠራሁ መስሎኝ ሳበድረው ፤ በጠየቅሁት ጊዜ እንደሚመልስልኝ በመተማ መን ነበር ። ለብዙ ጊዜ ወርቄን አልፈለኩኝም ነበር ። ደንታ ቢስ ሆኖ በጉዳዩ ይህን ያህል ያላሰበበት መሆኑን አይቼ ፤ ወርቄን እንዲከፍለኝ ጠየኩት ። እርሱ ግን ወር ቄን ሊከፍለኝ ፈቃደኛ ካለመሆኑም ሌላ ፤ በጭራሽ አላ በደርከኝም ይላል ። እንዲያውም መልሼልሃለሁ ይለኛል ! በበኩሌ ምስክር የለኝምና ፤ እንዲምልልኝ ወደ እርስዎ ዘንድ አቅርቤዋለሁ ። ከፍዬዋለሁ ብሎ የሚምል ከሆነ ይቅርታ አደርግለታለሁ ” አለ ።

"እህ አባት አዛውንቅ! ለዚህ ጉዳይ ምን መልስ አለ ዎት ?" ሳንቾ ጠየቀ ።

"ጌታዬ፣ እርሱ ገንዘብ ለእኔ ማበደሩና መበደሬ የማ ይካድ ነው ። ቃሌን ሳልለውጥ መስቀል ይገኔ እምላለሁ! ገንዘቡን በሙሉ መልሼለታለሁ" አለ ።

ሳንቾ ፣ በከዘራው ላይ ያለውን መስቀል ለሰውዬው ዘረጋለት፣ሽማግሌው ሰውዬ የራሱን ከዘራ ለሌላ ሰው አቀ በለና ለመሐላ ቀረበ ። እጁን በገዥው ሳንቾ ከዘራ ላይ ካለው መስቀል ላይ አሳረፈና ፣ ገንዘብ እንዳበደረው የማ ይካድ መሆኑን በመሐላ አረጋገጠ።ነገር ግን የተበደረውን ገንዘብ በሙሉ እንደ መለሰለትም ጭምር ቃሉን ሰጠ።

ሳንቾ ፣ ወደ ባለገንዘቡ ሰውዬ ፊቱን መለስ አደረገና፣ "እህ . . . .ምን ትላለህ ?"

"መልካም ። ጎረቤቴ ጥሩ ክርስትያን በመሆኑ፣በሐ ሰት ይመሰክራል ብዬ አልጠረጥረውም ። ምናልባት እሱ መልሶልኝ ሊሆን ይችላል፤እኔ ግን ዝንጋኤ ስለሚያጠ ቃኝ አትፍረዱብኝ" አለ ።

ባለምርኩዙ ከዘራውን ተቀበለና ሁሉቱም ከፍርድ ቤቱ ወጥተው ሔዱ።ሳንቾ አንገቱን ደፍቶ፣እጁን በግንባሩ ላይ አድርጎ ለጥቂት ጊዜ ካሰበ በኋላ ድንገት ድምፁን ከፍ አድርጎ ፣ "ባለከዘራው ሰውዬ የት ደረሰ ? በፍጥነት መል ሳችሁ አምጡልኝ" አለ ። ሁለቱም ሰዎች ወደ ፍርድ ቤቱ ተመለሱ ።

"አንተ መልካም ሰው ፣ እባክህን ከዘራህን ለማየት እፈልጋለሁ ። አንድ ለማወቅ የምፈልገው ነገር አለ" አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

"እሺ ጌታዬ — ይኸውልዎ" አለ ባለምርኩዙ ።

ሳንቾ ምርኩዙን ተቀበለና ፡ ወዲያው ለከሳሹ ለውዬ ሰጠና ፡ “ ያውልህ ይህን ምርኩዝ ውሰድ — ገን ዘብህን አግኝተሃል ማለት ነው ” አለው ።

“እንዴት ሊሆን ይችላል ጌታዬ ? ይህ ከዘራ በዐ ሥር ወቄት ወርቅ እንዴት ይገመታል ? ” ሲል ጮኸ ።

“ግምቱ ካልሆነ ፡ እንግዲያውስ ቃላቱ ደደብ እኔ ነኝ ማለት ነው ። ፈቃድህ ሆኖ ከዘራውን ለእኔ ከመለስ ክልኝ ምን እንደሚፈጠር በዐይንህ ታየዋለህ ” አለ ሳንቾ።

ሳንቾ ፡ ከዘራውን ተቀብሎ በሁለት እጁ ከያዘ በኋላ ሁለት ቦታ ቅምጥል አድርጐ ሰበረው ። ከከዘራዉ ውስጥ ዐሥር ወቄት ጠርቅ ዱብ ዱብ አለ ። በፍርድ ቤቱ የነበሩ ሁሉ እጅግ ተደነቁ ። ይህ ሰው ጥበበኛዉ ዳግማዊ ሰለሞን ነው እያሉ ያደንቁ ጀመር ። ሐቁ ግን ሳንቾ ጥንት እንዲህ ያለ ቀልድ ፡ በአንድ ራቅ ባለ ከተማ መደ ፈጉን ሰምቶ ነበርና ፡ ዛሬ እሱ ሲሞክረው እንደ አጋጣሚ ሠመረለት ። ዘመን ያስፈበት ታሪክ ቢሆንም ፡ በባትሪያ ሕዝብ ዘንድ ግን አዲስ ነገር ሆነ ። የፍርዱ ማክተሚያ አንዱ ሽማግሌ የኃፍረት ማቁን ተከናንቦ ሲሔድ ፡ ሌላኛዉ ገንዘቡን አግኝቶና ተደስቶ መግባቱ ነበር ።

በዚህ ዐይነት ልዩ ልዩ አስቸጋሪ ፍርዶች ፡ ‘ ለአገረ ገዥው ’ ለሳንቾ ቀረቡለት ። አዲሱ አገረ-ገዥም ለሁ ሉም ተስማሚ ብያኔ በመስጠቱ ፡ ሕዝቡ በዚህ ጥበበኛ ዳኛ ችሎታ ሲደነቅ ፡ ነገር ግን ከሞኛኛ ራስ ውስጥ ይህን ያህል ጥበብ በመፍለቁ አስገራሚ ሆኗል ። ይህ ሁሉ አድ ናቆትና ክብር ቢሰጠውም ፡ ሳንቾ ግን በደሴት ገዥነቱ አልተደሰተም ።

ሆዱን ሞልቶ እንዲበላ አልተፈቀደለትም ። ሐኪም ዘወትር አጠገቡ ይቆምና ለጤናው የማይስማማ ምግብ

እንዳይበላና እንዳይጎዳ ይከላከላል ። የሚወደውን የዶሮ ጥብስ መመገብ አልቻለም ፤ ምንም እንኳ ለወጉ ተብሎ ዘወትር ጥብስ ገበታው ላይ ቢኖርም ፡ ከመጐምጀት በስ ተቀር ምንም ሊያደርግ አልቻለም ።

በአደባባይ የሚፈጸመው ሥነ ሥርዓት ሳንቾን እጅግ አደከመው ፤ መልኳም ጽዱ መልበስ አሰለቸው ። የሌሊት እንቅልፍ በጠባቂ ዘበኞች ይጨናገፍ ጀመር ። በመጨ ረሻም ከመስፍኑ አንድ አሳዛኝ ደብዳቤ ደረሰው ።

ደብዳቤው በብዙ ማስጠንቀቂያዎች የተሞላ ነበር፤ ጠላት ደሴቷን ሊወር ወደዚያው በማምራት ላይ እንደሆነ ደብዳቤው ያትታል ። አራት ሰዎች ግን ቀደም ብለው ወደ ከተማዋ በመግባት አገረ ገዥውን ለመግደል እንደ መጡ ይተርካል ። መስፍኑ ሳንቾን በደብዳቤ ሲመክረው ፤ በጣም እንዲጠነቀቅና የቀረበለትን ምግብ ሁሉ እንዳይ ነካ ፡ ከቀመሰ ግን በተመረዘ ምግብ እንደሚሞት ይገል ጽለታል ።

ይህ ሁሉ መስፍኑ በሳንቾ ላይ ለመቀለድ የፈጠረው ቢሆንም ፡ ሳንቾን ግን ክፉኛ አስደንግጦታል ። ሳንቾ ወደ ባራታሪያ ግዛት ከመጣ ሳምንት ዐልፎታል ። ዕረፍት አግ ኝቶ አያውቅም ። ድካምና ረሃብ ተፈራረቁበት ። በሥራ ብዛት አምሽቶ እንዲተኛ ይደረጋል ።

አንድ ቀን አምሽቶ ሊተኛ ሲዘጋጅ ፡ ከአቅራቢያው አውራ ጎዳና ከባድ ድምፅ ሲያስተጋባ ተሰማው ፤ በድምፁ ከባድነት ተደናገጠና ምን እንደሆነ ለማየት ወጣ አለ ።

ደወሎች ያቃጭላሉ ፤ ነጋሪቱ ይጎሰማል ፤ ሕዝብ ይንጫጫል ፤ ሳንቾ በፍርሃት ተርበደበደ ። ነጠላ ጫማውን ተጫምቶ ወደ በሩ ወጣ ።

ብዙ ሕዝብ ችቦ አብርቶ ፥ ጎራዴ መዞ ፥ በከፍተኛ ድምፅ እየጮኸና እየተግተለተለ ወደ ሳንቾ ቀረበ ።

"ክቡር አገረ - ገዥያችን ሆይ ! ጦር መጣ ! ጠላት ደሴታችን ውስጥ ዘልቆ ገብቷል ። ይምጡና ጦራችንን መር ተው ያዋጉን ። ለእርስዎም ተስማሚ የሚሆን መሣሪያ እነሆ ! " ይል ጀመር ሕዝቡ ።

"እንዴታ ! አስታጥቁኝ እንጂ ! በድል አድራጊነት እንድንወጣ ለሁላችንም መልካም ዕድል እመኛለሁ " አለ ሳንቾ ፓንሳ ፍርሃቱ ሳይለቀው ፥ ግን ጀግና ለመምሰል እየሞከረ ።

ሁለት ጋሻ አምጥተው ፥ አንዱን በደረቱ ሌላውን በጀርባው ላይ በገመድ ጥፍር አድርገው አሠሩለት ። ጦር አስጨበጡትና ፥ "እንግዲህ ክቡር ገዥያችን ሆይ ! ሠራዊ ቱን ይምሩ ! "

"እንዲህ ጥፍር አድርጋችሁ አስራችሁኝ እንዴት አድርጌ ልመራችሁ እችላለሁ ? " ሳንቾ ተበሳጭቶ ጠየቀ። ትክ ብሎ ለተመለከተው ፥ በትላቅ ዛጎል ውስጥ ያለ ዔሊ ይመስል ነበር !!

"እግሮቼን እንኳ ለማጠፍ አልችልምና ልትሸኩ ሙኝ ይገባል " አለ ሳንቾ ።

"ክቡር አገረ ገዥ ሆይ ! ይህ ተገቢ ንግግር አይደ ለም ። ፍርሃት ነው እንዲህ አሽመድምዶ የያዘዎ ! የጠላት ጦር በየደቂቃው እየገፋ በመምጣት ላይ ስለሆነ ፥ ይልቅስ ይነሡና ይምሩን" አለ ከሰዎቹ አንዱ ።

ምስኪኑ ሳንቾ ሊራመድ ሞከረ ፤ ነገር ግን መንቀሳ ቀስ ባለ መቻሉ ከመሬት ላይ ወድቆ ሲዘረጋ ፥አካላቱ

በሙሉ ብትንትን ያለ መስሎት ነበር ። እመሬት ላይ እንደ ተበረረ እንዲያነሡት ሰዎቹን ተማጠነ ።

ድንገት ችቦው ሁሉ ድርግም ብሎ ጠፋ!ሕዝቡ አፍላ ጦርነት ውስጥ ገብቶ ሲቆራቆስ ይሰማው ነበር ! ግግሹ ሳንቾን እየረገጠ ይደናቀፋል ፤ እኩሌታው እየረመረመው ያልፋል ፤ በሕይወቱ እንዲህ እንደ ዛሬው ፍርሃት ገብቶት አያውቅም ነበር ።

“ምነው ይህች ደሴት ወዲያ በተወረረችልኝ ! ወይም ምነው ሞቼ ባረፍኩትና ከዚህ ጭንቀት በተገላገልኩ” እያለ በሐዘን ያጉተመትም ጀመር ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ፡ “ ድል አደረግን ! ድሉ የኛ ሆነ ! ኧረ ለመሆኑ ክቡር አገረ-ገዥያችን የት ደረሱ ?” እያለ ሕዝቡ ሲጮኽ ሳንቾ ሰማ ።

“ኢባክችሁን እርዱኝ እዚህ ነው ያለሁት ። እንሡኝ እርዱኝ ! ” እያለ በደከመች ድምፁ ጩኸቱን ቀጠለ ።

ጋሻዎቹን ፈትተው ሳንቾን ተሸክመው ወደ መኝታ ክፍሉ ወሰዱት ።አልጋው ላይ ትንጋለ ፤ ሕሊናውን ስቶ ፣ ትንፋሽ በማጣቱ፤ይህንን ቀልድ ያዘጋጁት ሰዎች እንኳ በርግጥ የሞተ መስሏቸው በጣም ደነገጡ ። ሆኖም ቀስ በቀስ ሕይወት ዘራ ።

“ስንት ሰዓት ሆነ ? ” ሳንቾ ጠየቀ ።

“እኩለ ቀን ሊሆን ነው ”መለሱለት ።

እንዲትም ቃል ሳይተነፍስ ልብሱን ቀስ በቀስ ደራርቦ ለባብሶ እንዳበቃ ፣ሽምድምድ እያለ በዝግታ ወደ ውጭ ወጣ ። ሰውነቱ ደቅቆ ፣ ጉልበቱ ዝሎ ስለነበር፣ ላየው ያሳዝናል ። አህያው ግራጭ ታስሮበት ወደ ነበረው ጋጣ

ሰተት ብሎ ገባ ። ከእንስሳው አንገት ላይ ተጠምጥሞ ይስመው ጀመር ። እንባውን እያዘራና አህያውን እየታከከ ፣

"ውዱ ግራጫዬ ! ታማኙ ጓደኛዬና የመጨረሻው ዘመዴ ! ሙያዬና ተግባሬ እንቶን ትንሹን ፍጡር መመገብና መንከባከብ በነበረበት ጊዜ ፣ሰዓታት ሳይሰሙኝ ያልፉ ፤ ቀኖች ሳይታወቁኝ ይበራሉ ፤ ዓመታት በሰላም ይነጉዱ ነበርና ፣ የደስታዬ ፣ የፈንጠዝያዬ ዘመን ነበር ። ነገር ግን ፣ እንህ በተስፋ ማማ ላይ ከወጣሁ ጀምሮ ፣ ሺህ ጠላት አፈራሁ ፤ ሺህ ሥራ ሠራሁ ፤ አራት ሺህ ችግርና ውጣ ውረድ ደረሰብኝ " እያለ ሳንቾ ፓንሳ አነባ ።

አህያውን እያንጋገረ ልጓም አውጥቶ ፣ ኮርቻ አምጥቶ ግራጫውን ጫነ ። በኮርቻው ላይ በቅስታ ወጣና ከተመቻቸ በኋላ ልጓሙን እሳምሮ ጨበጠ ።

"ከመንገዴ ላይ ገለል በሉ !" አለና በዙሪያው በነበሩት ሰዎች ላይ ካምባረቀ በኋላ ፣ " ወደ ነጻነቴ እመለሳለሁ ። እኔ የደሴት ገዥ ወይም ለደሴት ተከላካይ ለመሆን አልተፈጠርኩም ። ሕዝቦቼ ሆይ ተባረኩ ! ለጌታዬ ለመስፍኑ ያተረፍኩት ወይ ያጎደልኩት እንዳችም ነገር እንደሌለ አስረዱልኝ ። ወደዚህች ደሴት ስመጣ ቤሳ ቤስቲን አልነበረኝም ። ስሔድም ምንም አልያዝኩም።አሁን መንገዱን ልቀቁልኝና ልሔድበት !" በማለት በከፍተኛ ድምፅ ጮኸባቸው ።

ይህን ተናግሮ አህያውን 'ሒድ !' አለና ፣ ጌታው ዶን ኪኾቴ ወደሚገኝበት ቀበሌ በዝግታ ጉዞውን ቀጠለ ። በመጨረሻ ሳንቾ መስፍኑ ቤተ-ግንብ ሲደርስ አገር ተደነቀ ። ሁሉም ከልብ በደስታ ተቀበሉት ። የደረሰበትንም ታሪክ በጥሞና እስከ መጨረሻው አደመጡት ። ሳንቾም ውጉን በሰፊው ይጠርቅላቸው ጀመር ።

“የተሾምኩበትን ደሴት ማስተዳደር ከጀመርኩ እነሆ ስምንት ቀን ሆኖኛል ። በእነዚህ ሁሉ ጊዜያት ውስጥ በቂ ምግብ አልበላሁም ። በቂ ጊዜ በማጣት እንኳንስ ጉቦ ልበላ ይቅርና ፣ የደከምኩበትን ቀለቤን በወጉ አልተቀበልኩም ። ጠላቶቼ አጥንቴን አደቀቁት ፤ ሕይወት ከባድ ሸክም ሆነችብኝ ። ቢሆንም ሰው ያስባል እግዜር ይፈጽማልና ለሁላችንም ደኅንና ሰላሙን ይስጠን ። ማንም ሰው ቢሆን ይህንን የኔን ዐይነት ጽዋ አልጠጣም አይበል ፤ በተረፈ በቅቶኛል ፣ አፌን በዳቦ ” አለና ሳንቾ ፓንሳ ንግግሩን ገታ ።

“ግድየለም ሳንቾ ! ግድየለም !” አለና ዶን ኪኾቴ ፣ “አገረ ገዥ ከተሾመበት አገር ከብሮ ቢመለስ ፣ ዘርፎ ነው ይባላል ። ባዶ እጁን ቢመለስ የማይረባ ይባላል ። ነገር ግን አንተ ሕሊናህ ንጹሕ ከሆነ የሚያስፈራህ ነገር የለም” አለ ዶን ኪኾቴ ፣ ቃሉን ለስለስ አድርጎ ።

“ እውነትዎን ነው ጌታዬ ! ግን ’ኮ ከእንግዲህ ፡ ‘ ቢሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል ’ እንደሚባለው ጉቦ ባለ መብላቴ ደደብ እያሉ ይሰድቡኛል እንጂ ፣ ዘራፊ ነው አይሉኝም !! ” አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

የሣራት ሳው ባለሆቴል

አንድ ማለዳ የበጋው ወር ሲኪተት ሲል ፣ ዶን ኪኾቴ ጥሩሩን እንዲያቀርቡለት በመጠየቁ መስፍኑ እጅግ ተገረመ ።

“ ጌታዬ ሆይ ! ለአዲስ የጀብዱ ሥራ ልቤ ተነሣሥቷል ያላንዳች ውጤት እዚህ በከንቱ መቀመጥ አልችልም ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“ከእኛ ጋር መኖሩ አልተስማማህምን ? ለምን ተለ ይተኸን ለመሔድ ትፈልጋለህ ?” መስፍኑ ጠየቀው ።

“በእርግጥ ስላደረጉልኝ ውለታና ደግነት አመሰግ ናለሁ ። እዚህ በተድላና በደስታ እያሌ ቀናት አሳልፌ አለሁ ። ነገር ግን ፡ በዓለም ላይ ሥራንና መሥዋዕትነትን የሚጠይቁ ጉዳዮች ሞልተዋልና መሔድ አለብኝ ።”

ዶን ኪኾቴ ፡ መስፍኑና ሴትዮቱን ተሰናብቶ ፈረሱ ላይ ተቀምጦ ወደ ሣራጐሳ አመራ ። ሳንቾ ፓንሳም እንደተ ለመደው ግራጫ ላይ ሆኖ ጌታውን ተከተለ ። በጉዞአቸው ላይ ያጋጠማቸውን በሙሉ ለመዘርዘር ጊዜና ቦታ ስለ ሌለ እንለፈውና ፡ አንዳንዱን ብቻ በማንሣት ጥቂት እንተ ርክላቸው ።

ዶን ኪኾቴና ፓንሳ የሚሔዱበትን አገር ሳያውቁና ሳያቅዱ ፡ እንዲያው በዘፈቀደ ቀንን ሰዓት እንዲያስብ ትትውለት ፡ በዝግታ ጉዞአቸውን ወደፊት ቀጠሉ ። በጉዞው ጊዜ ሁሉ ጠረኛው አዲስ የጀብዱ ሥራ ለመፈ ጸም ከጠላት ጋር በወኔ ለመግጠም ንቁና ተቁላትሮ ሲገ ሥግሥ ያስገርም ነበር ።

አንድ ቀን ፡ ምሽትገደማ ከአንድ ከተማ ክልል ወደ ሚገኝ ሆቴል ጌታና ጋሻ ጃግሬ ደክመውና ተርበው ደረሱ ፤ የሆቴሉ ባለቤትም ከበሩ ላይ በታላቅ አክብሮት ተቀበ ላቸው ።

“እባክዎን በረዥም ጉዞ ለተዳከሙ ሁለት እንግዶችና ለከብቶቻቸው የሚሆን ማረፊያ ይፈልጉልን ?”

“እንዴታ ይገኛል እንጂ ! ይህ ማረፊያ ሥፍራ በማራጉሳ ውስጥ ተወዳዳሪ የሌለው ውብ ቦታ ነው ” አለ ባለ ሆቴሉ ።

ከከብቶቻቸው ወረዱ ። ሳንቾ ሮሲናንቴንና ግራጭን ወደ ጋጣ ወሰዳቸውና የሚበሉትን ሰጥቷቸው ፤ ጌታውን ለመጠበቅ ወደ ማረፊያው ቤት ተመለሰ ።

"መልካሙ አስተናጋጃችን ሆይ ! ለእራት የሚሆን ምን ምን ይገኛል ?" ሲል ሳንቾ ጠየቀ ።

"የአፍዎንና የሆድዎን ስፋት ገምተው ይጠይቁን እንጂ ፤ የሚፈልጉትን ሁሉ ለማግኘት ይችላሉ" ሲል የሆቴሉ ባለቤት መለሰ ። በሰማይ የሚበሩ አዕዋፎች በምድር የሚርመሰመሱ ተንቀሳቃሾች ፣ በባሕር ያሉ ዓሣዎች ቢፈልጉ እዚህ ቤት በብዛትና በዐይነት ሊያገኙ ይችላሉ" አለው ።

"እሺ እንግዲያውስ ጥቂት ዶሮዎች ቢቀቅሉልን ይበቃናል ። ጌታዬ እንኳ ይህን ያህል ምግብ አይደ ፍሩም፤ እኔ ግን መዋጥ እንጂ ማላመጥ አላውቅም" አለው ።

"አዝናለሁ ። ምንም ዶሮ የለኝም ። ዶሮዎቼን በሙሉ ጭልፊት ወስዶብኛል" አለ ።

"እንግዲያውስ ዳክዬዎች ይቀቅሉልን ።"

"የምን ዳክዬ አመጣብኝ ! ሃምሳ ዳክዬዎች ነበሩኝ ! ትናንት ገበያ ልኬ ተሸጡ ። እና . . . አንድም ዳክዬ አልተረፈኝም ። ከዶሮና ከዳክዬ በስተቀር ሌላ የሚወዱትን ይጠይቁኝ" አለ ።

"የወይፈን ቅቅል ፣ ወይም የጠቦት ብግ ቅቅል ብና ገኝ ያፈካናል !" አለ ።

"ከሁለቱም ዐይነት የሚበቃችሁን ያህል ለሚመጣው ሳምንት እናዘጋጅላችኋለን ፤ ለጊዜው ግን ይህን የመሳሰሉ የሥጋ ምግቦች የሉንም" አለ ።

"የእንቁላል ጥብስና የዓሣማ ሥጋ አምጡልን" አለ ሳንቾ ።

"ቀልደኛ ነዎትና ! ዶሮና ዳክዬ የለኝም እያሉኩዎ ! ማን የወለደውን ዕንቁላል እንዳቀርብልዎት ነው የሚያዝዙኝ !"

"ከቡር ያገር ባላባትና ባለ ሆቴል ፣ ለወሬዎ አልባዬ ያድርጉለትና ምን ዐይነት ምግብ እንዳለ ብቻ በአጭሩ ይንገሩኝ !" ሲል ሳንቾ ተስፋ በቆረጠ አነጋገር ጠየቀ ።

"እሺ ! በቤት ውስጥ የሚገኙትን እዘረዝርልዎታለሁ ። በእውነቱ ሳይበዛ ወይም ሳያንስ ፣ ለጊዜው የማገኛላችሁ ፣ ጥንድ የላም ሽሆናዎች ከአደንጓሬና ከዓሣማ ሥጋ ጋር በሽንኩርት ጣዕም ባለው ሙያ የተቀመመ ፣ ሆኖ 'ብሉኝ ! ብሉኝ !' እያለ እስካሁን ይጮሃል !"

"ሁሉንም ለኔ ለብቻዬ በቅድሚያ ይገፍያቸዋልሁና ማንም ሰው እንዳይነካብኝ !" አለ ሳንቾ ፓንሳ ።

"እረ ማንም ሊነካብዎ የሚፈልግ የለም ! ሰዉ ሁሉ ጨዋ ነው ። መንገድ ለመሔድ ሲነሣ እንኳ ፣ ወጥቤቱን አስከትሎ ፣ አገልግሉን አሳዝሎና ፣ ስንቁን ሰንቆ ስለሚጓዝ ፣ ይህን የሆቴል ምግብ ማንም አይነካብዎትም ።"

"ለጨዋነት ከሆነ ፣ ጌታዬን የሚያህል ጨዋ አይገኝም ። ሆኖም ፣ ብረት ድስት ተሸክሞ መጓዝ ክብሩ አይፈቅድለትም" ሲል ሳንቾ በምጸት ተናገረ ።

በመጨረሻም ፣ አስተናጋጁ ድስቱን እንዳለ አቀረበላቸውና ፣ ሁሉም በአንድነት ሆነው በሽንኩርት ጣፍጦ የተሠራውን የላም ሽሆና ይመገቡ ጀመር ።

ጀግናው ጦረኛና ጋሻ ጃግሬው ፡ ከችግር ጋር የተለ ማመዱ በመሆናቸው ፡ የቀረበላቸውን ከመብላት በስተቀር ማማረጥ ከረሱ ሰንብተዋል ።

ዕረፍት አድርገው በማግሥቱ የተለመደ ጉዞአቸ ውን ቀጠሉ ። መንገዳቸውን በማራጎሳ ግዛት ውስጥ ከማ ድረግ ይልቅ በሌላ አቅጣጫ ወደ ባርሴሎና አቀኑ ።

የዶን ኪኾቴ ታሪክና ዝና ፡ ጀግናውን ቀድሞ ለሕዝቡ ደርሶ ነበርና ፡ የባርሴሎና ነዋሪዎች በአክብሮት ተቀብለው፤ በደስታና በፈንጠዝያ ያስተናግዱት ጀመር ። በደስታና በዓለም በዚህች ከተማ ውስጥ ሰንብተው ፡ አይተው የማያውቁትን አስደናቂ ነገሮች ሁሉ ጎብኝተው ባሕሩን እየተዘዋወሩ በመመልከት ሰነበቱ ።

የጨረቃ ጦረኛ

አንድ ቀን ጧት ፡ ዶን ኪኾቴ ሙሉ ትጥቁን ታጥቆ ነፋስ ለመቀበል ወደ ባሕር ዳርቻ በፈረሱ ተጓዘ ። ለውጊያ የተቀሰቀሰ ስሜት ነበረው ።

"እሰባበሰ ፡ ትጥቄና ወኔዬ የተሟላ ነው ። ለሰው ልጅ ምግብና መጠጥ እንደሚያስፈልጉት ሁሉ ፡ ለእኔም ውጊያ ያስፈልገኛል " አለ ዶን ኪኾቴ ለራሱ ።

ለብቻው እየተናገረ በፈረሱ ሲጓዝ ፡ አንድ ጦረኛ ወደ እርሱ አቅጣጫ ሲመጣ ታየው ። ጦረኛውም ከራስ ጸጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ በጦር ልብስ ያጌጠና ፡ በጋሻ ውም ላይ የምታብራ የጨረቃ ሥዕል ተሥሎበታል ።

ዶን ኪኾቴ አትኩሮ ተመለከተው ። ንግግሩንም ለመ ስማት ቸኰለ ። ጀግናውም ፡ "እጅግ ስምህ የገነነው ጀግና

ጦረኛ ዶን ኪኾቴ ዴ ላ ማንቻ ሆይ ! እኔንም ዕወቀኝ ፤ የጨረቃው ጦረኛ እባላለሁ ። የመጣሁትም ካንተ ጋር ልፋለም ነው ። አመጣጤም ስሟ ያልታወቀውን የእኔ ዋን እመቤት ፣ ማንም እንደማይስተካከላትና ፣ እሷም ከቶቦሳዋ ዱልሲኒያ የላቀች ወደር የሌላት ቆንጆ መሆን ዋን ላሳምንህ ነው የመጣሁት ” አለው ።

“አይደረግም !! ይልቁንስ በተቃራኒው የእኔን እንድ ታምን እናዝዝሃለሁ ። አንተ ! ወደር የሌላትን እመቤት ዱል ሲኒያን አይተሃት አታውቅም ። ብታያት ኖሮ ከእርሷ ጋር በውበት ተመሳሳይነት ያለው ፍጡር አለመኖሩን ታረ ጋግጥ ነበር ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

“የተሸነፈ ይናዘዝ ! እኔ ያሸነፍኩ እንደሆነ ፣ ወደ አገርህና ወደ ቤትህ ልትገባ ፣ የጦር መሣሪያህን ለአንድ ዓመት ያህል አስረክበህ በሰላምና በጸጥታ ልትኖር ግዴታ ትገባለህ ” አለ ኮስተር ብሎ ።

“እኔስ ባሸንፍ በምን ግዴታ ቃል ትገባለህ ? ” ዶን ኪኾቴ ጠየቀ ።

“ራሴ ወይም የራስ ቅሌ ሳይቀር ፣ በትእዛዝህ ሥር ይወላል ። ፈረሱና የጦር መሣሪያዎቼ የአንተ ምርኮ ሆነው ፣ የጀግንነት ታሪኬ በሙሉ ካንተ የጀብዱ ሥራ ዎች ጋር ተዳምረው ያንተን ዝና እንዲያገለግሉ ቃል ገብቻለሁ ” አለ የጨረቃው ጦረኛ ።

“በግጥሚያውና በግዳጁ ተስማምቻለሁ ። በውለ ታችን መሠረት ልፈጽም ቃል እገባለሁ ። ሆኖም ፣ እኔ የምኮራው በራሴ ጀግንነት ብቻ ነው እንጂ ፣ ያንተን ጀግን ነት ከራሴ ሙያ ጋር ማዳመሩን በሕይወቴ አልመኝም ፤ ስማንኛውም ከውጊያዉ ሜዳ የቆቸውን እቅጣጫ እንደ ምትመርጥ አሳየኝና ፣ የፍልሚያዉን ፍጻሜ በፍጥነት እን መልከት ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

ሁለቱም ጦረኞች ፈረሶቻቸውን አዙረው በርቀት ለሊያይተው ቆሙ ። ከወዲያ ወዲህ መልስ ቀስስ አሉና እንዳች ምልክት ሳይጠብቁ ወጊያ ገጠሙ ። የጨረቃው ፈረሰኛ ፈረስ ከሮሲናንቴ ይበልጥ ፈጣን በመሆን ፤ በዶን ኪኾቴ ላይ እንደ መብረቅ ወረደበት ። ግጭቶት ሲያ መንገድ ሲያመልጥ እንደ ጉድ ታየ ። እንግዳው ጦረኛ በጦሩ ለመጠቀም ጊዜ አላገኘም ። እንደገና አካሔዱን አመቻችቶ ፤ እየከነፈ መጥቶ ዶን ኪኾቴን ክፉኛ ከፈረሱ ላይ ገልበጠው ። ዶን ኪኾቴና ፈረሱ ሮሲናንቴ ያለ እንዳች ድጋፍ ከመሬት ወርደው ተዘረጉ ።

የጨረቃው ጦረኛ ከፈረሱ ላይ ዱብ አለ ። ጦሩን በዶን ኪኾቴ ጉሮሮ ላይ አቅመና ፤ "ጌታዬ ተማርከሃል! ያለበለዚያ ግን ሕይወትህ በእጄ ውስጥ ነው ያለችው! ቃልህን ፈጽም !" ሲል አምባረቀበት ።

ዶን ኪኾቴ በአጠዳደቁ ክፉኛ ተጎድቷል ። እያቃሰተ ቃሉ የገባበትን ኑዛዜ ያወርደው ጀመር ።

"የቶቦሶዋ ዱልሲኔ በዓለም ከሚገኙ ቆንጆዎች ሁሉ የበላይነት ያላት መሆንዋን በውቂላት በቃሌ ጸንቻለሁ ። እኔ ግን ዕድለቢስ ጦረኛ መሆኔን አምኛለሁ ። እባክህን ጦርህን በጉሮሮዬ ሰድደህ ሕይወቴን አጥፋት !" ሲል ዶን ኪኾቴ ተማጸነ ።

የጨረቃው ጦረኛም ፤ "ጌታዬ ይህንንስ አላደርግውም ፤ የቆንጆይቱን ሙያ ፤ ታሪክና ዝና ለመሻር አልፈቅድም ። በበኩሌ የምፈልገው ፤ ታላቂቱና ገናናው ዶን ኪኾቴና እኔ በገባነው ግዳጅ መሠረት ፤ ለአንድ ዓመት ጊዜ ወደ ቤቱ ተመልሶ ቢገባ ነው የሚያስደስተኝ" አለ የጨረቃው ጦረኛ ።

“እሺ መልካም ! የእመቤቲቱን የዱልሲኒያን ጥሩ ታሪክ የማትቃወም ከሆንክ ፣ የምትፈልገውን ሁሉ ልፈጽምልህ ዝግጁ ነኝ ” ሲል ዶን ኪኾቴ ሙትት ባለ ድምፅ ተናገረ ።

ዶን ኪኾቴን ከወደቀበት መሬት ላይ አንሥተው ፊቱን ሸፈኑት ። ሰውነቱ ዝሎ ፣ ጉልበቱ ደክሞና መላ ሰውነቱ ተጎድቶ ነበር ። ሮሲናንቴ እዚያው ከወደቀበት አሸዋ ላይ መነሣት ተስኖት ተጋድሟል ። ሳንቾ ፓንሳ አዝኖና ተክዞ ፣ የሚያደርገው ነገር ጠፍቶት እንደ በድን ፈዝዞ ቆሟል ።

የጨረቃው ጦረኛ ወደ ከተማ እየጋለበ ሔደ ። ውጊያውን ይመለከቱ ከነበሩት ሰዎች መካከል ጥቂቱ ፣ ተከትለውት ይሮጡ ጀመር ። እንደ ደረሱበትም ማንነቱን አጥብቀው ከጠየቁ በኋላ ፣ ለምን ይህን ክፉ ሥራ በታጠቅውና በሰው ላይ ጉዳት በማያደርሰው በዶን ኪኾቴ ላይ እንደ ፈጸመ ጠየቁት ።

“ሳምሶን እባላለሁ ። የቅርብ ጎረቤቱ ነኝ ! ይህንን ውጊያ የፈጸምኩበት ምክንያት እሱን ሊጎዳው ሳይሆን ፣ ወደ ቤቱና ወደ አገሩ እንዲመለስ በጀግና ፍልሚያ ሥርዓት መሠረት ተሸንፎ ቃል እንዲገባልኝ ነው ። ይህ ሰው አንድ ዓመት በጸጥታ መንፈስ ዕረፍት እንዲያደርግ ቢገደድ ፣ በጦረኛነት ስሜትና ወኔ የተጠናወተው እብደት ጨርሶ የሚለቀው ፣ እሱም ሙሉ ጤነኛ ሆኖ የሚድን ይመስለኛል ” በማለት በሰፊው ገለጸላቸው ።

ለካንስ ይህ ሰው ፣ ከዚህ ቀደም ባለ ብልጭልጭ ሩና ተብሎ ከዶን ኪኾቴ ጋር ፍልሚያ ገጥሞ ፣ ጦረኛውን ከልክፍቱ ለማዳን ሞክሮ ሳይሳካለት ቀርቶ ፣ ወደ አገሩ የተመለሰው ሳምሶን ካራስኮ ኖሯል ። !!

የመጨረሻው ገድል

ዶን ኪኾቴ ድል በመሆኑ እጅግ በጣም አዘነ ። በሐዘንና በትካዜ ተውጦ ከአልጋው ላይ ሳይነሣ ስድስት ቀን ያህል ተኝቶ ሰነበተ ። ሳንቾ ፓንሳ ከአጠገቡ ሳይለይ ለብዙ ቀናት አጽናናው ።

"ጌታዬ ሆይ ! ራስህን ቀና አድርግና የምትችል ከሆንክ ተደሰት " አለና ሳንቾ ፓንሳ፥ "በማናውቀው አገርና ሥፍራ እየተዘዋወርን የጀግንነት ሙያ ከመፈለግ ፥ ወደ አገራችን እንግባ " ሲል ምክር አዘል ቃላት ወረወረ ።

"ምንም እንኳ በየፍልሚያው ጉዳት የሚደርሰዉ በእኔ ቢሆንና አንተም ለእኔ ብታስብልኝ፥ችግሩ ባንተ ይብሳል " አለው ዶን ኪኾቴ ።

ዶን ኪኾቴ በአዲስ የተስፋ ጭላንጭል እየተመራ፥ በአዲስ ድፍረትና ወኔው ታድሶና ፥ ባርሴሎን ዶኀና ሰንብቶ ብለው፥ ሁለቱም ወደ አገራቸው ጉዞአቸውን ቀጠሉ ። ዶን ኪኾቴ በሮሲናንቴ ላይ ወጥቶ ፥ጥሩሩንና ቍሩን አውልቆ፥የመንገድ ልብሱን ለብሶ ሲጓዝ ፥ ሳንቾ ፓንሳ የዶን ኪኾቴን ጥሩሩና ቍሩን በግራጭ አህያው ላይ ጭኖ ፥ በእግሩ ይከተለው ጀመር ።

"ሮሲናንቴ ባይደክምብኝ ኖሮ በጭራሽ አልሸነፍም ነበር " እያለ ዶን ኪኾቴ ስለ ፍልሚያው ለሳንቾ ፓንሳ እያወጋው ፥ ሁለቱም ፊታቸውን ወደ ላ ማንቻ አዙረው ለብዙ ቀናት ገሠገሡ ። ምንም እንኳ ዶን ኪኾቴና ሳንቾ

ቢፈጥኑም ፤ እንስሶቻቸው ጎታቶች በመሆናቸው አሁንም አሁንም በየመንገዱ ዕረፍት ማድረግ ነበረባቸው ።

በመጨረሻዉም ቀን ፡ ወደ አንድ ተራራ ጫፍ ላይ ብቅ ሲሉ ፤ሰላማዊ የሆነችው ያገራቸው መንደር ከለምለሙ ኮረብታ በታች ታየቻቸው ። መንደሯ እንደ ታየች ፡ ሳንቾ በጉልበቱ ተንበርክኮ ይጮኽ ጀመር ።

“ለብዙ ጊዜ የናፈቅሁሽ አገሬና መንደሬ ! ዐይንሽን ከፍተሽ ልጅሽን ሳንቾ ፓንሳን ተቀበይው ። ይኸውም ልጅሽ እምብዛም ከበርቴ ሳይሆን ጥሩ ሆኖና ተቀጥቶ ወደ አንቺው ዘንድ መጥቶልሻል ። አንቺ የተዋብሽ መንደር ! እጅሽን ዘርግተሽ ልጅሽን ዶን ኪኾቴንም ተቀበይው ! በሌሎች ጀግኖች ስለ ተሸነፈ ፥ እሱም በበኩሉ የራሱ አሸናፊ የመሆንን ዕድል አግኝቷል ። ይኸውም ድል ከማንኛውም ዐይነት ድል የበለጠ ነው …” እያለ ሳንቾ ለረዥም ጊዜ ተናገረ ።

“መንፎሸፎሸክን ትተኝና ወደ መንደራችን በጊዜ እንድንገባ እርምጃህን ፈጠን አድርግ ” አለ ዶን ኪኾቴ በቁጣ ።

ዳገቱን ወርደው ቁልቁለቱን ሲያያዙ ፥ የቀድሞ ወዳጆቻቸው የሆኑትን የንስሐ አባትዬውን ፥ ጸጉር አስተካካዩንና ታማኙ ሳምሶን ከራስኮንን አገኙዋቸው ። ዶን ኪኾቴ ከፈረሱ ዱብ ብሎ ሁሉንም በናፍቆትና በፍቅር ዐቀፎ ሳማቸው ።

“ስአንድ ዓመት ያህል በአገሬና በቤቴ ለመኖር ስል ተመለስሁ ፤ እረኛ ሆኜ ብቻዬን በሜዳ ውስጥ ለመኖር አስቤአለሁ ። ብዙ ሥራ ከሌለባችሁ ከእኔ ጋር ብትሆኑ ደስ ይለኛል ” አለ ዶን ኪኾቴ ።

ወዳጆቹና ጎረቤቶቹ በሐሳቡ የሚስማሙ መሆናቸውን ገለጹለት ።

በብዙ ሕፃናት ተከበውና ታጅበው ሁሉም ወደ ዶን ኪኾቴ ቤት አመሩ ። የዶን ኪኾቴ የቤት ሠራተኛና የእኅቱ ልጅ ኩብላዩን ጦረኛ ለመቀበል በናፍቆት ይጠባበቁ ጀመር ። ዶን ኪኾቴ እደጅ እንደ ደረሰ ፤

“ውድ የሆንሽው የእኅቴ ልጅ ሆይ ! ለጥቂት ጊዜ በቤቴና ባገሬ ውስጥ ለመቆየት ተመልሼ መጥቻለሁ ። በቅርቡ እንቺን ትቼ መደዴ የሆነውን የእረኝነት ሕይወት ለመኖር እንዛለሁ ። ለጊዜው ጤናዬ የተሟላ ስላልመሰለኝ ደጋግፋችሁ አልጋዬ ላይ አውጡኝ ” አላት ዶን ኪኾቴ የእኅቱን ልጅ በናፍቆት እያየ ።

ሌሊትና ቀን በወግ በማዕረግ ጠበቁት ፤ ተንከባከቡትም ። ሆኖም በዚያ ሁሉ ውጣ ውረድ ሰውነቱ ሰልሎ ሥጋው አልቆ ነበርና ፣ በየዕለቱ ድቅቅ ሙቅት ይል ጀመር ። የንስሐ አባትዬው ጸጉር አስተካካዩና ሳምሶን ካራስኮ ዘወትር ከአጠገቡ ሳይለዩ ይጠይቁት ነበር ። ደግ ጋሻ ጃግሬው ሳንቾ ፓንሳ ከጌታው አልጋ አጠገብ ሳይለይ አስታመመው ፤ ምንም እንኳ ዘመድ አዝማድና ጓደኛ ቢደክምለትም ፣ ሰውነቱ እየደከመ ይሔድ ጀመር ።

በስድስተኛዉ ቀን ሐኪም መረመረው ። በአሥጊ ሁኔታ እንደሚገኝና ሕይወቱም እንደማትሰነብት ተገለጸለት ። ዶን ኪኾቴም እንቅልፍ እንዲወስደው ስለ ፈለገ ከመኝታ ክፍሉ እንዲወጡለት ጠየቃቸው ። መልኩንም ሲመለከት ሕይወቱ የምታልፍና ወደዚህ ዓለም የማይመለስ መስሎ ታየው ። እንደ ወጡለትም ሰላማዊ ዕንቅልፍ ይዞት ጭልጥ አለ ።

ስድስት ሰዓት ላይ ዐይኖቹን ከፈተ ። ጤነኛ መሆኑንና ሕመሙ እንደ ለቀቀው ሁሉም ተረዱለት ። ትንሽ ቆየት አለና ፡

"የሞቴ ጊዜ ተቃርባለች ። ኑዛዜ ማድረግ አለብኝ ፤ ወዳጆቼን የንስሐ አባቴን ፣ ጸጉር አስተካካዩንና ሳምሶን ካራስኮን ጥሩልኝ " አለ ዶን ኪኾቴ በተሰባበረ ድምፅ ።

እኒህ ወዳጆቹ ዘወትር ቤቱ ደጃፍ ላይ ሆነው ጤንነቱን ይከታተሉ ነበርና ፣ ጥሪውን እንደ ሰሙ ወዲያው ተከታትለው ገቡ ። ዶን ኪኾቴ እነርሱን ሲያያቸው እጅግ በጣም ደስ አለውና ፤

"እንኳን ደኅና መጣችሁ ዘመዶቼ ! ከዛሬ ጀምሮ ስሜ 'ዶን ኪኾቴ ዴ ላ ማንቻ' መባሉ ቀርቶ ፣ ያገሬ ሰዎች ይጠሩኝ በነበረው 'ደጉ አሎንሶ ኪኻኖ' መባል አለበት ። አሁን እእምሮዬ ትክክል በመሆኑ እንዚያ አሽባሪ መጻሕፍ[illegible]ማንበብ የደረሰብኝን መንገላታት ሁሉ ልገንዘብ ችያለሁ ። እኒያ ከንቱ ታሪኮችና የጭንቆላ መጻሕፍት ያደረሱብኝን በደልና መደለል እያስታወስኩ እጸጸታለሁ ! ' ሰዓቴ የተቈጠረች በመሆኗ ጠበቃዬንም ጥሩልኝና የኑዛዜ ቃሌን እንዲቀበለኝ አድርጉልኝ" አለ ፡ ዶን ኪኾቴ በደከመ ድምፅ ።

ሁሉም እርስ በእርስ ተያዩና እጅግ በጣም ተገረሙ ። ሳምሶን ካራስኮ ጠበቃውን ለመፈለግ ወጥቶ ሔደ ።

ሕመምተኛው፡ ጀግና ጠበቃዉ መጥቶ እስኪገባ በተቀመጠ ጊዜ ፊቱ እንደገና ጸዳል ለበሰ ። ከአልጋው ላይም ተነሥቶ ተቀመጠ ።

የኑዛዜው ቃልም በተገቢው ሥነ ሥርዓት ተጻፈ ። መልካም ሥራ ለፈጸመውና ትእዛዙንም አክብሮ እስከ

መጨረሻው ሳገለገለው ለሳንቾ ፓንሳ ገንዘብ ተናዘዘለት ። የማይንቀሳቀስ ንብረቱን ለእኅቱ ልጅ አወረሳት ። ይኸ ውም የኑዛዜ ወረቀት በአሉንሶ ኪኻና በራሱ ተፈረመ ። የንስሐ አባትዬዉና ጸገር አስተካካዩ ምስክርነታቸውን በፊርማቸው አረጋገጡ ።

ሕመምተኛው ጆ[illegible] ሊስ ሦስት ቀን ሙሉ አንዳች ነገር ሳያውቅና ሲያጣጥር ሰነበተ ። በሦስተኛዉ ቀን ከቀትር በኋላ እስከ መጨረሻው ወደ ማይቀሰቀስበት የዕንቅልፍ ዓለም ገባ ።

ይህን የመሰለ መልካም ሰው ፣ ተወዳዳሪ የሌለው ጀግና ተፈጥሮባት አይታ የማታውቀው ስፓኝ ፣ በባለ ሙያው ታሪክ ኮርታ እነሆ ዝናውንና ወጉን ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ እንዲናኝ አድርጋለች ።